# ኮዛ ኖስትራ



ትርጉም፡- መኩሪያ መካሻ

የተወሳሰበ ታሪክ ያለው የሲሲሊ ማፊያ አስደናቂ ታሪክ

# ኮዛ ኖስትራ

ደራሲ ጆን ዳይኪ

ትርጉም - ከመኩሪያ መካሻ

ሐምሌ 2007 ዓ.ም

# መግቢያ

ስለማፊያ ታሪክ ስናነብ በቅድሚያ ለአንባቢ ግልጽ መሆን ያለባቸው ሁለት ነገሮች አሉ - የማፊያ ቤተሰብና የደም ትስስር ያለው የማፊያ የዘር ግንድ። ሁለቱ የተለያዩ ናቸው። ይህ መጽሐፍ በዋናነት የሚያጠነጥነው በሁለተኞቹና ከደም ትስስር የተነሳ በዘመዶቻቸው ተገፋፍተው የማፊያ አባል እንዲሆኑ ስለተደረጉት ነው። "የማን ዘር ጎመን ዘር" እንዲሉ በዘር ግንድ ተተብትበው ለማፊያ ይሰራሉ። እርግጥ ነው ማፊያ ወይም "ኮዛ ኖስትራ" ምስጢራዊ ድርጅት ነው። በመሆኑም ከማፊያ ጋር ስላላቸው ግንኙነት አባላቱ ለወገኖቻቸው ትንፍሽ ማለት አይችሉም። ይህ ምስጢራዊ ድርጅት ምስጢርን መጠበቅ በሚለው የዝምታ (ኦሜርታ) መርሁ በመመራት ድርጅቱን ለ150 ዓመታት አስጠብቋል።

ሁለቱ የማፊያ ቤተሰቦች የሲሲሊ ማፊያ እና የአሜሪካ ማፊያ ሲባሉ ከግለሰብ ቱጃሮች፣ ነጋዴዎች፣ ፖለቲከኞችና የሠራተኛ ማህበራት ጋር ግንኙነት መስርተዋል። በተመሳሳይ መንገድም ከኩባንያዎች፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ቡድኖች ጋር እጅና ጓንት ሆነው ተራምደዋል። ይህም የሆነው ኩባንያዎቹም ሆኑ ፓርቲዎቹ በህብረተሰቡ ውስጥ ህልውናቸውን ለማረጋገጥ የማፊያን ከለላ በመፈለጋቸው ነው።

ይህ መጽሐፍ እንደ ሌሎች በማፊያ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ሊያነሱት የሞከሩትን ታሪካዊ ጉዞን ለማሳየት ይጥራል። በመሆኑም የማፊያ አለቆች ከፍትህ ለማምለጥ ያደረጉትን ድብብቆሽ በስም፣ በሥፍራ እየጠቀሰ ያስነብባል። ከስሞችና ቦታዎች (ከተሞች) አጠቃቀም አንፃር ታሪኩ እንዳይወሳሰብ በፀሐፊው ጥረት የተደረገባቸው ቢሆንም

መለወጥም ሆነ ማስቀረት ታሪኩን ወደመደምሰስ ስለሚወስደው በየታሪኩ ውስጥ እንደየአስፈላጊነታቸው መጠቀሳቸው አልቀረም። በዚህ ረገድ አንባቢ እንዳይሰለች ለማሳሰብ እወዳለሁ።

ምንም እንኳ ብዙ ሰዎች ማፊያ የሚባል ነገር የለም ወይም ደግሞ የነበረው ሚና ይህን ያህል የጎላ አይደለም በማለት ለማንኳሰስ ቢጥሩም ነውጠኛ ጥንካሬውን እያጎላ ሄዷል። ለዚህም እማኙ የሩሲያ፣ የቡልጋሪያ፣ የሞንቴኔግሮ፣ የበርማ፣ የኡክሬይን፣ የቼቺኒያ፣ የቻይና... ወዘተ. ማፊያዎች መፍሰሃቸው በቂ ማሳያ ይሆናል። አልፎ ተርፎም በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ከማፊያ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው መንግስታት ተመስርተው ሥልጣንና ሀብት በመቀራመት ይምነሽነሻሉ። በሕዝብ ላይ ነግሰውና እንደመኸርገር ተጣብቀው ደሙን ይመጣሉ። ማፊያ ሀገር ያለው ድርጅት እስከ መሆን ደርሷል ሲሉ ፀሐፍት የሚያስረዱትም ለዚህ ነው።

ወደ ማፊያ የኋላ ታሪክ ስንመለስ ሁለት ትዕይንቶች ያጋጥሙናል። የመጀመሪያው ሜሎድራማዊ ይዘት ያለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ትራጂካዊ ነው። በዚህ መጽሐፍ የሰፈረው የሲሲሊ ማፊያ ታሪክ ሁለተኛውን እውነታ ይዞ ለአንባቢ እውቀት ይሆን ዘንድ በትርጉም መልክ የቀረበ ነው።

* * *

ግንቦት፣ 1890 በሮማ ከተማ በሚገኘው ትያትር ኮንታንዚ የቀረበ አንድ ኦፔራ ነበር። እስከዛሬም ድረስ የተዋጣለት ኦፔራ ተብሎ በተመልካቹ ይደነቃል። በፔትሮ ማስካኚ የተዘጋጀው የ"ገጠሬው ፈረሰኛ" ታሪክ በሲሲሊ ገበሬዎች መካከል የሚታየውን ምቀኝነት፣ ክብርና ብቀላን በትረካ ያቀርባል። ኦፔራው በሰላሳ የመድረክ ገቢር ተቀናብሮ የቀረበ ሲሆን በወቅቱ ታዳሚ የነበረችው ኢጣልያዊቷ ንግሥት ኦፔራውን እየተመለከተች ሌሊቱን ሙሉ በጭብጨባ አድናቆቷን ገልጣ ነበር። በተለያዩ ሀገራት ኦፔራው በኋላም ዓለም አቀፍ ዝናው በመናኘቱ መድረክ ላይ ቀርቧል። ኦፔራው ለመድረክ ከበቃ ከጥቂት ወራት በኋላ የ26 ዓመቱ ማስካኚ ለጓደኛው በፃፈው ደብዳቤ "አንዴ ጽፌ ያዘጋጀሁት ኦፔራ የእድሜ ዘመን ቱጃር አደረገኝ" ሲል ገልጿል።

ለኦፔራው በተዘጋጀው የ"ገጠሬው ፈረሰኛ" ላይ የቀረበውን ሙዚቃ ማንም የሚረዳው ነበር። ማርቲን ስኮርሴስ "በተቆጣው ወይፈን" ኦፔራ ላይ ያቀረበው ሙዚቃም ውስጥ የአሜሪካ-ኢጣልያውያንን የምቀኝነትና ኩሩ ወንዳወንድነትን ያመላከተ ነበር። ኦፔራው በኋላም ፍራንሲስ ፎርድ ኮፓላ ባዘጋጀው የጡት አባት ቁጥር ሶስት ፊልም ላይ በአጃቢነት ቀርቧል። ልክ በ1870 በቲያትሮ ማሲሞ እንደቀረበው የፈረሰኛው ኦፔራ ሁሉ፣ በዚህም ፊልም ውስጥ የማፊያው ነፍስ ገዳይ ቄስ መስሎ ገደላ ይፈጽማል። የዶን ሚካኤል ካርሲኦን ልጅ መሪ ዘፋኝ ሆኖ ይቀርባል። በፊልሙ ፍፃሜ ምቀኝነትንና ኩራትን የሚገልፀው ሙዚቃም የሽማግሌውን ዶን አማሟት ያጅባል።

በፈረሰኛው ኦፔራ ታሪክ ውስጥ ስለ ሲሲሊና ስለ ማፊያ ሥነ-ተረት የቀረበው እምብዛም ታዋቂነት ያላገኘ ቢሆንም የሲሲሊ ማፊያ አፈሌላዊ ርዕዮት ነበር ማለት ግን ይቻላል። በወቅቱ ማፊያና ማፊያዊነት ድርጅት ሳይሆን በሲሲሊያውያን ደም ውስጥ የታተመ የማንነት ጉዳይ ነው ተብሎ ይታሰብ ነበር። ዛሬም ቢሆን ስለ ማፊያ ወንጀለኝነት ስንናገር የጥንቱን ሥነ-ተረት መሰረት ሳናደርግ ማቅረብ አይቻለንም።

ሁለተኛው ታሪክ ደግሞ የሚወስደን ከፓሌርሞ ከተማ ኤርፖርት ወደ ተራራው መንገድ ላይ የሚያወጣን ነው። ግንቦት 1992 ልክ 12 ሰዓት ላይ ወደ ተፈፀመ ጉዳይ ይወስደናል። አጭር፣ ደልዳላ ሰውነት፣ ፂማም የክብር ሰው የሆነውን ጆቫኒ ቡርስካን እናገኛለን። ቆም ብሎ ካፓቹ ወደ ተሰኘችው ትንሽ ከተማ የሚታጠፈውን መንገድ በአትኩሮት ይመለከታል። የእሱ ሰዎች በአሥራ ሶስት እንስተኛ መያዣዎች (ገንቦዎች) 400 ኪሎ ፈንጂዎችን ሞልተዋል። ከቡርስካ በትንሽ ሜትሮች ራቅ ብሎ አንድ ሽምግል ያለ ማፊያ እያጨሰ በሞባይል ስልኩ ያወራል ከዚያም በድንገት ባያኖኩላሩን አውጥቶ መንገዱን መመልከት ጀመረ። ተከታተለው የሚመጡ ሦስት መኪኖች መቃረባቸውን እንደተመለከተ "ቀጥሉ" ሲል እንባረቀ። ደግሞ ደጋግሞ "ቀጥሉ" አለ።

ቡርስካ እንዳረጋገጠው የተከታተሉት መኪኖች እንደተጠበቀው ሳይሆን በዝግታ ይከታተሉ ነበር። ከዚያም ለሶስተኛ ጊዜ "ቀጥሉ" የሚለውን ትዕዛዛዊ ድምፅ እንደሰማ የማፈንጃውን መቆጣጠሪያ ተጫነ። በዚህ ጊዜ እጅግ ከፍተኛ ፍንዳታ ተሰማ። የመጀመሪያዋ መኪና ሰማይ ላይ ጉና በእሳት ተንቀለቀለች። ከዚያም 70 ሜትር ያህል ርቃ በወይራው ማሳ ውስጥ ወደቀች። ሁለተኛዋ መኪና ጥይት የማይበሳት ፊያት ክሮማ ሜዴል ስትሆን ሞተሯ ፈንድቶ በሰማይ ላይ ተበታተነች። ሦስተኛዋ ጉዳት ቢደርስባትም እንደሌሎቹ ድራሿ አልጠፋም ነበር። የፍንዳታው ተጎጂዎች የፀረ-ማፊያውን የፍርድ ሂደት የሚመራው የዳኛ ጆቫኒ ፊልኮኔና ሚስቱ እንዲሁም አጃቢዎቹ ነበሩ።

የካፓቺው ፍንዳታ ኢጣልያ እንድትበረግግና ተስፋ እንድትቆር ያደረገ ሂደት ነበር። ብዙ የመንግስት ባለሥልጣናት ኢጣልያዊ መሆናቸው አንኳ አሳፍሮአቸዋል። የካፓቺው ፍንዳታ የማፊያን ማን አለብኝነትና ጉልበት አመላክቷል። እውነተኛው የማፊያ ታሪክ ከፈረሰኛው የሥነ-ተረት አቀራረብ ወጥቶ የተፃፈው ከካፓቺው ፍንዳታ በኋላ ነው ማለት ይቻላል።

* * *

የገጠሬው ፈረሰኛ ታሪክ በግጭት የተሞላ ከፍተኛ ሥነ-ጥበባዊ ብቃትን ይዟል። ወጣቱ ጋሪ ነጂ አልፊዩ፣ በወጣቱ ወታደር ቱሪዱ አማካኝነት እንዲጠጣ የተሰጠውን መጠጥ አልጠጣም ሲል እንመለከታለን። በወቅቱ ምንም አይነት የአፍ-እላፊ ያልታየ ቢሆንም ድርጊቱ ወደ ሞት እንደሚያመራ ግን አያጠራጥርም። ይህ የቆየ ኋላ ቀር እሴት ሁለቱ ሰዎች በተመላለሱት ጉዳይ ተጠቃሎ ይቀርባል። ሁለቱም ክብራቸው እንደተነካ በመረዳታቸው ትክክለኛው እዳ መክፈያ መፍትሔ ደግሞ ብቀላ መሆኑን ተቀበሉት። ባህሉም እንደሚያስገድደው ቱሪዱ እናቱን በእንባ ተለይቷት ወደማይቀረው ብቀላ አልፊዮን ለመገናኘት ወደ ማሳው ይመጣል። ከዚያም ከሩቅ ሥፍራ የምትመጣ ሰቴ ባለጠንካራ መንቆር ወፍ "ቱሪዱ ተደለ!" ብላ ስታበስር መጋረጃው ይዘጋል። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በትዕይንት መልክ ይቅረብ እንጂ የጊዜው የሲሲሊ ባህላዊ እሴት መገዳደልና ብቀላ ነበር። በ1890 ደግሞ

ማፊያ ገዳይና ውስብስብ የወንጀለኛ ድርጅት ሆኖ ወጥቷል። ዓለምአቀፋዊ ክንዱም ወደ አሜሪካ ተዘርግቷል።

በሲሲሊ ዋና ከተማ በፓርሌሞ የአካባቢው የማፊያ አባላት የሆኑ ፖለቲከኞች በጣንክና በሼር ማጭበርበር ሥራ ተሰማርተው ኖረዋል። ከተማዋን ለማደስ ተብሎ ከተመደበው በጀትም የአንበሳውን ድርሻ ያነሱት እነዚሁ ማፊያዎች ናቸው። በወቅቱ በሕብረተሰቡ ውስጥ ተንሰራፍቶ የነበረው አስተሳሰብ ማፊያን እንደ ወንጀለኛ ድርጅት የሚመለከት ሳይሆን የሲሲሊያውያን ባህላዊ እሴት አድርጎ ነው። ይህም ሁለት ነገሮችን ይዟል - ኃይልን የመጠቀም ሲሲሊያዊ ጉጉትና አረቦች ሲሲሊን ይዘዋት በነበረ ጊዜ ከአረቦች የወረሱት ራስን የማኮፈስ ኩራት። ይህ ስለ ሲሲሊና ስለማፊያ ያለ አመለካከት በራሳቸው በጣልያኖች (በሰሜን ኖቹ) እንዲሁም በሌሎች የውጭ ሀገር ዜጎች ጭምር ትክክለኛ ምልከታን አላገኘም። ለዚህም ነው የሲሲሊያውያን ባህል ከማፊያዊነት ጋር ሲጣረዝና ሲደበላለቅ የኖረው። ሁኔታው "ሁሉም ሰው ጥፋተኛ ከተባለ፣ ማንም ጥፋተኛ የለም" የሚለውን የኢጣሊያውያን አባባል ያስታውሳል።

ማፊያውያን ባሳላፏቸው የአንድ ከተኩል ምዕተ-ዓመት እድሜ ስለእነሱ ይተረክ የነበረው ጥርጣሬን፣ ውሸትንና ጣልቃ ገብነትን ሲፈጥር የኖረ ቢሆንም ይህ ዓይነት መጽሐፍ አጥሮ ሲዘጋጅና ለአንባቢ ሲቀርብ በዚህ ዙሪያ የመረጃ ዋጋው ከፍተኛ ነው።

* * *

በታሪክ ተጠቃሽ ከሆነው የካፓቼው በምብ ፍንዳታና ከዚያም በኋላ ማፊያ በወሰዳቸው ርምጃዎች ከ1,000 ያላነሱ ሰዎች ተገድለዋል። ይህ ቁጥር የማፊያ የክብር ሰዎችን፣ ዘመዶቻቸውን፣ ፖሊሶችን፣ ፖለቲከኞችንና ንፁህ ዜጎችን ያጠቃልላል። ሰዎች በየመንገድ ላይ ተረሽነው ወይም ደግሞ ወደ ሚስጢራዊ ስፍራ ታፍነው ተወስደው ጠፍተዋል። ሰውነታቸው በአሲድ እንዲቃጠል ሁኗል። በየጉድባው እየተገደሉ ተጥለዋል። በባህር እየተጣሉ የዓሳ ነባሪ ቀለብ ሁነዋል። ሰውነታቸው እየተቆራረጠ ለአሳማ ምግብነት ተሰጥቷል። ማፊያዎች በኮርሊኦኔዎች አመራር ዙሪያ ምስጢራዊ የሞት ቡድኖችን በመጠቀም

ጠላቶቻቸውን መንጥረዋል፣ አልፎ ተርፎም በመላው ሲ.ሲ.ሊ. አምባገነን ኃይል ፈጥረዋል፣ ሕብረተሰቡንም በጭካኔ ድርጊታቸው ገዝተዋል፡፡

በማፊያ ታሪክ ጎልተው ከሚወጡ ሰዎች መካከል "የሁለት ዓለሞች አለቃ" የሚባለው ቶማሶ ቡስኬታ አንዱ ነው፡፡ ከአትላንቲክ ማዶ ለማዶ በሚተያዩ ሀገሮች ላይ ማፊያዊ ፍላጎቱን ለመጫን በመፈለጉ ነበር ይህ ስም የተሰጠው፡፡ ቡስኬታ የተያዘው በብራዚል ሲሆን ወደ ጣልያን በሚመልሱት ጊዜም ራሱን ለማጥፋት ሁሌም በኪሱ ይዞ የሚጓዘውን ገዳይ መድሃኒት ወስዶ ነበር፡፡ ይሁንና እንዳሰበው አልሆነም፤ በመርማሪዎች እጅ ወደቀና ከ17 ዓመቱ ጀምሮ አባል የሆነበትን ምስጢራዊ ቡድን ታሪክ የሚያውቀውን ያህል የእምነት ቃሉን ለመናዘዝ ሞከረ፡፡ ኑዛዜውንም ለመቀበል የተመረጠው ሰው ጆቫኒ ፋልኮኔ ነበር፡፡

ፋልኮኔ ድንቅ አእምሮ የነበረውና በአስተዳደጉም የመካከለኛ ገቢ ካለው የማዕከላዊ ፓርሌሞ ከተማ ቤተሰብ የተገኘ ልጅ ነው፡፡ ፋልኮኔ ሲናገር "ከልጅነቴ ጀምሮ የማፊያ ጠረን ይሸተኝ ነበር" ብሏል፡፡ በወጣትነቱ የካቶሊክ ቴኒስ ክለብ አባል ሆኖ ሳለ በኋላ እጅግ ነውጠኛ ከሆነው የማፊያ አባል ቶማሶ ስፓዳሮ ጋር በአንድ ቡድን ሁነው ተጫውተዋል፡፡ የፋልኮኔ ቤተሰቦች በእንደዚህ ዓይነት ወጣቶች ተጽዕኖ ሥር እንዳይወድቅ ሲሉ ሥራ ወዳድ፣ ሃይማኖቱን አጥባቂና ሀገር ወዳድ እንዲሆን አድርገውታል፡፡ በአቃቤ ህግነት የከወናቸው ሥራዎቹ ምስጋናን ያተረፉለት ሲሆን ማፊያን ለመመርመር የተጠቀመበት ብልሃትም "የፋልኮኔ ዘዴ" እስከሚል ስያሜ ያጎናፀፈው ነበር፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ለፋልኮኔ ስለማፊያ ውስጠ-ሚስጢር ዘክዝኮ የነገረው ቡስኬታ ነበር፡፡ ፋልኮኔ ስለ ቡስኬታ የመረጃ ጠቃሚነት ሲናገርም "ለእኛ እሱ ካለምንም የምልክት ቋንቋ እንድንግባባ ያደረገን መምህር ነው" ሲል አቆላምጦታል፡፡

ፋልኮኔ በማፊያው አለቃ ቡስኬታ ላይ ባደረገው የረጅም ሰዓታት ምርመራ ስለድርጅቱ ምሉዕ የሆነ ግንዛቤ ጨብጧል፡፡ በተረጋጋ መንገድም በገጽታ፣ በስምና በወንጀል መከላከል ያለውን ቁርኝትም ተረድቷል፡፡ የማፊያን የዕዝ መዋቅር፣ ዘዴና አስተሳሰብ ለማወቅም

ችሏል። ከዚህ በተጨማሪ ፖሊሶችና የተለያዩ መርማሪዎች "ኮዛ ኖስትራ" የሚለው መጠሪያ በአሜሪካ ለሚገኘው የወንጀል ድርጅቶች መጠሪያ አድርገውና አቃለው ነበር የሚመለከቱት። ዳሩ ግን ለኢጣልያው ማፊያም በመጠሪያነት እንደሚያገለግል ከመረዳት ባለፈ የኮዛ ኖስትራን የፒራሚዳዊ የዕዝ-መዋቅርን ቡስኬታ የነገረው ዘከዝኮ ነበር።

የማፊያ አወቃቀር ከጓድ (በአሥር ሰው) ደረጃ ተነስቶ ወደ ኮሚሽን ደረጃ የሚያድግና የተያያዘ ሲሆን እያንዳንዱ ጓድም የራሱ መሪ አለው። የጓድ መሪው በአካባቢው ለተመረጠ የማፊያ ቤተሰብ አለቃ ተጠሪ ነው። የማፊያ ቤተሰብ አለቃው ደግሞ ከጎኑ ምክትልና አማካሪዎች አሉት። ሦስት የማፊያ ቤተሰቦች ደግሞ በአንድ ወረዳ ሥራ ይጠቃለላሉ። የወረዳው የማፊያ አለቃ የአጠቃላይ የማፊያ ኮሚሽን አባል ሲሆን በክፍለ ሀገር ደረጃ (በሲሲሊ) የማፊያ አለቆች ይሰየማሉ። በተግባር ሲታይ ግን በፓሌርሞ አካባቢ አለቆችና በሲሲሊ ማፊያ ውስጥ የበላይነት ያላቸው ናቸው። በሲሲሊ ካሉ 100 የማፊያ ቤተሰቦች ውስጥ 50ዎቹ ቤተሰቦች ያሉት በፓሌርሞ አካባቢ እንደሆነ ይታወቃል።

ቡስኬታ ቃሉን በሰጠበት ወቅት እንዳረጋገጠው በድርጅቱ ውስጥ 5,000 የክብር አባላት የታቀፉ ሲሆን፣ ከሁሉ በላይ መርማሪዎችን እጅግ ያስደመመው ግን የድርጅቱ ውስጣዊ ዲስፕሊን ነበር።

በተግባር እንደተረጋገጠው ከሆነ የሲሲሊ ማፊያ የወለደው የአሜሪካው "ኮዛ ኖስትራ" ተመሳሳይ መዋቅር ያለው ሲሆን በድርጊት ግን የተለያዩ ድርጅቶች ናቸው። በመሆኑም አንድ የሲሲሊ ማፊያ አባል የአሜሪካ የማፊያ አባል ተደርጎ አይወሰድም። በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት የሚተሳሰረው በደምና በንግድ ሥራ ብቻ ነው።

ከማፊያ አለቆች እና ወደገቦች የተሰበሰበው መረጃ 8 ሺህ 607 ገፆች ያሉት ትልቅ ማህደር የወጣው ሲሆን 342 ማፊያዎች ላይ ፍርድ ተሰጥቷል። በጠቅላላው 2665 ዓመታት የሚቆጠር የእስር ፍርድ ውሳኔ ተላልፉአል። ምንም እንኳ መርማሪ እና ዳኞች ለመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ቢደርሱም ማፊያ ደግሞ ገዳይ ቡድኖችን በማሰማራት ዳኛ ፋልኮኔን እና ሌሎች የህግ ሰዎችን፣ ፖለቲከኞችንና ፖሊሶችን ፈጅቷል።

ይህ መጽሐፍ እስካሁን ከታተሙትና የማፊያን ምስጢራዊ ታሪክ ከሚያጋልጡ መጽሐፍት አንጻር ከማፊያ አመሰራረት እንስቶ የድርጅቱን ውስጠ-ሚስጥር በዝርዝር የሚያመላክት ነው:: መጽሃፉ ጥቃቅን የማፊያ ጉዳዮችን በማንሳት ታሪካዊ ገለጻዎችን በስም፣ በገጽ፣ በቦታና፣ በወንጀሉ ዓይነት ዘርዝሮ ስለሚያቀርብ ምሉዕ የሆነ ስዕል ለአንባቢው እንደሚሰጥ ይታመናል::

በዛሬዋ ዓለማችን ኮዛ ኖስትራ በጣልያንና በአሜሪካ ብቻ የተገደበ አይደለም። "ማፊያ ሀገር አለው" (mafia has the country) የሚለው ብሂል በተለያዩ ሀገራት እውነት እየሆነ ነው። የማፊያ መንግስታት ተቋቁመዋል። በማፊያ መንግስታት ውስጥ የመንግስት ሹመኞች ራሳቸውን በሀብት አሳብጠዋል። ዘመዶቻቸው፣ ወገኖቻቸው እና ጓደኞቻቸው የሕዝብን ገንዘብ ተመሳጥረው ያዘርፋሉ። በዚህም ጡንቸኛ ይሆናሉ። ያሻቸውን ያደርጋሉ። ተፈጥሮአዊ ሞትን ከመቋቋም በመለስ ያለውን ሁሉ ያደርጋሉ። የፖለቲካ ተጽእኖ ያሳድራሉ። ከሌሎች አለም አቀፍ ጉልበተኞች ጋር ተመሳጥረው የራሳቸውን ስልጣን ያጠናክራሉ። ስለዚህ ማፊያ ስል የሆኑ ፕሮፌሽናል ወንጀለኞችን ብቻ ያቀፈ አይደለም። በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ዳኞች፣ የደህንነት ሹሞች፣ የፖሊስ አዛዦች፣ ወታደራዊ መኮንኖች፣ አንዳንዴም ጥግ በደረሰ ሁኔታ የሀገር መሪዎችን ወይም ቤተሰቦቻቸውን የሚያጠቃልል ሊሆን እንደሚችል ይህ መጽሐፍ እንደማገናዘቢያ ይጠቅማል። እያዝናናም ያስተምራል።

መልካም ንባብ።

# 1

# የማፊያ አፈጣጠር

## ምስለ-ማፊያ (ኮዛ ኖስትራ)

ኢጣልያ ለዓለም ቋንቋዎች ካበረከተቻቸው እንደ "ፒሳ፣ ስፓጌቲ፣ ኦፔራ፣ ዲዛስተር" ካሉ ቃላት ጋር "ማፊያም" ይደመራል። ማፊያ ከሲሲሊ ደሴት አንስቶ እስከ አሜሪካ የተዘረጋ ነውጠኛ ቡድን ነው። በዛሬ ጊዜ በዓለም የተንሰራፉት የቻይና፣ የጃፓን፣ የሩሲያ፣ የቼችን፣ የአልባኒያ የቱርክና የሌሎች ሀገሮች ነውጠኞች በዚሁ ቅፅል ስም ይጠራሉ።

በራሷ በኢጣልያ የተለያዩ አካባቢዎች በተለያዩ ስሞች የሚጠሩ ማፊያዎች አሉ። "ሳክራ ኮሮና ዩኒታ፣ ካሞራ፣ ንድራጌታ" የመሳሰሉ ሌሎች የማፊያ ቡድኖች አሁንም የአካባቢው ንጉሥ ሆነው ያስገብራሉ።

የሲሲሊ ማፊያ ስልጣንና ገንዘብን የሚያገኘው ሰዎችን በመግደልና ራሱን በተለየ መንገድ በማደራጀት ሲሆን የራሱን "ጥላ መንግስት"፣ ሕገ ወጥ ቢዝነስና ሚስጥራዊ ማህበረሰብን በመፍጠር ይንቀሳቀሳል።

ኮዛ ኖስትራ የሲሲሊ ማፊያ ምስጢራዊ ድርጅት ነው። (ቀጥታ ትርጉሙ "የእኛ ጉዳይ" /our affair/ ማለት ነው።) ኮዛ ኖስትራ የራሱን ግዛት ይዞ የሚንቀሳቀስ መንግስት መሰል የማፊያ ቡድን ሲሆን በተወሰነ ክፍል የራሱን "መንግስታዊ-ጥላ" ፈጥሮ ታክስ ያስከፍላል፣ የሚቀናቀኑትን እየነቀሰ አውጥቶ ይገድላል። ማፊያ ማናቸውንም ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ባሉባቸው ሥፍራዎች ሁሉ በመገኘት ግብር ይጥላል። ወንጀለኞችና ቀማኞች ሳይቀሩ "ፒሶ" (Pizzo ቀረጥ) ይከፍላሉ። ማንኛውም ማፊያ (Mafioso) አንድን የመኪና ነጋዴንም ሆነ የመኪና

ሌባን እንዳይነኩ ጠባቂ ዘብ ሆኖ ሊቆምላቸው ይችላል። ስለዚህ ከህጋዊም ሆነ ከህገ ወጥ ወገን ብቸኛው ተጠቃሚ ማፊያ ብቻ ነው። በመሠረቱ ማፊያ አማራጭ መንግስት ሳይሆን በመንግስት ህጋዊ መዋቅር ውስጥ በመስረግ የራሱን ጥቅም የሚያራምድ መሰሪ ድርጅት ነው።

"ኮዛ ኖስትራ" ትልቅ የቢዝነስ አካል ነው። ምክንያቱም በማስፈራራት መንገድ ትርፍ ያጋብሳል። ስለዚህ በማናቸውም መንገድ ጡንቸኛ ነው። የመግደል ተግባሩን ሕጋዊ ለማድረግ ዳኞችን፣ ጠበቆችን፣ ጋዜጠኞችን፣ ፖሊሶችን፣ ፖለቲከኞችን ገዝቶ ያሰልፋል።

ኮዛ ኖስትራ ምስጢራዊ ማህበረሰብ ሲሆን አባሎቹን በከፍተኛ ጥንቃቄ በመመልመል በባህሪያቸው ላይ ውልፍጥ የማያደርግ ገደብን ይጥላል። ዋነኛው "ኮዛ ኖስትራ" ከአባላቱ የሚፈልገው ባህርይ ምስጢር ጠባቂነትን፣ ፍፁም ተገዢነትንና ሽብር ለመፍጠር ወደኋላ አለማለትን ነው።

የተወሳሰበ ታሪክ ያለው ይህ የማፊያ ማህበረሰብ አሁንም ቢሆን ብዙ ያልተመለሱ ጥያቄዎች አሉበት። ይህ ሕገ-ወጥ ድርጅት እንዴት ጠንካራና ለመረዳት የሚያስቸግር ሆነ? ለዚህ ጥያቄ የሚቀርበው መልስ የማስረጃ አለመገኘት ነው ቢባልም ማፊያ ለ150 ዓመታት ያህል የኖረው ምስክሮችን በማስፈራራት፣ ፖሊስና ፍ/ቤቶችን ሙሰኞች እያደረገ በመዝለቁ ነው። ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ሳይቀሩ የማፊያ መጠቀሚያዎች ሆነዋል። ሰባት ጊዜ የኢጣልያ ጠቅላይ ሚኒስትርና የዕድሜ ዘመን ሴናተር የሆኑት ጁሊያ ኢንዲሪዩቲ በማፊያነት ያጋለጣቸውን ጋዜጠኛ እንዲገደል በማድረግ ይወቀሳሉ። የጠቅላይ ሚኒስትር ሲልቪዮ በርሎስኮኒ ፓርቲ የሆነው "ፎርሳ ኢታሊያ" ከ"ኮዛ ኖስትራ" ጋር ስምምነት እንደነበራቸው ፀሐፍት አረጋግጠዋል። የማፊያው ቀንደኛ መሪ የነበረው ቶማሶ ቡስኬታ የአንዲሪዮቲን ሁኔታ ለፍ/ቤት ቀርቦ መስክሯል።

በወቅቱ ቡስኬታ ምስጢር ያለማውጣትንና "የክብር ሰውነትን" (Man Of honor) በጥሶ የወጣ የማፊያን የዝምታ (Omerta) አሰራር ቀድሞ የሰበረ በመሆን ይታወቃል። ምንም እንኳን ዝምታን ሰብሮ

ምስክርነቱን በህግ ፊት ቢያቀርብም በኢጣልያ መንግስት አስራር ፍ/ቤቶች ከመጤፍ ቆጥረውት ውሳኔ ሰጥተውበት አያውቁም፡፡

"የክብር ሰው" ዋነኛው የማፊያ የአሰራር ዘዴ ነው፡፡ "የክብር ሰውነት" ቁጥብነትና ሚስጢራዊነት ሲሆን በኮድ መነጋገር ወይም ትርጉም ያለው ዝምታን ይይዛል፡፡ "በኮዛ ኖስትራ" ማንም ሰው መናገር ወይም መጠየቅ ካለበት በላይ ሌላ ነገር ውስጥ ገብቶ አይዘባርቅም፡፡

ማፊያ ገና በ1860 እንደተመሰረተ የተለያዩ ስሞችን ይዞ ተነስቷል፡፡ ወንድማማቾች፣ «የተከበረ ማህበረሰብ»ና አሁን ደግሞ «ኮዛ ኖስትራ» በሚል፡፡ ጊዜ እየተለዋወጠ ይሂድ እንጂ የማፊያ ደመኛና የተቀናጀ ዘዴ አሁንም ይሰራል፡፡ ከሲሲሊ የሎሚ ማሳ የተነሳው ማፊያ ዛሬም እስከ ማንሃተን ጎዳናዎች ይንቀሳቀሳል፡፡ ስለዚህ ይህን ምስጢረኛ ድርጅት ለማወቅ ውስብስብ አሰራሮቹን ማጤን ያስፈልጋል፡፡

## የሲሲሊ ሁለት መልኮች

የሲሲሊዋ ፓሌርሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የኢጣልያ ከተማ የሆነችው ሰኔ 1860 የተኩስ ማቆም ስምምነት ከተፈፀመ በኋላ ነበር፡፡ በወቅቱ የተሸነፉ ወታደሮች በሰልፍ እንደ እባብ እየተጠመዘዙ ወደ "ኔፕልስ" ለመጓዝ ባህሩ ዳርቻ ላይ ተጠባበቁ፡፡ ከዚያ በፊት ሲሲሊ የምትገዛው በኔፕልስ ቁጥጥር ሥር እንደነበር ታሪክ ያስታውሳል፡፡ በግንቦት፣ 1860 በጁሴፔ ጋሪባልዲ በሚመሩና አንድ ሺህ በሚጠጉ ወደ ዘማች ባለቀይ ሸሚዞች ነፃ ወጥታ ከአዲሲቱ ኢጣልያን ጋር ተቀላቀለች፡፡ ፓሌርሞ ነፃ እንደወጣች ጋሪባልዲ ሠራዊቱን አጠናክሮ ወደ ዋናው የኢጣልያን ግዛት ገሰገሰ፡፡ መስከረም እንደባተ በኔፕልስ የጀግና አቀባበል ተደረገለት፣ ከወር በኋላ የያዛቸውን ግዛቶች ለጣልያን ንጉስ አስረከበ፡፡ የቀረበለትን ስጦታ ላለመቀበል በመወሰን ወደተወለደባት ደሴት "ካፕሬራ" ጥቂት ጓዞቹንና ለማሳው የሚሆኑ ያህል ዘሮችን ጠቅልሎ ተመለሰ፡፡ ታሪክ እንደመሰከረው ጋሪባልዲ ሲሲሊንና ደቡባዊ ኢጣልያን ከዋናው የኢጣልያን ግዛት ጋር ያቀላቀለ ጀግና ነበር፡፡

ምንም እንኳን የጋሪባልዲ ድርጊት አስመስጋኝና ወደር የሌለው ቢሆንም የሲሲሊ ማንኑነት ከሌላው የኢጣልያን ክፍል ጋር በተቃራኒው የሚታይ ሆኗል፡፡ ይህች ተራራማ ደሴት "አብዮታዊ የባሩድ ቀለህ»

ተብላ ትታወቃለች፡፡ በወቅቱ የ2.4 ሚሊዮን ሕዝብ ከአዲሲቷ ኢጣልያን ጋር ሲቀላቀል ሜራን፣ ዘረፋንና ሌሎች ወንጀሎችን ያነሳሳም ሆኗል፡፡

የኢጣልያን ንጉሥ ሚኒስትሮች አብዛኛዎቹ ከሰሜናዊ ኢጣልያ የተውጣጡ ከበርቴዎች በመሆናቸው ከደቡቦችም የራሳቸውን ብጤ በመፈለግ መልካም መንግስትንና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማምጣት ይተጉ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ተባባሪ የሚሆኑ ሰዎችን ከማግኘት ይልቅ ያልጠበቁት ተቃውሞ ገጠማቸው፡፡ በተለይ የኢጣልያ መንግስት በሲሲሊ የማይታወቀውን ወታደራዊ አገልግሎት በማወጁ ተቃውሞ በረታ፡፡ ሲሲሊያውያኑ የአርበኝነት አብዮቱ ካጎናፀፋቸው ድል አንዱ ታክስ አለመክፈልን አድርገው ይገምቱ ስለነበር ህጋዊ መንግስታዊ አሰራሩን መቃወም ቀጠሉ፡፡ በ1862 ራሱ ጋሪባልዲ በሁኔታው ባለመደሰቱ ጣልያንን ወግቶ ሮማ ከተማን ለማጥቃት አስቦ ነበር፡፡ ሆኖም ግን በፓፓው ሥር የምትተዳደረውን ሮማን ከመያዙ በፊት የጣልያን ጦር "ካላብሪያ" ላይ የጋሪባልዲን ምኞት አጨናገፈው፤ እንዲያውም በተኩሱ መሃል እግሩ ላይ እንዲቆስል ሆነ፡፡ ለዚህም ነው ሮማ እስከ 1870 ድረስ የኢጣልያ ዋና ከተማ ሳትሆን የቆየችው፡፡ የጣልያን መንግስት በጋሪባልዲ ጥቃት በመደናገጡ በሲሲሊ ወታደራዊ ህግን አወጀ፡፡ በመሆኑም የሲሲሊን የፖለቲካ ድጋፍ ሊያገኝ አልቻለም፡፡ የተከፈተው ወታደራዊ እርምጃ ተጠናክሮ ጦሩ ከተማ ውስጥ እንዲሰፍር ተደረገ፡፡ የጅምላ እስርና ካለፍርድ መጋዝ ቢስፋፋም ሁኔታው ባለበት እየረገጠ ሄደ እንጂ አላገገመም፡፡ ከብዙ ጊዜ በኋላ (ከ1876) ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሲሊያውያን በአዲሱ የኢጣልያን መንግስት ውስጥ ውክልናን አግኝተው ሁኔታው የተሻሻለው፡፡

ሌላዋ የሲሲሊ ከተማ ፓሌርሞ ናት፡፡ ጋሪባልዲ አካባቢውን ባጠቃ ጊዜ አብዮታዊ ቡድኖች ከአካባቢው ኮረብቶች ወደ ከተማዋ አመሩ፡፡ በከተማዋ ውስጥ ሰፊና ሰቅጣጭ ወሬዎች ተሰራጩ፡፡ "ሰው የሚበሉና ደም የሚመጡ" ነውጠኞች ገብተዋል እየተባለ በሰፊው ስለተነዛ ከተማዋ ዳግም በወታደራዊ ዕዝና አገዛዝ ሥር ወደቀች፡፡ የፓሌርሞ ውብ አቀማመጥ ለመጤዎች እጅግ አስደማሚና ልብ ሰቃይ ነው፡፡ የጋሪባልዲ ተዋጊዎች በመጀመሪያ ሲመለከቷት "የአፍላነት ዘመንን ቅኔያዊ ርዕይ የምታሟላ ከተማ ናት" ሲሉ መስክረውላታል፡፡ የከተማዋ ግድግዳዎች

በሎሚና በወይራ ዛፍ የተዋቡ፣ ከጆርባው የሚታየው ተረተር ደግሞ ተፊጥሯዊ የአምፊ ቴአትር መልክ በያዙ ኮረብቶቿ በአራት ማዕዘን (Quattro Canti) ተገናኝተው በ17ኛ ክ/ዘመን ጀምር አንድ አደባባይ (Piazza) ፈጥረዋል። በእያንዳንዱ ማዕዘን የሚታዩት የባልኮኒና የኮርኒስ ገፅታዎች የከተማዋን አራት ማዕዘናት ያንፀባርቃሉ። ከተማዋ ባህር ዳርቻ ላይ በመቆርቆሯ ማለቂያ የለሽ በሆነው የበጋ ወቅት ነዋሪዎቿ ጋሪዎቻቸውን ይዘው የሽቱ መዓዛ ባላቸው ዛፎች መሃል ይንሸራሸራሉ ወይም አይስክሬምና በረዷማ ውሃ እየጠጡ የከተማው ባንድ የሚጫወተውን ሙዚቃ ያጣጥማሉ።

ሌላው ፓሌርሞን የጎበኘ ሁሉ የሚደነቅበት በቁጥር ከ194 ያላነሱ የማምለኪያ ሥፍራዎች መኖራቸው ሲሆን ቁጥር ስፍር በሌላቸው መነኩሴዎችና መነኩሲቶች መሞላቱ ይበልጥ ያስደምማል። ፓሌርሞ የተለያዩ ባህላዊ ቅርሶች አሻራቸውን የጣሉባት ከተማ ናት ማለት ይቻላል። እንደሌሎቹ የሲሲሊ ደሴት ከተሞች ወራሪዎች ደሴቷን በያዙ ቁጥር ሰርተው ያለፉት ሃውልቶች ተከማችተውባታል። ከጥንት የግሪክና ሌሎች የሜዲትራንያን ጉልበተኞች፣ ማለትም ከሮማውያን እስከ በርበንስ ድረስ ሲሲሊን የግላቸው አድርገው አልፈዋል። የግሪክ አምፊ ቴአትር፣ የሮማውያን ቪላዎች፣ የአረብ መስጊዶችና የአበባ ሥፍራዎች፣ የኖርማ ካቴድራሎች፣ የህዳሴው ዘመን ቤተመንግስቶች፣ የባሮክ ቤተ ክርስቲያናት... ደሴቲቱን ልዩ ውበት የሚሰጡአት መስህቦች ናቸው።

ሲሲሊ በሁለት ቀለሞች የምትመሰል ደሴት ናት። በአንድ ወቅት የሮማ የእህል ማከማቻ መጋዘን የነበረች ስትሆን ከዚያም በኋላ ለብዙ አመታት ስንዴ በሰፊው የሚመረትባት ወርቃማ አውድማ ሆና ቆይታለች። ሌላኛው የደሴቲቱ ቀለም የቅርብ ጊዜውን መልክ የያዘ ነው። ዐረቦች በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ሲሲሊን ከወረሩና ከያዙ በኋላ አዲስ የመስኖ ቴክኒክ፣ የሎሚ፣ የብርቱካንና የወይን ፍራፍሬዎችን በአካባቢው አስተዋወቁ። በዚህም ምክንያት ሲሲሊ የተለያዩ ባህላዊ እሴቶችን ይዛ ቆየች።

ወደ ዋናው ነጥብ እንመለስና የኢጣልያ ገዢዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ሲሲሊ ማፊያ የሰሙት በ1860ዎቹ ችግር ውስጥ በገቡ ወቅት ነበር። ግልፅ የሆነ ሀሳብ ስለ ማፊያ ሳይኖራቸው ከመካከለኛው ዘመን

ተያይዞ የመጣ ኋላቀር ሁኔታ አድርገው ተመለከቱት:: እንደሚታወቀው የሲሲሊ ተፈጥሯዊ ውበትና እህል አብቃይ መሬቶቿ ለሰፊው ሕዝቧ እምብዛም የጠቀመ አልነበረም:: ረሀብተኛ ገበሬዎቿ እጅግ ጨካኝ በሆኑ አለቆቻቸው ይበዘበዙና ይጨቆኑ ነበር:: በዚህም የተነሳ ብዙ ጣልያኖች ማፊያን የዚህ ግፍና ኋላቀርነት ምልክት አድርገው ይቆጥሩታል:: አንዳንድ በጎ አሳቢዎች "ማፊያ በአንድ የባቡር ድምፅ ድምጥማጡ ይጠፋል" እስከማለት ቢደርሱም እስከዛሬ ድረስ ፈፅሞ ሊሞት አልቻለም:: ምክንያቱም ለማፊያ የተገዙ የክብር ሰዎች (Men of honours) ይበልጥ ማፊያ እንዲጠናከር ረዱ:: ቶማሶ ቡስኬታን የመሳሰሉ ሰዎች እንኳ ሳይቀሩ ማፊያ የተጀመረው በመካከለኛው ዘመን የፈረንሳይ ወረራዎችን ለመመከት የተነሳ ተቃውሞ አድርገው ይገምቱ ነበር:: ዳሩ ግን የማፊያ መነሻ መሠረት ጥንታዊ አልነበረም:: ማፊያና አዲሲቱ የጣልያን መንግስት በአንድ ላይ የተወለዱ ናቸው:: ማፊያ የተወለደው በወርቃማዋና ቢጫዋ የማፊያ ዕምብርት ሲሲሊ ሲሆን ከዚያም እየጎለበተ የሄደው ሀብት በተከማቸባቸው ዙሪያ ገባውን ዳርቻ ላይ ነበር፤ በተለይ ብርቱካንና ሎሚ ኤክስፖርት በሚደረግባት የፓሌርሞ ወደብ ላይ::

## የክብር ሰዎች

ቁጥር ሥፍር የሌላቸው ፊልሞችና ልብ ወለዶች የማፊያን ወንጀለኝነት አድበስብሰው ውብ ቅርፅ ይሰጡታል:: ምንም እንኳን በሲኒማና በልብ ወለድ የሚቀርበው በሙሉ ውሸት ነው ባይባልም፣ ተቀባብቶ የሚተወን ድራማ ነው:: ማፊያዎችም (Mafiosi) እንደ ማናቸውም ሰው በመሆናቸው የየዕለት ድራማቸውን በሲኒማ ሸራ ላይ ሲቀርብ ይደሰቱበታል:: ለምሳሌ ቶማሶ ቡስኬታ "የጡት አባት" ፊልም ታላቅ ወዳጅ ነበር:: በፊልሙ ውስጥ ሌላው የማፊያ አባል የማይክል ኮርሊዮንን እጅ የሚስምበት ሁኔታ ግን በማፊያ የእውነተኛ ታሪክ ውስጥ የለም:: የተዋናዩ የማይክል ኮርሊዮ ገፀ ባህርይ ጉትትን፣ ኃላፊነትትንና ቤተሰብን ያቀናጀ አኗኗር ከእውነተኛው የማፊያ አባላት ጋር በእጅጉ ተቆራኝቷል::

በማፊያ አሰራር "የክብር ሰው" ማዕረግ ያገኘ ማፊያ በቀላሉ የማታለል፣ ነገር ለመፍተል ወይም ማፊያዎች የሚመሩበትን መመሪያ

ለማውጣት ወይም እንደገና ለመፃፍ ይችላል። ክብር ልዩ ትርጉም አለው በኮዛ ኖስትራ አሰራር። "የክብር ሰው" የሆነ የማፊያ አለቃ ያልተቋጩ ጉዳዮች እንኳን ቢኖሩ ለአባላቱ የመግለፅ ስልጣን አለው። ለምሳሌ እንደ ጆቫኒ ቡርስካ የመሳሰሉ ገዳዮችን ሁኔታ ለመግለፅ ይቻላል። በነገራችን ላይ ቡርስካ በኮዛ ኖስትራ ውስጥ "lo Scannacristiani" "የክርስቲያኖች ጉሮሮ ቆራጭ" ተብሎ ይታወቃል፣ በሲሲሊ ውስጥ ክርስቲያን ማለት "የሰው ልጅ" ማለት ሲሆን በማፊያ ደግሞ "የክብር ሰው" የሚለትን ያህል ትርጉም አለው። ቡርስካ ዋናው የገዳይ ቡድን አለቃ ሲሆን ለአለቆች አለቃ ለሆነው ለቶቶ ሪና ነው ሪፖርት የሚያደርገው። የቡርስካ ቡድን በገዳይነቱ የታወቀና የአልካምን ቤተሰቦችና ነፍሰ ጡር ወዳጁን ሳይቀር ገድሏቸዋል።

ይህ "የክርስቲያኖች አንገት ቆራጭ" (ቡርስካ)፣ ሳንቲኖ ዲ ማቲኦ ለተባለው ሌላኛው የክብር ሰው ጓደኛ ሲሆን ማቲኦ ጁሰፔ የተባለ ትንሽ ልጅ ነበረው። ትንሹን ጁሰፔ በቤተሰብ ቅጥር ግቢ ቡርስካ በወዳጅነቱ ያጫውተዋል። ይህ ሁሉ ታዲያ የነበረው ማቲኦ የማፊያን ሚስጢር ለመንግስት አሳልፎ ከመስጠቱ በፊት ነበር። ማቲኦ የማፊያን ሚስጥር አሳልፎ እንደሰጠ ሲደርስበት ቡርስካ ትንሹን ጁስፔን ለስድስት ወራት አግቶ አሰቃይቶታል። ከዚያም ጥር 1996 ጁስፔ ገና 14 ዓመት እንደሞላው ታንቆ እንዲገደልና በአሲድ ሰውነቱ እንዲቃጠል አድርጓል።

ከሁለት ወር በኋላ ይህ "የክርስቲያኖች አንገት ቆራጭ" ቤቱ ተከበበ። አራት መቶ ፖሊሶች ቤቱን ከበው በነበረ ጊዜ ቡርስካ ከቤተሰቡ ጋር ተቀምጦ በማፊያ ስለተገደለው ዳኛ ፋልኮኒ ዜና ይመለከት ነበር። ፖሊስ ቤቱን ሲበረብር ከመኝታ ክፍሉ እጅግ ውድ የሆኑ የቬርሳቼና የአርማኒ ብራንድ ልብሶችን፣ በቀይ ሻንጣ የታጨቀ 15 ሺህ ዶላር፣ ጂኤስኤም /GSM/፣ የሞባይል ስልክና ዕንቁዎች ተገኝተውበታል።

"ክብር" በማፊያ የታዛዥነት ጉዳይ ነው። ለማፊያ ከደም ትስስር ይልቅ "የክብር ማህበረሰብ" አባልነት የበለጠ ሥፍራ አለው። የኮዛ ኖስትራን ፍላጎት ከዘመድ አዝማድ ፍላጎት ማስበለጥን ይጠይቃል። ለምሳሌ ኤንዞ ቡርስካ (የቡርስካ ወንድም) በተለያዩ የግድያ ወንጀሎች የተካፈለ ቢሆንም የክብር ሰው ሆኖ አያውቅም። ስለ ዘመዶቹ መጠየቅ ካለመቻሉም በላይ በኮዛ ኖስትራ ውስጥ ስላላቸው ሥፍራ በሚዲያ

ከሚቀርበው ውጭ አያውቅም። እንዲያውም ለብዙ ጊዜያት የገዛ አባቱ የአካባቢ ማፊያ አለቃ መሆኑን ሳያውቅ ኖሯል። ሌላው ቀርቶ ለጋብቻ እንኳን ከአካባቢው የማፊያ አለቃ (ካፖ) ፈቃድ ሳያገኝ አንድ ማፊያ ሚስት ማግባት አይችልም። በአብዛኛው ግን ብዙ ማፊያዎች የሚያገቡት "የክብር ሰው" ልጆችን ወይም እህቶችን ነው። ሴቶች በማፊያ ቤተሰብነት የሚኖሩ ከሆነ የማፊያን ጉዳይ የመደገፍ ግዴታ አለባቸው። በማፊያ አሰራር ግን ሴቶች በአባልነት አይመለመሉም፣ "ክብርም" የሚሰጠው ለወንዶች ብቻ ነው።

በአንድ ወቅት ዳኛ ፋልኮኔ ማፊያን ከኃይማኖት . ጋር ነበር ያወዳደሩት። "አንድ ወደሌላ እምነት የተቀየረ ሰው ቄስ ከመሆን አይመለስም፣ ማፊያ የሆነም ማፊያነቱን አይለቅም" ነበር ያሉት። ማፊያዎችና ኃይማኖት በመሠረቱ የሚነጣጠሉ አይደሉም። ብዙዎቹ የክብር ሰዎች አማኞች ናቸውና። ለምሳሌ የማፊያው ኃላፊ ኒቶ ሳንታፓኦላ መስገጃያና አንድ አነስተኛ የዕምነት ሥፍራ ከቪላው ጋር አስገንብቶ ነበር። ላይ ላዩን ኃይማኖተኛ ይምሰሉ እንጂ እንደነዚህ አይነት ሰዎች የተረገሙ ናቸው። አንድ የማፊያ ወዶ-ገብ (Pentito) በአንድ ወቅት አራት ህፃናት እናቱን በማታለላቸው ታንቀው ጉድጓድ ውስጥ እንዲጣሉ ማድረጉን ተናዟል። እንደ "ክርስቲያኖች አንገት ቆራጭ" ሁሉ ብዙዎቹ ከፍተኛ የማፊያ ኃላፊዎች የመግደል ተግባር ከመፈፀማቸው በፊት "እግዚአብሔር በሚያውቀው በእጄ እንዲጠፉ ያደረጉ ራሳቸው እንጂ እኔ አይደለሁም፣ እኔ መወቀስ የለብኝም" ብለው እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንፁህ ነኝ የሚሉ ናቸው።

የካቶሊክ ቤተክርስቲያንና ቄሶቿም ቢሆኑ ይህን ድርጊት አይናቸው እንዳላየ ሆነው እንደሚያልፉ ይታወቃል። እንዲያውም ቤተክርስቲያናት እነዚህ ሰዎች እጃቸው በደም የጨቀየ መሆኑን እያወቁ እርዳታ ከማፊያ አለቆች ይቀበላሉ። እንዲያውም አንዳንድ የቤተክርስቲያን የቅርብ ሰዎች የታወቁ ገዳዮች ናቸው። ስለዚህ ማፊያዎች የራሳቸው የዕምነት መንገድ አላቸው። ማፊያዎች ሰዎችን ሲገድሉ ከገንዘብና ከስልጣን በላይ ባለ አንድ የግል ዕምነታቸው ይህን ድርጊት እንደሚፈፅሙ ያምናሉ። ስለሆነም "ክብር" እና "እግዚአብሔር" ከአፋቸው ጠብ አይሉም።

ለማፊያዎች "ክብር" ሙያዊ ዋጋ ያለው ታላቅ ነገር ሲሆን የቡድኑን ማንነት ይበልጥ የሚያጎላ ከመልካም ወይም ከክፉ ነገር ሁሉ ጀርባ ያለ ነው። ስለዚህ ማፊያነት ከሲሲሊያውያን ባህል ወይም ከካቶሊካዊነት ጋር ፈፅሞ አይገናኝም። "ክብር" የድርጅቱ የኩራት መንፈስ ነው። በአንድ ወቅት የካታኒያው ማፊያ አንቶኒዮ ካልዴርን ሲናገር "እኛ ማፊያዎች ነን፣ ሌሎች ግን ያው ተራ ሰዎች ናቸው" ሲል ለማፊያ "ክብር" ልዩ ቦታ እንዳለው ገልጿል። አንድ ማፊያ "ክብር የለሽ" ከሆነ አልባሌ ሰው ተደርጎ ይቆጠራል።

ማፊያዎች በተለይም "የክብር ሰዎች" ሲያዙ ለመንግስት ሚስጢር አይወጡም። ምክንያቱም የሚገዙት "ዝምታ" (Omerta) በሚል ኮድ ነውና። ዝምታውን ላለመስበር ስለሚደረግ የማፊያዎች ጥረት አንድ ምሳሌ እናንሳ። በ1993 ኒኖ ጆይ በታሰረበት እስር ቤት እንዳለ በቴኒስ ጫማው ማሰሪያ ገመድ ራሱን አንቆ መንግስትን ኩም አድርጓል። በመጨረሻም ፅፎ ያስቀመጠው ማስታወሻ እንደሚከተለው ይነበባል፦

*"ከአስራ ሰባት ዓመት በፊት (ኮዛ ኖስትራን ከተቀላቀለ ጀምሮ ማለቱ ነው) ያጣሁትን ሰላምና ደስታ በዚህ ምሽት አግኝቻለሁ። ሰላምና ደስታዎቼን ባጣሁ ጊዜ ጭራቅ እሆናለሁ። እነዚህን መስመሮች ለመፃፍ እስከምንሳሳ ድረስ ጭራቅ ነበርኩ... ወደ ማልመለስበት የወዲያኛው ዓለም ከመሄዴ በፊት ይቅርታን ከእናቴና ከእግዚአብሔር ዘንድ እለምናለሁ፣ ምክንያቱም ፍቅራቸው ወሰን የለውምና። ሌላው ዓለም ግን ፈፅሞ ይቅርታ ሊያደርግልኝ አይችልም።"*

# 2

# ዶ/ር ጋላቲ፣ የሎሚው ማሳና የደም ምህላው

የማሬያ ዘዴዎች እጅግ ስልተው የወጡት የፍራፍሬዎች ኢንዱስትሪ በተስፋፋበት ዘመን ነው። ሎሚ የኤክስፖርት ምርት ሆኖ ታዋቂነትን ያገኘው በ1700ዎቹ ሲሆን ከዚያ በኋላ በመካከለኛው የ19ኛ ክፍለ ዘመን በሲሲሊ የፍራፍሬዎች ምርት እጅግ እየተስፋፋ ሄደ። ለዚህ ደግሞ ዋናውን ሚና የተጫወተው የብሪታንያ የአኗኗር ዘዴዎች መለወጣቸው ነበር። አንደኛው ምክንያት በ1795 የብሪታኒያ ሮያል ባህር ኃይል ሎሚን ለድድ በሽታ መድኃኒትነት በስፋት መጠቀም መጀመሩ ሲሆን፣ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የቤርጋሞት ተክል ለዘይትነት ስለሚያገለግል ሎሚና መሰል ፍራፍሬዎች 'ለኤርል ግሬይ' ሻይ ጣዕም መስጫነት በሰፊው ጥቅም ላይ በመዋላቸው ሰፊ ምርት ከ1840ዎቹ ጀምሮ በኢንዱስትሪ ውጤትነት መቅረብ ጀመረ።

የሲሲሊ ሎሚና ብርቱኳን ወደ ኒዮርክና ሎንዶን በሰፊው መጓጓዛቸውን ቀጠሉ። በ1834 ብቻ 400,000 ሳጥን ሎሚ ኤክስፖርት ተደረገ። በ1850 ወደ 750,000 አሻቀበ። በ1880ዎቹ መካከለኛ ዓመታት በየዓመቱ ወደ ኒዮርክ የሚላከው የፍራፍሬ ምርት 2.5 ሚሊዮን ሳጥን ሲደርስ አብዛኛው ምርት የሚጓጓዘው ከፓሌርሞ ነበር። በጀኔራል ጋሪባልዲ የትጥቅ ትግል ወቅት /1860/፣ የሲሲሊ የሎሚ ማሳ ከሁሉ ከአውሮፓ የእርሻ ምርቶች ይልቅ አትራፊ ሲሆን ከፓሪስ አጠገብ ከነበሩ ማሳዎች ሁሉ በመጠኑ ይበልጣል።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን የፍራፍሬ ምርት እጅግ አዋጭ ንግድ በመሆኑ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት አስፈልጎታል። መሬቱ ተመንጥሮ

መጽዳትንና በርከን መሠራትን፣ እንዲሁም ማከማቻ መጋዘኖችና መንገዶች መገንባት ነበረባቸው። በእርሻው ማሳ የሚገነቡ የግንብ አጥሮች፣ ፍራፍሬዎቹን ከዘራፊና ከንፋስ እንዲከላከሉ ሆነው ስለሚሰሩና መስኖ መዘርጋት ስለሚያስፈልግ ወጪው ከፍተኛ ነበር። አንዴ ዛፉ ከተተከለ በኋላ ፍሬ ለማፍራት ስምንት ዓመታትን ያስጠብቃል፣ ከዚያ በኋላ ብቻ ነው ትርፋማነት የሚታሰበው።

የሎሚውና የሌሎች ፍራፍሬ ዛፎች ከፍተኛ ክብካቤን ይፈልጋሉ። በቀላሉም ይጠቃሉ። በአጋጣሚ ማሳው የውሃ መቋረጥ ቢገጥመው በአንዴ እምሽክ ሊል ይችላል። በማሳዎች ላይ በሲሲሊ ዘራፊዎች ተከታታይ ጉዳት ይደርስ ነበር። የአካባቢው በዘራፊዎች መጠቃትና ከፍተኛ ትርፍ መገኘት የማፊያን ተገን-ማግኘት አስፈላጊ እንዲሆን አደረገ።

ምንም እንኳ ማፊያ በሲሲሊ ግዛት ጠርዞች ላይ የሎሚ ምርት በነበረበት ምዕራባዊ ሥፍራ ሁሉ የነበረ ቢሆንም በፓሌርሞ ዙሪያ እየተጠናከረ መጣ። በወቅቱ 200,000 ነዋሪ የነበራት ፓሌርሞ የምዕራባዊ ሲሲሊ የፖለቲካ፣ የፍትህና የገንዘብ ማዕከል ነበረች። ከሲሲሊ ወደብ ሁሉ የንብረትና የገንዘብ ዝውውር መጠኑ በፓሌርሞ እጅግ ከፍተኛ ነበር። ፓሌርሞ የጥቃቅን ንግድ ልውውጥ፣ የጅምላ ገበያ ማዕከል ብቻ ሳትሆን ዋና ወደብ ሆና ታገለግላለች። ለዚህም ነው ከሲሲሊ ወደብ በተለየ ሁኔታ የእርሻ መሬት ሽያጭና ኪራይ የተስፋፋው። ፓሌርሞ እየበለፀገች ስትሄድ በሀብትና በሥልጣን ላይ በመመርኮዝ ማፊያ ፈርጥሞ ወጣ።

በማፊያ ታሪክ አንድ ድንቅ ሰው የመጀመሪያው የማፊያ ተጠቂ ሆነ። ይህ የመጥፎ አጋጣሚ ሰለባ የሆነው ሰው የተከበረው ቀዶ ጠጋኝ ሀኪም ዶ/ር ጋስፓሌ ጋላቲ ነበር። ስለዚህ ዶክተር የሚታወቀው ነገር ስለ ማፊያ ለባለሥልጣናት ጽፎ ካስገባው የምስክርነት ቃል የተገኘ «ዶክመንት» ሲሆን ስለ ትክክለኛነቱም የተረጋገጠ ሆኗል።

ዶክተሩ በ1872፣ የቤተሰቡን ውርስ ለማስከበር እህቶቹን ወክሎ ወደ ፓሌርሞ መጣ። ዋናው የውርስ ሥፍራ ነፎንዶ ፊላኔ የተሰኘው አራት ሄክታር የሎሚና የታንጀሪን ማሳ ሲሆን ከፓርሌሞ የአሥራ

አምስት ደቂቃ መንገድ ያስኬዳል። ሥፍራው ለሌሎች በዘመናዊነቱ በሞዴልነት የሚታይ ሲሆን ሦስት የፈረስ ጉልበት የአንፋሎት ማጠጫ ወፍጮ ተክሎ ማሣውን አለማ። ዳሩ ግን ዶክተር ጋላቲ ይህ ከፍተኛ ወጪ የወጣበት ማሳ በማፊያ አደጋ ውስጥ መውደቁን በወቅቱ አስታውቋል።

የቀድሞው የማሳው ባለቤት የነበረው የዶክተሩ ዋርሳ በድንገተኛ የልብ ድካም ሕመም የሞተው በየጊዜው ከማፊያ በሚደርሰው የማስፈራሪያ ደብዳቤ ነበር። ከመሞቱ ሁለት ወር በፊት ከአንፋሎት ማጠጫው ሠራተኛ እንደተረዳው ደብዳቤው የተላከው ከአካባቢው ተቆጣጣሪ ከነበረው ቤንዲቶ ካርሎ ሲሆን ይህ ግለሰብ «የአካባቢው ንጉሥ» ሆኖ ማስቸገሩን ቀጥሏል። የዶክተሩ ዋርሳ የንግድና የምርት መልካም ዝናው አሽቆለቆለ። የዚህ ሁሉ መጥፎ ድርጊት፣ ዕብለትና ሌብነት ተዋናይ የነበረው የአካባቢው ተቆጣጣሪ ካርሎ መሆኑ ግልፅ ነበር። ከዚህ በኋላ ዶክተሩ የተረከበውን ማሳ በራሱ ከመቀጠል ይልቅ ለሌላ ሰው ማከራየት አስፈላጊ መሆኑን ወሰነ። ከደረሰው ችግር መገላገልም አስፈላጊ ነበር።

ወደፊት ቦታውን ተረክበው ለመሥራት የፈለጉ ገበሬዎች ሲመጡ የማሳው ተቆጣጣሪ የነበረው ካርሎ የተለየ ሀሳብ በማቅረብ ሥፍራውን አሂዙሮ አሳያቸው። «በይሁዳ ደም ይሁንባችሁ፣ ይህ ሥፍራ መሸጥም ሆነ መከራየት የለበትም፣ ለዶ/ር ጋላቲም ይበዛበታል» ሲል አማለላቸው። ይህን የሰማው ዶክተር ግን ተቆጣጣሪውን ሽሮ በእሱ ፈንታ ሌላ ሰው ተካበት። በዚህ ጊዜ ተቆጣጣሪ□ ካርሎ «ከአፌ ዳቦዬ ተነጠቀ» በሚል በአካባቢው ቂጭቱን መግለፁ በአካባቢው ተደመጠ። ታዲያ የዶክተሩ የቅርብ ሰዎች ካርሎን መልሶ በተቆጣጣሪነቱ ሥራ እንዲያስገባው ቢጠያይቁም ዶክተሩ ግን ከአቋሙ ወይ ፍንክች አለ።

ሐምሌ 2 ቀን 1874 ዶክተር ጋላቲ የቀጠረው አዲሱ ተቆጣጣሪ በሎሚ ማሳው ቀጭን መንገድ ላይ ሲጓዝ ከጀርባው ተደበደበ። ይህ ድርጊት ማፊያዎች ከማሳ እርከን ውስጥ ተደብቀው የሚፈልጉትን ሰው የሚገድሉበት ዘዴ ስለሆነ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ተደብዳቢው ፓሌርሞ ሆስፒታል ቢወሰድም ሊድን አልቻለም። ሞተ።

የዶ/ር ጋላቲ ልጅ ወደ አካባቢው ማቢያ በመሄድ ካርሎ ከግድያው ጀርባ እንዳለ በመግለፅ ጥርጣሬውን አመለከተ። ዱሩ ግን መርማሪው ፖሊስ ይህን ጥቆማ ወደ ጎን በመተው ሌሎች የማይመለከታቸውን ሁለት ንፁሀን ዜጎችን በቁጥጥር ሥር አዋለ። ሆኖም ምንም ማስረጃ ስላልተገኘባቸው በነፃ ተለቀቁ። ከአካባቢው ፖሊስ ምንም ድጋፍ ያጣው ዶ/C ጋላቲ ሌላ ተቆጣጣሪ ዳግም ቀጠረ። ከዚህ በኋላ ሁኔታው ሌላ ሆነ። ዶ/C ጋላቲና ቤተሰቡ በተከታታይ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤዎች ይጎርፉላቸው ጀመር። በደብዳቤው ላይም "የክብር ሰው የሆነን እንደ ካርሎ ያለ ሰው ከሥራ ማስነሳትህና በምትኩ 'ልክስክስ ጆሮ-ጠቢ' መቅጠርህ ልክ አይደለም" ሲል ደብዳቤው ያስፈራራል።

ይህን አዲስ የማፊያዎች የቃላት አጠቃቀም ዶ/C ጋላቲ እንዲህ ሲል ያስረዳል - በማፊያ ቋንቋ ሌባና ነፍስ-ገዳይ "የክብር ሰው ነው።" ተበዳይ ደግሞ "ልክስክስ ጆሮ-ጠቢ ይሰኛል" በማለት።

ዶክተሩ ስባት የተለያዩ የማስፈራሪያ ደብዳቤዎችን ይዞ ወደ ፖሊስ አመለከተ። በፖሊስ በኩል ካሮሎና ተባባሪዎቹ እንደሚታሰሩ ተስፋ ተሰጠው። ዳሩ ግን መርማሪው - ቀደም ሲልም ጉዳዩን ያድበሰበሰው ነበርና አሁንም ለጉዳዩ ቁብ አልሰጠውም።

ካሮሎና ተባባሪዎቹ በቁጥጥር ሥር የዋሉ ቢሆንም ከሁለት ሰዓታት በኋላ እንዲፈቱ ተደረገ። ዶክተር ጋላቲም መርማሪው ፖሊስ የወንጀለኞች ተባባሪ መሆኑን በግልፅ ተረዳ።

ዶክተሩ የእርሻ ንግዱን ይበልጥ ለመከላከል ሲል ስለ አካባቢው ማፊያ ምሉዕ ስዕል ለማግኘት ጥረቱን ቀጠለ። ከአንዷት የቅርብ መንደር በሆነችው ኡዲቶሬ 'Uditore' በሃይማኖት ድርጅት ስም አንድ የማፊያ ቡድን እንደሚንቀሳቀስም ደረሰበት። አንድ ቄስና አባት ሮዛሪዩ የሚባል ባህታዊ አንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያንን የሚረዳ የርዳታ ድርጅት ይመራሉ። በተለይ አባት ሮዛሪዩ በቀድሞው የበርበን (Bourbon) አገዛዝ ወቅት የፖሊስ ሰላይና የእሥር ቤት ቄስ ስለነበር ከታሳሪዎች መረጃ በማሰባሰብ የሃይማኖቱን ሽፋን ይጠቀምበት እንደነበር ይታወቃል።

የመንደሪተ የማፊያ አለቃና የእርዳታ ድርጅቱ ፕሬዚዳንት የነበረው ሰው አንቶኒዮ ጂያሞና ሲሆን እጅግ ደሃ ከሆነ ቤተሰብ የተወለደና የቀን ሠራተኛ ነበር፡፡ የሀብቱ ምንጭና የሥልጣን ታዋቂነቱ የመነጨው ሲሲሊ ከኢጣሊያ ግዛት ጋር ከተጠቃለለች በኋላ ነው፡፡ 1848ና 1860 የተካሄዱ ተቃውሞዎች ጂያሞና ጥንካሬን ያሳየበትና ብዙ ጓደኞች ያፈራበት አጋጣሚ ፈጠሩለት፡፡ በ1875 ዕድሜው 55 ዓመት ሲሞላው ጂያሞና በሕብረተሰቡ ውስጥ ሥፍራ ያለው ሰው ሆነ፣ ከ150,000 ሊሬ በላይ ባለሃብት መሆኑን የፓሌርሞ ፖሊስ ሪፖርትም ያመለክታል፡፡ ይህ ሰው ከሕግ ያመለጡ ወንጀለኞችን በማስጠለል ይታወቅ እንጂ ሁሉንም በየተራ እንደገደላቸው ተገምቷል፡፡ በወንጀለኝነቱ ከህግ በማምለጥ ወደ አሜሪካን ከተሻገረው ወንጀለኛ ወዳጁ ጂያሞና ብዙ ገንዘብ መቀበሉ ታውቋል፡፡ ዶ/ር ጋላቲ ስለ አንቶኒዮ ጂያሞና ባህሪይ ሲገልፅ "እኩይ፣ ተጠራጣሪና ግልፍተኛ" ሲል ገልፆታል፡፡

ማፊያ በአካባቢው የፖሊስ አሠራር እጁ እንዳለ ግልፅ ነበር፡፡ ስለዚህ ስለ ተቀጠረው ሰው አገዳደል ለዋናው አቃቤ-ህግ መርማሪ ማመልከት የግድ እንደሆነ ተረዳ፡፡ ይህ ዕምነቱ ይበልጥ የጠነከረው ዶክተሩ ለፖሊስ አቅርቦት ከነበረው ከሰባት የማስጠንቀቂያ ደብዳቤዎች ውስጥ በጣም አስፈላጊው የሆነው አንድ ደብዳቤ ተቀንሶ ስድስቱ ብቻ ተመልሶለታል፡፡ ይህ ዓይነቱ ሰንካላ አሠራር በአካባቢው የፖሊስ ጣቢያዎች የተለመደ መሆኑንም በአቃቤ ህጉ መርማሪ ለዶክተሩ ተነግሮታል፡፡

አዲስ የማስፈራሪያ ደብዳቤ ለዶክተር ጋላቲ አሁንም ደረሰው፡፡ በደብዳቤውም በማምንት ጊዜ ውስጥ የቀድሞውን ተቆጣጣሪና የማፊያ "የክብር ሰው" የሆነውን ወደ ሥራው እንዲመልስ የሚያዝ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ዶክተር ጋላቲ የቀረበለትን የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ፈፅሞ አልተቀበለም፡፡ የማስጠንቀቂያው ጊዜ እንዳለፈ ጥር፣ 1875 ዶክተሩ የቀጠረው አዲሱ የማሳው ተቆጣጣሪ በጠራራ ፀሐይ ሦስት ጊዜ ተተኮሰበት፡፡ በዚህ ወንጀል ካሮሎ እና ሌሎች ሁለት ተጠርጣሪዎች በፖሊስ ተያዙ፡፡

የደረሰው ጉዳት ለዶክተር ጋላቲ አንድ ያልተጠበቀ ዕድል ፈጠረለት፡፡ የተተኮሰበት ተቆጣጣሪ በደረሰበት አደጋ አቅሉን ከመሳቱ

በሬት፤ ጉዳት ያደረሱበትን የማየት ዕድል አግኝቶ ነበር፡ ከሳናጊ የተነሳ በመጀመሪያ በሆስፒታል ተኝቶ ፖሊስ ለአቀረበለት ጥያቄ ምንም ዓይነት መልስ አልሰጠም። በኋላ ግን ሕመሙ ሲበረብትና ማጣጣር ሲጀምር መርማሪውን በመጥራት ቃሉን ሰጠ። ከሰጠውም ቃል በጥይት የደበደቡት የታሰሩት ሦስት ሰዎች መሆናቸውን አረጋገጠ።

በዋና አቃቤ-ህግ መርማሪ ድጋፍ ዶክተር ጋላቲ ቁስለኛውን ቤት ተቀን ለማዳን ሳይበዝን ሠራ። ዶክተሩ ከዚያ በኋላ ልጅና ሚስቱን ከቤት እንዳይወጡ በማድረግና ወደ ውጪም ሲንቀሳቀስ ሽጉጡን ከራሱ ሳይነጥል መንቀሳቀሱን ቀጠለ። ሆኖም የማስጠንቀቂያ ደብዳቤዎች መጉረፋቸውን አላቆሙም። ደብዳቤዎቹ ወደ ዶክተሩ በጎረፉ ቁጥር ደግሞ የቤተሰቡ ሁኔታ ይበልጥ ተረበሸ። በተለይ በማስጠንቀቂያው እንደተገለፀው ከቲያትር ቤት ሲመለሱ በጩቤ ተወግተው እንደሚጣሉ የሚገልፀው ማስፈራሪያ ዋነኛው ነበር። ታዲያ ማፊያዎቹ ዶክተሩ የወር የቲያትር ትኬት እንዳለው ያውቁ ስለነበረ ነው በውስጥ አውቃነት ማስጠንቀቂያ የሚልኩት። ይህ ብቻ ሳይሆን በዋናው የአቃቤ-ህግ ምርመራ ጽ/ቤት ውስጥ የማፊያ ወኪሎች አማካኝነት የዶክተሩ ማስረጃዎች እንደተጠለፉ ከሚላኩለት ደብዳቤዎች ማረጋገጥ ተችሏል።

ቁስለኛው የዶክተሩ ተቀጣሪ ምንም ዓይነት ህጋዊ ከለላ ማግኘት ስላልተቻለው ሁኔታዎችን በግሉ በቁጥጥር ሥር ማድረግ የግድ ሆነበት። ከቁስሉ እንዳገገመ ወደ አንቶኒዮ ጂያሞና በመሄድ ሰላም ለማስፈን ጠየቀ። ወደ አንድ የግብዣ ቦታ ጠርተው ሰላም በመካከላቸው ሰፈነ።

ሁኔታው ያላማረውና ዙሪያ-ፈትል የሆነበት ዶክተር ጋላቲ ዘመዶቹን እንኳ ሳይሰናበት ለአሥራ አምስት ዓመታት የለፋበትን ንብረቱን እርግፍ አድርጎ በመተው ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ወደ ኔፕልስ እግሬ-አውጪኝ አለ። ማድረግ ግን የነበረበት አንድ ነገር ነበር፣ አንድ የመጨረሻ ማስገንዘቢያ በመፃፍ ጉዳዩን ወደ ሮማ ሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ማሳወቅ። በሪፖርቱ ውስጥም የUditore መንደር በ1874 ስምንት መቶ ነፍሶች የሚኖሩባት ስትሆን እሱ ግን በግል የሚያውቃቸው ሁለት ሴቶችና ሁለት ህፃናትን ያካተተ 23 ሰዎች መገደላቸውን ገለፀ። ሆኖም ግን ጉዳዩን ለማጣራት የተወሰደ አፋጣኝ

እርምጃ እንኳ አልነበረም፡፡ በኋላም የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ፓሌርሞ ላለው የፖሊስ አዛዥ ጉዳዩን እንዲከታተል መልዕክት ላከ፡፡ የዶክተሩን በጋላቲ ጉዳይ አንድ ወጣት የፖሊስ መርማሪ እንዲያጣራ ተመደበ፡፡ ሆኖም ግን የተገኘ ውጤት አልነበረም፡፡ በUditore መንደር ማፊያ የተጀመረውን ምርመራ ለማክሸፍ የማፊያ አባላት እንዲሸሸጉ አደረገ፡፡ ከአንቶኒዮ ጂያሞና ጎን የመሬት ባላባቶች፣ ፖለቲከኞችና የህግ ሰዎች ሳይቀሩ በደጋፊነት ቆሙ፡፡

የንፁሀን ዜጐች ግድያ፣ በአካባቢው ሃይ! የማይባሉ ወንበዴዎች በጀብደኝነት መንሰራፋታቸው በተለያዩ የውንብድና ቡድኖች መካከል ያለ ውድድርና ትብብር መጠናከሩና፣ እንዲሁም ማናቸውም የማፊያ ዘዴ ሁሉ በሎሚ ማሳዎቹ ውስጥ እስከ 1870 ድርስ ይተገበሩ እንደነበር የዶክተሩ መግለጫዎች ያመለክታሉ፡፡ በመጨረሻም ለዚህ ሁሉ ማን አለብኝነት ማፊያን ልዩ ያደረገው - አባላቱን የመመልመል ሥርዓት እንደሆነ ስለ ማፊያ ያጠኑ ሁሉ ዕምነታቸውን ገልፀዋል፡፡

## ማፊያ አባላቱን እንዴት ይመለምላል?

ምንም እንኳ የUditore ማፊያን በዶክተር ጋላቲ ማሳሰቢያዎች ወደ ፍርድ ማቅረብ ባይቻልም ማፊያ "በደም መሐላ" የሚሠራ ምስጢራዊ ማህበር መሆኑን ጠቁሟል፡፡ በአንቶኒዮ ጂያሞና ዕዝ ሥር የተደራጁት የአባልነት ምልመላ ልዩ ሥርዓት የሚከተሉ ሲሆን በአሁኑም ጊዜ የማፊያ "የክብር ሰውነት" ሥርዓቱን ተከትሎ እንደሚከናወን ታውቋል፡፡

ዶክተር ጋላቲ በ1875 ለሀገር ውስጥ ደህንነት ሚኒስቴር ማሳሰቢያውን ሲፅፍ ሚኒስትሩን ስለ ጉዳዩ በትክክል ለማጣራት ከፈለጉ እስቲ "የፓሌርሞ ፖሊስ አለቃ ስለጉዳዩ ሪፖርት እንዲያቀርብ ይጠይቁት" ሲል አሳስቧቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ነው የፖሊስ አዛዡ ለመጀመሪያ ጊዜ የማፊያን የአባልነት የመመልመያ ሥርዓት ይፋ ያደረገው፡፡ በፖሊስ አለቃው አገላለፅ ማፊያ በ1870ዎቹ በአባልነት የክብር ሰውነትን የሚያገኘው በካቦዎችና በምክትል ካቦዎች ሥር ነው፡፡ አንዱ የማፊያ አለቃ የሚመለምለውን ዕጩ ማፊያ፣ እጁን ወይም ክንዱን ወደላይ በመያዝ ከበጣ በኋላ የሚወጣውን ደም በቅዱሳን ስዕል ላይ እንዲረጭ ያደርጋል፡፡ ከዚያ በኋላ ግለሰቡ የማፊያ ድርጅት ፍፁም

ታማኝነቱን ለመግለጽ ደሙ የተረጨበት ቅዱስ ስዕል እንዲቃጠል ተደርጎ አመዱ ሲበተን መሐላው ተከናወነ ማለት ነው። ይህ ድርጊት የሚያስተላልፈው መልዕክት ማፊያን የከዱ አባላት የሚደርስባቸው ዕጣ ተቃጥሎ እንደ አመድ መበተን መሆኑን ያሳስባል። ከዚህ በኋላ ማናቸውም የማፊያ አባል የታዘዘውን ከመፈፀም ወደ ኋላ አይልም። ለምሳሌ ዋና ዳኛ ፋልኮኒን በካፒቺ ፈንጂ እንዲጐዱ ያደረገው የአባልነት ሥርዓቱን ወዲያው ተቀብሎ የመጣ የ19 ዓመት ወጣት እንደነበረ ይታወሳል። ይህንንም ወጣት ወደ ማፊያ ድርጅት እንዲቀላቀል ያደረገው የማፊያ ኃላፊ የነበረው አባቱ መሆኑ ደግሞ የማፊያን ጭካኔያዊ አሠራር ያሳያል።

አንድ ቀን ብሩስካ ወደ ገጠር ድብቅ የመዝናኛ ሥፍራ ተወሰደ። በወቅቱ ብዙ የማፊያ የክብር ሰዎች እንዲያውም ዋና የማፊያ የጡት-አባት የሆነው "አጭሬው ሪና" ጭምር ተገኝቶ ነበር። ከዚያም ቡርስካን "ሰውን ስትገድል ምን ይሰማሃል? ወንጀል መሥራትስ?" ሲሉ ጠየቁት። ቡርስካ አላወቀም እንጂ እንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ከተሰብሳቢ ሲቀርቡ የአባልነት የምልምላ ሥርዓት መጀመሩን ያመለክታል።

በመሃሉ ቡርስካ ወደ ውጪ እንዲወጣ ተደረገ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተመልሶ ተጠራ። የማፊያ አባላቱ በተሰበሰቡበት የቡርስካ አባት ወደ ውጪ እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ እነዚህ የማፊያ መልማዮች ሽጉጥ፣ ባለ ሁለት መውጊያ ጦርና ቅዱስ የመላዕክት ስዕል በመሃላቸው አቁመው ጠበቁት። ከመካከላቸው አንድ የክብር ሰው ብድግ ብሎ "ቡርስካ! እድሜ ልክህን በእስር እንድታሳልፍ ቢፈረድብህ ታማኝነትህን ትቀጥላለህ? አትክደንም? ሲል ጠየቀው። ከዚያም "የኮዞ ኖስትራ ማህበር አባል መሆን ትፈልጋለህ?" ሲል ሌላ ጥያቄ ጨመረለት። ቡርስካ ትንሽ ራሱን ካረጋጋ በኋላ ተስፋ በሚሰጥ ሁኔታ - "ይህን ወዳጅነት እፈልገዋለሁ፣ እነዚህን ወንጀሎች እወዳቸዋለሁ" ሲል መለሰ። ከዚያም አንደኛው የክብር ሰው ጣቱን ይዞ ወጋው። ቡርስካ ደሙን ወደ ቅዱስ-ስዕሉ ላይ ረጨው። "የጡት-አባት ሪና" እሳት በስዕሉ ላይ ለኩሰ፣ ከዚያም "ኮዛ ኖስትራን ከካድህ ሥጋህ እንደዚህ ቅዱስ ስዕል ይቃጠላል" ሲል አስጠነቀቀው።

በማፊያ ድርጅት ውስጥ ራስን በማፊያ አባልነት ማስተዋወቅ ፊጽሞ የተከለከለ ነው። ከዚያ ይልቅ ሌላ ሦስተኛ የማፊያ አባል በሾርኒ "ጓደኛችን ነው" ወይም ደግሞ "ሁስታችሁም እንደኒው አንድ ናችሁ" በሚል የአቀራረብ ፎርሙላ ያስተዋውቃቸዋል። የጡት-አባት የሆነው ሪናም በዚህ መንገድ ነበር የቡርስካ አባት ተመልሰው እንዲጠሩ ካደረገ በኋላ "አባትና ልጅን" የክብር ሰው መሆናቸውን ያሳወቃቸው።

ከምዕተ-ዓመት በፊት ማፊያ አባሎቹን የሚያስተዋውቀው እንደሚከተለው በሚስጢር ኮድ በታሰረና በጥርስ ህመም በሚጀምር ምልልስ ነበር፡

ሀ፡ በአምላክ ደም! ጥርሴ ታሟል (ወደ ላይኛው የጥርስ ክፍል በማመልከት)

ለ፡ የእኔም ታሟል።

ሀ፡ መቼ ጀመረህ?

ለ፡ እመቤታችን ቅድስት ማሪያም በተበሰረላት ዕለት

ሀ፡ የት ነበርክ?

ለ፡ በፓሶ ዲ ሪጃ

ሀ፡ ሌላስ ማን ነበር?

ለ፡ መልካም ሰዎች።

ሀ፡ እነማን ነበሩ?

ለ፡ አንቶኒዮ ጂያሞና ቁጥር 1፣ አልፎንሶ ስፓቶላ - ቁጥር 2፣ ወዘተ...

ሀ፡ እንዴት ነው ያን ክፉ ነገር የሚፈጽሙት?

ለ፡ ዕጣ አወጡና አልፎንሶ ስፓቶላ አሸነፈ። ቅዱስ-ስዕልን ወሰደና በደሚ ቀባባው። ከዚያም አቃጠለው። አየር ላይ አመዱን በተነው።

ሀ፡ ምን እንድታመልክ ነገሩህ?

ለ፡ ፀሐይና ጨረቃን

ሀ፡ አማልክትህ ማነው?

ለ፡ አየር

ሀ፡ የየትኛው መንግሥት አባል ነህ?

ለ፡ የአመልካች ጣት፡፡

በእነዚህ ምልልስ ውስጥ "ፓሶ ዲ ሪጃኖ" ሌላዋ በፓርሴሞ ጥጋት ያለች መንደር ናት፡፡ የተጠቀሰው "ፀሐይና ጨረቃ፣ አየር እና አመልካች ጣት" የሚያመለክቱት አንድ "አዲስ አባል" የማፊያ ቤተሰብ ሙሉ አባል መሆኑን ነው፡፡ በአጠቃላይ የማፊያ ድርጅቶች አባላት እርስ በእርስ የማይተዋወቁ የወንጀለኞች ትስስር ድር ሲሆኑ የአባልነት ምልመላ ሥርዓቱ የማፊያ ሥነ-ተረት (Myth) በአካባቢው እንዲሰራጭ ረድቷል፡፡ ይህ የማፊያ ሥርዓት መሠረቱ ከማንሶንስ (Mansons) የመጣ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፣ የማሶንስ ምስጢራዊ ማህበረሰብ በመጀመሪያ ከፈረንሳይ ወደ ሲሲሊ የተስፋፋው በኔፕልስ በኩል በ1870 አካባቢ ሲሆን አሠራሩ መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሲሲሊያውያን ዘንድ የበርበንን ሥርዓት (Bourbon Regime) ለመቃወም ሲባል ተቀባይነትን አገኘ፡፡ የማንሶስ ሚስጢራዊ ድርጅት የአባልነት ምልመላ አቀባበል ሥርዓት ሲያካሄድ አባላቱ ለከዲዎች ማስፈራሪያ የሚሆን ባለ ሁለት ባላ በደም የተነከረ ጦር ይይዛሉ፡፡ እነዚህ የማሶኒክ ስውር ቡድኖች "ከሰል አንዳጆች" (Carbonari) ሲባሉ አርበኝነታዊ ዓላማ ነበራቸው፡፡ በሲሲሊ ደግሞ እነዚህ ስውር ቡድኖች ወደ ወንጀለኛና የፖለቲካ ቡድንነት ተለውጠው ቆይተዋል፡፡

ይህን የማንሶስ ሥርዓት መከተል ለማፊያ ብዙ ጥቅሞችን ሰጥቶታል፡፡ ዋነኛው ጥቅም ማፊያን የሚከድ አባል እንዳይኖር በመካከላቸው መተማመንን ፈጥሯል፡፡ ሌላው ጥቅም የሥርዓቱ መናር ወጣት አባላት የተነሳሱና ለምንምና ለማንም ወደኋላ እንዳይሉ አደንድኖአቸዋል፡፡ ሚስጢራዊው ድርጅት ከአባቢው ካሉ ወንጀለኛ ቡድኖች መተማመን ኖሯቸው በየራሳቸው ክልል እንደልብ እንዲንቀሳቀሱ ረድቷል፡፡ ታዲያ ይህ እጅግ ውስብስብና ሚስጢረኛ ድርጅት ከየት እንደመጣ ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ ስለ "እኩይ ተጠራጣሪና ግልፍተኛው" አንቶኒዮ ጂያሞናን ስለ መሳሰሉ የነበሩ ሰዎች በዝርዝር መረዳት ማፊያን ለማወቅ ይጠቅማል፡፡

# 3

# ባሮን ኮሎና፣ ሕቡዕ ቡድን እና የሽብር ኢንዱስትሪ

ከጋሪባልዲ የሦስት ዓመት የነፃ አውጭ ዘመቻ በኋላ የሲሰሊው ባላባት የተሟላ መረጃ ስለ ማፊያ አቀረበ። ይህ ሰው ኒኮላ ቱሪሲ ኮሎና ሲሆን የተቀናጀ የማፊያ የግድያ ሙከራ ተደርጎበት ነበር። የቦኖቡቼኖው ባላባት /ባሮን/ ኮሎና አንድ ምሽት ከመሬቱ ወደ ፓሌርሞ ተመለሰ። የተጓዘበት መስመር እጅግ የበሰፀገ የገጠር መንገድ ሲሆን የሎሚ ተክሎች በሰልፍ ተተክለውበት ዓይን ይስባሉ። በኖስ እና በኦሊቡሳ መንደሮች መሐል አምስት ሰዎች ከተለያዩ አቅጣጫዎች በፈረሶቹና በጋሪዎቹ ላይ በድንገት ተኮሱበት። ቱሪሲ ኮሎናና የጋሪው ነጂ የአፀፋ ተኩስ አካሄዱ። ወዲያው ከአረንጓዴው ማሳ ጥጋት የቆስለኛ ጩኸት ተሰማ። ገዳይ ቡድኖቹ ተኩሳቸውን አቁመው ቁስለኛውን አሸሹ።

ቱሪሲ ጥቃቱ ከደረሰበት ከዓመት በኋላ "ማህበራዊ ደህንነት በሲሲሊ" በሚል ርዕስ ስለጉዳዩ ፃፈ። ይህ ጥናት ጣልያን አንድ ከሆነች በኋላ ስለ ማፊያ የተነተነ፣ እሰጣ-ገባና ድብልቅልቅ ስሜትን የፈጠረ የመጀመሪያው ጥናት ነበር። በቀረበው ጽሑፍም ኮሎና ስለሕቡዕ ድርጅቱ በሚገባ የሚያውቅና ተአማኒ መሆኑን አስመከረል። ቱርሲ ኮሎና በ1860ዎቹ የሲሲሊን አብዮት በመምራት ረገድ ድንቅ ሚና ተጫውቷል። ይህ ሰው የፓርሌሞ ብሔራዊ ጦር መሪ ሲሆን አብዮቱ ወደሥርዓት አልበኝነት እንዳይለወጥ የሚቻለውን ሁሉ አድጓል። በ1864 ስለወንጀል የሚያትት አነስተኛ መጽሐፍ በፃፈበት ወቅት የኢጣልያ ፓርላማ አባል ሆነ፤ በኋላም በ1880ዎቹ የፓርሌሞ ከንቲባ በመሆን ሁለቴ አገልግሏል። ዛሬም እንኳ ቢሆን በፓርሌሞ የከተማ ም/ቤት

"በፓላሶ ዶሴ አኩይሌ" ውስጥ ከመገብ በላይ የእብንበረድ ሐውልት ተሰርቶለት ይታወሳል፡፡

በጣልያን መንግሥት በኩል በሲሲሊ ያለው ሁኔታ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አዲሱን መንግሥት ለማሳጣት ሲሉ ሕግና ሥርዓት እንዲጣስ ይገፋፋሉ የሚል ክስ ሲሰማ፣ በተቃዋሚው ጎራ ደግሞ መንግሥት እንቅስቃሴያችንን ለመግታት የሕግና የሥርዓት መጓደልን እያጋነነ እኛን ለማፈን ይፈልጋል በማለት ይከሳሉ፡፡ ቱርሲ ኮሎና ግን ሁለቱንም ጎራ ሳይደግፍ እውነተኛውን መስመር በመያዝ በሲሲሊ የተደራጁ ወንጀለኞች እየተጠናከሩ መምጣታቸውን ካገኘው ልምድ በማስረዳት፣ መንግሥት የሚያሳርፈው ጠንካራ ጡጫ ደግሞ ሁኔታውን ከማባባስ በላይ የሚፈይደው ነገር እንደሌለ አስረግጦ ሲያስረዳ ቆይቷል፡፡

ምንም እንኳ በየጋዜጦች ላይ የሚወጡት ዜናዎች በገደላ ወንጀሎች የተሞሉ ቢሆንም በፓሌርሞ ግን የሚቀርበው ሪፖርት ከሕግ-አልባነት ጋር መያያዙን ኮሎና ያሳስብ ነበር፤ እንዲህ እያለ፡-

> *"ከእንግዲህ ራሳችንን ማታለል የለብንም፡፡ በሲሲሊ ሕቡዕ ቡድን ተደራጅቶ ደሴቲቷን እያመሳት ይገኛል፡፡ ሕቡዕ ቡድኑ ለሌሎች መከታ እየሆነና በአፀፋውም ገመናውን እየሸፈኑለት ነው፡፡ በየገጠሩ ከገበሬዎችና ከእረኞች ጥበቃ ይደረግለታል፡፡ ቡድኑ ለነጋዴዎች ጥበቃ እያደረገ እሱም በተራው እየተጠበቀ ነው፡፡ ፖሊስ ለሕቡዕ ቡድኑ ባለው ፍራቻ የሚይዛቸው በጣም ጥቂቶቹን ወይም ምንም ነው ማለት ይቻላል፡፡ ፍርድ ቤቶችም ሕቡዕ ቡድኑን ይፈራሉ፤ ማፊያም ምስክሮችን ስለሚያስፈራራ ምንም ዓይነት ማስረጃ አይቀርብበትም፡፡"*

እንደ ቱሪሲ ኮሎና ዕምነት ሕቡዕ ቡድኑ ርዕይ ካላቸው ገበሬዎች እየመረጠና ከፓሌርሞ አካባቢ ስፋፊ እርሻዎችን ከሚቆጣጠሩትም ባላባቶችን ይመለምላል፡፡ በጣም የሚገርመው መቀረጥ የነበረባቸው እህሎችና ሌሎች ዕቃዎች በግብር መሰብሰቢያ ኬላዎች እንዳይቀረጡ ይደረጋሉ፡፡ ከገጠር የተዘረፉ ከብቶችን ወደ ከተማው ልኳንዳ አራጆች ሲያቀርቡ የሕቡዕ ቡድኑ አባላት የሚግባቡበት የተለየ የምልክት ቋንቋ አላቸው፡፡ ከቡድኑ አባላት ውስጥ የተወሰኑት የተዘረፉ ከብቶች እንዴት

እንደሚሸጡ የተካኑ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ እንዴት እንደሚያጓጉዙና የነብሶች መለያ ምልክቶች እንዲጠፉ የማድረግ ብቃት አላቸው። ከአካባቢው የመንግሥት አውታሮች ሳይቀር ከለላ የሚሰጣቸው በመሆኑ ተራው ዜጋ በፍራቻ እንዲዘፈቅ አድርጎታል። ሌላው ቀርቶ ታማኝ ዜጎች ሳይቀሩ በገጠሩ ሰላም ሊወረድ ይችላል በሚል ተስፋ ወደ ቡድኑ ሆረዋል።

እንደ ማናቸውም የሽብር ቡድን የሕቡዕ-ቡድኑ አባላት በወቅቱ ለነበረው ጨካኝና ሙሰኛ የበርበን ፖሊስ ጥላቻ ነበራቸው። ለአብዮቱም ከፍተኛ ድጋፍና ወኔ ያሳዩት አብዮቱ እሥር ቤቶች እንዲከፈቱ፣ የፖሊስ ሪከርዶች እንዲቃጠሉ፣ ፖሊሶችንና ጠቋሚዎችን በአጋጣሚው ለመጥፋት እንዲያግዛቸው ነበር። ሕቡዕ ድርጅቱ ተስፋ አድርጎ የነበረው አብዮታዊው መንግሥት በአሮጌው ሥርዓት ለተወነጀሉ ምህረትን፣ በሚሊሻነት እንዲመለመሉና የሥራ ዕድል እንደሚከፈትላቸው ያምኑ የነበረ ቢሆንም የጠበቁት አልተፈፀመም። እንዲያውም አዲሱ የኢጣልያ መንግሥት በወንጀለኞች ላይ ይበልጥ የቁጥጥር ልጓሙን አጠበቀ።

የቱሪሲ ኮሎና ሪፖርት ከወጣ ከአራት ወራት በኋላ ነበር "ማፊያ" የተሰኘ ስያሜውን ሕቡዕ ድርጅቱ የያዘው። ይህ ድርጅት የራሱን ፍ/ቤቶች በመሰየም ደንቡን በጣሱት ላይ የማያዳግም የሞት ቅጣት እየጣለ የሕቡዕ ቡድኑን "የዝምታ ኮድ" ያስከብራል።

በድርጅቱ ውስጣዊ መመሪያ መሠረት ወታደራዊ ፖሊሶችን (Carabinicrc) የሚቀርብና የሚያናግር፣ ሌላው ቀርቶ አንዲት ቃል የተለዋወጠ እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሮ በሞት ይቀጣል። ይህ ዓይነቱ ሰው ድርጅቱን "በማሳቀል" ሰበብ ምህረት-የለሽ ሁኔታ ይደርስበታል። ማሳቀል (Humility) በማፊያ አባባል ትርጉሙ ተቃራኒ ነው። "ማሳቀል" ለሕቡዕ ቡድኑ ፍፁም አክብሮትና ተገዢ መሆን ማለት ሲሆን ማንም አባል የሌላውን አባል ፍላጎት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት የለበትም። "ማንም አባል ለፖሊስ ወይም ለፍትህ አካላት የተፈጠረውን ወንጀል ማሳወቅ አይኖርበትም" የሚለው አጠቃላይ መርህ "በማሳቀል" ውስጥ ይካተታል።

"ማሳቀል" (Humility) - በኢጣልያ ቋንቋ Umilta፣ በሲሲሊ ቀበሌኛ ቋንቋ ደግሞ Umirta ሲሆን ከዋናው ትርጉም ያፈነገጠ ቃል ነው። ይህ ቃል ማፊያዎች የሚጠቀሙበት "ምስጢር ያለማውጣትነትን የፍፁም ዝምታ" ትርጉም የሆነውን የOmerta ቃል መሠረት ነው ማለት ይቻላል። "Omerta" /ኦሜርታ/ የማፊያ ምስጢር ያለማውጣት ኮድ፣ ለፖሊስ ምንም ያለመናገር ጭጭ፣ ዝም ማለት ነው።

ቱርሲ ኮሎና ለመንግሥት በሰጠው ምክር ችግሩ የሚፈታው "ወንጀለኞችን በመስቀልና በማሰቃየት" አይደለም፣ ከዚህ ይልቅ የሲሲሊን ሕዝብ የባህርይ ሁኔታ ለመለወጥ ተግቶ መሥራትና "ለሁለተኛ ጊዜ ሲሲሊያውያንን ሕዝባዊ ክርስትና ማስነሳት ይሻላል" ሲል አበክሮ መክሯል።

???

ከተወሰኑ አስርተ-ዓመታት በኋላ በ1876 ሊኦፖልዶ ፍራንቼቲና እና ሲድኒ ሶኒኖ የተባሉ ሁለት ወጣት፣ ሀብታም፣ የለማ-አእምሮና የይሁዲ ዝርያ ያላቸው ምሁራን ከቱስካኒ ፓሌርሞ ደረሱ። ወደዚያ ያመሩት ከአሽከሮቻቸው ጋር ሲሆን በሲሲሊው ሕብረተሰብ ላይ የግል ጥናት ለማድረግ ነበር። ምንም እንኳ ዶ/ር ጋላቲ ከፃፈው ማሳሰቢያ ወዲህ "ማፊያ" የሚለው ቃል በሁሉም ሰው ምላስ ላይ የሚንገዋለል ቢሆንም ትርጉሙ በትክክል ምን እንደሆነ ግን የሚታወቅ አልነበረም። ፍራቼቲናም ሆነ ሶኒኖ ማፊያ የወንጀለኝነት አደገኛው ገጽታ እንደሆነ ምንም ጥርጣሬ አልነበራቸውም፤ ሆኖም የነበረውን የተለያየ የሀሳብ ጭጋግ ለማስወገድ ቆርጠው ተነስተዋል።

ወዲያው ሲሲሊ እንደደረሱ፣ ሶኒኖ ለጓደኛው በፃፈው ማስታወሻ ስለኒኮሎ ቱሪሲ ኮሎና፣ የኖቬቼኖው ባላባትና ስለ ሕቡዕ-ቡድኑ ኤክስፐርት ስለሆነው ሰው የተዘጋጀው ገላጭ ቃል እንደሚከተለው ይነበባል፡-

"እዚህ አካባቢ እንደሚወራው ከማፊያ ጋር ቁርኝት አለው /ኮሎናን ማለቱ ነው/። ይህ እኛን አያገባንም። መጀመሪያ ከእሱ ቃል መስማት አለብን... ነግሬሃለሁ፣ ስለባሮን ቱሪሲ ኮሎና የነገርኩህን ለማንም ትንፍሽ እንዳትል፣ ከማፊያ ጋር ግንኙነት ያለው ይመስላል። በአንድ

ጓደኛው በኩል ሾልኮ ከደረሰው ግን እንዴት እንደሚያስተናግደን ይታየኛል::"

በእርግጥም ስለቱሪሲ ኮሎና የነበረው አሉባልታ በየቦታው ተሰራጭቷል:: ሌላው ቀርቶ የራሱ የፖለቲካ ቡድን አባላት ሳይቀሩ በሮም ፍርድ ቤት ቀርበው ፍራቻቸውን ገልፀዋል::

በ1860፣ ቱሪሲ ኮሎና ዋናውን የሕቡዕ-ቡድን መሪ የሆነውን ሰው በብሔራዊ ጦሩ ውስጥ የሻምበልነት ማዕረግ ሰጥቶ ተቀብሎታል:: ሰውየው ሊመረጥ የቻለው ባለው ሥልጣንና ወታደራዊ ልምዱ ሲሆን፣ ቀድሞ አንድ አብዮታዊ ቡድንን በመምራት ተሳትፏል:: ይህ ጣት የተቀሰረበት ሰው አንቶኒዮ ጃሞና መሆኑ ሲታወቅ ቀደም ሲል የዶ/ር ጋላቲን ንብረት ለመንጠቅ ሲያሴር እንደነበር ይታወሳል:: የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር የዶ/ር ጋላቲን ክስ ሲያጣራ በወቅቱ ኮሎና እንደ አንድ የአካባቢው ባላባት ጃሞናን ደግፎት ነበር:: ሌላው ቀርቶ ለጃሞና የፍ/ቤት መከላከያ የፃፈው የቱርሲ ኮሎና ጠበቃ ሲሆን በ1875 በፖሊስ በቀረበው ሪፖርት መሠረት የማፊያ የአባልነት ምልመላ የተካሄደው በቱሪሲ ኮሎና መሬት ላይ መሆኑ ተገልጿል::

በ1876 ከአጥኚዎቹ ከፍራንቼቲና ሶኒኖ ጋር ቱርሲ ኮሎና ባደረገው ሦስት ቃለ-ምልልሶች በወንጀል ጉዳዮች ላይ ግልጽ ሰው አልሆነም ነበር:: ከሁለት ዓመት በፊት፣ አራት የእሱ ሠራተኞች ከመሬቱ ላይ ተወስደው በወንጀለኝነታቸው መታሰራቸው ሲታወቅ "እንደ እኔ ያሉ የመሬት ባለሀብቶች ሁሌም ተጠቂዎች ናቸው" ሲል ነበር አምርሮ የተናገረው:: "ባላባቶች የመሬታቸውን ሀብት ለመጠበቅ ሲሉ ከወንበዴዎች ጋር መልካም ግንኙነት ፈጥረዋል፤ ምክንያቱም ምርቶቻቸውንና ዛፎቻቸውን ሌላ የሚያስከብርላቸው ኃይል ስለሌለ" በማለት ነበር ያስረዳው:: ይህን ሲል ግን አንድ ጊዜ እንኳ ስለ ህቡዕ-ቡድኑ ትንፍሽ አላለም::

ቱሪሲ ኮሎና በ1864 ስለ ማፊያ የፃፈው ፓምፍሌት ዋና ምንጩ ምናልባትም ራሱ አንቶኒዮ ጃሞና ነበር:: ፓምፍሌቱን በሚጽፍበት ወቅት ኮሎና እንዳስቀመጠው ሲሲሊን ከኢጣልያ ጋር መዋሃድ በሲሲሊ የሚታየውን የውንብድና ሁኔታ ያስቀረዋል ብሎ አሳስቧል:: ምናልባትም

የኢጣልያ መንግሥት በሲሲሊ ሁኔታዎችን እስከሚስተካከል ድረስ የማፊያ የክብር ሰው ከሆነው ጃሞና ጋር ለአጭር ጊዜም ቢሆን ኮሎና መተባበር አስፈልጎታል። ደግሞም የሲሲሊ ማፊያ ባለው መዋቅራዊ ልዩ አካሄድ እንደ ቱሪሲ ኮሎና ካሉ ፖለቲከኞች ጋር ግንኙነትን ካልፈጠረ ዓላማውን ሊያሳካ አይቻለውምና ይህን መንገድ መጠቀሙ የግድ ነበር። በማፊያ የማወራረጃ ዶክመንት ውስጥ የተገኘው መረጃ የሚጠቁመው ማንኛውም ተፅዕኖ የሚያሳድር ፖለቲከኛ ባለው ተአማኒነት የተነሳ ለማፊያ ጠቃሚ መሆኑ ተጠቅሷል። ለዚህም ነው መንግሥት የሚወስናቸው የኮንትራትና የመሬት ሽያጭ ወሬዎች ቀድመው ለማፊያ የሚደርሱት፣ በተጨማሪም የመንግሥት መ/ቤት የሥራ ቦታዎች በቀጥታ የሚያዙት ከማፊያ ጋር ግንኙነት ባላቸው ሽሪኮች ብቻ ነው።

ዋነኛ የሕቡዕ-ቡድኑ መሪ የሆኑት እንደ ጃሞና ያሉት ሰዎች ከአብዮታዊው ሁኔታ በኋላ ከኢጣልያ መንግሥት ጋር አብሮ ለመሥራት ተነሱ። ያለፈውን ሁኔታዎቻቸውን ወደኋላ በመተው በአዲሲቱ ኢጣልያ የደም-ሥር ውስጥ መንቀሳቀስን ጀመሩ።

## የሽብር ኢንዱስትሪ

ስድኒ ሶኒኖ እና ሊዮፖልዶ ፍራቼቲ ሁለቱም የእንግሊዝ ሊብራሊዝም አድናቂዎች ናቸው። ሶኒኖ መጠሪያ ስሙን ያገኘው ከእንግሊዛዊቷ እናቱ ነው። ወደ ሲሲሊ ሲደርሱ ያጋጠማቸው እነሱ የማይገባቸው ቀበሊኛ ቋንቋ ነበር። ደሴቲቱ ከጥንት ግሪካውያን ሥነ-ተረት ጊዜ ጀምሮና በጋዜጦች የፊት ገፅ ምትሃታዊ ሥፍራ እንደነበረች ሲወሳ ቆይቷል። ስለሆነም ለሚያጋጥማቸው ጭንቀትም ሆነ አደጋ ሁሉ ራሳቸውን አዘጋጅተዋል። በዚያ በ1876 የፀደይ ወራት በጉዞአቸው ጠመንጆችን፣ ባለ-ረጃጅም አፈ-ሙዝ ሽጉጦችንና አራት የመዳብ የውሃ መያዣ ገንዳ ይዘው ዘለቁ። ዓላማው በመዳብ ገንዶቹ በመጠቀም ባረፉበት ሥፍራ ትንኝ እንዳይደርስባቸው ለመከላከል እንዲረዳቸው የታሰበ ነው። ደሴቲቱ በሚገባ ያልተሰሩ መንገዶች ያሏት በመሆኑ አጥኚ ተጓዦቹ በፈረስ በመጠቀም ጥቃት እንዳያጋጥማቸው ተጠንቅቀው መጓዝ ነበረባቸው። በኋላ ላይ ፍራንቼቲ እንደፃፈው "በዚያ አስልቺ፣

ራቁቱን በቀረ መሬት ላይ መጓዝ ምትሃታዊ ቅዥትን ያሳድራል፣ አካይስታዊ መንፈስ ይጫጫናል" ሲል ነበር ስሜቱን የገለፀው።

ፍራንቼቲ በመጋቢት 24፣1876 ከትቦ እንዳስቀረው ከሆነ፣ እሱና ሶኒኖ ወደ ማዕከላዊው የሲሲሊ ካልታኒሴታ ከተማ ነበር የተጓዙት። ከሁለት ቀን በፊት አንድ ቄስ በጥይት ተመትቶ በባራፍራካ መንደር ይገደላል። ባራፍራንካ ደግሞ የማፊያ ዋና ይዞታ ነበረች። ቄሱ ተገድሎ ከተጣለበት 60 ሜትር ርቀት ላይ አንድ እማኝ ቆሟል። እማኙ ከሰሜን ኢጣልያዋ ከተማ ቱሪን የተላከው የመንግሥት የታክስ ተቆጣጣሪ ነበር። ይህ ሀቀኛ የመንግሥት ሠራተኛ ወደሚያጣጥረው ቄስ ተጠግቶ ማን እንደመታው ከቃሉ አረጋገጠ። ያ በጥይት የደበደበው ሰው ግን የቄሱ የእኅት ልጅ እንደነበርም ደረሰበት።

እጅግ በሁኔታው የደነገጠው የታክስ ተቆጣጣሪ ለወታደራዊ ፖሊሶች የሰማውን ለመንገር ፈረሱ ላይ ተቀምጦ ሸመጠጠ። ከዚያም ለቄሱ ዘመዶች ሁኔታውን ለማስረዳት ሄደ። ዘመዶቹ እንዳይደነግጡ ቄሱ ተመትቶ ወደተኛበት ሥፍራ እንዲከተሉት በማድረግ አረጋግቶ የደረሰውን ሁኔታ በጥሞና አስረዳቸው። እግረ-መንገዳቸውን የቄሱ ዘመዶች በልጁና በቄሱ መሃል 12 ዓመት ያለፈ ቁርሾ እንደነበረ አስረዱት። ቄሱ ራሱ ሀብታም፣ በሽብርና በሙሰኝነት በአካባቢው የሚፈራ ነበር። ዳሩ ግን ወንጀሉ ከተፈፀመ ከ24 ሰዓት በኋላ ታክስ ተቆጣጣሪው በፖሊስ ተይዞ በነፍስ ማጥፋት ወንጀል ዘብጥያ ተወረወረ። ታዲያ በምስክርነት የቀረበው ቄሱን የገደለው ወጣት ሲሆን፣ የአካባቢው ሰዎችና የቄሱ ዘመዶች ስለእውነተኛው ሁኔታ ቢያውቁም ዝምታን መረጡ።

ይህ በሆነ በሣምንቱ፣ ፍራንቼቲ እና ሶኒኖ የሲሲሊ ደቡባዊ ከተማ ወደ ሆነችውና በግሪክ ሀውልቶች ባሸበረቀችው አግሪጄንቶ ደረሱ። እዚህ ደሞ የፍራንቼቲ ማስታወሻ ሌላ ታሪክ ዘገበ። በሁለት ወንጀለኞች ላይ መረጃ ለፖሊስ ያቀረበችና ለመረጃዋ 500 ሲሬ /የድሮ የጣሊያን ገንዘብ/ የተቀበለች ሴት ነበረች። ሴትየዋ ገንዘቡን ከተቀበለች በኋላ የሴትየዋ ልጅ ከእሥር ተፈትቶ ወደ መንደሩ ተመለሰ። ታዲያ ከአካባቢው ማፊያ ለልጁ እናቱ ምን እንዳደረገች የተፃፈ ደብዳቤ ደረሰው። ልጅየው

እናትየው አዲስ ልብስ እንድትገዛለት አጥብቆ ቢጠይቃትም የሰጠችው የእንቢተኝነት መልስ ልጁን አበሳጭቶት ከቤቱ ወጣ። በኋላ ከአጎቱ ልጅ ጋር ወደ ቤት ተመልሶ እናቱን በጩቤ አሥር ቦታ ላይ ወጓት-ልጅየው ስድስቱ፣ የአጎት ልጅ ደግሞ አራቱ። ከዚያም አስከሬኗን በመስኮት በኩል መንገድ ላይ ወርውረው ጣሉት።

ሁለቱ አጥኚዎች ለሁለት ወራት በሲሲሊ በቆዩበት ጊዜያት ሁሉ ተመሳሳይ ሁኔታዎች አጋጥሟቸዋል። ሌላው ቀርቶ በጥናታቸው ወቅት ስለ ማፊያ ትክክለኛ ትርጉም ሲጠይቁ ብዙዎቹ በትክክል ማፊያን ለመግለፅ እንዳልቻሉ በሪፖርታቸው ጠቁመዋል። አንድ የወታደራዊ ፖሊስ መቶ አለቃ እንደነገራቸው "ማፊያን ለመግለፅ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው፣ ማፊያን በሚገባ ለማወቅ ሳምቡካ ከተማ መኖር አለባችሁ" ሲል ነበር የገለፀላቸው።

አጥኚዎቹ እነ ፍራንቼቲ ሲጓዙ የአካባቢው ነዋሪዎች ለአካባቢያቸው ከፍተኛ ኩራት ነበራቸው። "እንደ ልዩ ተክል እያንዳንዱን የሎሚና የብርቱኳን ዛፍ ይንከባከቡ ነበር" ሲል ፍራንቼቲ ገልጿል። ሆኖም ይህ ቀና አመለካከቱ ብዙም ሳይቆይ ጸጉር-በሚያቆም የግድያና የወንጀል ታሪክ ተለውጧል። "የብርቱኳንና የሎሚ መልካም መአዛ ተለውጦ የአስክሬን ሽታ መሽተት ጀምሯል፣ በአካባቢው የሽብር ኢንዱስትሪ ነግሷል" ነበር ያለው ፍራንቼቲ።

**???**

በፍራንቼቲ ግምት ማፊያ በ1812 ማለትም በናፖሊዮን ጦርነት ጊዜ እንግሊዞች ሲሲሊን ከያዙ በኋላ መመሥረቱን ያስቀምጣል። በወቅቱ እንግሊዞች ፊውዳሊዝም ከደሴቲቱ እንዲጠፋ አድርገዋል። የነበረው የፊውዳል ጦርነት በወል የመሬት ይዞታ ላይ የተመሠረተ ነበር። ንጉሱ ለባላባቶች መሬት ያከፋፍላል፣ ባላባቱ ደግሞ የየራሱን ጦር አደራጅቶ አስፈላጊው ሁኔታ ሲፈጠር ንጉሡን ያገለግላል። የባላባቶች ቃልም ሕግ ሆኖ ይቆማል። ለባላባቶች /ባሮንስ/ የሚሰጠው ልዩ ክብር ስፊና ማለቂያ የለሽ ነው። የበታቾችና አሽከሮች ለባላባት ሠላምታ ሲሰጡ እጅ ስሞ ደጅ መጥናት ግዴታ የነበረ ሲሆን ይህ ልምድ በጋሪባልዲ አማካይነት

በ1860 ተወግዷል። በስፔኖች የሚሰጠው "ዶን" (Don) የተሰኘው የክብር ማዕረግ ሲሲሊን ለሚገዙ ባላባቶችም ተሰጥቶ ሲሰሩበት ቆይተዋል።

የባላባቶች ሥልጣን መንሰራፋት የመንግሥት ፍ/ቤቶችና የፖሊስ ኃይል በእነሱ ተጽዕኖ ሥር እንዲወድቁ አድርጓል። በዚህም ምክንያት ሽብር "ዲሞክራሲያዊ" እንዲሆን ተደርጓል ሲል ፍራንቼቲ አስቀምጦታል። ፊውዳሊዝም ተገርስሶ ካፒታሊዝም ገና በማቆጥቆጥ ላይ እያለ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ለመክበር ሁሉም በራሱ የማን አለብኝነት መስመር መንቀሳቀስ ጀመረ። እንዲያውም የመንደር ወንበዴዎች በባላባቶች ከለላ እየተሰጣቸው ከህግ ውጭ ሆኑ። ከባላባቶች ላይ መሬት እየተከራዩ የሚያርሱ ማናጀሮች (Gabelloti) ሳይቀሩ ሕገ-ወጥነትን በመጠቀም ፍላጎታቸውን ለማሳካት ይጥሩ ነበር። ስለዚህ በሲሲሊ "ሽብር" ሌላው የካፒታል ማከማቻ ዘዴ ሆኖ ብቅ አለ።

ለፍራንቼቲ፣ ማፊያዎች የሽብር ኢንተርፕረነሮች ሲሆኑ በማፊያ አለቆቻቸው በኩል ሽብርን በተለያዩ የንግድ ሴክተሮች "ኢንቨስት" በማድረግ ገንዘብን በመሥራት ሞኖፖላቸውን ያስከብራሉ። ይህ ነው የሽብር ኢንዱስትሪ ማለት። ፍራንቼቲ እንደፃፈው፡-

> *"በሽብር ኢንዱስትሪ፣ የማፊያ አለቆች እንደ ካፒታሊስትና እንደ ማናጀር ናቸው። ወንጀለኞችን አስተባብረው ይሠራሉ... ሥራና ኃላፊነት አከፋፍለው ይቆጣጠራሉ፣ በሠራተኞች መካከል ሥነ-ሥርዓትን ያስከብራሉ /ሥነሥርዓት እንደ ማንኛውም ኢንዱስትሪ ዘላቂ ትርፍን ለማጋበስ እጅግ አስፈላጊ ነውና/። የማፊያ አለቆች ሁኔታዎችን በማጥናት ሽብር ለጊዜው እንዲገታ ወይም ተባዝቶ እንዲቀጥልና ጡንቸኛ እንዲሆን ስልት እየለዋወጡ ይንቀሳቀሳሉ። የገበያ ሁኔታን በማጥናት የትኛው ማፊያዊ ዘመቻ እንደሚፈፀም፣ የትኛውን ወገን መበዝበዝ እንዳለበትና የትኛውን የሽብር ዘዴ መጠቀም እንደሚያስፈልግ የማፊያ አለቆች ይወስናሉ።"*

ነጋዴዎችና ለፖለቲካ ሥልጣን ጉጉት ያላቸው ሰዎች ሁለት አማራጮች ነበራቸው፡- ራሳቸውን በጦር መሣሪያ ማደራጀት ወይም በሽብር ረገድ ስፔሻሊስት የሆኑትን ማፊያዎችን ገዝቶ መጠቀም።

መቼም ካፒታሊዝም፣ በተለይም ገና በለጋ ዕድሜ ላይ ሳለ፣ የራሱ ብልሹ ባህርይ አለበት። ፍራንቼቲ በሚያደንቀው የእንግሊዝ ማህበረሰብ እንኳ አሸባሪ ኢንተርፐረነሮች ነበሩት። ለምሳሌ በሳሴክስ (Sussex) በ1740ዎቹ የታጠቁ ቡድኖች ለራሳቸውና ከእነሱ ጋር ለተሳሰሩ ሻይ በድብቅ በማስገባትና በመሸጥ ከፍተኛ ትርፍን ያገኙ እንደነበር ይታወሳል። ለሀገር ውስጥ ገቢ ኃላፊዎች ጉቦ በመስጠት፣ የመንግሥትን ጦር በመጋፈጥ፣ በመሣሪያ የተደገፈ ዘረፋ የማካሄድ ሥራ ያከናውናሉ። አንድ የታሪክ ምሁር እንደገለፁት እንግሊዝ በ1720ዎቹ ሕገ-ወጥ ሪፑብሊክ ሆና የምትገለፅ፣ በዝምድና እና በመጠቃቀም የህዝብን ሀብት በዘዴ ለግል ጥቅም ማዋል የሚታይባት እንደነበረች ጠቅሷል።

ፍራንቼቲ በመጨረሻው የዕድሜ ዘመኑ በጣሊያን ፓርላማ ሁነኛ ሥፍራ ሳይኖረው ያገለገለ ሲሆን ይህ ነው የሚባል የፖለቲካ ሰውነት አልነበረውም። ዳሩ ግን በነበረው የአርበኝነት ስሜት በመነሳሳት ነው ስለ ሲሲሊ ማፊያ ጥናት ላድርግ በማለት ብሎ በግሉ የተንቀሳቀሰው። በኋላም አንደኛው የዓለም ጦርነት ሲፈነዳ ወደ ወሳኝ የመንግሥት አካል ገብቶ ብሔራዊ አርበኝነቱን ለማስመስከር ባለመቻሉ ይቆጭ እንደነበረ ጓደኞቹ አረጋግጠዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ጥቅምት፣ 1917 ኢጣልያ በካፐሬቶ ውጊያ መሸነፏ ሲገለፅ ክፉኛ ስሜቱ በመጎዳቱ ራሱን በጥይት ገድሎ እስከ ወዲያኛው አሸልቧል። ማፊያ ግን አሸባሪ ድርጊቱን ቀጥሏል።

# 4

# ማፊያ እንዴት ስሙን አገኘ?

በፓርሌሞ ቀበሌኛ ቋንቋ "ማፊዮዞ" (Mafioso) "ቆንጆ፣ ጎበዝ፣ በራስ-የሚተማመን" የሚል ትርጉም አለው:: ማንም "ማፊዩዞ" ተብሎ የሚጠራ ሰው "ማፊያ" የሚያሰኘው ብቃት እንዲኖረው ያስፈልጋል:: በዘመናዊው እንግሊዝኛ "Cool" ከሚል የእንግሊዝኛ ቃል ጋር መሳ-ለመሳ ነው::

ለመጀመሪያ ጊዜ ማፊዩዞ የሚለው ቃል የወንጀል ትርጉም እየያዘ የመጣው በሲሲሊ ቀበሊኛ በ1863 በቀረበው "የቪካሪያ እሥር ቤት ማፊዩዚ" I mafiusi di la vicaria) በተሰኘ ትያትር ሲሆን፤ ማፊዩዚ የእሥር ቤቱ ታሳሪ አባላት ናቸው:: አባላቱ የራሳቸው አለቃና የአባላልነት ምልመላ ሥርዓት ያላቸውና በቲያትሩ ውስጥ "ማክበር" እና "ማሳቀል" የሚሉ ቃላት በተደጋጋሚ ሲቀርቡ ነበር:: የትያትሩ ገፀ-ባህርያት የዛሬዎቹ ማፊያዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ ራሳቸውን ለመከላከያ የሚሆን "ፒሱ" (Pizzu) (በእኛ አገር የሻማ የሚባለውን) ይከፍፈላሉ:: "ፒሱ" በሲሲሊ ቋንቋ "መንቆር" ማለት ነው:: "ፒሱ" በመክፈል "የሰውየውን መንቆር ማርጠብ" የግድ ይሆናል:: ምንም እንኳ ቃሉ በእሥር-ቤት የተጀመረ ቢሆንም በቲያትሩ አማካኝነት ወደ ህዝባዊ ቃልነት ተለውጧል:: በኋላም የ1857ቱ የሲሲሊ መዝገበ-ቃላት "መንቆር" የሚል ትርጉም ብቻ የያዘው ቃል በኋላ ላይ በ1868 ተሻሽሎ "በማስፈራራት ገንዘብ ማግኘት" የሚል ተጨማሪ ትርጉም እንዲይዝ ተደርጓል::

የማፊዩዞ ቃል አንዴ ብቻ ነበር "Mafiusi di la vicaria" በተሰኘው ትያትር የቀረበው:: ከዚያ በኋላ በጣልያን የትያትር ጥበብ ውስጥ ዳግም አልቀረበም:: በኋላ ግን "ማፊያ"፣ "ማፊዩዞ" የተሰኙ ቃላት ልክ በትያትሩ

ውስጥ ሲቀርቡ እንደነበሩ ገፀ-ባህርያትን የተላበሱ ሰዎች ሲገኙ በሕብረተሰቡ ዘንድ ቃሉ በሰፊው በጥቅም ላይ ዋለ። መድረክ ላይ የዋለው ቃል፣ ወደ መንገድ ወጣ።

ለማፊያ ስያሜ መነሻነት ትያትሩ ብቻውን በቂ አልነበረም። ባሮን ቱርሲ ኮሎና በፃፈው ጽሑፍ "ሕቡዕ-ቡድን" ሲል ነበር ያስቀመጠው እንጂ "ማፊያ" ወይም "ማፊዩዞ" የሚሉትን አልተጠቀመበትም። ባሮን ቱርሲ የሚያውቃቸውን ወንጀለኞችን ወይም ህቡዕ-ቡድኑን "ማፊያ" ወይም "ማፊዩዞ" ብሎ ጠርቶ አያውቅም። ቃሉ በትክክል ጥቅም ላይ መዋል የቻለው መንግሥት ቃሉን /ማፊያን/ በመጠቀም ወደ ብሔራዊ የክርክር መድረክ ካቀረበ በኋላ ነው።

## ሥርገተ-ማፊያ በመንግሥት መዋቅር

ሲሲሊ ከጋሪባልዲ ነፃ የማውጣት ጦርነት በኋላ ከጣልያን ጋር ብትቀላቀልም ለብዙ ሲሲሊያውያን የመንግሥት ድርጊት በበጎ መልኩ አልታየም። እንዲያውም የኢጣልያ መንግሥት ከሊበራል መርሁ እያፈነገጠ ሄዷል ሲሉ ያብጠለጥሉታል። ለዚህም ሁለት ጉዳዮች ያነሳሉ፡- አንደኛው "የጩቤ-ውግ ሤራ" እና ሁለተኛው የአንቶኒዮ ካፔሎ የስቃይ ሰለባ መሆንን። እነዚህ ሁለት ነገረ-ጉዳዮች የጣልያንን መንግስት ተአማኒነት ሸረሸሩት፣ እንዲያውም ሲሲሊያውያኑ በማንኛውም ጉዳይ፣ የማፊያን ሁኔታን ጨምሮ መንግሥትን መጠራጠር ያዙ።

በአካባቢው ሰዎች በጩቤ እየተወጉ መጣላቸው ቀጠለ። በመንግሥት በኩል ጉዳዩን የማጣራት ሥራ ተጠናከረ። በዚህ ጊዜ "ሳንት ኤሊያ" የተባለ ባለባት በቀንደኛ ወንጀለኛነት ተጠረጠረ፣ በመኖሪያ ቤቱም ፍተሻ ተካሄደበት። ዳሩ ግን የጣልያኑ ንጉሥ ሳንት ኤሊያን በፓርሌሞ የትንሣኤ በዓል ላይ ወክሎአቸው እንዲገኝ አደረጉ። ምርመራው ዋጋ አጣ፣ በጩቤ የመውጋት ወንጀልም በረድ አለ፣ መርማሪዎቹም ሲሲሊን ለቀው ወጡ። ዳሩ ግን ሳንት ኤልያ "በጩቤ-ውግ ሤራ" ውስጥ ስለመኖሩ "ሆድ ይፍጀው" ሆኖ ቀረ።

በዚህ መሃል ደግሞ አንድ የተለየ ሁኔታ ተከሰተ። አንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋዜጠኛ አንድ ትኩስ ወሬ አነፈነፈ። አንድ ወጣት ተገዶ ወደ ፓሌርሞ ወታደራዊ ሆስፒታል መግባቱን ደረሰበት። አንቶኒዮ

ካፔሎ የተባለ ይህ ወጣት 150 ቦታ ላይ ተጠብሶ የአልጋ-ቁራኛ ሆኗል፡፡ በዶክተሮቹ በኩል የደረሰው ቃጠሎ "የህክምናው አንዱ ዘዴ ነው" ሲሉ ምክንያት ሰጡ፡፡ ጉዳዩ ፍ/ቤት ሲቀርብም የዶክተሮቹን አባባል እንደ ትክክለኛ ተደርጎ ተቀባይነትን አገኘ፡፡ ዕውነታው ግን ይህ አልነበረም፣ ካፔሎ ወደ ሆስፒታል ሲወሰድ ጤነኛ የነበረ ሲሆን፣ ከሰሜን ኢጣልያ የመጡ ሦስት ዶክተሮች ካፔሎ እንዲራብ፣ እንዲደበደብ በብረት ቁልፎች ጀርባው እንዲጠበስ አደረጉ፡፡ ዓላማቸው የማፊያ ክፂ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገ የምርመራ ዘዴ ነበር፡፡ በመጨረሻም ካፔሎ ከውልደቱ ጀምሮ ደንቆሮ መሆኑን ገልፆ አሳመናቸው፡፡ ወዲያው በጥር 1864 ከሆስፒታል እንደተለቀቀ በጋዜጠኛው አዘጋጅነት በፎቶው ሥር የመንግሥትን ጨካኝነት የሚገልፅ መግለጫ ታክሎበት በፓሌርሞ ከተማ ተሰራጨ፡፡

ሚያዚያ 25/1865 አንቶኒዮ ካፔሎ ስቃይ ከደረሰበት ሁለት ዓመት በኋላ የፓርሌሞ የደህንነት ኃላፊ ማርኩይስ ፊልፖ አንቶኒዮ ጉዩአስተሪዩ፣ የማስጠንቀቂያ ሪፖርት ለአለቃው ወደ ሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ላከ፡፡ እንደ ጉዩአስተሪዮ ያሉ ሰዎች ለአዲሱ የኢጣልያ መንግሥት ቁልፍ ሰዎች ናቸው፡፡ በየከተማው የመንግሥት ዓይንና ጆሮ ሆነው ተቃዋሚዎችን በመቆጣጠር፣ የህግንና የፀጥታን መከበርን ያረጋግጣሉ፡፡ በሪፖርቱ ውስጥ ጉዩአልተሪዮ "እጅግ ሥር የሰደደ አደገኛ የመናበብ ችግር በባለሥልጣናትና በሕዝቡ መካከል ይታያል" ሲል ይገልፃል፡፡ የዚህ ሁኔታ መፈጠር እንደ ማፊያ ያሉ የወንጀለኛ ማህበራት እንዲፈጠሩ ሁኔታዎችን አመቻችቷል ሲል ያረጋግጣል፡፡ ቀጥሎም "በመካከለኛው የ19ኛው ክፍለ ዘመን በፓሌርሞ ማፊያ ለተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች ጡንቸኛ ድጋፍን በመስጠቱ ተጽዕኖው አይሏል፣ አሁን ደግሞ መንግሥትን ከሚቃወም ማንኛውም ወገን ጋር ቆሟል" ይላል ጉዩአስተሪዩ፡፡ በጉዩአስተሪዩ ሪፖርትና በፓሌርሞ በሚደመጠው የከተማ ወሬ አማካኝነት የማፊያ ስጋት መንግሥት ጆሮ ደረሰ፡፡

በጉዩአስተሪዩ ማሳሰቢያ መሠረት መንግሥት 15,000 ጦር ለስድስት ወራት አሰማርቶ ሕዝቡን ትጥቅ እያስፈታ፣ ወንበዴዎችንና ወንጀለኞችን እያሰሰ በቁጥጥር ሥር እንዲያደርግ አዘዘ፡፡ ቢሆንም ማፊያን በማስገበር በኩል ዘመቻው የተዋጣለት ነበር ማለት አይቻልም፡፡

ከጉዩአስተሪዩ ሪፖርት በኋላ "ማፊያ" የሚለው ቃል በሰፊው ተቀባይነትን አገኘ። ያ "ህቡዕ-ቡድን" በፓሌርሞ ዕምብርት በነውጠኛ ወንበዴዎች፣ በመሬት ተከራዮች፣ በኮንትሮባንዲስቶች፣ በከብት ሰራቂዎች፣ በገበሬዎች፣ በህግ ሰዎች ሳይቀር ተጠናክሮ የሽብር ኢንዱስትሪን ፈጠረ። ሥልጣንና ሀብትን ከሎሚ ማሳ አንስቶ በእጁ አስገባ። ማፊያዎች ዘዴዎቻቸውን ወደ ቤተሰብና ወደ ቢዝነስ ግንኙነት አስባጥረው አስፋፉ። በእሥር ቤት እንኳ ታግተው እያለ ይህንኑ አሠራር ወደ ማፊያ ግንኙነት ያደራጁታል። በዚህ ሁናቴ እያሉ የጣልያን መንግሥት ሊጫናቸው ቢሞክርም "ህቡዕ-ቡድኑ" ወደ ማፊያነት አድጎ ብቅ አለ። በ1870ዎቹ በፓሌርሞ የተጠናከረ የማፊያ ቡድን ነበር። ማፊያ የራሱን ተከላካይ አደራጅቶና በፖለቲካ-ጓዶች ሽፋን የሴል መዋቅር አድርቶ ተንሰራፋ። እጅግም ፈረጠመ።

ከ1877 ጀምሮ ኢጣልያ ከቱርሲ ኮሎና በራሪ ጽሑፍ አንስቶ፣ በፍራንቼቲን የጥናት ሪፖርት ላይ ተንተርሶ፣ በዶክተር ጋላቲ ማሳሰቢያዎችና በሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጃዎች አማካይነት ስለ ማፊያ ዝርዝር ሁኔታ ቢቀርብም ማፊያን ማቆም አልተቻለም። ጥያቄው መሆን የሚገባው ለምን ማፊያን ማቆም አልተቻለም? ነው። ለዚህ ከፊል መልስ ሊሆን የሚችለው በወቅቱ የጣልያን መንግሥት በሌሎች ብዙ ችግሮች በመጠመዱ ሲሆን፣ ሌላውና ዋናው ምክንያት ማፊያ የኢጣልያ ሥርዓተ-መንግሥት የማይነጠል አካል መሆኑ ነው።

# 5

# ማፊያ በኢጣልያ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ መሰግሰግ (1876-1890)

## ማፊያ "የአካባቢው መንግሥታዊ መዋቅር መሣሪያ"

ዶክተር ጋላቲ ከኡዲቶሬ (Uditore) መንደር በማፊያ ተገዶ ንብረቱን ጥሎ ከጠፋና ሪፖርት ለመንግሥት ካቀረበ በኋላ ሁኔታው ተዳፍኖ ቢቆይም በ1875 ፓርላማው እንዲጣራ ትዕዛዝ አስተላለፈ። ዳሩ ግን ሁለት ዓመት ዘግይቶ በጥር 1877 የምርመራው ውጤት ቀረበ። ይህ የመጀመሪያው የፓርላማ የማጣራት ሂደት በራሱ የኢጣሊያ መሪዎች ምን ያህል ስለ ማፊያና ስለ ሲሲሊ ችግር እንደሚያውቁ ያመላክታል። ከ1875-1877 ያለው ጊዜ የኢጣልያ የፖለቲካ ሥርዓት ማፊያን ለመዋጋት አለመቻሉን ያስመሰከረበትና እንዲያውም ለማፊያ ዕድገት አስተዋፅኦ ማበርከቱን ያመላክታል።

ከኢጣልያ ነፃነት በኋላ የፖለቲካ ሥርዓቱን የተቆጣጠሩት ሁለት ፓርቲዎች ነበሩ። አንደኛው የቀኝ ክንፍ ፓርቲ የሆነው በሰሜን ኢጣልያ ወግ አጥባቂ ባላባቶች የሚመራ ሲሆን፣ የግራ ክንፍ ፓርቲው ደግሞ በደቡቦችና በሲሲሊ ሰዎች ተጠናክሮ በተቃዋሚነት የቆመ ነበር። ልዩነታቸው ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆን ባህላዊም ነው። በተለይ የደቡብ ተመራጮች "በጌታ ፖለቲካ" (Boss Politics) የሚያምኑና የደጋፊዎችን ድምፅ በመግዛት ሰሜኑ ደቡቡን የረሳው አድርገው የሚያምኑ ነበሩ።

ወደ ፓርላማው የማጣራት ሂደት እንመለስና ሂደቱ የተጀመረው በ1874 ሲሆን፣ ወቅቱ የቀኝ ክንፍ ፓርቲ በችግር የተዘፈቀበት ጊዜ ነበር፤ በሲሲሊ ደግሞ የቀኝ ክንፉ ፓርቲ እጅግ አናሳ ደጋፊዎች

ነበሩት። ለዚህም ነው ሲሲሊ የመንግሥት ችግር ሆና በቀዳሚነት የምትታየው። በዚያ ዓመት በተደረገ የምርጫ ዘመቻ የግራ ክንፉ ፓርቲ ዋና የምርጫ አጋፋሪ የነበረው ኒኮሎ ቱርሲ ኮሉና ሲሆን እሱን ደግሞ በጋሻ ጃግሬነት ሲረዳው የነበረው የማፊያ አለቃና ዶ/ር ጋላቲን ከንብረቱ ያባረረው አንቶኒዮ ጃሞና ነው። ምንም እንኳ ቀኙ ፓርቲ በደቡብ ቦታ ቢያጣም ዋናውን ሥልጣን በሮም መያዙ አልቀረም።

ከምርጫው በኋላ ሥልጣን በዋነኛነት የተቆናጠጠው ፓርቲ ተቃዋሚውን የግራ ኃይል ማብጠልጠል ጀመረ። ቀድሞ ከነበረው ፍረጃ ይበልጥ የሲሲሊን የግራ የፓርላማ አባላትን የሀገሪቱን አንድነት የማይፈልጉ፣ ሙሰኞች፣ ድምፅ ለማግኘት ወሮበሎችን የሚጠቀሙ ማፊያዎች አድርገው አሳቀሉአቸው። አጅግ ቀያጅና አማቂ ህጎች ወጡ። የወንጀለኛ ቡድኑ አባላትና የፖለቲካ ደጋፊዎች ካለምንም ፍርድ አምስት ዓመት ያህል እንዲታሰሩ የሚጠይቅ ህግ ነበር የወጣው። ኦፊሴሊያዊ ሪፖርት እንደሚያመለክተው የማፊያ የነውጥ ኃይል ምዕራብ ሲሲሊንም አዳረሰ።

ማፊያ የኃይል ርምጃዎችን እየወሰደና ምስክሮችን እያስፈራራ ህገ-ወጥነትን ከማስፈኑም በላይ አባላቱን ከሁሉም የሲሲሊ ማህበራዊ-መደብ መመልመሉን ቀጠለ። የደቡብ-ምዕራብ ሲሲሊ የደህንነት ኃላፊው ማፊያዎች "የተለዩ ሰዎች" መሆናቸውን እንደሚከተለው ይገልፃል:-

> *"ማፊያዎች የተከለከሉ መሣሪያዎችን በመያዝ፣ በመግደል፣ በመውጋትና በማታለል ይታወቃሉ። ለፈፀሙት ወንጀል ፍፁም ዝምታን ይከተላሉ። ባለሥልጣናትና አቃቤያነ-ህግ ፊት ሲቀርቡም ምንም ወንጀል እንዳልፈፀሙ ሁሉ ይክዳሉ፣ የሀሰት ምስክሮችን ያቀርባሉ፣ በሚቻላቸው ሁሉ የማታለል ተግባር ይፈጽማሉ።"*

አንድ የታይምስ ጋዜጣ የሮም ዘጋቢ "ምስጢራቸው ሊሰበር የማይችል ከጀሱይትስ (Jesuits) ወይም ከፍሪማስንስ (Freemasons) ጋር የሚመሳሰል ቡድን ነው" ሲል ነበረ የገለፃቸው። (በነገራችን ላይ ጁሱይስትና ፍሪማስንስ ሃይማኖታዊ ምስጢራዊ ማህበረሰቦች መሆናቸው ይታወቃል።)

ከምርጫ 1874 በኋላ በወጣ ጨቋኝ ህግ እነ ቱርሲ ኮሎናን የመሳሰሉ የሲሲሊ ፖለቲከኞችና ባለንብረቶች እመቃው ጠነከረባቸው፡፡ በመንግሥት ላይ የነበራቸው ዕምነት ተሸረሸረ፡፡ ትዕግስታቸው በመሟጠጡም ለተቃዋሚዎች ድምፃቸውን ሰጡ፣ የፖሊስ ኃይሉም ዋነኛ ተጠቂ መሆናቸውን አረጋገጡ፡፡ አሁን ፍጥጫው ለይቶለት በሁለት ካምፕ መሐል ፍልሚያው ተፋፋመ፡፡

ፍጥጫው በሰኔ 1875 የዕመቃ ህጉን ለማፀደቅ በተደረገ ክርክር ወቅት በግልጽ ታየ፡፡ ከሲሲሊ የመጡ የፓርላማ አባላት በየተራ እየተነሱ የሲሲሊ ደሴት መልካም ስም እንዲጠበቅ ተከራከሩ፡፡ አንዳንዶቹም ተቃዋሚን አፍ ለማስያዝ የተደረገ የመንግሥት ዘመቻ ነው ሲሉ ኮነኑ፡፡ ሲሲሊያውያን "ሞራለ-ስንኩል ስለሆኑ በጉልበት መገዛት አለባቸው" በማለት አንድ የመንግሥት የደህንነት ባለሥልጣን ያቀረበውን ሪፖርት በማስረጃነት አስደግፈው ተከራከሩ፡፡

በመጨረሻም አንድ ንግግር ክርክሩን አጦዘው፡፡ በተለይ የግራ ክንፉ ፓርቲ ደጋፊዎች ይህ ሁሉ ክርክርና ንትርክ ሲካሄድ አንድ ሰው ምንም ነገር ሳይተነፍስ ዝም ብሎ መቀመጡ አስገረማቸው፡፡ ይህ ሰው የፓሌርሞ ፍ/ቤት ዋና አቃቤ-ህግ የነበረው ዲዮጎ ታጃኒ ሲሆን ከ1868-1872 ባለው ጊዜ የቀኝ ክንፍ ፓርቲው እንዴት ባለ ሁኔታ ሲገዛ እንደነበር ስለሚያውቅ ያ ሰው እንዲናገር ፈለጉ፡፡ የግራ ፓርቲ ፓርላማ አባላት ይህን ሰው ምስጢራዊ መሣሪያቸው አድርገው ለመጠቀም ስለወሰኑ እንዲናገር ነካኩት፡፡ ታጃኒ ግን የመንግሥት ተቀጣሪ ሆኖ ስለሰራበት የዚያን ወቅት ሁኔታ ምስጢር ለማውጣት አልፈለገም፡፡ ግን ደግሞ ትዕግሥቱ አለቀ፡፡ ታጃኒ በቀረበው የግራዎች ትችት በመናደዱ ለምክር ቤቱ ንግግር ለማድረግ ብድግ አለ፡፡ ንግግሩን ከግራ ጎኑ በተቀመጠ ሰው ላይ በመጮህ "ማፊያ የለም ማለት ፀሐይ የለችም ብሎ እንደመካድ ነው፡፡" ከዚያም በሰላ መንፈስ ወደ ቀኞች ዞር በማለት ከ1866 ተቃውሞ በኋላ ፖሊስ ከማፊያ ጋር እንዲተባበር ማድረጋቸውን አጋለጠ፡፡

በሌላ በኩል ጁሴፔ አልባኔዜ በ1867 የፓርሴሞ ፖሊስ ዋና አዛዥ ነበር፡፡ ይህ ሰው ማፊያን ለሰላም አስከባሪነት መልሶ ወንጀለኞችን የመጠቀም ዘዴን ተግብሯል፡፡ አልባኔዜ ማፊያዎችን ወዳጅ በማድረግ፣

የምርጫ ድምፅ አሰባሳቢና ሙሰኛ ፖሊስ ነው ሲል አጋለጠው፡፡ በ1869 ታጃኒ ዋና አቃቤ-ህግ በነበረበት ጊዜ ፓሌርሞ አጠገብ ባለች ሞራሌ መንደር የተፈፀመው ወንጀል በብሔራዊ ጦር አዛዥ ፈቃድ ነበር የተካሄደው፡፡ በኋላም የተያዙ ሁለት ወንጀለኞች ስለሁኔታው እንዳያጋልጡ በሚል በደፈጣ ተገደሉ፡፡ የፖሊስ አዛዡ አልባኔዜ ስለጉዳዩ ምርመራ እንዳይደረግ ዕንቅፋት ከመፍጠሩ በተጨማሪ "ሕዝባዊ ሥርዓትን ለማስፈን ሲባል ባለሥልጣናት ግድያው እንዲፈፀም አድርገዋል" ሲል አፉን ሞልቶ ተናግሯል፡፡ ታጃኒ ግን ተስፋ ባለመቁረጥ አልባኒዜ በተገደሉ ሰዎች ወንጀል እንዲከሰስ አደረገ፡፡ ሆኖም በማስረጃ እጦት አልባኒዜ ሲለቀቅ ታጃኒ ሥራውን በገዛ ፍቃዱ በመልቀቅ ነው በግራ ፓርቲ ስም ለምርጫ የተወዳደረው፡፡

በፓርላማው ላይ እሳት ለብሶ፣ እሳት ጎርሶ ንግግሩን ያጠቃለለው እንዲህ ሲል ነበር፣ "የሲሲሊ ማፊያ አደገኛና የማይደመሰስ ኃይል አልነበረም፡፡ አደገኛነቱና ሊደመሰስ ያልቻለው የአካባቢው መንግሥታዊ አካል መሣሪያ በመሆኑ ነው" በማለት ንግግሩን ጨርሶ ተቀመጠ፡፡ ከዚያም በኋላ በታጃኒ ላይ የመግደል ሙከራ ተቃጥቶበት የነበረ ሲሆን በፓርላማው የተቋቋመው አጣሪ ቡድን በሲሲሊ እየተዘዋወረ ሁኔታዎችን አጥንቷል፡፡ ሆኖም ግን የኮሚቴው ሪፖርት ይፋ ሳይደረግ ቀርቷል፡፡ የቀረበው የኮሚቴው ሪፖርት ስለ ማፊያ የሰጠው ማጠቃለያ ትክክለኛ ነበር ማለት ያስቸግራል፡፡ እንዲያውም ማፊያን "እንኩቶ የድሆች ስብስብ፣ ሥራ የማይወዱ ወንጀለኞች የተሰባሰቡበት የመንግሥት ጠላቶች" በማለት ነው ሪፖርቱ ማፊያን አሳንሶ ያቀረበው፡፡ በ1877፣ የኢጣልያ ፖለቲከኞች ስለ ማፊያ በቂ ዕውቀት ቢኖራቸውም እንዳላወቁ ሆነው መታየትን መርጠዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ነው ማፊያ ወደ ጣልያን መንግሥታዊ ሥርዓት የመጀመሪያ ሥርገቱን ያጠናቀቀው፡፡

???

ሁለተኛው የማፊያ ሥረገት የቀጠለው የግራ ሕብረት መንግሥት መጋቢት 1876 ከተቋቋመ በኋላ ነው፡፡ አዲሱ የሀገር ውስጥ ደህንነት ሚኒስትር ጆቫኒ ኒኮቴራ ሲሆኑ ከጋሪባልዲ ጋር አብረው የተዋጉ የህግ ሰው ናቸው፡፡ ከማንም በላይ ስለ ደቡብ ኢጣልያ "የጌታ-ፖለቲካ" (Boss Politics) የሚያውቁ ነበሩ፡፡ መሥሪያ ቤቱ በፒያሣ ኖቮና ያለውን

መሥሪያ ቤት ለግራ ፓርቲዎች የድምፅ-ችግኝ ማፍሪያነት ተጠቀሙበት:: በዚህም ምክንያት በ1876 ምርጫ ግራዎች 414 የፓርላማ ወንበር ሲያገኙ ቀኞቹ 94 ብቻ እንዲያገኙና እንዲሸነፉ ሆነ::

ኒኮቴራ የወንጀል ጉዳዮችን በከፍተኛ ወኔና ትጋት የሚከታተል ይሁን እንጂ የሲሲሊ ህግና ሥርዓት እንደተፈለገው አልሰከነም:: አንዱም ሁኔታውን ያባባሰው ጂን ፎርስተር ሮስ የተባለ የድኝ ኩባንያ ማናጀር መታፈኑ ነው:: "ዘ ታይምስ" የተባለው ጋዜጣ በታገተበት ጊዜ ካለጉዳት መያዙንና በአፋኞቹ የተጠየቀው ገንዘብ ሲከፈል በነፃ መለቀቁን ሲዘግብ፤ ሌላው የአሜሪካ ጋዜጣ ደግሞ "ሚስቱ የተጠየቀውን ገንዘብ ከመክፈሏ በፊት የባሏን ጆሮ በፖስታ ተቀበለች" ሲል ዜናውን አጋግሎታል:: ፎርስተር ሮስ ከሚያዘወትርበት የፓሌርሞ ሀብታሞች መኖሪያ አካባቢ ስለማንነቱ ለማፊያ ሹክ እንደተባለበት ግልፅ ሲሆን እሱን ለማስለቀቅ የተከፈለው ወረታ በማፊያ ሰው አማካይነት ነበር የተከናወነው::

ኒኮቴራ የሀገር ውስጥ የደህንነት ቢሮውን እንደተረከበ ካገኘው መረጃ የደረሰበት ማጠቃለያ ቢኖር የሲሲሊ ሀብታሞች "ከማፊያ ጋር በጥልቀት ተቻችለው ይኖራሉ" የሚል ሆነ::

ሮስ ከታፈነ ከወር በኋላ ኒኮቴራ በፓሌርሞ ላይ አዲስ ኃላፊ በመመደብ የቤት ለቤት ፍተሻ እንዲካሄድና ተጠርጣሪዎች በብዛት እንዲጋዙ አደረገ:: ይህ አካሄድ የቀኝ ፓርቲዎች ሲያደርጉት እንደነበረው ሁሉ በግራዎችም ዘንድ የፖሊስ ህገ-ወጥነት ተባባሰ:: ኒኮቴራ አፈናውን በማጠናከር እሱ ማፊያ ናቸው ብሎ የገመታቸውን ሁሉ እየመታ ተራመደ:: አንድ የሲሲሊ ከበርቴና ከማፊያ ጋር ግንኙነት አለው ተብሎ የሚጠረጠር ሰው የኒኮቴራን ፀረ-ማፊያ ዘመቻ በመተቸት ጋዜጣ ላይ ፃፈ:: በዚህ የበገነው ኒኮቴራ የጋዜጣውን አዘጋጅ ወንድም በማሰር አሰቃየው:: ሆኖም የጋዜጣው አዘጋጅ መስመሩን የሚለውጥና የሚተባበር ከሆነ ወንድሙ እንደሚፈታት ቃል በመግባቱ ጋዜጣው መስመሩን እንዲለውጥ ተደርጓል:: ዳሩ ግን ኒኮቴራ "ነውጠኞቹን" ከሲሲሊ በማጽዳት በኩል የተሳካለት ነበር ተብሎ ተወድሷል:: ይህም የሆነው ከሲሲሊ ዕውቅ ፖለቲከኞች ጋር ሰጥቶ-የመቀበል የስምምነት ዘዴን በመጠቀሙ ነው::

"በነውጠኞቹ" ላይ ድልን ከተቀዳጁ ከአንድ ወር በኋላ ኒኮቴራ ከኃላፊነቱ ተነሳ። ጀብደኛና አምባገነንነቱ በግራዎች ዘንድ ሥጋትን የፈጠረ ሲሆን በቀላሉም ሊያጠቁት የሚችሉ ዒላማ ሆኖአቸዋል። በቀጣይ ዓመታት ፊዮዝ አቀጣጣዮች፣ "Stuppagghieri" ወንድማማቾችና "ፎንታና ኖቫ" የተባሉ የነውጠኛ ቡድኖች ለፍርድ የቀረቡበት ጊዜ ነበር። ብዙዎቹ የሞት ፍርድ ሲበየንባቸው ሌሎች ግን በፖለቲካ ሽፋን ሳቢያ ምንም ሳይሆኑ ቀርተዋል። ለዚህ ደግሞ በዘመነ-ኒኮቴራ የተደረገው ከማፊያ ጋር ንኪኪ ያላቸው ፖለቲከኞች ሂደቱን ለማርገብ ተሳትፎ በማድረጋቸው ነው። በዚህ ዘዴ ነበር ማፊያዎች ፖለቲካውን በማረጋጋት ተግባር ላይ የተሳተፉት። የማፊያ የክብር ሰዎች ከነጋዴዎች ጋር የቢዝነስ ትስስር ከመፍጠር አልፈው ፖለቲካዊ-ትስስር መፍጠር እንደሚያስፈልግ ለህልውናቸው ወሳኝ መሆኑን ተረድተውታል። የቀኝ ፓርቲዎች በሲሲሊ መንገድ፣ ድልድይ፣ ት/ቤት፣ ሆስፒታል፣ የከተማ ጽዳትና ደሳሳ ቤቶችን የማጽዳት ተግባር ሲፈጽሙ የግራዎች ግን ሰላም በማስፈን በሚል ስም ደራንት እያደሉ ራሳቸውንና ማፊያዎችን ጠቀሙ። ማፊያዎችም ግራዎች "የአካባቢው መንግሥት መሣሪያ" አድርገው ሊጠቀሙባቸው እንደፈለጉ ተገነዘቡ። ስለዚህ በዘመነ-ግራዎች ማፊያዎችና ፖለቲከኞች የጥፋት መሣሪያቸውን "ከእሪያ ሥጋ ማከማቻ ጋን ውስጥ ደበቁት እንጂ አላጠፉትም" እየተባለ ተተቸ። ዛሬም እንኳ ቢሆን "ማፊያዎች የአካባቢው መንግሥት አካል" ሆነው መሥራታቸውን ቀጥለዋል።

# 6

# የፋሻሪ ወንድማማቾችና የማፊያ ኑሮ በድኝ ሀገር

በሲሲሊ ደማቅ ተራሮች ላይ መሬቱን ቢጫ ያለበሰ አዲስ ነገር መታየት ጀመረ። ይህ አዲስ ነገር የኢንዱስትሪው አብዮት እጅግ ጠቃሚ ጥሬ ዕቃ ነበር። ሲሲሊን ያለበሳት ደማቁ ንጣፍ ቢጫው ድኝ ሲሆን ለተለያዩ ሥራዎች ማለትም ለማዳበሪያ፣ ለተባይ ማጥፊያ፣ ለማቅለሚያና ለፈንጂዎች መሥሪያ ያገለግላል። የአግሪጀንቶና የካልታኒሴታ መንደሮች ይህን ውድ የኢንዱስትሪ መጋቢ ጥሬ ዕቃ ሆዳቸውን ከፍተው ለመስጠት ተዘጋጅተዋል። በዚህም መሠረት በአካባቢው ቁፋሮው ደርቷል። ከዚያ የሚወጣው የድኝ ቃጠሎ ሰማያዊ ፈሳሽ እየለቀቀ በአካባቢው ሕዝብና ከብቶች ላይ ጉዳት ማድረሱንም ቀጥሏል። ሕይወት በድኝ ማዕድኑ አካባቢ እጅግ አስቸጋሪ ሆነ። በየቦታው ሰዎች ሩሓቸውን ስተው እየወደቁ ተጉዱ። እሳት እየተነሳም በአካባቢው መርዛማ ጭስ ይለቅ ስለነበር በ1883 ብቻ መቶ ሰዎች አለቁ።

የሲሲሊ የድኝ ማዕድን ሁኔታ በኢጣሊያ ትልቅ ብሔራዊ ውድቀት ተደርጐ ይቆጠራል፤ ምክንያቱም የጤና ችግር ከማስከተሉ በተጨማሪ በሰባትና ስምንት ዓመት ልጆች ላይ የጉልበት ቅጥር ሥራ ስለሚያካሄድ ጭምር ነው። ህፃናቱ አሰቃቂ ሕይወትን ይመራሉ። ሌላው ቀርቶ ለጉልበታቸው ምንዳ በቀጥታ የሚያገኙት አንድ ኩባያ ወይንና ሲጋራ ብቻ ሲሆን አነስተኛ ክፍያውም ቢሆን የሚሰጠው ለወላጆቻቸው እንጂ ለእነሱ አልነበረም። የሚሸከሙት ከባድ ቋጥኝ ወገባቸውን አጉብጦአቸው በእጅጉ ይሰቃዩም ነበር።

መጋቢት 1883፣ በሲሲሊ ደቡብ-ምዕራብ በፋቫራ ከተማ የሚሰራ የባቡር ሠራተኛ በቀጥታ ወደ ፖሊስ በማምራት "La Freatellanza፣ ወንድማቾች፣ የተባለ ምስጢራዊ ድርጅት እንድቀላቀል ተጠይቄያለሁ" ሲል ሹክ አለ። ይህን ጥያቄ መጀመሪያ ያቀረበለት አንድ ግንበኛ ሲሆን፣ ቀጥሎም በሌሎች አባላት እንዳትጠቃ ምስጢራዊ ድርጅቱ ልዩ የመገናኛ ምልክት ስላለው ለክለላነት ትጠቃምበታለህ ሲል ገለፁለት። ታዲያ የባቡር ጣቢያው ሠራተኛ ለፖሊስ ሹክ ያለው ከድርጅቱ ጀርባ የወንጀል ድርጊት መኖሩን በማረጋገጡ ነበር።

የካቲት ላይ በፋቫራ የክርስትና በዓል በሚከበርበት ወቅት ከአንዲት አነስተኛ ቡና ቤት ፊት ለፊት አንድ ሰው በሁለት አጥቂዎች ተገደለ። የክርስትና በዓሉን የሚያከብሩት ሰዎች በሞላ ተያዙ።

በኋላ ላይ በፋቫራ እንደተደመጠው ነፍሱ የጠፋው ሰው የወንጀለኞች ቡድን አባል ነበር። የዚህ ወሬ መናፈስ ይበልጥ እየተረጋገጠ የሄደው አንድ የገዳይ ቡድን ወገን ከከተማ ውጭ በተገደለ ጊዜ ሲሆን ግለሰቡ ከጀርባው ተተኩሶ ሲወድቅ፣ አንድ ጆሮውም ተቆርጦ ተገኘ። በሚቀጥሉት ቀናት የሁለቱም ቡድን አባላት መሣሪያ ታጥቀው ወደ ከተማዋ ገቡ። ዳሩ ግን ከባድ ግጭት ይነሳል ተብሎ ቢጠበቅም ዕውን ሳይሆን ቀረ። ፖሊስም ቢሆን ከዕንቅልፍ የነቃው የባቡር ጣቢያው ሠራተኛ ታሪኩን ከነገራቸው በኋላ ነበር።

በመጋቢትና በግንቦት 1883 ወራት መካከል በፋቫራና ከአካባቢው ከ200 ሰዎች በላይ በፖሊስ ተያዙ። የወንድማማቾች ቡድን መሪ የሆነው ሰው ሲያዝም የሚስጢራዊ ድርጅቱ ሰነድ ተገኘበት። ማን፣ መቼና ማንን እንደሚገድል ሲናዘዝ ሌሎች ተጨማሪ ማጋለጦችም ቀጠሉ። ከየጉድባው፣ ከድኝ ማምረቻ ጉድጓዶች የሞቱ ሰዎች አስከሬኖች ተለቀሙ። የወንድማማቾች ምልክትና የድርጅቱ መዋቅርም ተያዘ።

በወንድማማቾች ላይ በአግሪጀንቶ ከተማ በሚገኘው በቅዱስ አን ቤተክርስቲያን የቻለው ልዩ ፍ/ቤት በ1885 ስለ ወንጀለኞቹ ጉዳይ ማየት ጀመረ። አንድ መቶ ሰባት ሰዎች በሰንሰለት ታስረው በአራት ረድፍ ቀረቡ። ብዙዎቹ የቀረበባቸውን ክስ "ፖሊስ ስለደበደበን ነው የእምነት ክህደት ቃላችንን የሰጠነው" ሲሉ ሸመጠጡ። ዘዴያቸው ግን ሊሠራ

አልቻለም። «ወንድማማቾች» ጥፋተኛ መሆናቸው ተረጋግጦ እንዲታሰሩ ተደረጉ።

የፋቫራ ወንድማማቾች ጉዳይ ለፖሊስ ልዩ ሁኔታን ፈነጠቀለት። ከፓሌርሞ ርቆ በድን ማዕድን አካባቢ በሆኑት አግሪጀንቶና ካልታኒሴታ ሌላኛው የማፊያ ድርጅት መብቀሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እጃቸው ገባ። ዛሬ የታሪክ ተመራማሪዎች እንደሚያምኑት ባለሥልጣናት ከሚገምቱት በላይ «ወንድማማቾች» አደገኛ ድርጅት መሆኑን ነው። ማፊያ በሲሊሊም ሆነ በፋቫራ አካባቢዎች ሳይጠፋ የቆየው በተሰጠው እጅግ አናሳ ግምት ሲሆን፣ ፖሊስ ስለ «ወንድማማቾች» መረጃ ሲደርሰው ገና በእንጭጭ ደረጃ ላይ ነበር። የተመሠረተውም የክርስትና በዓል በሚከበርበት ወቅት ግጭት የፈጠሩ ሁለት ቡድኖችን በማስማማት አንድ ወጥ ድርጅት ሊቋቋም እንደሆነ ማህደራቸው ያስረዳል።

ዳሩ ግን «የወንድማማቾች» ደንብ ከድርጅቱ የቀደመ ሲሆን በተቀናጁት ሁለት ቡድኖች ዘንድ ሲተገበር ኖሯል። የዶክተር ጋላቲን ጽሑፍና የ Uditore ማፊያ ታሪክን ለሚያስታውሰው ሁሉ ደንቦቹ የታወቁ ናቸው። ለምሳሌ አባላቱን የሚመለምሉት ከአመልካች ጣታቸውን ከተበጣ በኋላ በቅዱሳን ስዕል ላይ ደሙን በመርጨት ይጀምራል። ከዚያም ቅዱስ ስዕሉ እንደተቃጠለ «ለወንድማማቾች ታማኝ መሆኔን አምናለሁ። ይህ ቅዱስ ስዕልና የደሜ ነጠብጣብ እንደነደደው ሁሉ እኔም መልሼ ደሜን ለወንድማማቾች አፈሳለሁ! ይህ አመድና ደም እንደማይመለስ ሁሉ እኔም ወንድማማቾችን አልክድም» በማለት ቃለ መሃላቸውን ያሳርጋሉ።

የ«ወንድማማቾች» መዋቅር ከኮዛ ኖስትራ መዋቅር ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። የወንድማማቾች ቡድኖቹ አሥር ሰዎችን (Decine) ባቀፈ አነስተኛ ጓድ የተከፋፈለ ሲሆን እያንዳንዱ ጓድ ለአባላቱ ብቻ የሚታወቅ መሪ አለው። መሪው በሌሎች «የወንድማማቾች» አባላትም ሆነ መሪዎች ዘንድ ፍፁም አይታወቅም።

መርማሪዎች በሚገባ እንዳረጋገጡት በአባላት መካከል ያለው ትስስር ከቤተሰብ ትስስር ይልቅ የተቀደሰ ተደርጐ እንደሚወሰድ አረጋግጠዋል። አንድ «የፋቫራ ወንድማማቾች» አባል የሆነው ሮዛሪዩ

ስለ ወንድማማቾች ለፖሊስ እንደተናገረው ዋርሳው ባንዳ በመሆኑ እንዲገድለው መመሪያ እንደሰጡት ገልጿል። የራሱን ዋርሳ ካልገደለ ግን ራሱን እንደሚገድሉት አስጠንቀቁት። ዋርሳውን ለመግደል ከተስማማ በኋላ ፍርሃቱን ለማስለቀቅ የወይን ብርጭቆውን አነሳና «ወይን ጣፋጭ ነው፣ ግን ደግሞ የሰው ደም የበለጠ ጣፋጭ ነው!» አለ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ዋርሳው በግድያ ወጥመድ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ሌሎች «ወንድማማቾች» ገደሉት። ለኑዛዜው ማስረጃ እንዲሆን ዋርሳው ወደተገደለበት ግንብ ወስዶ ለፖሊስ አስክሬኑን አሳየ። በመጨረሻም ወደ እሥር ቤቱ እንደተመለሰ ራሱን ሰቅሎ ተገላገለ።

ዛሬም ቢሆን ማፊያ በአባላቱ መካከል የደም ንኪኪ እንዲኖር ያደርጋል። ዝምድና ምንግዜም እንደዚህ ዓይነቱን ስውር ነውጠኛ ድርጅት ስለሚያጠናክር ወንድማማቾች፣ የአጐትና የወንድም ልጆች በድርጅቱ ውስጥ ይሰባሰባሉ። ሆኖም ግን የካፖውን ትዕዛዝ የማይፈፅሙ ከሆነ ከፍተኛ ቅጣትን ያስከትላል። አንድ የማፊያ የክብር አባል የሆነ ሰው ወንድም ኖሮት ያ ሰው ግዳጁን ካልተወጣ ለማፊያው ወንድም የሚሰጠው ትዕዛዝ የማያወላዳ ነው። ያለው ብቸኛ ምርጫ ወንድሙን መግደል ወይም ሁለቱም የሞት ፅዋቸውን መጨለጥ። ከዚህ ውጭ ሌላ አማራጭ መንገድ የለም። አንድን የቤተሰብ አባል ማጥፋት ለተወለኑ የክብር ሰዎች የበለጠ ኩራትን የሚያላብስ ነው። አንድ የማፊያ አባል በ1980ዎቹ እጁ ሲያዝ «እኔ ነኝ በራሴ ደም እጄን ያነፃሁት!» ሲል ነበር ጉራውን የቸረቸረው።

በወንድማማቾችና በፓሌርሞው የማፊያ ጐጥ መካከል ያለው መመሪያ ተመሳሳይ ነው። ምንም እንኳ ፋቫራና ፓሌርሞ በተቃራኒ አቅጣጫ ያሉና በመቶ ኪሎ ሜትሮች የሚለያዩ ቢሆንም ሁለቱም ድርጅቶች ተመሣሣይ መመሪያ ይጋራሉ። የዚህን ተመሳሳይነት የፈጠረውን ሁኔታ ለማሳየት አንድ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል። ይኸውም ከ1879 በፊት በኡሺካ (Ustica) የደሴት እሥር ቤት ውስጥ ከፖሌርሞ ከመጡ ማፊያዎች ጋር ታጉረው ነበር። በዚያ ጊዜ ይሆናል እንግዲህ የፋቫራዎቹ እሥረኞች በማፊያ አባልነት የተያዙት። ታዲያ ከእስር በቤቱ እንደተፈቱ ሙሉ የማፊያ አባል ሆነዋል ነው የሚባለው።

የፋብሪ ወንድማማቾች መርማሪዎች ልምድ እንደሚያሳየው ድርጅቱን የሚያስተሳስረው ሥርዓተ-ባህል «ኒላቀር» መሆኑን ነው፡፡ ለብቀላና ለፍፁም ምስጢረኝነት (Omerta) የሚገዛ ጥሬ መንፈስ ነው የወንድማማቾች ድርጅት ህይወት፡፡ ድርጊታቸው «ፍፁም በላኤ-ሰብ» መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡ ባጠቃላይ በፓሌርሞ የሎሚ ማሳ የማፊያዎች መፈልፈያ ማዕከል እንደሆነ ሁሉ የድኝ እንዱስትሪውም የማፊያዎች ማፍሪያ ሌላኛው ማዕከል ነበር፡፡

በማፊያ ድርጅት ዋነኛ ተጠቃሚዎቹና ዕውነተኛዎቹ ከበርቴዎች የማፊያ አለቆች ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ከስርቆት ያገኙትን ፍሬ እንደፈለጉት ሲንበሸበሹበት ይታያል፡፡ ታዲያ ማፊያዎች የሚሉትና የሚያደርጉት ሁሉ ለየቅል ነው፡፡ ጁሴፔ አሎንጃ» የተባለው ፖሊስ ስለዚህ ጉዳይ በአንድ ወቅት ስለ ማፊያዎችና ቋንቋቸው ሲገልፅ፡-

> *«ሰዎቹ ምናባዊ ሲሆኑ ሰፈራቸው ደግሞ ሞቅ ደመቅ ያለ ነው፡፡ የዕለት ተዕለት ቋንቋቸው ጣፋጭ፣ የተጋነነና ምስል ከሳች ነው፡፡ ዳሩ ግን የማፊያዎች ቋንቋ እጥር-ምጥን ያለ፣ አስተውሎትን የተላበሰ ሲሆን... ለምሳሌ 'የእኔ ውድ፣ አብረህ የምታወራው ሰው ደደብ ነው፣ ክብርህን የምታስጠብቀው እንዲህ ዓይነቱን እንደ ጠላት ስትቆጥረው ነው' የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ በጥሬ ትርጉም ሕፀፅ የለበትም፣ ግን ትርጉሙ በተቃራኒው ነው፡፡ እንዲህ ይተረጎማል ሰውየው አደገኛ ትምህርት ያስፈልገዋል፡፡ አሁን ግን ጊዜው አይደለም - ተወው፡፡ እንጠብቀው፡፡ ከዚያም ባላሰበው ጊዜና ቦታ እናገኘውና እናሳርፈዋለን» ማለት ነው፡፡ ዕውነተኛ ማፊያዎች ሽክ ብለው ይለብሳሉ፣ በባህርያቸውና በአነጋገራቸው ወንድማዊና ልስልሶች ናቸው፡፡ አንድ ማፊያ ለምትናገረው ነገር ልዩ ትኩረት ሰጥቶህ ያዳምጥሃል፡፡ ስድብና ጥፊን በትዕግሥት ያሳልፋል፡፡ ከዚያም፣ በዚያው ምሽት በጥይት ያሳርፍሃል፡፡*

# 7

# ሙስናና ማፊያ (1890-1904)

## የአዳዲስ ፖለቲከኞች መፍላት

ዶን ራፋኤሌ ፓሊሶሎ ገና በጥዋቱ ደንበኞቹን በፓሌርሞ Palazzo Villarosa ይቀበላል። ደንበኞቹ አበባ ወይም ሌላ ስጦታ ተሸክመው ሲመጡ እሱ ግን እንደ ተጀነነ አልጋው ላይ ብርድ ልብስ ደርቦ ይጠብቃቸዋል። አንዳንዶቹ በማዘጋጃ ቤቱ ሥራ ፈላጊዎች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ዝውውርና ዕድገት የሚፈልጉ ዳኞችና የፖሊስ ባለስልጣናት ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ የጦር መሳሪያ ፈቃድ ማግኘት የሚፈልጉ ወይም ከፖሊስ ክትትል ለማምለጥ ሲሉ እጅ ይነሱታል። አንዳንድ አማካሪዎች ደግሞ በኮሚሽን ወይም በኮሚቴ ውስጥ ሁነኛ ሥፍራ የሚፈልጉም ዶን ራፋኤሌን ይጎበኛሉ። የሁለተኛ ደረጃና የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሳይቀሩ ማርክ እንዲሻሻልላቸው ሲሉም ወደ ዶን ራፋኤል ይጎርፋሉ።

ዶን ራፋኤሌ ሰዎችን የሚንቅ ሳይሆን ሁሉንም በጥሞና የሚያዳምጥ ደርዝ ያለው ሰው ነው። ይጫወታል፣ ስለ ዘመድ አዝማድ ደህንነት አጥብቆ ይጠይቃል፣ ለሚገጥማቸው ሁሉ የዕርዳታ እጁን እንደሚዘረጋም ቃል ይገባል።

ከሰዓት በኂላ ደግሞ የራሱን የግል ጉዳይ ይከውናል፣ የሌሎችን ጉዳይ ሲፈፅም ይውላል። ዶን ራፋኤል በኢኮኖሚው አቋሙ የግል መሬት ያለው፣ በአካባቢና በክፍለ ሀገር የመንግስት መዋቅር በማማከር የሚሰራ፣ በባንክና በበጎ አድራጎት ተግባር ንቁ ተሳትፎ ያለው ነው። የባህር ኃይል የጤና ኢንሹራንስ ፈንድ ሥራ አስኪያጅ ሲሆን ማንም በሥልጣን ላይ ይውጣ እሱ ግን ሁሌም የመንግስት ደጋፊ ሆኖ ይሠራል። ዋና ዕቅዱና ዓላማው በፖለቲካው ውስጥ ተሞዳምዶ

መቀጠል ነው፡፡ በኢጣልያ በተለያዩ ሥፍራዎች ይህ አይነቱ አካሄድ ስር የሰደደ ነው፡፡ እርግጥ መራጮች ከፖለቲከኞች የሚፈልጉት ጥቅማ-ጥቅም በየትም አገር ያለ ነው፡፡ ፖለቲከኞችና የመንግስት ባለስልጣናት ሕዝባዊ ሃብትን ለሚፈልጉት መስጠት፣ ሥራ፣ ኮንትራት፣ ፈቃድ፣ ዕርዳታ ጭምር በማድረግ ሥልጣናቸውን ይገለገሉበታል፡፡ አልፈው ተርፈውም ለደጋፊዎቻቸው የግንኙነት ድር ፈጥረው ግላዊ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ የእከክልኝ ልከክልህ ፖለቲካ፣ መሞዳመድና ሙስና ባይሰፍን ኖሮ ማፊያ በሲሲሊ ህይወት ባልኖረው ነበር፡፡ ለዚህ ነው ዶን ራፋኤሌ ማፊያነቱን በዚህ የመሞዳሞድ ፖለቲካ ውስጥ ያጠናከረው፡፡

በሲሲሊ ከ1882 በኋላ የጅምላ ፖለቲካ ተስፋፋ፡፡ ምርጫ በድንገት ውድ ሆነ፡፡ ይህ ታዲያ ለፖለቲከኞችና ለማፊያዎች የአደጋና የመልካም አጋጣሚን ጊዜ ወለደላቸው፡፡ ዶን ራፋኤል ይህን አጋጣሚ ለመጠቀም ተግቶ ተነሳ፡፡ መሰሪ አካሄዱን ቀጠለበት፡፡ የዕርዳታ ድርጅቶችን ተገለገለባቸው፣ ወንበዴዎችን እየደበቀና እየተጠቀመባቸው የማፊያን ተግባር አጠናከረ፡፡ የተፅዕኖ አካባቢውን ከVillabate አንስቶ ወደ ደቡብ ምስራቅ "Caccamo, Termini Imerse" እና Cafali ግዛቶች አስፋፋ፡፡ የVillabate ዋና የማፊያ አለቃ (ዶን) ሲሆን በማፊያዎች ግብዣ ላይ ክብር ሰው በመሆን የማፊያ አሰራሩ እስከ ፓሌርሞ እንዲዘልቅ አደረገ፡፡ በዚህም ምክንያት የፓሌርሞ የፖለቲካ ድሩን በማጠናከሩ የአካባቢው የፓርላማ አባል ሆኖ ሦስት ጊዜ በ1890ዎቹ ለመመረጥ በቅቷል፡፡

ለምሳሌ ያህል የጦር መሳሪያ ፈቃድን እንኳን ብንወስድ የዶን ራፋኤሌና የማፊያን ጥብቅ ግንኙነት መረዳት ያስችላል፡፡ ፈቃድ ማግኘት እንኳ የሚቻለው አመራር ላይ ካሉ ፖለቲከኞች ድጋፍ ሲገኝ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለማፊያዎች መልካም አጋጣሚን የሚፈጥር ሆነ፡፡ በተለይ ምርጫዎች በሚካሄዱበት ወቅት አሠራሩ ስውር ዘዴን ያዘ፡፡ በሀገር ውስጥ ደህንነት ትዕዛዝ አካባቢው አለቃ የመሳሪያ ፈቃድ ሊነጥቅ እንዲችል ትዕዛዝ ተላለፈ፡፡ የዚህ ልዩ ትዕዛዝ መውጣት ዋና አላማው በምርጫ ወቅት ብጥብጥን ለማስወገድ ነው ተብሎ ቢነገርም እውነተኛው ዓላማ ግን ምርጫው ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ነበር፡፡ በዚህ ሰበብ ፖለቲከኞች ልዩ የፖለቲካ ጥቅም እንዲያገኙ ረድቶአቸዋል፡፡

የኢጣልያ የፖለቲካ ሥርዓት መበታተን ለዶን ራፋኤል ከፍተኛ ረዳት ሆነለት፡፡ በእከክልኝ ልከክልህ ፖለቲካና በተሞዳሟጅ ቡድኖች መካከል ምንም ልዩነት የሚታይ አልነበረም፡፡ ከላይ እስከ ታች ባለው የመንግስት መዋቅር፣ በብሔራዊና ክልላዊ ምክር ቤቶች ሳይቀሩ ይህ መያያዝ ፍንትው ያለ ዕውነታ ነበር፡፡ ከፖለቲካ ሥርዓቱ መበታተን ጎን በስትራቴጂካዊ ሁኔታ የተቀመጡ ህዳጥአን (Minority) ሥርዓቱን እንደ ልባቸው ምገውታል፡፡ በዚህ ረገድ ማፊያ ቀዳሚውን ሥፍራ ይዞ ነበር፡፡

በፖለቲካው ምህዋር ዙሪያ ዓይንና ናጫ የሆኑት የፖለቲካ ቡድኖች ለጥቂት ጊዜያት በሲሲሊ የፖለቲካ ውጥንቅጥ ተባብሶ የመበታተን አደጋ ገጥሟቸው እንደነበር ይታወሳል፡፡

በ1892 ሁለት የኢጣልያ አበዳሪ የገንዘብ ድርጅቶች ታጠፉ፡፡ ቀጥሎም በዚያው ዓመት Banca Romana ማለትም ገንዘብ ማተም የሚችለው ባንክ ሚልዮን ሊሬዎችን ማተሙን ቀጠለ፡፡ የሀሰት ሊሬዎች (የወቅቱ የጣልያን ገንዘብ) ተበተኑ፡፡ ገንዘቦቹ ለቀዳሚ የፖለቲካ ቁንጮች እየታደሉ የምርጫ ዘመቻቸውን እንዲያሟሙቁበት ተደረገ፡፡ የሊሬ መዳከም የብርና የነሐስ ሳንቲሞች የማይገኙ አደረጋቸው፡፡ ባጠቃላይ የሀገሪቱ የፋይናንስ ሥርዓት እስከነአካቴው ሊንኮታኮት ተቃረበ፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሲሲሊ በ1894 በመሬት ከበርቴዎችና በጉልበት ሠራተኞች መካከል የተነሳውን ሁካታ ለማስወገድ ጥረት ተጀመረ፡፡ በኋላም የሶሻሊስት ፓርቲው እንዲታገድ ተደረገ፡፡

በመጀመሪያው ሲሲሊያዊ ጠቅላይ ሚኒስትር ፍራንቼስኮ ክሪስፒ አማካይነት ጣልያን ያጋጠማትን ቀውስ ባልተጠበቀ አደገኛ መንገድ ለመፍታት ታቀደ፡፡ ይኸውም በኢትዮጵያ ላይ የቅኝ ግዛትን ድል ለመጎናፀፍ በሚል፡፡ ውጤቱ ግን የተገላቢጦሽ ሆነ፡፡ በ1896 በአድዋው ጦርነት 17500 የኢጣልያና በተጨማሪ የባንዳ (Askari) ጦር (በአብዛኛው ኤርትራውያን) የተጠናከረው ሠራዊት የተሻለ የውጊያ ብቃትና ወኔ በነበረው የኢትዮጵያ ጦር ብትንትኑ ወጣ፡፡ ይህም የመጀመሪያው የቅኝ ግዛት ኃይል ውርደቱን የተከናነበበት እንደነበር ይታወሳል፡፡

ሀገሪቱ (ኢጣልያ) ከቀውስ ወደ ቀውስ አዘቅት ወረደች፡፡ ሌላው ቀርቶ በዓመቱ በ1898 በሀገሪቱ የኢኮኖሚ መዲና በሆነችው ሚላን

አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታወጀ። ስማንያ ሰዎችም በመንግስት ጦር ተገደሉ። አድመኞች ተደብቀውበታል የተባለው የሚላን ካፑቺን ገዳም በአዳፍኔ ተደበደበ። የአዳፍኔው ጭስ ከአካባቢው ሲለቅ ጥቂት መናኒያንና የዕለት ሾርባቸውን ለመውሰድ የተሰለፉ ምንዱባን ብቻ በህይወት ተገኙ።

ከሚላኑ ሁኔታ በኋላ አንድ ወታደራዊ ሰው የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ ያዘው። ይህ ሰው ጀኔራል Luigi Pelloux ሲሆን ለጣልያ ንጉሥ ከልጅ ወታደርነት ጀምሮ ሲያገለግል የነበረ ነው። የዚህ ጀኔራል ዘመን በኢጣልያ መጥፎ ትዝታ ሲኖረው አምባገነናዊ አገዛዙን አስፍኖ ቆይቷል። የፕሬስ ነፃነት ታፈነ፣ የሠራተኛ ማህበራት ታገዱ፣ ተጠርጣሪዎች ካለ ምንም ፍርድ እንዲጋዙ ተደረጉ። ሆኖም ግን ጀኔራሉ በጣልያን ውስጥ መረጋጋት እንዲፈጠር አድርጓል። ከፕሮግራሞቹ አንዱም በሲሲሊ ሙስናን መዋጋት ነበር። ከዚያም ነሐሴ 1898፣ አዲስ የፖሊስ አዛዥ ማፊያን እንዲዋጋ በሚል መመሪያ በፓሌርሞ መደበ። በ1900 ይኸው የፖሊስ አዛዥ የደን ራፋኤሌ ፖሊስሎን የፖለቲካ ደጋፊዎችን እንደሚከተለው ገለፃቸው፡-

«ማፊያዎች ናቸው። የወንጀል ሪኮርድ ያለባቸው፣ በሕዝብና በሕዝብ ሀብት ላይ ቋሚ አደጋ የሚያደርሱ ወንጀለኞች። ዕጩዎቻቸው እንዲመረጡ ማስፈራራትንና ረብሻን የሚጠቀሙ... አልፈው ተርፈው ማፊያ የሚጠቀምበትን ዘዴ በፍራፍሬ ማሳዎች ባለቤቶች ላይ ቁጥጥርን የሚያሳድሩ ወሮበሎች» ሲል ነበር የገለፃቸው።

ዶን ራፋኤሌ አዲስ የማፊያ ፖለቲካ ፍል ብቻ ሳይሆን፣ የመጀመሪያው ከፍተኛ የማፊያ ተፈራጅ ሆኖ ቀርቧል። ራፋኤሌ በሀገሪቱ ውስጥ በ25 ዓመታት ውስጥ ዋና የዜና ርዕስ ሲሆን ደመኛው ሰው ደግሞ የፖሌርሞው የፖሊስ አዛዥ በማፊያ ታሪክ ውስጥ ልዩ ሥፍራን ይይዛል። የዚህ ሰው ስም ኤርማኖ ሳንጆርጂ (Ermanno Sangiorgi) ሲሆን እሱ ከትቦ ያኖራቸው ጽሑፎች በቅርቡ ነው ከቤተ-መዘክር ወጥተው ለዕይታ የቀረቡት።

## የሳንጆርጂ ሪፖርት

ሮማ በሚገኘው ማዕከላዊ የመንግሥት ቤተ-መዘክር ውስጥ ከተከማቹ ሥፍር ቁጥር ከሌላቸው መዛግብት፣ ከደህንነት ሚኒስቴር

መሥሪያ ቤት በተለያዩ ጊዜያት (ከ1898-1900) የተሰባሰቡ ሪፖርቶች ይገኛሉ። ከነዚህ ውስጥ ደግሞ የፓሌርሞ የፖሊስ አዛዥ በነበረው በኤርማኖ ሳንጆርጂ የተፃፈው ሪፖርት ነው። በ485 ገጾችና በቢጫ ወረቀት በገዛ እጁ የተፃፈውን ሪፖርት ማንበብ በራሱ እንደ አርኪዎሎጂስቶች ለብዙ ምዕተ-ዓመታት ከምድር ሥር የተቀበረ ማስር እየቦረሹና እየጠረጉ እንደማስቀመጥ ይቆጠራል። የተቀመጠው ዶክመንት ያልፈነዳ ቦንብ ከተቀበረበት እንደማውጣት ተደርጐ መታሰብ አለበት።

ሪፖርቱ የማፊያን ምሉዕ-ገፅታ የሚያሳይና የቀረበውም መረጃ አስተማማኝ፣ ዝርዝርና በሥርዓት የቀረበ ነው። ከዶክመንቱ የማፊያ ቡድኖች ከፓሌርሞ ስሜንና ምዕራብ ባሉ ከተሞችና መንደሮች ድራቸውን እንዳደሩ የሚገልፅ መዋቅር ይዟል። የማፊያ ቡድኖች (Cosca) አለቃና ረዳቱም ተገልፀዋል። ዝርዝር ግለ-ታሪካቸውም ቀርቦበታል። በጠቅላላው የ218 የክብር ሰዎች ግለ-ታሪክ ሰፍሯል። ማፊያ የተማከለ የገንዘብ ፈንድ ያለው መሆኑና ገንዘቡም ለታሰሩ የማፊያ አባላት ቤተሰቦችና ለዳኞች የሚሰጥ መሆኑን ዘርዝሯል።

የሪፖርቱ ፀሐፊ የሆነው ሳንጆርጂ ቀጥተኛና ቆፍጣና ፖሊስ ሲሆን በዕድሜውም ወደስድሳው ተጠግቶ ነበር። ፒሙ መሸበት የጀመረና በሰሜን ማዕከላዊ ኢጣልያ «ሮማኛ» ግዛት ነበር የተወለደው። ሳንጆርጂ ለብዙ ጊዜያት ተደብቆ የኖረና እምብዛም ስለ ግለ-ህይወቱ የሚታወቅ አልነበረም። በጥቂቱ ግን ዶ/ር ጋላቲ በ1875 ያቀረበውን ሪፖርት የመረመረና የፋቫራ ወንድማማች ማፊያን በ1883 በቁጥጥር ሥር ያዋለ ጃዊሳ ነበር። የፓሌርሞ ፖሊስ አዛዥ የሆነው በመጨረሻው የሙያው ማገባደጃ በ1898 ሲሆን በሀገር ውስጥ ደህንነት መ/ቤት የተመደበውም የሲሲሊን ማፊያ ጉልበቱን ኮድኩዶ እንዲያሳርፈው በሚል ነው።

የሳንጆርጂ ትረካ በአብዛኛው ያተኮረው በምዕራባዊው የፓሌርሞ ግዛት - «ወርቃማው ሸለቆ» በሚባለው ሥፍራ ነው። አካባቢው በተፈጥሮ ውበቱና ለእምነት በማደር ረገድ ከጥንት ሮማውያን ዘመን ጀምሮ ይታወቃል። በተለይም በሪፖርቱ ለአካባቢው ድብቅ የሆነው «የአራት ሰዎች መሰወር፣ የውድ ታሪካዊ ዕቃዎች መሠረቅንና እንደወጡ ስለሚቀሩ ሰዎች» በዝርዝር ፅፏል።

ከመጋቢት 27 - ሚያዝያ 8፣ 1900 ባለው ጊዜ ሳንጆርጂ ወታደራዊ ፖሊሶችን (Carabinieri) በማዘዝ በዝርዝር የተያዙ ማፊያ-ዎችን አስከበበ። እስከመጨረሻው ደቂቃ የታዘዙት ፖሊሶች ምንም እንዳያውቁ አድርጎ ምስጢር እንዳያፈተልክ ተጋ። በዚያ ዘመቻ ሰላሳ ሶስት የማፊያ ተጠርጣሪዎች ሲያዙ በተከታታይ ወራት ደግሞ እንዲሁ ከዚህ ቁጥር በላይ ተይዘዋል። በ1900 የፓርሌሞ ገዥ ባቀረበው ሪፖርት ሳንጆርጂ ማፊያን ወደ «ዝምታና እንቅስቃሴ አልባነት» ለውጦታል ሲልም አሞካሽቶታል።

ሳንጆርጂ በፃፈው ሪፖርት መሽኛ ደብዳቤ ላይ ለፓርሌሞ ገዥ ሲፅፍ፤ «የእኔ መ/ቤት ከጥሩ ዳኞች ጋር ይሰራ ዘንድ የእርስዎን የተከበረና ሕጋዊ ጣልቃ ገብነት እሻለሁ። የርስዎ ድጋፍ እጅግ ወሳኝ ነው። ምክንያቱም በሚያሳዝን መልኩ የማፊያ አለቆች የሚሰሩት በሴናተሮች፣ በፓርላማ አባላትና በሌሎች ተፅዕኖ በሚያሳድሩ ሰዎች ከለላ ነው። እነሱ ማፊዎች ይከልላሉ፣ በተራቸው ደግሞ ማፊያዎች ለእነሱ የጥበቃ ከለላ ይሰጣሉ» ሲል በቀጥታ የነበረውን «የፖለቲካ ሙሰኝነት» ገልጿል።

ሳንጆርጂ ወደ ፓሌሪሞ ሲላክ በተጨማሪ ከተሰጠው ዋና ግዳጅ ውስጥ በአካባቢው ዕውቅ በሆነው በዶን ራፋኤሌ ፓሊሶሎ ላይ ልዩ ክትትልና ትኩረት እንዲያደርግም መመሪያ ተሰጥቶት ነበር።

## የኖታርባራቶሎ መገደል

ከሲሲሊ ማህበራዊ ሊህቃን መካከል ማርቆስ ኢማኑኤል ኖታርባራቶሎ የመጀመሪያው ሰለባ ሆነ። በሲሲሊ ዋነኛው ተጠቃሽ ዜጋ ነበር። ለሦስት ዓመታት የፓሌርሞ ማዘጋጃ ሹም ሆኖ በታማኝነት አገልግሏል። በሀገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ሙስናን በመዋጋት የማፊያ ጠላትነቱን አስመስክሯል። እስከ 1890 የሲሲሊ ባንክ ገዥ ሆኖ በቀናነት በማገልገሉ የሕይወት ዋጋ ከፍሏል። በ1893 ኖታርባራቶሎ ተገደለ። ይህም ያልተጠበቀ ሁኔታ የሲሲሊን ማህበረሰብ ለሁለት ከፈለ፣ አልፎ ተርፎም ማፊያ ከፖለቲከኞች፣ ከሕግ ሰዎችና ከፖሊስ ጋር ያለውን ቁርኝት እንዲጋለጥ አደረገ።

ከብዙ ዓመታት በኋላ የኖታርባራቶሎ ልጅና የባህር ኃይል መኮንን ሊዮፖልኮ የአባቱን ግለ-ታሪክ ለንባብ አበቃ። በወቅቱ የ23 ዓመት ወጣት የነበረው ሊዮፖልኮ ከቤተሰቡ ጋር እንዴት እንዳሳለፈና አባቱ እውነተኛ ገዳይ ማን እንደሆነ በፅሁፍ አስፍሯል። አባቱ በጥረቱ ያለማት የመንዶሊላ መንደር መለወጥ የአባቱ ልዩ ጥረት እንደነበር አስነበበ። እውነትም አባቱ በመንደሪቱ ሎሚ፣ የወይራና የወይን ፍራፍሬዎች የተተከሉባት ሀብታም መንደር እንድትሆን ብዙ ጥሯል።

አባቱ ከመሞቱ በፊት ለደህንነቱ ከፍተኛ ሥጋት ነበረበት። በ1882 በወንበዴዎች ታፍኖ ለስድስት ቀናት በአካባቢው ተራራ ዋሻ ውስጥ ታስሮ ከቤተሰቡ ተለይቷል። በኋላም በድርድር ገንዘብ ከተከፈለ በኋላ ነበር የተለቀቀው። የመታፈኑ ሚስጢር ግን «ውሾን ያነሳ ውሾ ይሁን» በሚል ተድበሰበሰ። ይህ ነበር እንግዲህ ኖታርባራቶሎን ሲያሳስበው የኖረው።

ኖታባራቶሎ በ1893 ማለዳ ላይ በፈረስ ላይ ሆኖ ካለማት መንዶሊላ ተነሳ። ሁለት ሰዓት ተጉዞ ፓሌርሞ እንደደረሰ በአንደኛ ደረጃ የባቡር ክፍል ውስጥ ተሳፈረ። ያኔ ነው በነፃነት ተንፈስ ያለው። እስከዚያ ድረስ ግን በተነቃነቀ ቁጥር መሣሪያው ከእጁ ተለይቶ አያውቅም። ፍፁም ጠንቃቃ ነበር። ደግሞም ወንበዴዎች ባቡር አጥቅተዋል ተብሎ አልተሰማም ነበርና ተረጋግቶ ባቡር ክፍል ውስጥ ተቀመጠ።

እስከ ተርሚኒ ኢመርሴ ድረስ ተጓዳኝ ሰው ባቡር ክፍል ውስጥ አልነበረም። በእንቅልፍ እየተንጎላጀጀ ጉዞውን ቀጠለ። ባቡሩ ተርሚኒ ኢመርሴን 12፡23 ሲሆን አስራ ሶስት ደቂቃ ዘግይቶ ጣቢያውን ለቀቀ። ወዲያው ጥቁር ኮትና ቆብ የደፉ ሁለት ሰዎች ወደ ውስጥ ዘለቁ። ባቡሩ በተርሚኒና በትራቢያ መሐል ባለ የተራራ ውስጥ ሽለቆ እንደገባ ወዲያው በሁለቱ ሰዎች ተጠቃ። ከሚያንጎላጅጅበት በድንገት በሃይለኛ ድብደባ የነቃው ኖታርባራቶሎ የሞት ሞቱን ተናነቀ። ምንም እንኳን ኖታርባራቶሎ የ59 ዓመት ጎልማሳ ቢሆንም ግዙፍና የቀድሞ ወታደር የነበረ በመሆኑ ሰንጢያቸውን በእጁ ያዘ። እጁ ተሸረከተ። ከዚያም አጥቂዎቹ ብልቱ ላይ በጩቤ በያዙት ቢላዋ ወጉት። የእውር ድንብሩን

እየታገለ የእጁ የደም ማህተም ባቡሩ መስታወት ላይ ታተመ፡፡ ከዚያም እየተፈራረቀ 27 ቦታ ላይ ጨቀጨቀት፡፡

ባቡሩ ወደ ትራቢያ ጣቢያ እየነጎደ ነው፡፡ ኖታርባራቶሎ በደም አበላ ታጥቦና ትንፋሹ ተቋርጦ ባቡር ክፍል ወለል ላይ ተነጥፏል፡፡ አጥቂዎቹ ሻንጣውን መበርበር ተያያዙ፡፡ የወርቅ ሰዓት፣ የገንዘብ ቦርሳና የጦር መሳሪያ ፈቃዱን ወሰዱ፡፡ ገና አልመሸም፡፡ ባቡሩ በትራቢያ ጣቢያ ለጥቂት ደቂቃ እንደቆመ አፋፍሰው በመስኮት አስከሬኑን ለመወርወር ተዘጋጁ፡፡ ባቡሩ ተነቃንቆ «ኩረሪ ድልድይ» እንደደረሰ ወረወሩት፡፡

ሁለቱ ገዳዮች በሚቀጥለው ጣቢያ በደም የተጨማለቀውን ክፍል ከኋላቸው ትተው ወረዱ፡፡ ጉዳዩን የሚከታተለው የሚላን ፍርድ ቤት ቲኬት ተቆጣጣሪውንና የባቡር ዕቃ ቤት ጠባቂዎቹን ጠርቶ ቢያነጋግራቸውም ከክህደት ውጭ ሌላ መልስ አላገኘም፡፡ ከሳሽ የሟች ልጅ ሊዮፖልክ ግን ባቀረበው ክስ በኢጣልያ ታሪክ ታዋቂ እንዲሆን አስቻለው፡፡ «እንደማምነው ከሆነ አባቴ ላይ የተፈፀመው ግድያ ብቀላ ነው፡፡ አባቴን ፈፅሞ የሚጠላው ሰው ቢኖር የፓርላማ አባል የሆነው ዶን ሩፋኤሌ ፓሊሶሎ ብቻ ነው፡፡ ወንጀሉን እንዲፈፀም ያነሳሳው ወይም ድጋፍ ያደረገው ራፋኤሌ ነው» ሲል ክሱን አቀረበ፡፡

ሊዮፓልዶ ስለ ዶን ራፋኤሌ ሁኔታና ከአባቱ ጋር ስለነበራቸው ጠላትነት በዝርዝር አቀረበ፡፡ በ1882 የአፈና ድርጊት ውስጥ የዶን ራፋኤሌ እጅ እንዳለበት አባቱ ሲጠረጥር እንደነበር ተናገረ፡፡ «ዝርዝር ተጠርጣሪነቱን ለባለስልጣናት ባቀርብም ዶን ራፋኤሌ ለጥያቄ እንኳን ፍ/ቤት አልቀረበም፡፡ ምናልባትም ፈርተውት ይሆናል» ሲል በምሬት ተናገረ፡፡

በኋላ ግን የዶን ራፋኤሌ የፓርላማ የማይነካ መብት ተገፎ ፍ/ቤት እንዲቀርብ ተደረገ፡፡ እሱ ብቻ ሳይሆን የባቡር ጣቢያ ኃላፊ የነበረው ጁሰፔ ፎንታናም እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ከእስር ቤት ወደ ፍ/ቤት የቀረበው ዶን ራፋኤሌ ከስቶና ጠውልጎ፣ አገጩ ረዝሞ፣ ፍፁም ዓይኑን በጨው ታጥቦ ጥፋተኛ አለመሆኑን አስረዳ፡፡ «ብቸኛ ነኝ፣ ደሃ ነኝ፣ ለየትኛውም ፓርቲ የወገንኩ ሰው አይደለሁም፡፡ ሙት ወንድሜ በመጨረሻ ሲሰናበተኝ 'ራስህ ተከላከል፣

የቤተሰብህን ክብር አስጠብቅ' ነበር ያለኝ» ብሎ እንደጨረሰ በአፍንጫው ነስር ተንቦለቦለ፡፡

ፍርድ ቤቱ ከሚላን ወደ ቦሎኛ ዞረ፡፡ ጉዳዩ እየተንዛዛ አሥራ አንድ ወራት ፈጀ፡፡ 50 ቅፅ ማስረጃ ተሰበሰበ፡፡ 503 ምስክሮች ተደመጡ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ሦስት ሚኒስትሮች፣ ሰባት ሴናተሮች፣ አሥራ አንድ የፓርላማ አባላትና አምስት የፖሊስ አዛዦች ይገኙበታል፡፡ ከፍርድ ውሳኔው በፊት አንድ ዳኛ ሲሞት፣ ሁለት ዳኞች ደግሞ በበሽታ ሰበብ እንዲቀየሩ ተደረገ፡፡

ሐምሌ 30 ምሽት የዓመቱ ሞቃታማ ዕለት ነበር፡፡ በፍ/ቤቱ የሚበራው የጋዝ መብራት ክፍሉን ትንፋሽ አሳጣው፡፡ ከፍ/ቤት ውጪ ያለው መንገድ በሕዝብ ተጨናንቋል፡፡ ግማሽ ሻምበል የእግረኛ ጦር ፍ/ቤቱን ከቦታል፣ ሃምሳ ፖሊሶች፣ አርባ አምስት ወታደራዊ ፖሊሶች ሳንጃቸውን ወድረው በንቃት ይጠባበቃሉ፡፡ የኖታርባራቶሉን ጠበቃ ማፊያ ሊገደል ነው የሚለው ወሬ አካባቢውን አጨናንቆታል፡፡

በመጨረሻው ፍርድ ሊሰጥ ነው፡፡ ሁለቱ ተከሳሾች ዶን ራፋኤሌና ፎንታና የሰላሳ ዓመት ፅኑ እስራት ተፈረደባቸው፡፡ ዶን ራፋኤሌ የመጨረሻ ቃል ለመናገር ፍ/ቤቱን ጠየቀ፡፡ ተፈቀደለት፡፡ «ፍ/ቤቱ ተታሏል፡፡ እምልላችኋለሁ፡፡ ከመጀመሪያው ዕለት ጀምሮ እንደተናገርኩት እኔ ንፁህ ሰው ነኝ፡፡ እግዚአብሔር ይበቀልልኛል፣ እርሶን ማለቴ አይደለም የተከበሩ ዳኛ፣ እኔ ንፁህ መሆኔን እያወቁ እንድጠቃ ያደረጉኝ ሰዎችን ነው» ሲል ንግግሩን አጠቃለለ፡፡ ፎንታና ቀበል አድርጎ «በእናቴ መቃብር ይሁንብኝ፣ እኔም ንፁህ ሰው ነኝ!» ካለ በኋላ ሁለቱም በፖሊስ ተይዘው ዘብጥያ ወረዱ፡፡

አካባቢውን የከበበው ሕዝብ «ዳኛው ለዘላለም ይኑሩ! የቦሎኛ ፍርድ ለዘላለም ይኑር!» እያለ በኖታርባራቶሎ ጠበቃና በሊዮፖልዮ ላይ በደስታ ይጮሁ ነበር፡፡ በፓሌርሞ ደግሞ ሁኔታው በተቃራኒው ነበር፡፡ በሚቀጥለው ዕለት በፓሌርሞ ሱቆች ፊት ለፊት «ከተማችን በሃዘን ላይ!» የሚል ታፔላ ተለጥፎ ነበር፡፡ በኋላ ላይ የፖሊስ አዛዥ ሳንጆርጂ እንደተናገረው ይህ መፊክር ማፊያ ያሳተመውና ያሰራጨው ነው ሲል ሪፖርት አቅርቧል፡፡

ከስድስት ወር በኋላ ሁኔታዎች ተቀየሩ። የሮም ሰበር ሰሚ ፍ/ቤት የቦሎኛው ፍ/ቤት ውሳኔ የቴክኒክ ችግር አለበት ሲል የቀድሞውን ውሳኔ ሻረ። ነገሩ ለአንድ አስርት-ዓመት ከተብላላ በኋላ የፍሎሬንስ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት በ1903 እንደገና ተሰየመ።

የቦሎኛው ውሳኔ በ1940 ውድቅ ተደርጎ በአራት የዳኞች ድምፅ ብልጫ የፍሎሬንስ ፍ/ቤት «የቀረበው ማስረጃ ያልተሟላ በመሆኑ ተከሳሾች ነፃ ናቸው!» ብሎ ሲፈርድ ዶን ራፋኤል በድንጋጤ ተዘረረ። ፓሌርሞ ተደሰተች። «የፍሎሬንስ ዳኞች ከተማችንን ከቅሸት ታደጓት» ሲል.... አንድ ጋዜጣም ፃፈ። የዶን ራፋኤል ደጋፊዎች ፎቶውን ይዘው ጨፈሩ። ዶን ራፋኤል (የአካባቢው የማፊያ አለቃ) ወደ ቤቱ ሲገባ የጠበቀው ነገር «ቪቫ ራፋኤሌ!» የሚል አሽብራቂ መፈክር ነበር።

ከሳሽ ሊዮፖልዮ በ1947 የአልጋ ቁራኛ ሆኖ፣ በመሃንነት በፍሎሬንስ ከተማ አረፈ። ባለቤቱ ከሁለት ዓመት በኋላ የፃፈውን የአባቱን ግለ-ታሪክ አሳተመችለት። ሌላው ፍርድ ቤት በነፃ የለቀቀው ማፊያ ጁሶፔ ፎንታና ሲሲሊን ለቀቀ። አራት ትናንሽ ሴት ልጆቹን ይዞ የማፊያ ድርጊቱን ለመቀጠል ወደ ኒውዮርክ ተሰደደ።

# ሶሻሊዝም፣ ፋሽዝምና ማፊያ (1893-1943)

## ካርሊኦኔ ከተማ

ካርሊኦኔ ከፓሌርሞ በወፍ-በረር 35 ኪ.ሜትር ትርቃለች። አደልፎ ሮሲ ከኖታርባራቶሎ መገደል ስምንት ወራት በኋላ (በ1893) እንዲት አነስተኛ ባቡር ይዞ ባገጠጡ ተራሮች በኩል ሲያልፍ አራት ሰዓት ከሩብ ፈጅቶበታል። ባቡሩ የሚያልፍባቸው መንገዶች በሲሊሲ በጋ የተራቆቱ ናቸው። አንፀባራቂ ቋጥኞች፣ የወይራና የሎሚ ጥቁርና አረንጓዴ ፍሬዎች እንደ ከተማ ወታደር በየመስመሩ ተሰልፈው ከወዲያ ወዲህ ይታያሉ።

አደልፎ ሮሲ ሊበራል ለሆነው "La Tribuna" ጋዜጣ ይናገራል። ከአሜሪካ በቅርቡ የተመለሰ ሲሆን በአሜሪካ ያሳለፈው አሥርተ-ዓመታት

ራሱን በኑሮ ለመለወጥ መዋተቱን ይመሰክራሉ። በአሜሪካ ሳለ የil Progresso Italo-Americano የተባለ የኒውዮርክ ጋዜጣ አዘጋጅ ነበር። ወደ አውሮፓ ሲመለስ ስለ አሜሪካ መልካም ስም፣ ግልጽነትና ፈጣን ሕይወትን ሰንቆ የነበረ ሲሆን ከአሜሪካ ጋር ጣልያንን ሲያወዳድር ጣልያን እንደ መቃብር ሥፍራ ዝግና ምንም ለውጥ የሌላት ወና ሆናበታለች።

ሮሲ ከሚኖርበት አፓርታማ ውስጥ አንድ ወጣት የጦር - ሠራዊት መኰንን ይኖራል። በእያንዳንዱ ኢጣልያዊ አንደበት ስለሚነገረው ጉዳይ እያነሱ ማውጋት ጀመሩ - በተለይ ስለ ሲሲሊ ገበሬዎች የመቀመቅ ሕይወት። ሮሲ መኰንኑ የነገረውን ታሪክ እንደሚከተለው ዘግቦታል፡-

«የምታየው ሁኔታ እጅግ ይጐዳል። በአንድ የሐምሌ ሞቃታማ ዕለት ከወታደሮቼ ጋር ጉዞ ላይ ነበርን። ከአንድ የስንዴ ማሳ ስንደርስ እረፍት አደረግን። ከዚያም ውሃ እንዲሰጡኝ ለመጠየቅ ሄድኩ። የእህል ክፍፍሉ ተጠናቆ ስለነበር ከአንድ ዳውላ በላይ ገበሬዎቹ አላገኙም። ሁሉም ነገር ወደ መሬት ከበርቴው ነበር የሄደው። እጁን አገጩ ላይ አድርጎ አካፋውን ተደግፎ የተከዘ ገበሬ ቆሟል። በመጀመሪያ ተናደ በተሰጠው እርቦ ላይ አትኩሮ ተከዘ። ከዚያም ሚስቱንና አራት ወይም አምስት ልጆቹን እየተመለከተ ከዓመት ድካም በኋላ ያንን አነስተኛ እርቦ አገኘ። ታዲያ የጨው አምድ መስሎ ቆሟል፤ ከዚያም ከእያንዳንዱ ዓይኖቹ እንባ በዝግታ ይወርድ ነበር።»

ለዚህም ነው የኮርሊኦን ገበሬዎች በኮርሊኦን «ለሀቅ ያደሩ አለቆችን ፈልጎ ከማግኘት ነጭ ዝንቦችን ማግኘት ይቀላል» ሲሉ የሚናገሩት። ኮርሊኦን የምትኖረው ፓሌርሞን ለመመገብ ነው። 16,000 ነዋሪዎቿ በስንዴ ምርት ላይ የተሠማሩ ገበሬዎች ናቸው። ጠባብ መንገድ፣ ትናንሽ አደባባይና የባሮክ አብያተ-ክርስትያን የመንደሪቱ መለዮዎች ናቸው። አንድ የእንግሊዝ ተጓዥ በ1890ዎቹ ስለ ከተማይቱ ሲፅፍ «አመዳም፣ የገረጡ ሴቶች፣ ዓይናቸው የጐደጐዱ ወንዶች፣ በዳቦ ልመና የተጠመዱ ጭንቁርቁስ ልጆች፣ ድምፃቸው እንደ ፈረስ ድምፅ የጐረነነና ዓለምን የናቁ ሽማግሌዎች የሞሉባት» ሲል ነበር የገለፃት።

ሮሲ ወደታች ከተማ የመጣው መላ ሕይወቱን የእነዚህን ሰዎች ህይወት ለመለወጥ የሚጥረውንና ማፊያን በመታገል የታወቀውን ሰው ኢንተርቪው ለማድረግ ነበር።

የሲሲሊ ገበሬዎች ድህነት ዋነኛ ምክንያት ግልፅ ነው። የኮርሊአን የመሬት ከበርቴዎች ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በፓሌርሞ ከተማ ሲሆን መሬታቸው ለመካከለኛ ከበርቴዎች (Gabelloti) በአጭር የጊዜ ገደብ ኮንትራት ይሰጣሉ። በዚህ አጭር ጊዜ መካከለኛ ከበርቴዎቹ ከገበሬዎች ትርፍ ማጋበስ ስላለባቸው ምህረት የለሾችና ደም መጣጮች ናቸው። በእንደዚህ ዓይነት ሥራ የተሰማሩ ሰዎች ደግሞ ጠላት ማፍራታቸው አይቀሬ ነው። ንብረቶቻቸውንና ከብቶቻቸውን ከዘራፊዎች መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ስለዚህ እነዚህ ኪራይተኞች (Gabelloti) ከዘራፊዎች ጋር ግንኙነት አላቸው ወይም ዘራፊዎችንም ይቆጣጠራሉ። በተጨማሪም ከሌሎች ሕጋዊ የቢዝነስ አካላትም ጋር ግኑኝነታቸውን ያጠናክራሉ።

በሲሊሊ ያልተረጋጋ ኢኮኖሚ ውስጥ እነዚህ ሰዎች (Gabelloti) ከማፊያ ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ስለዚህ ማፊያን መቀላቀል ሥራቸውን ይበልጥ አስተማማኝ እንዲሆን ያደርጋል። «የክብር ማህበረሰብ መሆን በራሱ የማይገዙ ገበሬዎችን በወታደራዊ ጡንቻ ለማንበርከክም ይረዳል።»

አዶልፎ ሮሲ ወደ ኮርሊኦን ከመጓዙ በፊት የተጨቆኑት የምዕራብና ማዕከላዊ ሲሊሊ ገበሬዎች ፋሺ (Fasci) የተሰኘ ድርጅት መመስረት ጀመሩ። (ፋሺ ከአንድ ትውልድ በኋላ በቤኔቶ ሙሶለኒ ከተመሠረተው ወታደራዊ፣ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ፋሽስት ንቅናቄ ጋር ምንም ዓይነት ግኑኝነት የለውም።)

ፋሺኦ (Fascio) - ጥምረትን የሚገልጽ ትርጉም ያለው ሲሆን፣ ገበሬዎች በመሬት ከበርቴዎችና በተከራዮች ላይ ያላቸውን ተቃውሞ የሚያጠናክር የወንድማማችነት ማህበር ነበር።

በ1893 ለገ ቲት ወራት «ፋሺ» ንቅናቄ የሀገሪቱን የትኩረት አቅጣጫ ሳበ። የአካባቢው «ፋሺ» የተመሠረተውና የሚመራው በበርናርዲኖ ቬር ሲሆን በደሴቲቱ ውስጥ ጠንካራ ድርጅት ነበር። ቬሮ የማዘጋጃ ቤት ሠራተኛ የነበረ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን

ሳያጠናቅቅ ከት/ቤቱ ተባረረ። በአካባቢው የተመለከተው በደልና ሕጉ-ወጥ ሁኔታ እንዲወይን አደረገው።

ቬሮ ለገበሬዎቹ በቀበሊኛ ቋንቋና ከሀገሬው ተረት ጋር ንግግሮችን እያዋዛ ለትግል አነሳሳቸው። ንግግሮቹ ተምኔታዊ መሠረት ላይ የተመሠረቱ መተጋገዝ፣ ወንድማማችነት፣ ዲስፒሊንና የሴቶችን መብት ያካተተ ስለነበር ገበሬዎች ወደ ማህበሩ ተሰባሰቡ። «የወደፊቱ ዓለም የሶሻሊዝም ነው» እያለ በሰፊው ሰበከ። በበቅሎ ከመንደር መንደር እየተጓዘ መልዕክቱን ለገበሬዎች አሠራጨ። እሱ በተዘዋወረበት ሁሉ «ፋሺ» ተቋቋመ። ቬሮና ደቀመዛሙርቶቹ እጅግ በንዳዊነት የሚታዩ ሲሆኑ በተገናኙ ቁጥር የፍቅር መግለጫቸው አፍ ለአፍ እስከ መሳሳም ደርሶ ነበር።

ጋዜጠኛ ሮሲ ይህን በመስማቱ ነበር ቬሮን ለኢንተርቪው የፈለገው። ቬሮ በኢንተርቪው ሲገልጽ «የእኛ ድርጅት ስድስት ሺህ ወንድና ሴት አባላት አለው.... ሴቶቻችን የድርጅቱ ጥቅም ስለገባቸው ዛሬ ልጆቻቸውን ሶሻሊዝም ያስተምራሉ» ሲል ገለፀ። ሮሲ አባል ገበሬዎችን እየተዘዋወረ ኢንተርቪው አደረገ። ሶሻሊዝም ስትሉ ምን ለማለት ነው? ብሎ ለጠየቃቸው ጥያቄ «አብዮት!» ሲል አንደኛው መለሰ፣ ሌላው ደግሞ «ንብረቶቻችንን አንድ ላይ አድርገን በአንድነት መገልገል» ይላል። ሦስተኛው ደግሞ «50 ዓመቴ ነው ግን በሕይወቴ ሥጋ ተመግቤ አላውቅም!» አለው ለጋዜጠኛው። ጋዜጠኛው ሮሲ በገበሬዎቹ መልስ ይበልጥ ልቡ ተነካ።

አንድ ዕለት በቬሮ ቤት መስኮት ላይ ድንጋይ ተወረወረ። ቬሮ ልብሱን ቶሎ ለብሶ እውር ድንበሩን ከቤቱ ሲወጣ ከኪራይ ሰብሳቢውና (Gabelloti) ከተማውን ካስከበበው ሰው ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጨ። ከዚያም ቬሮን ወደ አንድ ቤት እንዲያመራ ካስገደዱት በኋላ የተሰበሰቡ ሰዎች መሐል ጣሉት።

በተሰብሳቢዎቹ ሰዎች መካከል አንድ ጠመንጃና የሰው ጭንቅላት አፅም የተሳለበት ወረቀት ተቀምጧል። ከዚያም አለቃቸው ብድግ ብሎ ቬሮ የምስጢራዊው ድርጅታችን አባል እንዲሆን እንፈልጋለን ሲል

ተደመጠ። ይህ የምስጢር ድርጅት «ወንድማማቾች» (Fratuzzi) የተሰኘው ነበር። ቬር «የወንድማማቾችን» መሃላ እንዲያሰማ ተደረገ። የታማኝነት ማረጋገጫ ሥርዓት ለማድረግ ሲል የቀኝ እጁን ይዘው ከአውራ ጣቱ ላይ በስፒል በጡት። ደሙ በስዕሉ አፅም ላይ እንዲረጭ ተደረገ። ከዚያም ተቃጠለ። በቃጠሎው መሃል የጎዳዊነት መግለጫ እንዲሆን ከማፊያዎቹ ጋር ተሳሳመ። ከዚህ በኋላ የCorlione ቡድን ማፊያ አባል ሆነ። ሶሻሊስታዊ ጀግናው ከማፊያ ጋር በእጅና ጓንትነት ለመቀጠል ወሰነ። እንደ ቬሮ ያሉ የፋሺ መሪዎችን በመያዝ ማፊያ ተጽዕኖ ማድረግ እንዳሰበት ያውቃል።

ማፊያ ዘላቂ የሆነ የፖለቲካ ርዕዮተዓለም የለውም። የሚሠራበት የፖለቲካ አስተሳሰብ ሳይሆን በስልት ብቻ ነው ለጊዜያዊ ጥቅም የሚንቀሳቀሰው። አድርባይነት ዋነኛ እሴቱ በመሆኑ ማህበራዊም ሆኑ ፖለቲካዊ ንቅናቄዎች ለማፊያ ተፅዕኖ ይጋለጣሉ።

በአንድ የሚያዚያ ዕለት ቬሮና የፋሺ ከፍተኛ የድርጅት ኃላፊዎች ከፓሌርሞ የማፊያ ሃላፊዎች ጋር ተገናኙ። ሆኖም በቀረበው ዓላማ ላይ ሊግባቡ ባይችሉም በኋላ ላይ ማፊያን መቀላቀሉ ቬሮ ህይወቱን እንዲያጣ አድርጐታል። የፋሺ ንቅናቄ ለመንግሥት ከፍተኛ ሥጋት በመሆኑ ንቅናቄውን ለመምታት መንግሥት ጦር አዘመተ። ከገበሬዎች ተቃውሞዎች በየቦታው ቢቀጣጠልም የመንግሥትን ኃይል ሊቋቋሙ አልቻሉም። 83 የሚሆኑ ገበሬዎች ተገደሉ። ቤርናርዲኖ ቬሮም ወደ ቱኒስ ለማምለጥ ሲል ተይዞ ወታደራዊ ፍ/ቤት ቀረበ። የቀረበበት ክስም በመንግሥት ላይ ተቃውሞ፣ ሲቪል ጦርነትና ብጥብጥ በማድረስ ተከሶ በጥፋተኛነት 12 ዓመት ተፈረደበት። ሆኖም በ1807 ከእሥር ቤት ተለቀቀ።

የኢጣልያ መንግሥት ገበሬዎችን በሚመለከት አዲስ አሠራር መከተል ጀመረ። በመሀል ያሉ ተከራዮችን ለማስቀረት ገበሬዎች ተደራጅተው ብድር መውሰድ እንዲችሉና መሬት እንዲከራዩ ሆነ።

የተመሠረቱት የሕብረት ሥራ ማህበራት እንዲኮላሹ ማፊያዎች ጥረታቸውን ቀጠሉ። ቬሮ ግን በሕብረት ሥራ ማህበራቱ ውስጥ ማፊያ

ጣልቃ እንዳይገባ ለማድረግ ሞከረ። ሆኖም መንገዱ አልጋ በአልጋ አልነበረም። ከካቶሊክ ፈንድ ሳይቀር አደጋ ገጠመው። ማፊያ፣ ቄሶችና ፖለቲከኞች እንደሚሞዳሞዱ የታወቀ ነው። ማፊያና ቤተ ክርስቲያን ተመሳሳይ ጥላቻ በሶሻሊዝም ላይ አላቸው። በ1910 ቬሮ በካቶሊኩ ከንቲባ ላይ ፀረ-ታክስ ተቃውሞን ከፈተ። ይህ ደግሞ ከማፊያ ጋር ቀጥተኛ ትግል መጀመሩን የሚያሳይ ምዕራፍ ነው። በአንድ የምርጫ ቅስቀሳ ላይ «ማፍያ ካቶሊኮች ውስጥ ሰርጎ መግባቱን» አጋለጠ። ታዲያ የገጠመው ሁኔታ ፈጣን ነበር። ድምፅ ለመስጠት በአንድ መድሃኒት ቤት በራፍ ላይ እንደቆመ በሁለት ጥይት ተተኩሶ ባርኔጣው ከላዩ ላይ ተበተነ። በተአምር ተረፈ። ማን እንደተኮሰበት በፍጥነት ሮጦ ሲመለከት ከሚያውቀው የማፊያ ሰው ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጩ። ቬሮም «እየህ የናንተ ልጆች ጭስ ማጨስ ብቻ ነው የቻሉት!» ሲል በለበጣ ተናገረው።

በአደባባይ ሲታይ ቬሮ አለመደንገጡን ቢያሳይም በግል ግን ተርበድብዷል። ማፊያ ከቀሳውስቱ፣ ከሕግ ሰዎችና ከፖለቲከኞች ጋር ያለውን ቁርኝት በትክክል ተረድቷል። ሊገድለው የነበረውን ተጠርጣሪ ቢከስም ማንም ሊመሰክርለት አልቻለም። ወዲያው ደግሞ የቅርብ ጓደኛውና የገበሬዎች ንቅንቄ መሪ የነበረው ሎሬንሶ ፓንፒንቶ በሩ ላይ በጥይት ተደብድቦ መሞቱን ሰማ። ስለዚህ «ኮርሊኦንን ቶሎ መልቀቅ አለብኝ፣ ማፊያ እንደሆነ ከዳተኛ አድርጎኛል። አሁን ምን ማድረግ አለብኝ? ወንጀለኛ ሆኜ ዲናሚት ይዤ ማፊያን መበቀል ወይስ ለማፊያ አንገቴን መስጠት?» ሲል ነበር ራሱን የጠየቀው።

የተለያዩ ፈተናዎች ቬሮን መፈታተን ጀመሩ። የገበሬዎች ሕብረት ሥራ ማህበር ንብረት እንዲታገድ ሆነ። እሱም ሁለት ዓመት በማስጠንቀቂያ ታሰረ፣ በ1913 ከእስር ሲፈታ የማጭበርበር ወንጀል ጥያቄ ከላዩ ላይ አልወረደም ነበር። ሆኖም በአካባቢው ገበሬዎች ጥያቄ ለምርጫ ቀረበ። ምንም እንኳን ማፊያ ድራሹን እንደሚያጠፋው ቢያውቅም ሌላ ምርጫ አልነበረውም። በመጨረሻም በ1914 የኮርሊኦኔ ከንቲባ ሆኖ ተመረጠ። የግል ሕይወቱም ተለወጠ። አንዲት ሴት ልጅ እንዳፈራ ስሟንም ጁሰፒና ሰብአዊ ሰላም "Giuseppina Pace Umana (Josphine Human Peace)» ሲል ሰየማት።

ህዳር 5፣ 1915 ደንገዝገዝ ሲል ኮርሊኦንን ለቀቀ፡፡ የትሪቡናን መንገድ አለፍ እንዳለ የተተኮሰ ጥይት ከክንዱ ሥር መታው፡፡ እንደምንም ብሎ ቡኒ ሽጉጡን አውጥቶ የአፀፋ ተኩስ ተኮሰ፡፡ ከሁለት አቅጣጫ በአምስት ጥይት ተደብድቦ ጭቃ ውስጥ ዘፍ አለ፡፡ ከዚያም ገዳዩ ወደ ተዘረረው ቤር ተጠግቶ ጭንቅላቱ ላይ አራት ጥይቶችን አርከፈከፈበት፡፡ አበቃ፡፡ ይህ ለሌሎች ማስጠንቀቂያ ነበር፡፡

በ1917 የኮርሊኦን ገበሬዎች የወገብ በላይ ሀውልት አቆሙለት፡፡ በ1925 ሐውልቱ በኦፊሴል ተመረቀ፣ ከዚያ ወዲያ ግን ሃውልቱ ተነቅሎ በመወሰዱ አልተገኘም፡፡ በ1992 (ከ67 ዓመት በኋላ) የፓሌርሞ ግራ ክንፍ ከንቲባ አዲስ ሀውልት አሰርቶ አቆመለት፡፡ በ1994 ግን ሀውልቱ ወደመ፡፡ ይህ የሚያሳየው ማፊያ ከመቃብር በኋላም ቢሆን ደመኞቹን እንደማይለቅ ነው፡፡

## ደረተ-ፀጉራሙ ሰውዬ

ጥር፣ 1925 ጠቅላይ ሚኒስትር ቤኔቶ መሶሎኒ ፓርላማ ቀርቦ ሁሉን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለመጨቆን የግል ሀላፊነት እንደተጣለበት ተናገረ፡፡ ከዚህ በኋላ የፋሽስት ፓርቲው በኢጣልያ ላይ መንግስት ሳይሆን ገዢ ሆኖ ተሰየመ፡፡ ከዓመት በኋላ በተደራጁ የሲሊሊ የወንጀል ቡድኖች ላይ እርምጃ እንደሚወስድ አስታወቀ፡፡

የጃንጂ አካባቢ የሆነው የማዶኒ ተራራ በጦር ተከበበ፡፡ ወታደራዊ ፖሊሶች ከወንበዴዎች ጋር የሚተባበሩትን ሁሉ አፈሱ፡፡ ወደ ጃንጂ የሚወስዱ መንገዶች ተዘጉ፡፡ ቴሌፎንና ቴሌግራፍ ተቋረጠ፡፡

የመጀመሪያው ወንበዴ ከተደበቀበት እጁን ሰጠ፡፡ «የማዶኒው ንጉስ» የተባለው ይህ ወንበዴ ጂታኖ ፌራሬሎ ነበር፡፡ ሚስቱንና ውሽማዋን ገድሎ ከተደበቀ አመታት አልፎታል፡፡ ይህ የ65 ዓመቱ ወንበዴ ኋላ ላይ እንደታወቀው እጁን የሰጠው ለፖሊስ ሳይሆን ለከተማው ከንቲባ ነበር፡፡ ከተወሰኑ ቀናት በኋላ የከተማው ሞረሽ ታዞ የሚከተለውን አበሰረ፡-

«የጃንጂ ነዋሪዎች ሆይ! የተከበሩ ሲዛሬ ሞሬ፣ የፓሌርሞው ፖሊስ ዋና አዛዥ የሚከተለውን ቴሌግራም ለከንቲባችን ለሕዝቡ

እንዲገለፅ አስተላልፈዋል፡፡ እንዲህ ይላል «በየስፍራው የተደበቁ ወንጀለኞች ሁሉ እጃችሁን በ12 ሰዓት ውስጥ ለአተማው ሀላፊዎች ስጡ! የተቀመጠው ጊዜ ካለፈ በኋላ ግን በቤተሰቦቻቸው፣ በንብረቶቻቸውና በሚደብቃቸው ላይ አይቀጡ ቅጣት ይወሰድባቸዋል!»

ሲዛሬ ሞሪ በተደራጁ ወንጀለኞች ላይ ርምጃ እንዲወስድ የተመረጠ ሰው ነው፡፡ በቅጽል ስሙ «ጠንካራው አዛዥ» ወይም «ደረተ-ጸጉራሙ ሰውዬ» ተብሎ የሚጠራ ሲሆን የተግባር ሰው የሆነና የወንጀለኞች ዋና ጠላት ነው፡፡

ሞሪም ሆኑ ሙሶሎኒ በማፊያዎች ላይ ጠንካራ እጃቸውን አሳርፈዋል፡፡ ብዙዎች ወደ ደሴት ላይ እስር ቤቶች ሲወሰዱ የእስር ርምጃው በፋሺስቶች እየተወሰነ ካለምንም ፍርድ የሚፈፀም ነበር፡፡ በወቅቱ ማፊያ መብቀል የማይችል ችግኝ ሆኖ ጠውልጓል፡፡

እንደሚታወቀው የፋሽስት ንቅናቄ የተመሰረተው መስከረም 1919 በሚላን ከተማ ሲሆን በጋዜጠኛውና በቀድሞው ተዋጊ ወታደር በቤኒቶ ሙሶሎኒ ነበር፡፡ ዓላማው «የቀበሮ ጉድጓድ አገዛዝ» በማምጣት አርበኝነታዊ ዲስፒሊንን በቀጨጨው የኢጣልያ ዲሞክራሲ ላይ ለመትከል ቆርጦ ተነሳ፡፡ ስለዚህም የመሬት ከበርቴዎችንና የፋብሪካ ባለቤቶችን ቀልብም ሳበ፡፡ በ1922 ሙሶሎኒ ወደ ሮም ባደረገው የተቃውሞ ጉዞ መንግስቱን የማይወጣው ተግዳሮት ውስጥ ከተተው፡፡ ከዚያም ጥምር መንግስት በማቋቋም ለቀጣይ ሁለት አስርት ዓመታት ሀገሪቱን ሙሶሎኒ ገዛት፡፡ ምንም እንኳን የፋሽስት ንቅናቄ የታችኛውን ክፍል የያዘ ባይሆንም የሲሲሊ ፖለቲካ በመሞዳሞድና በእከክልኝ ልከክልህ የሚራመድ በመሆኑ «ፋሽስታዊነት» ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ዱቼም በሲሲሊ ታዋቂ ሆነ፡፡ ሆኖም ይህ ወዳጅነት አልዘለቀም፤ ፋሽስቶች በማፊያ ላይ የመንጥር ዘመቻን ሚያዝያ 1923 ላይ ማካሄድ ጀመሩ፡፡

በ1924 ሙሶሎኒ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሲሲሊ በመርከብና በአይሮፕላን ታጅቦ አመራ፡፡ ትራፓኒ ክፍለ ሀገር ሲደርስ ዱቼ ስለ ሲዛሬ ሞሬ (ደረተ ፀጉራሙ ሰውዬ) እና ስለ ማፊያ አስቸጋሪነት ሰማ፡፡ ፋሽዝም እንዳይጠናከር ዋነኛው እንቅፋት ማፊያ እንደሆነም ዱቼ ተረዳ፡፡

ሙሶሎኒ ፓርሌሞ አጠገብ ባለች «ፒያና ዴይ ጊርቺ» እንደደረሰ የከተማዋ ከንቲባ የሆነውና የማፊያ አለቃ የነበረው ዶን ፍራቼስኮ ኩቺያ ጠባቂዎቹን አልፎ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ (ዱቼ) በጆሮው ጠጋ በማለት «ከእኔ ጋር ነዎት፣ በእኔ ከለላ ስር ነዎት። ለምን ይህን ሁሉ ፖሊስ ይዘው መጡ?» ሲል አንሾካሾከ። ዱቼ ምንም መልስ ሳይሰጥ በንዴት ሲጦፍ ዋለ። የዚህች ሁኔታ መከሰት ዱቼ ጦሩን ይበልጥ በማፊያ ላይ እንዲሰብቅ አደረገው። በዚህም «ደረተ ፀጉራሙ» ሞሪ የፓሌርሞ ፖሊስ አዛዥ ሆኖ በ1925 ማፊያን ለመመንጠር ተሾመ። ባደረገው ንግግር «ስሜ ሞሪ ነው። ሰዎች እንዲሞቱ አደርጋለሁ! (በጣልያንኛ ሞሪ ማለት ሞት ነው) ልክ ይህ አባሯ በንፋስ እንደሚወሰድ ሁሉ ወንጀለኞችን ከየመንደሮቹ አጠፋለሁ። 120 ወታደሮቹን ወደ መንደሮቹ በማሰማራት ከ150 በላይ ተጠርጣሪዎች ተያዙ። የማፊያ አለቃ የነበረው ቬቶም ተይዞ እስር ቤት በ1942 ሞተ።

ሞሪ ማፊያን በማስጨነቁ 500 የሚሆኑ ማፊያዎች ወደ አሜሪካ ተሰደዱ። ይህ ማለት ግን እንደነ ጁሰፔ ጀንኮ ሩሶ ያሉ የማፊያ አለቆች ከሞሪ አሰሳ አልተረፉም ማለት አይደለም።

በሰኔ፣ 1929 ቼዛሬ ሞሪ ከዱቼ ሙሶሎኒ ሥራው መጠናቀቁን የሚገልፅ አጭር ቴሌግራም ደረሰው። ምንም እንኳን አሞካሽ ንግግሮች ተደርገው ሞሪ የተሰናበተ ቢሆንም በስንብቱ ደስተኛ አልነበረም። የሞሪ ኦፊሴላዊ መስመር እስከነ አካቴው ተዘጋ። ፋሽዝም ማፊያን በሚቻለው ሁሉ መታ። ዳሩ ግን ማፊያን አልደመሰሰም። የሞሪ ጥረት የመጨረሻ ግቡን ሳይመታ በ1942 አረፈ። የማፊያ የመኖር ነፃነት ከወደ አሜሪካ ደግሞ ማቆጥቆጡን ጀመረ። ማፊያ ከሶሻሊዝም፣ ከፋሽዝምና በሲሊሲ በተቀሰቀሰበት ጦርነት አምልጦ የአሜሪካ የሕይወት አካል መሆኑን ቀጠለ።

# 8

# የማፊያ እግር መትከል በአሜሪካ (1900-1941)

## የጆ ፔትሮሲኖ ሩጫና ፍፃሜ

በ1901 እና በ1913 መካከል 1.1 ሚሊዮን የሚሆኑ ሲሲሊያውያን ወደ ውጭ አገር ተሰደዱ፡፡ ከአጠቃለይ የሲሲሊ የሕዝብ ብዛት አንድ አራተኛ መሆናቸው ነው። ከነዚህ ውስጥ 800,000 ሲሲላውያን አሜሪካንን ማረፊያቸው አደረጉ። ብዙዎቹ «የክብር ሰዎች» እና ጃዊሳ ወንጀለኞች በመሆናቸው ከለላ የምትሆናቸው ሀገር ሲፈልጉ ቆይተዋል፡፡

19ኛው ክፍለ ዘመን ከሲሲሊ እየጠፉ አሜሪካንን ቤታቸው አደረጉ፡፡ በተለይ በማፊያ የሚካሄደው የሎሚ ንግድ ፓሌርሞን ከኒውዮርክ ጋር አቆራኛት፡፡ በወቅቱ በጣሊያን ማህበረሰብ ውስጥ የተሰገሰጉ አደገኛ ወንጀለኞችን የአሜሪካ ፖሊሶች የአያያዙት በቀጥታ ከማፊያ ጋር ነበረ፡፡ የኒው ኦርሊየንስ የፖሊስ አዛዥ የነበረው ዴቪድ ሄንስ ጉዳይ ለዚህ ተጠቃሽ ነው፡፡

ስለ ማፊያ ወደ አሜሪካ መሻገር ሁለት መላምቶች ይሰነዝራሉ። የመጀመሪያው የተፈጠረው በሲሲሊያውያን የገፍ ስደት ወቅት ነው። በ1903 የማፊያ ግድያ ታሪክ በኋላ New York Herald ጋዜጣ ሲያሳስብ «ቦት ጫማ (ኢጣሊያ ማለቱ ነው) በአሜሪካ ላይ ወንጀለኞቿን እያራገፈች ነው፡፡ የስታትስቲክስ መረጃዎች እንደሚያረጋግጡት የደቡብ አውሮፓ አርባናቢሶች በሀገራችን በር ላይ እየተወረወሩ ነው» ሲል ነበር የተቸው፡፡ ለኒውዮርክ ነዋሪዎች የማፊያ ነገር እንደ ቀጥተኛ ወረራ ነበር የተቆጠረው፡፡

ሁለተኛው መላምት ደግሞ በቅርቡ የቀረበውና በ1960ዎቹና 70ዎቹ በአሜሪካ ውስጥ ነዋሪ ሆነው ስለተዋሃዱት ሲሲላውያን የቀረበ ነው። አትላንቲክን ያቋረጡት እኒህ የሲሲሊ ገበሬዎች ጥንታዊውን ወገኛ ባህላዊ አቀራረብ የተከተሉ ነበሩ። ታዲያ በቀጥታ የተጋፈጡት ከትልቅ የከተማ ካፒታሊዝምና ከፋብሪካ ፖለቲካ ጋር ነበር። የገጠር ባህላዊ አኗኗራቸውንም አልዘነጉትም። ማፊያም የተፈጠረው ጥንታዊው የሲሲሊውያን ቤተሰባዊና የክብር እሴት ከአሜሪካው ሕልም ጋር ሲጋጭባቸው ነው የሚል ታሪክ ይቀርባል። ዳሩ ግን ከተሜዋ አሜሪካና ሲሲሊ እንዲህ በሰፊው ፊጽሞ የሚራራቁ አልነበሩም። ለምሳሌ የሲሲሊዋ Corleone ከተማ ኋላቀር የመንደር ከተማ አልነበረችም፣ የእርሻ ኢንዱስትሪና የገበያ ኢኮኖሚ፣ የመሞዳሞድ ፖለቲካና የተደራጀ ሕገ-ወጥነት የተስፋፋበት ከተማ ሆና ትታወቃለች። ስለዚህ አዶልፎ ሮሲ እንደፃፈላት ምግባረ-ሰናይነት አይታይባትም። ሆኖም ወደ አሜሪካ የተሰደዱት ሲሲሊያውያን ገንዘብ አጠራቅመውና ግንኙነት ፈጥረው ወደ ሲሲሊ መመለስ ነበር ዓላማቸው።

በመጀመሪያ አትላንቲክን አቋርጠው አሜሪካ እንደተሳፈሩ የተሠማሩት በግንባታ ሥራ ላይ ነበር። ይህንኑ የግንባታ ሥራም ለማግኘት ቢሆን በካቦ ሥርዓት (Patrone System) መተሳሰር ያስፈልጋል። «ካቦው» ነው ሰደተኞችን ሥራ የሚያስይዘው። በኢጣሊያ ማህበረሰብ (በአሜሪካ) ሥልጣን ኢንቬስት የሚደረገው በተቋም ላይ ሳይሆን በጠንካራና በተያያዙ ግለሰቦች ዙሪያ ነው። ለዚህ ነው በአሜሪካም ሙስናና ሕገ-ወጥነት ተጣምረው የሚታዩት።

የኤልሳቤጥ ጐዳና የሲሲሊ ማህበረሰብ የሚኖርበት የኒውዮርክ ማዕከል ነው። በ1905 ብቻ 8,200 ኢጣሊያኖች፣ አብዛኛዎቹ ሲሲሊያውያን ነበሩ በElisabetta (በኤልሳቤጥ ጐዳና) የሚኖሩት። ሲኒማ፣ የጣፋጭ ሱቆችና ምግባ-ምግቦችን መደዳውን ከፍተው ሲነግዱ ለተመለከተ ሁኔታው የጣሊያንን ኑሮ ያስታውሳል። አሜሪካኖች ይህንን ሁኔታ በጥንቃቄና በሀዘኔታ ይመለከቱታል። ሆኖም ግን የጣሊያኖች ተስፋ በኒውዮርክ የለመለመ ነበር። በተለይ «ትንሿ ኢጣሊያ» በኒውዮርክ ከተመሠረተች በኋላ ብዙዎቹ ስደተኛ ጣሊያናውያን በንብረት ገበያው

ውስጥ ኢንቬስት ማድረግ ጀመሩ። ከጣሊያን በስደት የሚጉርፉት ሴቶች በይበልጥ በትምህርት ላይ ትኩረት አደረጉ። ጣሊያኖቹ ይህን የጉር አጋጣሚ ራሳቸውን ለማሻሻል ተጠቀሙ። ማፊያ በአሜሪካ ውስጥ ራሱን ሲያቋቁም ሰዎች እንደሚያስቡት በፍጥነት አልነበረም። የመጀመሪያው ፈጣኑ ሂደት ተብሎ የሚታወቀው በተወሰነ የንግድ ሥራ በተለይም ዕፅ ንግድ ላይ ያተኮረ ነበር። የማፊያ የክብር ሰዎች የሆኑት ሁሉም ነጋዴዎች አልነበሩም፤ ብዙዎቹ «የድብቁ መንግሥት» አስተዳዳሪዎች እንጂ። ከዚህ ቀደም በሲሲሊ የነበረውን የእክክልኝ ልክክልህ ፖለቲካ ማራመድ እንዲሁ ቀላል አልነበረም። የሁለት የጣልያን-አሜሪካውያን ሰዎች የጆ ፔትሮሲኖና የጁሴፔ ፒዱ ሞሬሎ ታሪክ ማፊያንም ወደ አሜሪካ መዘዋወሩን ማየት ያስችላል።

አንዲት መካከለኛ ዕድሜ ላይ ያለች ፍራንሴስኮ ካኖርስ የተባለች ወይዘሮ በምሥራቅ 11ኛው ጎዳና ስትጓዝ ያልተጠበቀ አስደንጋጭ ነገር አጋጠማት። አንድ በሚገባ የለበሰና በቅርቡ ጠጉሮ በልቶ እንደነበረ የሚያመለክት ሰው በአንድ በርሜል ውስጥ ተጥሎ ተገኘ። የሴትየዋ ጩኸት ሁለት በአካባቢው ሲዘዋወሩ የነበሩ ፖሊሶችን ቀልብ ሳበ። በሥፍራው ሲደርሱ ሬሳው ገና ትኩስ ነበር።

የፖሊስ ምርመራ ውጤት እንዳረጋገጠው ሰውየው አንገቱ ላይ 18 ቦታ ተወግቷል። የተገኘው አስክሬን ሲታይ ሰውዬው በደንብ የለበሰ ሲሆን ከተጣለበት በርሜል ውስጥ ሲወጣ የጣሊያን ስፓጌቲና የአትክልት ትርፍራፊዎች ተገኝተውበታል።

በወቅቱ የኒውዮርክ ጋዜጦች «የበርሜሉ አስክሬን» በሚል ርዕስ የፃፉት ርዕስ በአሜሪካ ላይ አደገኛ ወንጀለኞች «ከቦት ጫማዋ» አገር ወረራ እንደተፈጸመ አድርገው አሰፈሩ። ይህ የመጀመሪያው ፍንጭ ነበር የሲሲሊ ስደተኞች ባረፉበት አካባቢ ማፊያ እንደነበር የጠቆሙበት። ይህ ብቻ አይደለም ከስድስት ዓመት በኋላ ጣሊያን - አሜሪካዊው ጆ ፔትሮሲኖ በፓሌርሞ መገደሉንና በማፊያ ታሪክ የተፈፀመ ታላቁ ወንጀል የታየበትን ታሪክ አሰፈረ።

«የበርሜሉ አስክሬን» ከተገኘ ከአንድ ቀን በኋላ ፖሊስ ዘጠኝ የሚሆኑ የማፊያ ቡድን አባላትን አሰረ። እነዚህ በፖሊስ ጥብቅ ክትትል

ሥር የነበሩ የማፊያ ተመራማሪዎች የሀሰት የአሜሪካ ዶላር በዘይት ቆርቆሮ ደብቀው ሲያስገቡ እንደከረሙ ተደርሶበታል፡፡ ገንዘቡ ኒውዮርክ እንደደረሰ ወደተለያዩ ምሥራቃዊ ዴርቻዎች በማፊያ የትስስር መንገድ ይሰራጭ ነበር፡፡ የተገደለው ያ «የበርሜሉ አስከሬን» ቀደም ሲል ወደ አንድ ሳሎን መግባቱ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ሳሎን ደግሞ የ34 ዓመቱ ጆሴፔ ፒዱ ሞሬሎ ንብረት ሲሆን፣ ይህ ሰው የማፊያ ቡድን መሪ እንደሆነ ታውቋል፡፡

ሞሬሎ ሲያዝ ታጥቆ የነበረና ከሞተው ሰውዬ ጋር የሚመሳሰል ሲጋራ ይዞ ነው የተገኘው፡፡ ፖሊሶቹ ሲጠይቁት መልስ ለመስጠትም ፈቃደኛ አልነበረም፡፡

«የበርሜሉ አስከሬን» ታሪክ ለማግኘት ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረገው ሃምሳ አለቃ ፔትሮሲኖ ሲሆን፣ በአቋሙ አጭርና ደልደል ያለ ተክለ-ሰውነት፣ የተበጣጣ ፊትና ቅርጽ አልባ አፍንጫ ነበረው፡፡ በ1860 ነው ሳሌርኖ ከተማ አጠገብ የተወለደው፡፡ በወጣትነቱ ወደ አሜሪካ ተሰደደ፡፡ በመጀመሪያ በኒውዮርክ ከተማ የሕዝብ ት/ቤት ተምሮ የመንገድ ጽዳት ሠራተኛ ሆነ፡፡ ትንሽ እንደቆየ በአንድ የፖሊስ መኮንን እርዳታ ወደ መለዮ ለባሽነት ተቀየረ፡፡

በኒውዮርክ የፖሊስ መምሪያ ቀስ በቀስ ዕድገት ሲያገኝ በዚያው አንፃር የጣሊያን ስደተኞችና ወንጀለኞች በቁጥር እየጨመሩ ሄዱ፡፡ በፔትርሰን፣ በኒውጀርሲ ያሉ የኢጣልያ አናርኪስቶች ፕሬዚደንት ዊልያም ማክንሌይን ሊገድሉ ማሴራቸውን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ተበተነ፡፡ በ1901 ማክንሌይ የፓን-አሜሪካን ኤግዚቢሽን ለመክፈት ቡፋሎ ከተማ እንደተገኙ ግን ተገደሉ፡፡

አስከሬኑ በርሜል ውስጥ ተጥሎ ከተገኘ ከጥቂት ቀናት በኋላ ፔትሮሲኖ 50 ኪሎ ሜትር ከሐድሰን ወንዝ በላይ ደርሶ ሲንግ-ሲንግ እስር ቤት አጠገብ ደረሰ፡፡ በትንሿ ኢጣሊያ የሚገኙ ጠቋሚዎቹ ጁሰፔ ፕሪሞ የተባለና በእሥር ላይ የሚገኝ ሰው ሟቹን ሊለይ እንደሚችል ነገሩት፡፡ ፕሪሞ የሟች ፎቶ ሲቀርብለት ዋርሳው በንዴቶ ማዶኒያ መሆኑን ወዲያውኑ አረጋገጠ፡፡ ማዶኒያ የሀሰት ዶላር አዟዟሪ የማፊያ

አባል ሲሆን የዲ ፕሪሞን ንብረት ማካካሻ ከሞሬሎ ለመውሰድ ነበር የሄደው፡፡ ዳሩ ግን ሳይመለስ በዚያው ቀረ፡፡

ፔትሮሲኖ እንደተመለሰ ከታሰሩት የማፊያ ተጠርጣሪዎች ውስጥ አንገተ - ወይፈኑን ቶማሶ ፔቶ በቅጽል ስሙ «በሬው» ተብሎ የሚታወቀው ላይ ትኩረት አደረገ፡፡ «በሬው» በርሜል ውስጥ የተጣለውን ሰው ስለመግደሉ ከፍተኛ ጥርጣሬ ተደረገበት፡፡ በ1903 ፍርድ ቤት በዚህ ጉዳይ ላይ ተሰይሞ ተጠርጣሪዎችም ቀረቡ፡፡ የሟች ልጅ ተጠርቶ «ከበሬው» እጅ የተገኘውን ሰዓት እንዲያረጋግጥ በፍ/ቤቱ ተጠየቀ፡፡ አንድ መርማሪ ቀጥሎ የሆነውን እንዲህ ሲል ያስታውሰዋል፡- «ልጁ ሰዓቱን አትኩሮ ከተመለከተ በኋላ ሊናገር ሲል የኮቴ ድምድምታና ማጉረምረም ፍ/ቤቱ ውስጥ ሲሰማ ልጁ ዝምታን መረጠ፡፡ ከተሰብሳቢዎቹ አንዱ ዘሎ አፉን እንዳይናገር ያዘው፡፡ ልጁ ከዚህ በኋላ የአባቱ ሰዓት ስለመሆኑ እርግጠኛ አልሆነም፡፡»

ዲ ፕሪሞ ከእስር ቤት ወጥቶ እንዲመሰክር ተጠራ፡፡ በእሱና «በበሬው» መካከል የደም ቁርሾ ነበረ፡፡ ዳሩ ግን ፕሪሞ መልካም ጓደኛው እንደነበር አረጋገጠ፡፡ ሆኖም በእሥር ቤት መቆየቱን መርጦ ሳያጋልጠው ዝምታን (ኦሜርታን) መረጠ፡፡

???

ፔትሮሲኖና የፖሊስ ኃይሉ ከታሰሩት የማፊያ ተጠርጣሪዎች እንዳረጋገጡት የበርሜሉን አስከሬን የገደሉት የወይን ጠጅ፣ ዘይትና ሌሎች የእርሻ ምርቶች ኢምፖርት የሚያደርጉ ናቸው፡፡ የፍራፍሬ፣ የዘይት፣ የአይብና የወይን ንግድ ለማፊያ ጥሩ ሽፋን ሆኖለታል፡፡ እነዚህ የንግድ ዘርፎች ገንዘብና ሀብት ለማጋበስ በእጅጉ ረድቶአቸዋል፡፡

የመሳሪያ ፈቃድ ጉዳይም ከዚህ ቀደም በሲሲሊ እንደሚደረገው ቀጥሏል፡፡ የሞሬሎ የማፊያ ቡድኖች ምንም እንኳ ተጠርጥረው የተያዙ ቢሆንም በከተማ ውስጥ የጦር መሣሪያ የመያዝ ፍቃድ ነበራቸው፡፡ ይህ ጉዳይ በኒውዮርክ ሄራልድ ጋዜጣ ላይ እንደወጣ የፖሊስ ኮሚሽነሩ 322 ፈቃድ የተሰጣቸውን እንዲሰረዝ አድርጓል፡፡

ሲሲሊ ባሉ ማፊያዎችና በአሜሪካ ማፊያ መሐል የጠበቀ ግንኙነት እንዳለ የተረጋገጡ መረጃዎች ያመለክታሉ። ለምሳሌ ያህል የሞሬሎ ቡድን ማፊያ አባል የነበረው ዶን ቪቶ ካሽዩ-ፌሮ (Don Vito Cascio-Ferro) በፔትሮሲኖ ሲፈለግ የነበረ ሲሆን በኋላ ላይ በሲዛሬ ሞሪ (በፖሌርሞው ፖሊስ አዛዥ) መያዙ ታውቋል። «የበርሜሉ አስከሬን» ከመገደሉ በፊት ከፖሊስ ክትትል ለመሸሽ ሲል «ፌሮ» አስቀድሞ ወደ ሲሲሊ አምልጧል። ከዚያም ወደ አሜሪካ በሎሚ ኢምፖርተርነት መሄዱ ነው የተነገረው። በ«በርሜሉ አስከሬን» ጉዳይ ብዙዎች ማፊያዎች ሲያዙ ፌሮ ግን የነበረበትን ሥፍራ ለወጠ። ከኒውዮርክ 12,000 ሲሲሊያውያን ወደሚኖሩበት ጠንካራ የማፊያ ማዕከልም ተጓዘ። በዚህ አኳኋን፣ የሞሬሎን ቡድን ሌላ አዲስ ሰደተኛ ተቀላቀለ። ይህ ሰው ጁሴፔ ፎንታና ሲሆን በኢማኑኤሌ ኖታርባራቶሎ ክስ «ነፃ» ሆኖ እንደተለቀቀ ይታወሳል። ሞሬሎ፣ ካሺኦ - ፌሮና ፎንታና የተለያዩ የማፊያ ቡድኖች (Cosche) የክብር ሰዎች የነበሩ ናቸው።

የሞሬሎ ማፊያ ቡድን ልክ እንደ ሲሲሊው በኒውዮርክም በትስስርና በካቦ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ድሩን አድርቷል። ከለላ የመሆንና ከፖሊስ ጋር መሞዳሞድን በእጅጉ ይተገብራል። የአዲሲቷን ሀገራቸውን ፖለቲካ ካለመረዳት ለአነስተኛ ጥቅም የምርጫ ድምጽ እስከ መስጠት ይደርሳሉ።

ምንም እንኳ የማፊያ አሠራር የታወቀ ቢሆንም የኒውዮርክ የተለየ ባህሪ ነበረው። አሜሪካ የበለጠ ተንቀሳቃሽና አንድ ወጥ ያልሆነ ሕዝብ የሚኖርባት ሀገር መሆኗ ከጣሊያን ለየት ያደርጋታል። ስለዚህ ማፊያም በአዲሱ ዓለም ተንቀሳቃሽ መሆን ነበረበት። እንደ ኒኮላ ጀንቲሌ ያሉ ወጣት ሲሲሊያውያን የማፊያን ቡድኖች ተቀላቅለዋል። ጀንቲሌ በ1905 ነው በፊላዴልፊያ የማፊያ አባል የሆነው። ወደ ተለያዩ ከተሞችም ተዘዋውሮአል። በማንሃተን፣ ፒትስበርግ፣ በክሌቭላንድ፣ ቺካጐ፣ ሚልውኪ፣ ካንሳስ ሲቲ፣ ሳን ፍራንሲስኮና ካናዳ ጭምር እየተዘዋወረ ማፊያን አገልግሏል።

ከተጠቀሱት ሥፍራዎች ሁሉ ኒውዮርክ የማፊያ አመራር ወንበር ስትሆን ከሲሲሊ ለሚመጡ ሰዎችና ንብረቶች ዋና መረማመጃ

ነበረች፡፡ ፒዱ ሞሬሉም እስከ 1909 ድረስ የመላው አሜሪካ ቅርንጫፍ ዋና አለቃ ነበር፡፡

የሞሬሎ ማፊያ በድን በትንሿ ኢጣሊያ ነገሶ የቆየ ሲሆን በኒውዮርክ ማንሃታን ከሌሎች ቡድኖች ጋር በትግል ውስጥ ኖሯል፡፡ ማፊያ (ኮዛ ኖስትራ) Gas House Gang, the Gophers, the Hudson Dusters እና Pearl Buttons ከተሰኙ ቡድኖች ጋር ተቻችሎ መኖር ነበረበት፡፡

ቀድሞውኑም የሲሲሊ ማፊያ በኒውዮርክ ለመንሰራፋት ዕቅድ ነበረው፡፡ ኋላም ኒውዮርክ እንደደረሰ እንደተመኘው ሊንሰራፋ አልቻለም፡፡ እርግጥ አሜሪካ ናት ማፊያን ወደ ዋነኛ የንግድ ምልክትነት የለወጠች፡፡ የአሜሪካ ሚዲያ ለተቀናጀው የኢጣልያኖች የወንጀል ድርጊት ሁሉ «ማፊያ» የሚለውን ቃል በስፋት በመጠቀም ማፊያን አገነነች፡፡ እንደ ማኖ ኔራ (ጥቁር እጅ) በሚል የሚታወቀው ማፊያ የሸብር ሥራውን እንዴት እንደሚሠራ ለማሳያ ያህል ለታወቀው የብሩክሊን ኮንትራክተር ኒኮላ ካፔሉ የፃፈው ማስፈራሪያ እንደሚከተለው ይጠቀሳል፡- «እኛን በ72ኛው መንገድና በ13ኛው ጐዳና ብሩክሊን ላይ ካላገኘኸን ነገ ከሰዓት በኋላ ቤትህ በፈንጂ ይታጠራል፣ አንተና ቤተሰብህ ትገደላላችሁ፡፡ ለፖሊስ የእኛን አላማ ከገለጽክም ተመሳሳይ ርምጃ ይወሰድብሃል» ሲል ይደመድማል፡፡ ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ባለመስጠቱ ተጨማሪ መልዕክት ተላከለት፡፡ 10,000 ዶላር እንዲከፍል ታዘዘ፡፡ ከዚያም ሶስት የቆዩ ጓደኞቹና አንድ ሌላ የማይታወቅ ሰው ተጨምሮ 1000 ዶላር እንዲከፍል ተደረገ፡፡ ከዚያም እነዚሁ ሰዎች በሌላ ጊዜ ተመልሰው መጥተው ጭማሪ ገንዘብ ጠየቁ፡፡ ካፔሎ ለጠቅላላ ሀብቱ በመስጋት ለፖሊስ ሄዶ ጉዳዩን አመለከተ፡፡ «ጓደኞቹ» ታስረው ተፈረደባቸው፡፡

«የጥቁሩ እጅ» ደብዳቤ ግን አልተቋረጠም፡፡ «የጥቁሩ እጅ ደብዳቤ» የሚለው ልዩ መለያ ሆኖ የተመቀኛኙ ጐረቤታሞች፣ የንግድ ተፎካካሪዎችና አታላዮች ሳይቀሩ «የጥቁሩን እጅ ደብዳቤ» እየላኩ ማስፈራራት በኒውዮርክ የተለመደ ሆኖ ነበር፡፡

???

«የበርሜሉ አስከሬን ጉዳይ ጆ ፔትሮሲኖን በኒውዮርክ ነዋሪዎች ዘንድ ጀግና አደረገው፡፡ ፔትሮሲኖ በሥራው ትጉህ እንደነበር ብዙ

ወንጀሎችን አሲዞ ወደ ደሴቲቱ (ሲሲሊ) አስመልሷቸዋል። ለዚህም በኒውዮርክ የፖሊስ ዲፓርትመንት ዕድገቱን እያሳካ ተጓዘ። ጥር 1905 የፖሊስ ክፍሉ የኢጣልያ ጉዳይ ኃላፊ ሆኖ ተመደበ። ከዚያም ለመጀመሪያ ጊዜ የኢጣሊያ አሜሪካዊ የፖሊስ መቶ አለቃ ሆነ። በ1907፣ አደሊና ሳሊኖን በጥንታዊው ቅዱስ ፓትሪክ ቤተክርስቲያን «በትንሿ-ኢጣልያ» ዕምብርት አገባት።

በቀጣዩ ዓመት ዶን ሩፋኤሌ ፖሊሶ ኒውዮርክን ሲጎበኝ እንዲከታተለው ጆ ፔትሮሲኖ ተመደበ። ይሄ ሰው ከዚህ ቀደም ኢማኑኤል ኖታርባራቶሎ እንዲገደል ትዕዛዝ ያስተላለፈ ሲሆን 20,000 ዶላር ላዋጡለት ማፊያዎች ምስጋና ለማቅረብ በሚል ሰበብ ነበር ኒውዮርክ የገባው። አንድ የኒውዮርክ ሄራልድ ሪፖርተር ስለ ጉብኝቱ ሲጠይቀው «በኢጣሊያን ዜጎች ውስጥ የመልካም ዜግነት ሥነ-ምግባር ለማስረጽ ነው እዚህ የመጣሁት» ሲል ተመጻደቀ። ከማፊያ ጋር ስለነበረው ግንኙነት ሲጠየቅ ደግሞ ከት ብሎ ስቆ ስለ ማፊያ እንደማያውቅ አስተባበለ።

የጆ ፔትሮሲኖ ዝና ግን በአሜሪካም ሆነ በጣሊያን ማፊያዎች ዘንድ ገናና ስለነበረ አዳዲስ ስደተኞች ሳይቀሩ ይህን ባለ ዝና ለማወቅ ይጓጉ ነበር። አንድን የBrooklyn የወንጀል ቡድን አስሶ ለኢጣልያ መንግሥት በማስረከቡ በ1908 በኢጣሊያ መንግሥት አንድ የወርቅ ሰዓት ተሸለመ።

ምንም እንኳ ሽልማቱ ጥሩ ማበረታቻ ቢሆንም ፔትሮሲኖ እና አለቆቹ የጣሊያን ባለሥልጣናት የወንጀለኞችና የአናርኪስቶችን ወደ አሜሪካ መጉረፍ ሊያቆሙ ከቶ ባለመቻላቸው ደስተኞች አልነበሩም። በ1909 ፔትሮሲኖ የፖሊስ መምሪያ የልዩ ክትትል ክፍል ኃላፊ ሆነ። የመጀመሪያ ግዳጁ ከሲሲሊ ሆኖ የማፊያና የወንጀል ድርጊት ያለባቸው ቡድኖች ውስጥ ሰርጎ በመግባት ከአሜሪካ ማፊያ ጋር ግንኙነት ያላቸውን በመጠቆም ከአሜሪካ እንዲጋዙ ማድረግ ነው ግዳጁ።

በ1909፣ የካቲት ወር ላይ ፔትሮሲና ጣሊያን ከተማ ጀኖዋ ደረሰ። ከዚያም ወደ ፓሌርሞ ቀጠለ። ሆኖም ባልተጠበቀ ፍጥነት ተገድሎ እስክሬኑ ሚያዝያ 1909፣ ወደ ኒውዮርክ ተመለሰ። የፖሊስ

ኃይል በክብር ተሰልፎ የፔትሮሲኖን አስከሬን በኒው ዮርክ ተቀበለው:: በወቅቱ የኒው ዮርክ ሔራልድ እንደገመተው 20,000 ሕዝብ ቀብሩ ላይ ተገኘ:: ሠርጉን በሰረገበት ቤተክርስቲያን አስክሬኑ ተመልሶ አረፈ:: ፔትሮሲኖ በፍጥነት የማፊያ ሰለባ የሆነው የሲሲሊን ማፊያ አሳንሶ በመመልከቱ እንደነበር ይነገራል::

የኒውዮርክ ፖሊስ እንደሚጠረጥረው ከሆነ የፔትሮሲኖ አሟሟት «ከበርሚሉ አስክሬን» ጉዳዮች ጋር የተያዘ ነበር:: በኋላም እንደተረጋገጠው መሬሎና ጁሴፔ ፎንታና (በቅጽል ስሙ «ካፌሮ») ገደላውን እንዳካሄዱ ታውቋል:: «ፌሮ» በሚያዝበት ወቅት በኪሱ የፔትሮሲኖን ፎቶግራፍ ይዞ ነበር:: በዚሁ ምክንያት ለእሥር ተዳረገ:: በኋላ ኢንተርቪው ከእስር ቤት ሲደረግለት «በሕይወቴ አንድ ሰው ብቻ ገድዬአለሁ - ሳልፈልግ ያደረኩት ነው» ሲል ተናግሯል:: ሟች ግን ጆ ፔትሮሲኖ ነበር:: አሜሪካዊውና ፖሊሱ ፔትሮሲኖ በፒያሣ ማሪና በቆመው የጋሪባልዲ ሐውልት ፊት ለፊት ቆሞ የኤሌክትሪክ ባቡር እየጠበቀ ሳለ ሁለት ሰዎች አራት ጥይቶችን ተኮሱበት:: በሶስት ጥይት ተመቶ ወደቀ:: ጥቁሩ እጅ "Mano nera" ያንን ተርብ ፖሊስ ከሩጫው አቆመው::

## የኮላ ጄንቲሌ አሜሪካና የአልኮል ክልከላው መዘዝ

በአሜሪካ ውስጥ የተደራጀ ወንጀለኛነት እንዲስፋፋ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣው ጉዳይ የወንጀለኛ ቡድኖች መሰባሰብ ወይም የወንጀለኛ አለቆች ከሲሲሊ ወደ አሜሪካ መግባት ብቻ አይደለም:: የክልከላ ሕግ መጽደቅ ነው:: በጥር፣ 1919 ከአንደኛው የዓለም ጦርነት መጠናቀቅ በኋላ በተለይ በጀርመን መጠጥ ጠማቂዎች ላይ የተነሳው ተቃውሞ በአሜሪካ ሕገ መንግሥት ላይ አሥራ ስምንተኛው ሕግ እንዲወጣ ሆነ:: ይህም ሕግ የአልኮል መጠጦች ምርት፣ ሽያጭና ዝውውር እንዲታገድ አደረገ:: በዚህ ጊዜ ነው ማፊያ በዚህ ክልከላ ውስጥ እጁን የሰደደው:: ከድብቅ የመጠጥ ንግድ ከታክስ ነፃ የሆነ ትርፍን ወንጀለኞች ማጋበስ ጀመሩ:: ክልከላው ሊሠራ ባለመቻሉ 2 ቢሊዮን ዶላር ወደ ጥቁር ገበያው እንዲፈስ ሆነ:: (በኋላ ግን ክልከላው በ1933 ተሰርዟል::)

ብዙዎች ተራ አሜሪካውያን መጠጥ መጠጣት ስለሚወዱ የክልከላው ጥቅም ሊገባቸው አልቻለም። ይህን ቀዳዳ ያገኙት ማፊያዎች የጠጪዎች የቅርብ ጓደኞች ሆኑ። ከድብቅ መጠጥ የሚገኘው ገቢያቸው አሻቀበ። ፖሊሶች፣ ፖለቲከኞችና ዳኞች የድርሻቸውን ከዚህ ያልተጠበቀ ትርፍ መካፈል ጀመሩ። በርግጥ ይህ ሲባል ጣሊያኖች ብቻ አልነበሩም የተከለከለ መጠጥ አዟዟሪዎች (Bootleggers)። በኒውዮርክ መጠጥ አዟዟሪዎች ከነበሩት 50 በመቶዎቹ ይሁዲዎች ሲሆኑ፣ ጣሊያኖች 25 በመቶ ብቻ ነበሩ። የመጠጥ ክልከላው ሕግ መጽደቅ ማፊያዎች ይበልጥ እንዲጠናከሩ አድርጓል። ለዚህም ዋነኛው ማሳያ የሚሆነው በ1920ዎቹ ዓመታት ኒኮላ ጀንቲሌ የተባለው ማፊያ ነው። ይህ ሰው በሲሲሊ ተወልዶ የማፊያ አባል የሆነው ደሞ በፊላደልፊያ በ1905 ነበረ። በቅፅል ስሙ «ኒክ» ወይም «ኮላ» ተብሎ ይታወቃል። በ1963፣ ኮላ በወቅቱ ሰማኒያ ዓመት ዕድሜ ላይ የደረሰ ሲሆን ኑሮውንም ከአሜሪካ ተመልሶ በሮማ አድርጓል። የራሱን ግለ ታሪክ ለመፃፍ ያልተጠበቀ ውሳኔ አደረገ። የግል ሕይወቱን ታሪክ የፃፈ የመጀመሪያው የማፊያ «የክብር ሰው» ነበር ማለትም ይቻላል።

«ኮላ» ራሱን ውስጠ ጉምዛዛ ሽማግሌ ሰው መሆኑን ገልጿል። ምንም እንኳ ልጆቹ በሙያ መስክ የተሰማሩ ታታሪዎች ቢሆኑም ከወንጀለኛ ደም የተፈጠሩ መሆናቸው ደግሞ በሌላ በኩል ሲያሸማቅቃቸው ኖሯል።

የኮላ ጀንቲሌ ግለ ታሪክ ራሱን «የክብር ሰው» መሆኑን ለማሳየት ሙከራ ያደረገበት ትረካ ነው። አንድ ወጣት ሰው በ1949 ከሰዓት በኋላ ከኮላ ጋር እያወጉ እንዳሳለፉ ተናገረ። ኮላ በወሬው መኻል ግማሽ ቀልድ እየጣለ «ለትንሹ ፕሮፌሰር» (Duttureddu) ስለ ራሱ አወጋ። በተለይም «ለትንሹ ፕሮፌሰር» (በወቅቱ ማፊያ የመሆኑን ስሜት እንደሚከተለው «ለትንሹ ፕሮፌሰር» የሚል ቅፅል የተሰጠው) ወጣትና ተማሪ ስለነበረ ነው ትንሽ ፕሮፌሰር የሚል ቅፅል የተሰጠው) እንዲህ ሲል ተረከለት፦

*«ትንሹ ፕሮፌሰር! አሁን እዚህ ሳልታጠቅ ብመጣ ሽጉጥህን ታወጣና እኔ ላይ ታልማለህ ከዚያም ኮላ ጀንቲሌ፣ ተንበርከክ ትለኛለህ። ምን*

*አደርጋለሁ? እንበረከካለሁ። ኮላ ጀንቲሌን አስገድደህ እንዲንበረከክ በማድረግህ ማፊያ ነህ ማለት አይደለም። የእኔ ትንሽ ፕሮፌሰር! ለምን? ብለህ ጠይቀኝ። በተራዬ አንተ ተመልሰህ እንድትንበረከክ ማሳመን አለብኝ። አንተ ስትንበረከክ ያኔ እኔ ማፊያ ነኝ። አንተ ግን በፈቃደኝነትህ ካልተንበረከክ ተኩሼ እገድልሃለሁ። ይህ ማለት ግን አሸነፍኩ ማለት ሳይሆን ትንሹን ፕሮፌሰር አጣሁ ማለት ነው።»*

ይህ አባባል የሚያሳየው ኮላ ጀንቲሌ ራሱን ከመሳሪያ ነጥሎ መመልከት የማይችል ነውጠኛ መሆኑን ነው። ሌላው ከኮላ ጋር የተያያዘው የማፊያ ሰው ጆ ቫላንቺ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ በአሜሪካ ያለው የማፊያ ድርጅት «የእኛ ጉዳይ (Cosa Nostra)» መሆኑን ለዓለም አሳወቀ። ይህ ሰው ለአሜሪካ ኮንግረስ ንዑስ ኮሚቴ በ1963 ስለተደራጀ የወንጀለኛ ቡድን ያደረገው ገለፃ የብዙዎችን ቀልብ ስቦ ነበር። በፕሬዚዳንቱ ወንድማቸው የተሾሙት ሮበርት ኬኔዲ ስለዚሁ ሲናገሩ «ትልቁ የደህንነት ሥራችን የተደራጀ ወንጀልን ለመዋጋት የደረስበት ልዩ ግኝት» ሲሉ ነበረ ያሞካሹት። «የቫላንቺ ሰነድ» የተሰኘው መጽሐፍ በወቅቱ በብዛት ተሸጦ እንደነበረ ይታወሳል።

ኮላ ጀንቲሌ ከታወቁት የማፊያ አለቆች ከእነ አል ካፖኔ፣ ከሉኪ ሊቺያኖ፣ ቪንቼንዞ ማንጋኖ፣ አልበርት አናስታዚያ፣ ቪቶ ጀኖቪዜ ጋር በ1920ዎቹና 30ዎቹ ውስጥ በሚገባ ሰርቷል። በ1920፣ በኒውዮርክ ብቻ አንድ ሚሊዮን ትውልድ ኢጣሊያኖች ነበሩ። ከነዚህም ውስጥ ግን እጅግ በጣም ጥቂቶች ነበሩ ወንጀለኞቹ። የማህበረሰቡ ሐብት እየጨመረ ሲሄድ ሕገ-ወጥ የንግድ መስመርም ፈረጠመ። በኢጣሊያ ሀገር ያሉ ወንጀለኞችም ከአሜሪካው ጋር ትብብር ፈጠሩ። በጣሊያን-አሜሪካውያን ማህበረሰቦች ውስጥ የጐዳና ሎተሪ በጣም የተዘወተረ ሲሆን ከደቡባዊ ኢጣሊያ ጋር የሚመሳሰሉ የምግብ ቤቶች መደራጀትም እንዲሁ ሌላው የወንጀለኞች ዒላማ እንዲሆኑ በር ከፈቱ። ከኢጣልያኖች መስፈር ጋር የኒውዮርክ ሁኔታም ተቀየረ። በ1880፣ 95 በመቶዎች ነዋሪዎች አይሪሾች የነበሩ ቢሆንም በ1919 ላይ ግን 75 በመቶዎቹ ጣሊያኖች

ሆኑ። በተለይ ደግሞ በብሩክሊን ምሥራቃዊ ክፍል ዋነኛ ኃይል ነበሩ። በዚች የወደብ ከተማ ኮንትሮባንድ፣ ዝርፊያና ማስፈራራት በሰፊው ተንሰራፉ። ብዙዎቹ የወደብ ማህበሩ ኃላፊዎች በደም የተቆራኙ ዘመዳሞች ነበሩ። እነ አልበርት አናስታዚያና ቪንቸት ማንጋኖ በተባሉ የማፊያ አለቆች ይመራሉ።

ወደ ኮላ ጀንቲሌ የኋላ ታሪክ ስንመለስ፣ በ1903 አሜሪካ ሲገባ የ18 ዓመት ጐረምሳ ነበር። ከዚያም ወደ ካንሳስ ሲቲ ከተዛወረ በኋላ የአልባሳት የሽያጭ ሠራተኛ ሆኖ ማገልገል ጀመረ። በአብዛኛው የሚያቀርባቸው ምርቶችን በማታለል ይሸጣል። በሥራውም ምክንያት ኮላ በተለያዩ የአሜሪካ ከተሞች ጋር የግንኙነት ድሩን አሰፋ። በ21 ዓመቱ በፊላደልፊያ የማፊያ አባል ሆነ። ከአምስት ዓመታት በኋላ ወደ ትውልድ ሥፍራው ገንዘብና የኑሮ ደረጃውን ለውጦ ተመለሰ። ሚስት አግብቶና ወልዶ «የክብር ማህበረሰቡን» ለማገልገል እንደገና ወደ አሜሪካ ተመለሰ። ሚስቱና ልጁ ግን እዚያው ሲሲሊ ደሴት ላይ ቀሩ።

በ1915 ወደ ፒትስበርግ ተመልሶ ለእሱ ብቻ ያደሩ ወጣት አባላትን (Picciotti) መለመለ። እነዚህ ወጣቶች ኮላ እንዲገን አስተዋጽኦ አድርገዋል። ኮላ የመሠረታቸው እነዚህ የወንጀለኛ ማህበረሰቦች ከካላብሪያና ከኔፕልስ የመጡ ወንጀለኞች የተሰገሰጉበት ሲሆን ዋነኛ የኃይል መሠረታቸው የፍራፍሬና የአትክልት ገበያ ሆነ። በፒትስበርግ የኮላ ዝና በፍጥነት ተመነደገ። እንደ ኔፕልስ ሁሉ የካሞራ ማፊያ ቡድንም በዚሁ ከተማ ይነቃነቅ ነበር። ስለዚህ ኮላ የሲሲሊያውያን ማፊያ «ዋና ካፖ» ለመሆን ወጣት አባላቱን (Picciotti) አሰማራ። የወጣቶች ቡድንና የካሞራ ቡድን እንዲነጋገሩ በራሱ ሊቀመንበርነት ዋና ዋናዎቹን ማፊያዎች ጠራ። ኮላ ለሲሲሊያውያን ልዩ ክብር ነበረውና «አንድ ጉዳት በሲሲሊያውያን ላይ ብታደርሱ ድራሻችሁን አጠፋለሁ!» ሲል ዛተባቸው። በዚህም የከተማዋ ዋና ካቦነቱን አረጋገጠ። ኮላ «ከዚያ ምሽት በኋላ በፒትስበርግና በአካባቢው ያሉ የካሞራ አባላት ድራሻቸው ጠፋ» ሲል የሲሲሊ ማፊያዎችን ብቻ ማጠናከሩን አረጋገጠ። አንድ የፒትስበርግ ማፊያ ካፖ በጥይት እንዲገደል ካደረገ በኋላ «ልዩና ምቾት»

ባለው የአስከሬን ሳጥን ታሽጐ ወደ ሲሲሊ እንዲጓዝ አደረገ። ከዚህ በኋላ ኮላ ጀንቲሌ የከተማው ዋና የማፊያ አለቃ ሆነ።

ኮላን ከሌሎች የማፊያ አለቆች ለየት የሚያደርገው በአሜሪካ ውስጥ ተነቃናቂ የማፊያ ቡድን መፍጠር መቻሉ ነው። ማፊያዎች ከፊላ ደልፊያ ወደፒትስበርግ፣ እንደገና ወደ ብሩክሊን፣ ካንሳስ ሲቲ ወይም ወደብሩክሊን ተመልሰው እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋቸዋል። እነዚህን ተንቀሳ ቃሽ ቡድኖች ኮላ «ቦርጌታ» (Borgate) ሲል ሰየመ። (በነገራችን ላይ ቦርጌታ ፓሌርሞ አጠገብ ያለች የክብር ሰዎች አነስተኛ ከተማ ናት።)

የሞት ፍርድ ለሁሉም በአሜሪካ ላሉ ክፍሎች የሚተላለፈው «በቦርጌታ» ሲሆን ዋና ዋና የማፊያ አለቆችን የያዘ «ምክር ቤት» ይዞ ነው እጅግ ወሳኝ ውሳኔዎችን የሚያሳልፈው። ከዚህ በላይ ያለው «ጉባዔ» ደግሞ ካፖዎችን ይሰይማል። በዚህ ጉባዔ ላይ 150 የሚሆኑ የማፊያ አለቆች ከመላይቱ አሜሪካ ይሰባሰባሉ። ይህ ስብስብ በአብዛኛው ማይም ሰዎችን የያዘ ሲሆን ዋናው ከነዚህ ሰዎች የሚፈለገው «እንደበተ ርቱዕ» መሆንን ብቻ ነው።

ኮላ ጀንቲሌ በተደጋጋሚ ከአሜሪካ ወደ ሲሲሊ የሚመለሰው በሽታውን ለማስታመምና ከውጥረት ራሱን ለማዝናናት የኃይል ማግኛ ባትሪ ቻርጅ ለማድረግ ነው። ሁሌም ግን ሲሲሊ የመንፈስ እርጋታ የሚያገኝባት ስፍራ ሳትሆን አንዳንዴም በሚፈፀሙ ወንጀሎች ሳቢያ ህቡዕ የሚገባበት የጭንቅ ሁኔታን ትፈጥርበታለች። እንደነ ፒዱ ሞሬሎ ያሉ የአሜሪካ የማፊያ አለቆችን፤ ማለትም «በበርሜሉ አስከሬን» ግድያ የሚጠረጠሩትን በሲሲሊ ይቀበል ነበር። ሲሲሊ በመቀመጡ ግን ከአሜሪካ የመጠጥ ሽያጭ የሚገኘውን ከፍተኛ ገቢ ለማግኘት አልቻለም። የአልኮል መጠጥ መከልከልን አስታኮ በካንሳስ ሲቲ ለፀጉር ቤቶች አልኮል የሚያከፋፍል ኩባንያም ነበረው። ይህ ኩባንያ ኮላ የሂም መላጫ አልኮል ለመጠቀም የሚያስችል ንፁህ አልኮል እንዲያገኝ ረድቶታል።

የአልኮል መጠጥ መከልከል ኮንትሮባንድ አልኮል ነጋዴዎችንና ወጣት የወንጀል ቡድኖችን ፈጠረ። በተለይ እነዚህ መጠጥ አዟዟሪዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ አሜሪካ ተወልደው ያደጉ ጣሊያን-አሜሪካውያን

ናቸው። እነዚህ ናቸው እንግዲህ ለኮዛ ኖስትራ ጣልያናዊም፣ አሜሪካዊም መልክ የሰጡት።

ሌላው ማፊያ ስልባቶሪ ሉቺያኖ ሲሆን የድኻ ከተማ በሆነችው ሌርካራ ፍሪዲ ተወለደ። በ1905 ገና የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሆኖ ነው ሲሲሊን የለቀቀው። በ18 ዓመቱ ናርኮቲክ በመያዝ ወንጀል ጥፋተኛ ተባለ። ይህ ሰው ናርኮቲክ ተጠቃሚም፣ አከፋፋይም ነበር። የአልኮል ክልከላ ሕጉ ከወጣ በኋላ ነው ታዋቂ የአሜሪካ ማፊያ ወንጀለኛ ሆኖ የቀረበው። በሚገባ የሚታወቅበት ስም ቻርልስ ላኪ ሉቺያኖ ተብሎ ነው። «ላኪ» የሚለው ቅጽል ስም ያገኘው ሌሎች ተቀናቃኝ ቡድኖች ሞተ ብለው አንገቱ ላይ ለእማኝነት ከቀረው ጠባሳ ጋር ከጣሉት በኋላ □ትለኛ ሆኖ በመትረፉነበር። ሉቺያኖ ከሌሎች ማፊያዎች ጋር ተቀላቅሎ ማፊያነቱን አጠናክሮ ቀጠለ።

ከዚሁ ስም ጋር በቅርብ የሚታወቅ የማፊያ ወንበዴ ደግሞ ፍራንክ ኮስቴሎ ተብሎ የሚጠራው ሌላው ሰው ነው። በ1891 ነው ከኢጣሊያ ጫፍ የእግር አውራ ጣት ከተማ በሆነችው ኮዜንዛ የተወለደው። ገና የአራት ዓመት ህፃን ሳለ ነው ወላጆቹ ወደ ምሥራቃዊው ሐርለም ያመጡት። ከአሜሪካ ሕግ ጋር የተላተመው ሰውን በማጥቃትና በሥርቆት ክስ በ1908 ነበር። የመጀመሪያ ጥፋት ስለነበር ባይፈረድበትም፣ በ1914 ግን ፈቃድ የሌለው መሣሪያ በመያዝ ወንጀል አንድ ዓመት ታሰረ። ከዚያም ከፖለቲከኞች ጋር ተሞዳምዶ አሻንጉሊት፣ ምላጮችና የቁማር ማሽኖችን የሚያመርት ኩባንያ ባለቤት ሆነ። የኒውዮርክ «የቁማር ማሽኖች ንጉሥ» እስከ መባልም ደረሰ።

ከዚሁ ጋር ሳይጠቀስ የማያልፈው የማፊያ ወንበዴው አል ካፓኔ ነው። በዊልያምስ በርግ ከተማ ተወልዶ «የፋይቭ ፖይንት» ወንበዴዎች ቡድን አባል ሆነ፤ ከዚያም በ1920ዎቹ የቺካጎ ማፊያ ቡድን መሪነቱን ያዘ። ምንም እንኳ ነጋዴ ቢሆንም የማፊያን ድር በቺካጎ በማስፋፋት ነበር ይበልጥ የሚታወቀው። የተከለከሉ መጠጦችን ለማዘዋወር ከከባድ መኪና አሽከርካሪዎች ጋር የ50 ለ50 ስምምነት በማድረግ ብዙ ሠርቷል። ይበልጥ ግን ይህ ሰው በ1929 በቅዱስ ቫሌንታይን ቀን የደረሰውን ፍጅት በመምራት ሲታወቅ በተጨባጭም ወንጀሉን

በተመለከተ ፖሊስ አልደረሰበትም። ይህ ሰው ሌሎች የወንበዴ ቡድን አባላትን በቺካጐ 2122 ሰሜን ክላርክ ጐዳና የፖሊስ ዩኒፎርም በመልበስ ግድግዳ አስይዞ ነበር ሰባቱን ያስረሸናቸው።

እነ ሉቺያኖ፣ ኮስቴሎና ካፔና ናቸው ይበልጥ ማፊያን አሜሪካዊ ያደረጉት። በዚህ ዙሪያ የኮላ ግለ-ታሪክ ሁሉንም የማፊያን ድርጊት ዘርዝሮ አውጥቷል ማለት አይቻልም። ሲሲሊ ውስጥ ስላሉ «የክብር ሰዎች» እና ከአሜሪካ ጋር ስላላቸው ግንኙነት አነስተኛ መረጃ ብቻ ነበር የሰጠው።

በማፊያ መሪዎች መካከል «የአለቆች አለቃ» የካፖዎች ካፖ ሆኖ ለመገኘት ከፍተኛ የሕይወት መስዋዕትነትን ያስከፍላል። ለምሳሌ ኮላ ከሲሲሊ ወደ አሜሪካ ከተመለሰ በኋላ «የበርሜሉ አስከሬን» ቡድን መሪ የነበረው ፒዱ ሞሬሎ ነሐሴ 1930 ቢሮው ውስጥ ተተኩሶ ነበር የተገደለው። ኮላም ስለ አገዳደሉ ምንም ዓይነት ማስረጃ አላቀረበም - «ተከድኖ ይብሰል» ነበር የተባለው ድርጊቱ። ኮላ ጀንቲሌ ወደ አሜሪካ የተመለሰው በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ሚራንዛኖ የተባለውን የማፊያ ዋና አለቃ ለመተካት እንደሆነ ተናግሯል። ይኸው ጉባዔ ሌላውን የማራንዛናን ተቀናቃኝ «ጆ» የተባለውን አለቃ ከሥልጣኑ በማባረር ጊዜያዊ የአለቆች ሁሉ አለቃ (Capo Dicapi) በሥፍራው አስቀምጧል። አላማውም አጠቃላይ የማፊያን ድርጅት የሚያምሰውን ቅራኔ ለማስወገድ ነው ተብሏል። በአሜሪካ ማፊያ ድርጅት ውስጥ የአለቆች ሁሉ አለቃ ለመሆን እርስ በእርስ መበላላት ዋናው ስልታቸው ሲሆን ካፓኔ፣ ማሴራን፣ ማራዛኖም ሆኑ ሌሎች ተበላልተዋል። ለምሳሌ በሉቺያኖ የተቀጠሩ ነፍስ ገዳዮች ማራዛኖን ወግተውና ተኩሰው በፓርክ ጐዳና ላይ ጥለውታል። ከዚህ በኋላ ነው ሉቺያኖ ማፊያን በአሜሪካ ዘመናዊ ሆኖ እንዲቋቋም አድርጐታል የሚባለው። እንዲያም ሆኖ ግን የመጠፋፋት ሂደቱ በመቀጠል በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች በካፖዎቹ ካፖ ትዕዛዝ ዘጠና የሚደርሱ ማፊያዎች እንዲወገዱ ተደርገዋል።

ማፊያን አሜሪካዊ የማድረግና ከአሮጌው ዓለም ማቆራረጥ የቀድሞውን የሀገረ ኢጣሊያንን ተለምዶአዊ የማፊያ አሠራርን ለውጦታል። የማፊያ ጥንቅርም ተለውጧል። ሌሎች ከኒአፖሊና ከደቡብ

ኢጣሊያ ያሉ (ከፓሌርሞ ውጪ ማለት ነው) የሌላ አካባቢ ኢጣልያኖች ጭምር የማፊያ አባል ሆነውበታል። እርግጥ እንዲያም ሆኖ በአንዳንድ ሥፍራ የሲሲሊያውያን የበላይነት ይታይበታል። ለምሳሌ የቡፋሎው ካፖ ስቴፋኖ ማጋዲኖ ከ1920ዎቹ እስከሞተበት 1974 ድረስ ለረዥም ዓመታት የማፊያን ቡድን መርቷል።

???

የአልኮል መጠጥ ክልከላው ከተቋረጠ በኋላ አሜሪካ ለተከታታይ አራት ዓመታት በኢኮኖሚ አዝቅጠት ውስጥ ዳከረች። ይህ ሁኔታ የተደራጀውን የወንጀለኞች ቡድንን ከመሞት ታደገው። ኮላ ጀንቲሌ ወደ አዲስ ኢኮኖሚያዊው ዕድገት ተመነደገ። በትንሿ ኢጣሊያ ማንሃተን የቁማር ቤት ሸሪክ ሆኖ መሥራቱን ቀጠለ።

በአሜሪካ የፀጥታና የፍትህ አካላት የተቀጣጠለው የአደንዛዥ ዕፅን ንግድ የሚያጠፋ ዘመቻ ለኮላ ጀንቲሌ ማጣፊያው እንዲያጥርበት አደረገው። በ1937 ኒው አርሊያንስ ላይ በፌዴራል የደህንነት ኃይል ታገተ። በወቅቱ ሲያዝ ግን ከቴክሳስ እስከ ኒውዮርክ የአደንዛዥ ዕፅ አከፋፋዮችን ያደራጅ ነበር። ብሩክሊን ላይ ያለውን ካፖውን ካማከረ በኋላ የዋስ መብቱን ተጠቅሞ ወደ ሲሲሊ ዳግም ላይመለስ ተሰደደ። በ1980ዎቹ የተገኘው ማስረጃ እንደሚያረጋግጠው የፖርሌሞ ማፊያ አለቆች የኮላን ቤተሰቦች ለአሜሪካኖች ሲሉ ኮላን እንዲገድሉት መጠየቃቸው ተረጋግጧል። ማንም ግን ኮላ ጀንቲሌን ለመግደል አልተስማማም። በመጨረሻ የሕይወት ዘመኑ ልጡ የራስ፣ መቃብሩ የተማሰ ሆኖ ጉረቤቶቹ ሰሀን የፓስታ ምግብ እየመፀወቱት ኖሮ ሞተ።

ከ1930ዎቹ በኋላ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት መፈንዳት ለአሜሪካ ወንጀለኞችና ማፊያዎች የእፎይታ ጊዜን ፈጠረላቸው። በሲሲሊም ቢሆን ጦርነቱ ለማፊያ ማገገም የመድህን ዋስትናን ሰጠው።

# 9

# ጦርነትና የማፊያ ዳግም ውልደት (1943-1950)

## ዶን ካሎ እና የክብር ማህበረሰቡ ዳግም ውልደት

ሐምሌ 14፣ 1943 ጠዋት። አንድ የአሜሪካ ተዋጊ አውሮፕላን በቪቢላልባ (Villalba) ከተማ ላይ ዝቅ ብሎ በረረ። ሁኔታው ከተሜውን ወደ መንገድ ላይ ወጥቶ እንዲመለከት ገፋፋው። አውሮፕላኑ በቤቶቻቸው ጣራ ላይ እያንዣበበ ወርቅማ ቢጫ ባንዲራ መሰሉ ላይ የ«ረ» ቅርጽ ያለበትን ሲያውለበልብ የከተማው ነዋሪ እንደ ጉድ ይመለከት ነበር። በተለይ በራስ መንሶር ጆቫኒ ቪዝዚ መኖሪያ ቤት ላይ ሲደርስ አብራሪው አንዲት አነስተኛ ጥቅል ነገር ጣል አደረገ። ዳሩ ግን አንድ ኢጣልያዊ ወታደር ወዲያውኑ ጥቅሉን ወስዶ ለወታደራዊ ፖሊሶች (Carabincri) አዛዥ አስረከበ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከአራት ቀናት በፊት ደግሞ «ዘመቻ ሐስኪ» ተካሂዶ 160,000 የተባበሩት ኃይላት ጦር አባላት በደቡብ - ምሥራቅ ሲሲሊ ላይ ተቆናጠጡ። ከዚያም 300,000 የአሜሪካና የብሪታንያ ወታደሮች ተከተሉ። ከዚህ በኋላ ከፍተኛ የጦር ኃይል በአካባቢው ይርመሰመስ ቀጥሏል። እንግሊዞች በሰሜን - ምሥራቅ አድርገው ወደ ካታኒያ፣ መሲናና ወደ ሲሲሊ ዋና እንብርት ሲጓዙ፣ አሜሪካኖች ደግሞ ወደ ሰሜንና ምዕራብ ተጓዙ። ይህ ወቅት የተባበሩት ኃይላት ከናዚ ኃይል አብራ የነበረችውን ጣሊያንን ሲወሩ የመጀመሪያ መሆኑ ነው።

ቪላልባ የሲሲሊ ማዕከል ስትሆን ይህን ያህል ዋና ስትራተጂካዊ ግብ ልትሆን አትችልም። ቪላልባና አካባቢው የሚታወቁት የደሀ ምግብ

የሆነውን ተልባ በማምረት ነው፡፡ የከተማው ህይወት ነፍስ የሚዘራው ደግሞ በፒያሣ ማድረቹ ሲሆን እዚያም ቢሆን ሁለት ቡና ቤቶች፣ የሲሲሊ ባንክና አንድ ቤተ-ክርስቲያን በመኖሩ ነው አካባቢው ደመቅ የሚለው፡፡

በሚቀጥለውም ዕለት ተዋጊው አውሮፕላን ያልተለመደ አርማውን ይዞ በአካባቢው ታየ፡፡ ሌላ ጥቅል ነገር ተወረወረ፤ በዚህ ጊዜ ግን ጥቅሉ የተወረወረው ለትክክለኛው ሰው ነበር፡፡ በናይለን የተጠቀለለው ዕቃ በሲሲሊኛ ቃላት "Zu Calo" - «አጐት ካሎ» የሚል ቃል ተጽፎበታል፡፡ «ካሎ» የማፊያ አለቃ ሲሆን ዶን ካሎጌሮ ቪዚን ደግሞ የቄሱ ታላቅ ወንድም ነው፡፡ ጥቅሉ ዕቃ በቪዚኒ ጠባቂ የተወሰደ ሲሆን ወርቃማው ቢጫ ናይለን መሐሉ ላይ «ረ» ፊደል ተጽፎበታል፡፡

በዚያ ምሽት አንድ መልዕክተኛ ቪላልባን ለቆ "Zu Peppi" ለተባለ ሰው አንድ መልዕክት ጣለ፡፡ መልዕክቱ እንደሚከተለው ይነበባል፡- «ማክሰኞ በ20ኛው ቀን ቱሪ (Turi) ለገበያ ወደ ሴርዳ ከጥጆች ጋር ይሄዳል፡፡ ለፍራፍሬዎች ጭራሮ፣ ለከብቶች ደግሞ በረት አዘጋጅ፡፡ የባህር ማደዎቹም እንዲዘጋጁ ንገራቸው» ይላል፡፡

ደብዳቤው በሚስጥራዊ ኮድ የተዘጋጀ ሲሆን "Zu Peppi" ደግሞ «አጐት» ጁሴፔ ጂንኮ ሩሶ ነው፣ የሙሶሜሊ አካባቢ የማፊያ አለቃ፡፡ ይህ የተደረገው «ቱሪ» የተባለው ሌላው ማፊያ የአሜሪካንን ሞተራይዝድ ጦር እንደሚመራ ለሩሶ መንገሩ ነው፡፡ ዶን ካልጌሮ ቪዚኒ ደግሞ በዚያው ዕለት ከተወሰኑ የጦር አባላት (ከላሞች) ጋርና ከታንኮች (ከበሬዎች) ከዋናው አዛዥ (ከወይፈኑ) ጋር ከአካባቢው ይነሳል፡፡ በጂንኮ ሩሶ ሥር የሚመሩት ማፊያዎች የውጊያውን ወረዳ (ጭራሮ) እና ለእግረኛው (በረት) ሽፋን ይሰጣሉ፡፡

ሐምሌ 20፣ ከሰዓት በኋላ፣ ሦስት ታንኮች ወደ ቪላልባ በር ተንደረደሩ፡፡ በታንኮቹ ዋና ጉልላት ላይ ከዚህ ቀደም የታየው የ«ረ» ምልክት ነበረበት፡፡ አንድ አሜሪካዊ ወታደር ከታንኩ መስኮት በኩል ታየ፡፡ በሲሲሊ ቀበልኛ አሜሪካዊው ዶን ካሎ የት እንዳለ ጠየቀ፡፡ ይህ ወሬ ለሽማግሌው የማፊያ ካፖ እቤቱ ድረስ ሽው አለው፡፡ 66ኛውን የልደት በዓሉን ለማክበር አራት ቀኖች ብቻ ነበር የቀሩት፡፡ አሜሪካኖች

መቃረባቸውን እንዲሰማ በፍጥነት ወደ እነሱ አቀና፣ ከዚያም ጠባቂው አግኝቶ የሰጠውን «ረ» ምልክት ያለበትን መሐረብ እያውለበለበ ተጠጋቸው። ከዚያም ታንኩ ላይ ተሳፍሮ ሄደ።

ከዚህ በኋላ በቪላልባ ወሬው ሁሉ በማፊያዎች ዘንድ ስለ ዶን ካሎ ሆነ። ዶን ካሎ በቻርለስ ላኪ ሉቺያኖ (በባንዲራው ላይ ያለው ምልክት «ረ» የተሰየመው በዚህ ሰው ነው) አማካይነት ለአሜሪካ መንግሥት ቅርበት እንዳለው ወሬው ተዛመተ። ሉቺያኖ ከታሰረበት የአሜሪካ እስር ቤት ተፈትቶ ለወረራው ማፊያዎችን እንዲያስተባብር የተዘጋጀ ሰው ነበር።

ከስድስት ቀናት በኋላ ዶን ካሎ በአንድ ትልቅ የአሜሪካ መኪና ሆኖ ግዳጁን አጠናቆ ወደ ቪላልባ ተመለሰ። ከዚህ በኋላ ካሎ በአሜሪካ ድጋፍ ማፊያን በሲሲሊ ማህበረሰብ ውስጥ ከፋሽዝም የጨለማ ጊዜያት በኋላ ዳግም ለመመለስ ዝግጅቱን አጠናቀቀ።

ብዙዎች ሲሲሊያውያን ስለ ዶን ካሎና ስለ ቢጫው መሐረብ ታሪክ አሁን ድረስ ያውቃሉ፣ ያምናሉም። በቪላልባ ከተማ ለተባበሩት ጦር አባላት በደስታ የተሞላ የደመቀ አቀባበል ነበር የተደረገው። ምክንያቱም ፋሽዝምና ጦርነት ካመጣባቸው ፍዳ በመላቀቃቸው ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ሲሲሊያውያኑ አሜሪካንንም ይወዱአታል፣ ብዙ የአሜሪካ ስደተኛ ጣልያናውያን ከአዲሱ ዓለም ገንዘብ ቋጥረው፣ ተምረውና ፈጣን ነጋዴዎች ሆነው ስለተመለሱም ዓይናቸውን ጥለውባቸዋል።

የተባበሩት ጦር በሲሲሊ ላይ በተረማመደ ቁጥር ከተሞችን ከፋሽስቶች ነፃ እያወጣ ወደፊት ቀጠለ። ከተሞች በአመራር እጦት ባዶ እንዳይቀሩ የሲሲሊ - አሜሪካዊ አስተርጓሚዎች ኃላፊነቱን አስረከቡ። ብዙዎች የገጠር ማዕከላት ወደ አካባቢው የክብር ሰዎች ይዞታነት ተለወጡ። እንደሚታወቀው እነዚህ የማፊያ የክብር ሰዎች የፋሽስት እመቃ ተጠቂዎችም እንደነበሩ ይታወሳል።

አሜሪካኖች የየከተሞች ከንቲባዎችና የአካባቢው አስተዳደሮችን ወደ ስልጣን በሚያወጡበት ጊዜ የቤተክርስቲያን ሰዎችን ነበር የሚያማክሩአቸው። ዶን ካሎም ከእነዚህ ተጠቃሚ ሰዎች አንዱ ሆነ። ቀደም ሲል እንደሚታወሰው ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጋር የቅርብ

ቁርኝት አለው፣ ሁለት ወንድሞቹም ቄሶች ናቸው። እንዲያውም አንዱ አጐቱ ቄስ-ገበዝ ሲሆን ሌላው የሙሮ ሉካኖ አቡን ነበር።

ዶን ካሎ የቪላልባ ከተማ ከንቲባ ሆኖ አንገቱን ቀና አድርጐ እንደ ሰላም ፈጣሪ ይቆጠር ገባ። እንዲያውም ቀደም ሲል የነበረው የፋሽስት ከንቲባ ከመገረፍ እንዲድን ያደረገው ካሎ ነው። በሥልጣን-ሲመቱ ላይ አሜሪካዊ መቶ አለቃና የካልታኒሴታ ቤተክርስቲያን አቡን የተገኙ ሲሆን ከውጭ ሆነው ማፊያዎች ደስታቸውን ያሰሙ ነበር! «ማፊያ ለዘለዓለም ይኑር! ዶን ካሎ ለዘለዓለም ይኑር!» የሚል ጩኸት ከአዳራሹ ውጪ በድምቀት አስተጋብቷል። ዶን ካሎ ታዲያ የመጀመሪያ አጣዳፊ ሥራው ከዚህ ቀደም ከወታደራዊ ፖሊስ ዋና መምሪያ የተጠራቀመውንና እሱን ወንጀለኛ የሚያሰኘውን ዶክመንት ማጥፋት ነበረበት። የቆየ ማንነቱን የሚያሳዩ ዶክመንቶችን በማጥፋት የወደፊቱን የማፊያ አለቃነት ተስፋውን ማመቻቸቱን ቀጠለበት።

ነሐሴ 17፣ 1943። የተባበሩት ጦር ሲሲሊ ላይ ካረፈ ከ38 ቀናት በኋላ። ጄኔራል ሰር ሀሮልድ አሌክሳንደር ሲሲሊ ሙሉ ለሙሉ በተባበሩት ጦር ኃይል ሥር መውደቋን ቴሌግራም ለቸርችል አስተላለፈ። ለሚቀጥሉት ተከታታይ ስድስት ወራት ደሴቲቱ በተባበሩት ወታደራዊ አስተዳደር (Allied Military of Occupied Territory - AMGOT) ሥር ትቆያለች። በዚህ በAMGOT ሥልጣን-ዘመን ነበር ማፊያ የሲሲሊን የፖለቲካ ቅርፅ ለማበጃጀት በለስ የቀናው።

AMGOT - ሁሉ በእጁ፣ ሁሉ በደጁ ቢሆንም ደሴቲቱ ግን ሙልጪ የወጣች መንግሥት ሆና ነበር። 4 ሚሊዮን ዜጐቿ በባሰ የድህነት አዘቅት ውስጥ ይዳክሩ ነበር። የምግብ አቅርቦት አነስተኛ ከመሆኑም በላይ በጦርነቱ የተነሳ የባቡር መስመሮች ክፉኛ ወድመዋል። የወንጀል አሀዙ አሻቀበ። እስረኞች በነበረው ግርግር ከየዙብጥያው አምልጠው ሕዝቡን ተቀላቀሉ። ጥቁር ገበያው ይበልጥ ደርቶ ሕዝቡ በጭንቀት ተወጠረ። ልክ ከመጀመሪያው ዓለም ጦርነት በኋላ እንደነበረው ውንብድናው ተመልሶ ተንሰራፋ።

የማፊያ የውንብድና ማዕበል እየተስፋፋ ሄደ። አንድ የፓርሌሞ የፖሊስ መምሪያ ሪፖርት እንዳስታወቀው ማፊያ ሥልጣን የያዘባቸውን ከተሞች እንደሚከተለው ዘርዝሯል፡-

*በቪላልባ ማፊያ የከተማውን ምክቤት ይዟል፣ ከንቲባው የኮቶኔው ሰው አራጅ ነው --- የአሜሪካኖች ጦር ከመጣ ወዲህ በባሪኒዮ፣ በሚስልሜሪ፣ በሲፋላ፣ በዲያና፣ በቪላ ፍራቴ እና በሎጊታ ያሉ ማፊያዎች ንብረቶችን ወደ ራሳቸው አዛውረዋል፡፡ የጀርመን ጦር ጥሎ የሸሸውን ጠመንጃና ጥይት በእጃቸው አስገብተዋል--- ትናንት ወንጀለኞች የጋንጂን ም/ቤት አጥቅተዋል፡፡ በባሮን ስጋዲሪ፣ በባርን ማርቺያናና በባሮን ሊደስትሪ ላይም ጥቃት ሰንዝረዋል፡፡*

እንደእውነቱ ከሆነ ማፊያዎች ቀደም ሲል በጠንካራው ፖሊስ አዛዥ የተወሰደባቸውን የቀድሞ ጥቃት ለመበቀል መነሳታቸውን ያሳያል ሁኔታቸው፡፡

ከስድስት ወራት በላይ በዘለቀው የAMGOT አስተዳደር በሲሲሊ የፓርቲ-ፖለቲካ እንቅስቃሴ ታግዶ ቆየ፡፡ ጊዜያዊ መንግሥትም በአካባቢው መፍጠር ሁኔታውን ወደ ተባባሰ ጉዳና ሊመራው እንደሚችል ገምተው ነበረ የተባበሩት ጦር አዛዦች፡፡ የሲሲሊ ፀረ-ፋሽስት ቡድኖችም ቢሆኑ ሀገር የመምራት ብቃት አልነበራቸውም፡፡ ስለሆነም የተባበሩት ጦር ኃይሎች ጊዜያዊ አስተዳደር የግራ ዘመም አስተሳሰብ በምንም መንገድ እንዲያሸንፍ አይፈልጉም፡፡ ሆኖም ግን ማፊያና ፖለቲከኞቹ «የአካባቢ መንግሥት መሣሪያዎች» ሆነው ለመሥራት ታትረዋል፡፡ በAMGOT አስተዳደር ወቅት የስትራተጂክ አገልግሎት ጽ/ቤት (Office of Strategic Service) የተባለው የCLA ቅድመ-መረጃ ሰብሳቢው አካል ከከፍተኛ የማፊያ አባላት ጋር ግንኙነት መሥርቶ ነበር፡፡ የኮርሊኦኑ (ኢጣሊያ) ተወላጅ ጆሴፍ ሩሶ የፓርሌሞ ኃላፊ ሆኖ ከማፊያ ጋር ያለውን ግንኙነት ያቀናጃል፡፡ ሩሶ ስለማፊያ አለቆች ሲናገር «አለቆችን ሁሉ ለማወቅ ችያለሁ፡፡ ግንኙነታቸውን መልሰው ለማጠናከር ፈጽሞ ጊዜ አይፈጅባቸውም» ብሏል፡፡

መስከረም፣ 1943 መጨረሻ ላይ የተባበሩት ኃይላት ሉቺዮ ታስካ በርዶናሮን የፓርሌርሞ ከንቲባ አድርገው ሾሙት፡፡ ይህ ሰው ለእንግሊዞች ታማኝ ቢሆንም በኋላ ላይ እንደተረጋገጠው የማፊያ የክብር ማህበረሰብ አባል ነበር፡፡ ሌሎች ተመሳሳይ ሰዎች በመላዋ ሲሲሊ

ኃላፊነት ተሰጣቸው። በተለይ ታስካ በርዶርናሮ ደስቲቱን ለመቆጣጠር የሚያስችል አዲስ የትግል መስመር ቀየሰ። በዚህም የሲሲሊ ተገንጣይ እንቅስቃሴን መሠረተ። ተገንጣዮቹ በአሜሪካ ንሥር አሞራ ክንፍ ሥር የተጠለለች ነፃ ሲሲሊን ነበር የተመኙት። ተገንጣይ የመሬት ከበርቴዎች ዋነኛ ጥላ ከለላቸው ያደረጉት ደግሞ መሬታቸውን የሚጠብቅላቸውን ማፊያን ነበር።

በጥር፣ 1944 የፖለቲካ ነፃነቱ ዳግም ከተመለሰ በኋላ ሲሲሊ ከኢጣልያ ጋር እንድትቀላቀል ዝግጅት ተጀመረ። ከዚህ በኋላ ነበር አንድ የተገንጣዮች ቡድን መሪ የማፊያ ዋና መንበር በሆነችው ባጌሪያ ከተማ ላይ ንግግር ያደረገው። ይህም አንደሪያ ፊኖኪያሮ ኤፕሪሌ የሚባለው ከንፈረ-ስሱና አንደበተ-ርቱዕ ሰው ነው። በንግግሩ ውስጥ ስለ ቸርችልና ስለሩዝቬልት መናገር ከመውደዱም በላይ ከእነዚህ መሪዎች ጋር በየእለቱ በስልክ እንደተነጋገረ አድርጐ ያወራል። እንዲህም አለ፡- «ማፊያ በእውነት የሌለ ከሆነ ሊፈጠር ይገባል። ምንም እንኳ በግሌ የወንጀልና የጥቃት ተቃዋሚ ብሆንም እኔ የማፊያዎች ጓደኛ ነኝ» (በኋላ ላይ ቶማሶ ቡከኬታ እንዳረጋገጠው ይህ ሰው አንድ የማፊያ ቤተሰብ ኃላፊ ነው)።

የካቲት፣ 1944፣ የAMGOT አስተዳደር በሲሲሊ አበቃና አዲሱ የኢጣሊያ መንግሥት አስተዳደሩን ተረከበ። በዚያን ወቅት ማፊያዎቹም ሆኑ ተገንጣዮቹ ቡድኖች የአጐት ሳም የሜዲትራኒያን አካባቢ የአጐት ልጆች መሆናቸውን አስመስክረዋል። በብዙዎች ዘንድ በወቅቱ የታየው አስተዳደር በአሜሪካ ጥበቃ ሥርና በማፊያ ኢምብልታ ነፊነት የሚቆይ ራስ-ገዝ መንግሥት ነበር።

???

«በተልባ ምርት የተገኘው ምንዳ ቪላልባን የክብር ሰዎች ማዕከል አድርጓልን?» የሚለው ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ይሆናል።

የአሜሪካ የመረጃ ሰዎች (ወኪሎች) ዶን ካሎን እንደማፊያ ዋነኛ አለቃ አድርገው ነው የተንከባከቡት። በፓሌርሞ ያለው የአሜሪካ ቆንሲላ በ1944 ጽ/ቤቱን ሲከፍት በመረጃ አሰባሰብ በኩል ያተኮረው በስትራቴጂክ አገልግሎት ጽ/ቤት (OSS) ላይ ነው። የስትራቴጂክ አገልግሎት ጽ/ቤቱ

ደግሞ የመረጃ አሰባሰቡን ጉዳይ እምነት ያሳደረው በማፊያና በዶን ካሎ ላይ ነበር። በአንድ ወቅት የፓሌርሞው የስትራተጂክ አገልግሎት ጽ/ቤቱ ኃላፊ ጆሴፍ ሩሶ ሌሎች የማፊያ አለቆችንና ዶን ካሎን «በወር አንዴ» ይገናኛቸው ነበር። ካሎ በምስጢር ስም «ወይፈኑ እንቁራሪት» ተብሎ በድርጅቱ ዘንድ ይታወቃል።

የኋላ ታሪኩ እንደሚያስረዳው በ1922 እምብዛም ያልተማረው ዶን ካሎ በዲኝ ማዕድን እንዱስትሪ ዘርፍ ለመሳተፍና የጣሊያ-እንግሊዝን ማዕድን ኩባንያ ለመመሥረት ከአንድ ቡድን ጋር ወደ እንግሊዝ መጓዙ ይታወሳል።

ለዶን ካሎ ቤተክርስቲያንና የፖለቲካ ግንኙነቱ የተደራጀ የኃይል መሠረት ሰጥቶታል። ዘመቻ «ሐስክ» ከተካሄደ በተከታታይ ዓመታት አንጀሎ ካማራታ የተባለው የካልታኒሴታ የፖሊስ አዛዥና ኋላም ለግብርና ሥርዓት ለውጥ ኮሚሽነር የነበረው ሰው ለዶን ካሎና ለእቡት የቅርብ ሰው ነበር።

የተካሄደው የኢኮኖሚ ለውጥም ዶን ካሎን ብዙ ረድቶታል። የጦርነትና የፋሽዝም መከሰት የእንስሳትና የእህል ምርትን ለሲሲሊ ኢኮኖሚ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች አደረጋቸው።

ዶን ካሎ የመጨረሻ መኖሪያውን በፓሌርሞ ሶሌ ሆቴል ያደረገ ሲሆን ፊር ጃኬት በለበሱ ሁለት ወጣቶችም ይጠበቃል። የዶን ካሎ የፖለቲካ ተጽዕኖ ለማፊያ ልዩ ሥፍራ አለው። ከድኀረ ጦርነቱ የሲሲሊ ለውጥ በኋላ ማፊያ የተረጋጋ ሕይወትን እንዲመራ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። የተነሳሳው የመገንጠል ጥያቄ ከስሞ ኢጣሊያ-አቀፍ ፓርቲ በመጐልበቱ ማፊያን በተለምዶአዊው ዘዴ ማለትም የአካባቢ አስተዳደር መሣሪያ አድርጎ የመጠቀም ትልም ተነደፈ።

መስከረም፣ 1945 በቪላልባ ከተደረገ ጦርነት አንድ ዓመት በኋላ በተገንጣይ መሪዎች ስብሰባ ላይ የተገኘ ብቸኛው ማፊያ ነበር ዶን ካሎ። ስብሰባው ወታደራዊ ጣልቃ ገብነትን ተልሞ የተንቀሳቀሰ ቢሆንም ከAMGOT አስተዳደር እንዳበቃ የተገንጣይነት ህልምም አብሮ ከሰመ። ከዚህ በኋላ የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲ (CDP) ሌላ ተጨማሪ የፖለቲካ ኃይል ሆኖ ወጣ። ዶን ካሎም ከተገንጣዮች ይልቅ የክርስቲያን

ፓርቲው ሰዎች የእርሱን ፍላጐት ሊያስፈጽሙ እንደሚችሉ ተገነዘበ። ደግሞም የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲው አዲሱ የጣሊያን መንግሥት ሲቋቋም ይዞት የተነሳው አጀንዳ የቤተሰብ እሴት፣ የግል ሀብትና ማህበራዊ ሰላም እንዲሰፍን የሚለውን መፈክር ነበረ። የክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲው የቫቲካንንም ድጋፍ አግኝቷል። ቀዝቃዛው ጦርነት በ1947 እንደተጀመረ የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲ ከጣሊያን ኮሚኒስት ፓርቲ በተቃራኒነት በመቆም የአሜሪካንን ድጋፍ ሻተ። እንደሚታወቀው የጣሊያን ኮሚኒስት ፓርቲ በምዕራብ አውሮፓ ጠንካራ የኮሚኒስት ፓርቲ እንደነበር ይታወሳል። በ1948 ለመጀመሪያ ጊዜ በኢጣሊያ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ከሙሶሎኒ መውደቅ በኋላ ተመሠረተ። ይህም ክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲ ለተከታታይ አርባ አምስት ዓመታት ወደ ሥልጣን መንበር እንዲመነደግ አደረገው።

የቆየውንና በመሞዳሞድ ላይ የተመሠረተውን ፖለቲካ የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፖርቲው ማፊያን በመያዝ በሽርክና አቀፈው። በፋሽዝም ጊዜ በፖለቲከኞችና በወንጀለኞች መካከል የነበረው መቀራረብ አስቸጋሪ የነበረ ሲሆን አሁን ግን ሁኔታው ተቀየረ። የእከክልኝ ልከክልህ ግንኙነት ደራ። በሲሲሊያውያን አባባል «አንዱ እጅ ሌላውን ያጥባል!» እንደ ሚባለው ሆነ።

በማፊያ የክብር ሰዎችና በክርስቲያን ዲሞክራሲ ፓርቲ መካከል ያለው ግንኙነት በምስጢር የተያዘ ነበር። በ1948 በአንድ የምርጫ ዕለት ዶን ካሎና ጓደኛው የሙሶሜሊ የማፊያ አለቃ የሆነው ጁሴፔ ጄንኮ ሩሶ በፓርቲው የምረጡኝ ዘመቻ የምሣ ግብዣ ላይ በክብር ተገኙ። ይህ በፓሌርሞ የሚገኘው ሆቴል የፍሎሪዩ ቤተሰብ የጥንት ቤተ-መንግሥት ነበር። ሁለቱም የማፊያ አለቆች በአንድ ጠረጴዛ ላይ የፓርቲው ቀዳሚ ሰዎችን መስለው ተቀመጡ። በ1950 የጄንኮ ሩሶ ታላቅ ልጅ ሲያገባ ዶን ካሎ በጋብቻው ስነ-ሥርዓት ላይ ከክርስቲያን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ የሲሲሊ አካባቢ ፕሬዚዳንት ጋር ተጋባዥች ነበሩ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ መገኘት ለማፊያ አለቆችም ሆነ ለፖለቲከኞች ምንም ዓይነት ሃፍረትን አይፈጥርም። እንዲያውም ማፊያና ፖለቲከኞች እንዴት ተባብረው ጐን ለጐን እንደሚሠሩ ይበልጥ አመላካች ነው።

በ1950 የመሬትን ጥያቄ የመጨረሻ እልባት በሲሲሊ እንዲያገኝ ያደረገው ይኸው የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲ ነው። ይህም የመሬት

ክፍፍል የአካባቢ ፖለቲከኞችን በሚጠቅም የመሞዳሞድ ዘይቤ ነበር የተካሄደው። በዚህም የተንሳ ሙስኝነት ሥር ሰደደ። ለበጀት የተመደበው ገንዘብ አንድ ሦስተኛው ለአስተዳደራዊ ወጪዎች እንዲውል ሆነ። ብዙ የመሬት ከበርቴዎች መሬቶቻቸውን ለማፊያዎች በሰፊው ሸጡ። ዶን ካሎ በዚህ መሐል ተጠቃሚ ሆነ። መሬቱን መላልሶ በመሸጥ ብዙ ትርፍ አጋበሰ።

በዚያው ዓመት መንግሥት ወደ ኋላ የቀረውን የሲሲሊንና የደቡብ ኢጣሊያን ኢኮኖሚ የሚለውጥ አዲስ ፕሮግራምን ይፋ አደረገ። ይህ ወቅት ማፊያ ዕድሜ እንዲያገኝ ልዩ ሁኔታን ፈጠረለት። ምክንያቱም በሲሲሊ ሀብት በማካበትና ዋና የሀብት ምንጩን ለመቆጣጠር ከፖለቲከኞች ጋር እንጂ ከመሬት ከበርቴዎች ጋር መገናኘት ዋጋ እንደሌለው ሁኔታው ያመለክታል። የኢጣሊያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እየተጠናከረ በሄደ ቁጥር የማፊያ ሚና ጭራሹኑ እንዲጠፋ ለማድረግ ተቃርቦ ነበር። ዳሩ ግን ተቃረበ ይባል እንጂ ማፊያ ሊጠፋ አልቻለም።

ከፋሽዝም መውደም በኋላ የማፊያ አለቆች ግንኙነታቸውን ዳግም የመሰረቱት የግል ግንኙነቶችን (የሰው ለሰው) በማድረግ ነው። በተለይ እንደ ዶን ካሎ ያሉ ሰዎች የዚህን የሽግግር ዘመን ሚና ለመጫወት ሁነኛ ሥፍራ ነበራቸው። በዚህም ዘዴ ነው ማፊያ ከውድቀት እንደገና ሊያገግም የቻለው።

በመጨረሻ ዘመኑ ዶን ካሎ ለአንድ ጋዜጣ በሰጠው ቃለ-ምልልስ ባልተጋነነ መንገድ ነበር ስለ ሥራው የተናገረው። ጋዜጠኛው እንደ ዋዛ ስለ «ማፊያ» ሲያነሳበት - ዶን ካሎ እየሳቀና እያጉተመተመ «ማፊያ ለመሆኑ በሕይወት አለ?» ሲል ነበር መልሶ በለበጣ የጠየቀው።

ዶን ካሎ በ1954 በወንድሙ ልጅ ክንድ ላይ ለዘለዓለሙ አንቀላፋ። የጣሊያን ጋዜጠኞች የመጨረሻ ቃሉን ለታሪክ አስቀርተዋል «ሕይወት ምንኛ ቆንጆ ነች!» የሚል ተወዳጅ አባባሉን። በመጨረሻ የሕይወት ዘመኑ አንድ ሚሊዮን ሊሬ በጥሬ ገንዘብ ያስቀረ ሲሆን ሌላው የሀብቱን መጠን ማግኘት አልተቻለም። በመሠረቱ የማፊያ አለቆች የሀብት መጠንን ለማግኘትና ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው።

በሰፈሩት ቁና መስፈር አይቀርምና ካሎ እስከመጨረሻው አሸለበ። በመጨረሻው እስክሬኑ ሲሸኝ በአራት የጥቋቁር-ፈረሶች ሠረገላ በብዙ ለቀስተኛ ፖለቲከኞችና ማፊያዎች ታጅቦ ነበር ግብአተ-ቀብሩ የተፈፀመው። የቪላልባ ዋና ማዘጋጃ ቤት አዳራሽና የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲ ጽ/ቤቶች ለአንድ ሳምንታት እንዲዘጉ ተደረገ። በቤተክርስቲያን ደጅም የሚከተለው የሀዘን እንጉርጉሮ ተሰቀለ --

«የርህሩሆች ሩህሩህ
የታላቆች ታላቅ
ቃሉን የተገበረ
ማፊያ ወንጀለኛ አለመሆኑን ያስመሰከረ።
ለሕግ የበላይነት የቆመ
የሁሉን መብት ያከበረ
የታላቅነት ባህሪይ የተላበሰ
ያ የፍቅር ሰው ታወሰ።»

የቪላልባ ገበሬዎችም ቢሆኑ ስለ ዶን ካሎ «ብዙ ጓደኛና ገንዘብ ያለው፣ ፍትህን የማስከበር ብቃት የተላበሰ ጀግና» ብለው ነበር የሚያሞካሹት።

# 10

# ጦርነትና የማፊያ ዳግም ውልደት (1943-50)

## ከእነ ግሬኮስ ጋር ተዋወቁ - ደም ደምን ያጥባል

የማፊያ የወደፊት ዕጣ ያረፈው በቪላልባ ሳይሆን በባሕላዊ የማፊያ ዋና ቤዝ በሆነው ፓርሌሞ ነው። በጠንካራው የፖሊስ አዛዥ ሲዛሬ ሞሪ ክንድ ከመሞት ማፊያ የዳነው በዚችው በፓርሌሞ መንደር ውስጥ በመጠለል ነው። እንዲህ ዓይነቱ ራስን የማዳንና የመሸሸግ ሥልት የማፊያ የክብር ሰዎች ሀብት እንዲያፈሩም ሆነ የቤተሰባቸውን የክብር ደረጃ እንዲጠብቁ በእጅጉ ረድቷቸዋል።

ከ1946-47 ባለው ጊዜ ሰብአዊነት የጎደለው የማፊያ ጦርነት ተካሂዷል። ጦርነቱ የተካሄደው በፍራፍሬ ምርቷ በምትታወቀው የሲያኩሊ መንደር ሲሆን ከፓርሌሞ በስተምሥራቅ ትገኛለች። በኋላ ላይ በማፊያ ጉዳይ የፓርላማ ምርመራ ሲካሄድ የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ጦርነቱ የተካሄደው በደም በተሳሰሩ ሁለት ቤተሰቦች መካከል እንደነበር ታውቋል። በእነሱ የርስ በርስ ትግል መሃል እጅግ ጠንካራ የሆነ ማፊያ በመጪዎቹ አሥርት-ዓመታት ውስጥ ይወለዳል። የሲያኩሊው ጦርነት የሲሲሊውን ትውፊታዊ አባባል ያስታውሳል - «ደም ደምን ያጥባል» የሚለውን።

አንድ ቤተሰብ በሲያኩሊ አካባቢ ለተከታታይ ትውልዶች የሚውል ልዩ ክብርን በስሙ ተክሏል። ይህ ስም ግሬኮ ነው። በ1946 ይህን የቤተሰብ ስም የያዙ የሲያኩሊንና የአካባቢዋን አጎራባች መንደር የሆነችው የክሮቼ ቬርዴ ጂያርዲኒን ሰዎች ናቸው። ሁለቱ የግሬኮ

ጎሣዎች ምናልባትም የጋራ የሆነ የዘር ግንድ ያላቸው ሲሆኑ በሳንደርጂ ሪፖርት ውስጥ የሲያኩሊን ሰዎች የማፊያ ካፖዎች (Capomafia) ተብለው ይታወቃሉ። ራሳቸውን የዚህ የዘር ሀረግ ቅርንጫፎች መሆናቸውን ለማሳየት ከሁለቱ ጎሳዎች የተውጣጡ ቤተሰቦች ለልጆቻቸው ስም ሲሰይሙ እጅግ ተመሳሳይ ስሞችን ይሰጡ ነበር። ከመካከላቸውም ሦስት ፍራንቼስኮዎች፣ ሦስት ሮዛዎችና ሦስት ጂሮላማዎችን፣ አራት ሳልቫቶሬዎችንና አራት ጁስፔዎችን መሰየማቸው ይነገራል። ከዚሁ በተጨማሪም ቅጽል ስም ለማፊያ ሌላው አስፈላጊ ነገር ነው። በሁለቱ የማፊያ ቤተሰቦች መካከል ግንኙነታቸው የጠነከረው የሲያኩሊው የማፊያ አለቃ የጂያርዳንን የማፊያ አለቃ ልጅ ባገባ ጊዜ ነበር። ዳሩ ምን ያደርጋል በጋብቻ የተደያዘው የዝምድና ሰንሰለት እንደጠነከረ አልቀጠለም።

የጂያርዳንና የሲያኩሊን ግሬኮዎች እርስ በርስ ያፋለማቸው ጦርነት የተጀመረው ነሐሴ 24 ቀን 1946 ነበር። ተጠቂም የሆኑት የሁለቱ ጎሳ ቤተሰቦች የሲያኩሊን ቅርንጫፍ ቤተሰቦች ነበሩ። እነሱም ሁለት ወንድማማቾች ሲሆኑ አንዱ 59 ዓመቱ፣ ሌላኛው ደግሞ 77 ዓመት ሽማግሌ ነበር። በሁለቱ አዛውንት ማፊያዎች ላይ በተከፈተው ጦርነት መትረየስና ቦምቦች በጥቅም ላይ ውለዋል።

ታዲያ ማንም አካል በነፍስ ማጥፋት ወንጀል የተከሰሰ አልነበረም። የሲያኩሊ ሕዝብ ግን የጥርጣሬ ዓይኑን ያሳረፈው በጂያርዲኒው የማፊያ አለቃ ላይ ነበር። ይህ ሰው እንግዲህ ሌላኛው የግሪኮ ቤተሰብ ሲሆን ታሪካቸው በመቶ አለቃ ፒዱ ሪኮርድ ውስጥ ሰፍሯል።

በሁለቱ ግሬኮዎች መካከል የተነሳው ትግል ከፍተኛው የጡዘት ደረጃ ላይ የደረሰው መስከረም 17 ቀን 1947 ላይ ነው። የጂያርዲኒ የማፊያ ቡድን በሲያኩሊ ፒያሳ ላይ በተደረገው ጦርነት አንድ ከፍተኛ አባሉ በመትረየስ ተተኩሶበት ወደቀ። በዚህ ጊዜ ሁለት ሴቶች ባልኮኒ ላይ ሆነው ይከታተሉታል። አንዷ ሴት አንቶኒና (59 ዓመቷ) እና ሮሳሊና (19 ዓመት) የሲያኩሊ ማፊያ የቀድሞ ሚስትና ልጅ ናቸው። እነዚህ ሴቶች ወደ ታች ሲመለከቱ ሰውየው ቆስለ እንጂ አልሞተም ነበር፣ ታዲያ ከባንኮኒያቸው ወርደው በሽንኩርት ቢላዋ ጨረሱት። (በማፊያ የገደላ ተግባር ሴቶች በዚህ መንገድ መሳተፍ የተለመደ

አይደለም) አንቶኒና ሮዛሊናም በተራቸው አልቀረላቸውም፡፡ በተገደለው ሰውዬ ወንድምና እህት እነሱም በጥይት ተደበደቡ፡፡ አንቶኒና ስትቆስል ልጇ ሮሳሊና ግን ተገደለች፡፡ ገዳያቸው ራሱን ለማጥፋት ቢሞክርም የአንቶኒና ልጅ ግን ደርሶ ጨረሰው፡፡

የፓርሌሞ ባለሥልጣናት የሁኔታውን በዚህ መቀጠል አልወደዱ ትም፡፡ ስለዚህ በመቶ አለቃ ፒዱ ላይ ተፅዕኖ በማድረግ መጠፋፋት እንዲቆም ሞከሩ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የሲያኩሊ ጦርነት በመላው የማፊያ ጦርነት ላይ ያልተጠበቀ ሕዝባዊ ትኩረትን ሳበ፡፡ መቶ አለቃ ፒዱ የአካባቢው ፀጥታ ስለሚመለከተው ሰላምን ለማስከበር ኃላፊነቱን ተቀብሎ ተንቀሳቀሰ፡፡ መቶ አለቃ ፒዱ ከቬላቤት ሠፈር ካለ የማፊያ ካፖና ከአካባቢው ቤተሰቦች ጋር ትስስር ያለው ሲሆን ከአሜሪካ ማፊያዎች ጋር ግንኙነቱ ከጠነከረው የማፊያ አለቃ ጋር መሥራት ነበረበት፡፡ ይህ ወቅት ደግሞ ከአሜሪካ የተመለሱ የክብር ሰዎች በሲሲሊ ትልቅ አክብሮትን ያገኙበት ጊዜ ነበር፡፡ ስለዚህ የእንደዚህ ዓይነት ሰዎች እጅ ካልተያዘ ሰላምን ማምጣት እንደሚያስቸግር በመቶ አለቃው ዘንድ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ ለምሳሌ ያህል ጆ ፕሮፋቺ የተባለው የአሜሪካ - ብሩክሊን ኒውዮርክ የማፊያ መሪ ሲሆን ተመልሶ በሲሲሊ መኖር ጀምሮ ነበር፡፡ ይህ ሰው የግሬኮዎች ጦርነት ወደ ሰላም እንዲመጣ ከፍተኛ ሚና መጫወቱ ይታወቃል፡፡

መቶ አለቃ ፒዱም በፕሮፋቺ የተሰጠውን ምክር በመቀበል ነበር ብዙ የታተረው፡፡ ሁለት ዋርሳዎቹ እሱ በሚያስተዳድርባቸው የታንጀሪን የፍሬፍሬ ማሳዎች ውስጥ ኃላፊነትን እን□ያገኙ ተደረገ፡፡ በጦርነቱ የተሳተፉ የግሬኮ የአጎት ልጆች ፍሬፍሬ□ችን ኤክስፖርት በማድረግ ንግድና የአውቶብስ ኩባንያ ባለቤቶች ሆነዋል፡፡ የተከሰተው ሰላም ለመቶ አለቃ □ዱ ክብርን አጎናፀፈው፡፡ ከቪላባቴ ማፊያ ጋር የነበረው ግንኙነት የጠነከረው ልጁ የቪላባቴ ማፊያን ልጅ ባገባ ጊ□ ነው፡፡

በግሬኮዎች መካከል የተከሰተው ደም መቃባት ለምን እንደተፈጠረ ለፖሊስ ግልፅ አልሆነለትም፡፡ ይህም የሆነው ማፊያ በሚከተለው የዝምታ (Omerta) የሚስጢር አያያዝ ዘዴ ምክንያት ነው፡፡ የፖሊስ ሹክ ባዮች እንደተናገሩት ከሆነ ከሰባት ዓመት በፊት በተከሰተ የወጣቶች ጠብና መገዳደል ምክንያት እንደሆነ ታውቋል፡፡ በ1939 ጥቅምት ወር

በቤተክርስቲያን በጓል አከባበር ላይ ስድስት ወጣቶች በዓሉን ለማክበር ከጂያርዲን ወደ ሲያኩሲ መጡ። ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ የመቶ አለቃ ፒዱ ልጆች ነበሩ። እንደ አካባቢው ሰው ሁሉ ወደ በቤተክርስቲያን ገብተው አገዳሚ ወንበር ላይ ተቀመጡ። በወቅቱ የጂያርዲኖ ግሬኮ ልጆች እዚያ ነበሩ። ከዚያም ሰጠብ ተፈላለጉ። ማታ ከበቤተክርስቲያኑ ወጥተው ሲሄዱ የሲያኩሲ ግሬኮዎች ሽጉጥና ቢላዋ ታጥቀው ኖሮ ሰጠብ ተዘጋጁ። ከዚያም የመቶ አለቃ ፒዱ የ17 ዓመት ልጅ ጁሴፔ ተገደለ። የሲያኩሲው የአጎቱ ልጅ ቆሰለ፣ ከአራት ዓመት በኋላ እሥር ቤት እንዳለ ሞተ። ይህ ሁኔታ ነበር የ1946ቱ ጦርነት መነሻ ተብሎ የሚታሰበው። መቶ አለቃ ፒዱ በዚህ ቂም በቀል በመነሳት ነበር ከ1946-47 ባለው ጊዜ ውስጥ የሲያኩሲ-ጂያርዲንን አካባቢ በቁጥጥሩ ሥር ያዋለው።

እንግዲህ ከላይ የቀረበው ቤተሰባዊ ትሥሥርና ፍትጊያ የሚያሳየው ማፊያ በደም የተሳሰሩ የቤተሰብ አባላትን በመጠቀም የማፊያን አገዛዝ ለማስፈን እንደሚሠራ ነው። በ1946-47 ሚኬሌ በ20ዎቹ የዕድሜ ደረጃ ላይ ነበር፣ ከ30 ዓመት በኋላ ግን ሚኬሌ ግሬኮ የማፊያ አለቆች አለቃ (Boss of Bosses) የተሰኘውን ደረጃ አገኘ። ሚኬሌ ፈገግታ የለሽና ዝምተኛ ካፖ ነበር። ውድ ዋጋ ያላቸውን ልብሶች ለብሶ ሽክ ማለት የሚያዘወትር ሰው ሲሆን «ጳጳሱ» በሚል ቅጽል ስም ይታወቃል።

ሲያኩሲ ከ1946-47 ጦርነት ጭር ብትልም ሰልባቶሬ ጁሊያኖ «የመጨረሻው ወንበዴ» እስከሚገደል ሰላሟ አልተረጋገጠም ነበር።

## የመጨረሻው ወንበዴ - የሞንቴሊብሬው ንጉሥ

ከመጀመሪያው ከ1860ዎቹ የማፊያ አመሠራረት ጀምሮ ማፊያ ከወንበዴዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበረው። የማፊያ የክብር ሰዎች ከወንበዴዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት ነበረው። የማፊያ የክብር ሰዎች ወንበዴዎችን ለመገልገል ሲፈልጉ ይከላከሉና ይጠቀሙባቸዋል፣ በኋላም አገልግሎታቸው ሲያበቃ ወይም ካልተመቹዋቸው አሳልፈው ለፖሊስ ይሰጡዋቸዋል። ሰልባቶሬ ጁሊያኖ ምህረት የለሽ ገዳይና የወንበዴዎች ጃዊሳም ከዚህ ድርጊት የሚያመልጥ አልነበረም። ማፊያ ከፋሽስታዊ መዳፍ እጅ ከወጣ በኋላ የኢጣሊያ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት

በመመሥረቻው ወቅት በራሱ ዜናች ላይ የጭካኔ ተግባር የፈፀመ ድርጅት ነው። ወንበዴው ሰልቫቶሬ ጁሊያኖ የዚህ ገፍ አካል ነበር።

ምንም እንኳን ለባለሥልጣናት የማይመች ኢጋማይ ቢሆንም ሰልቫቶሬ ጁሊያኖ ለፎቶ ጋዜጠኞች ራሱን አዘጋጅቶ ነበር። በኩራት መንፈስ ወደ ካሜራው እየተመለከተ ያረቱን ገልብጦ ነበር የተነሳው። እስካሁንም ድረስ የወንበዴው ገጽታ ታሪኩን በሚያውቀው ሰው ዕዝኑ-ልቡና ውስጥ ያታያል። በኢጣልያ ከሁለተኛው የንለም ጦርነት በኋላ 41 ግለ-ታሪኮች የተፃፈለት ሰው ቢኖር ቀዳሚው ሰልቫቶሬ ጁሊያኖ ነው።

ስለ ሰልቫቶሬ ጁሊያኖ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን ፊልምም ተሰርቷል። የፍራንቼስኮ ሮሲ - ሰልቫቶሬ ጁሊያኖ የሚለው የ1961 ፊልም ወንበዴው ከሞተ ከአንድ አሥርተ-ዓመት በኋላ ቀርቧል። የጁሊያኖ ፊልም የተሠራው ሞንቴሊብሬ በተባለው ተራራማ ሥፍራ ሲሆን የወንበዴውን ትክክለኛ ጠመንጃ ነበር የፊልሙ አዘጋጅ የተጠቀመው። ይህ ሁሉ የተደረገው ፊልሙ ከእውነታው ጋር ተቀናጅቶ እንዲቀርብ የተከፈለ ድካም ነበር። የጁሊያኖ እውነተኛ ውንብድና ያረፈው በፊልሙ ውስጥ ባለው አለባበሱ ሳይሆን ወንበዴው ከገበሬዎች፣ ከፖሊስ፣ ከጦሩ፣ ከፖለቲከኞችና ከሚዲያው ጋር ባለ ግንኙነት ነው ሲል አዘጋጁ ሮሲ ያሳስባል። ከሁሉም ግን የመቼቱ ማዕከል ማፊያ ነው።

???

ሳልቫቶሬ ጁሊያኖ የቤተሰቦቹ አራተኛ ልጅ ሲሆን የተራራማዋ አካባቢ ሞንቴሊብ ሰው ነው። ሥፍራዋ ከፓርሌሞ አሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ትርቃለች። ወጣት ሆኖ የአሜሪካ የሆነውን ነገር ሁሉ አምላኪ ነበር። የፖለቲካ አመለካከቱም እንደዚያው።

የጁሊያኖ የሩኖነት ዘመን የተጀመረው የተባበሩት ጦር ኃይሎች ጣልያንን ከያዙ በኋላ ነው። 21 ዓመት ሲሞላው የአንድ ኤሌክትሪክ ኃይል ኩባንያ ዕቃ ተላላኪ የነበረ ሲሆን በወቅቱ ወታደር ፖሊሶች የጥቁር ገበያ እህል ተሸክሞ ያዙት። ዋዘኛ አልነበረምና የያዘውን ወታደራዊ ፖሊስ ገድሎ ወደ ተራራው አፈተለከ።

ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ በታጠቀው መትረየስ ብዙ ለዎችን ፈጀ። ብዙ የቤተሰቡ አባላት ደብቃችሁታል ተብለው ታሰሩ። 1944 በእስ

እርዳታ እስረኞቹ የሞንሪያሊን እሥር ቤት ሰብረው ወጡ። ከዚህ በኋላ የመጀመሪያው የጁሊያኖን የፋኖ ቡድን አስኳል ተመሠረተ።

በሚቀጥሉት ዓመታት ጁሊያኖ ቡድኑን በተሻለ መንገድ ማዘጋጀት ነበረበት። የቡድኑ አባላት በጥቁር ገበያ፣ በስርቆት፣ በማገት ከተሰማሩ በኋላ የውንብድና ግዳጃቸውን ፈጽመው ሕብረተሰቡ ውስጥ ይዋሃዳሉ። ጁሊያኖ ራሱን እንደ ሮቢን ሁድ አዘጋጅቶ ለሕዝቡም አስተዋውቋል ማለት ይቻላል። በማስገደድ የሌሎችን ዝምታና ትብብር መግዛትም ተሳክቶለታል። አሳልፎ ሊሰጠው የተጠረጠረ ሁሉ ምህረት-የለሽ ቅጣት ስለሚከተለው የፋኖ ንጉሥነት ገጽታ እንዲላበስ አድርጎታል። በእጁ የጠፉ ሰዎች ብዛትም 430 ደርሰው እንደነበር ተረጋግጧል።

ጁሊያኖ ከማፊያ ጋር ያለው ግንኙነት የተዋጣለት መስመርን የተከተለ ነው። ከማፊያ የክብር ሰዎች ከለላን ባያገኝ ኖሮ በሲሲሊ እንዲያ ሆኖ ሊቆይ ባልቻለ ነበር። አንድን ሰው ጁሊያኖ ካገተ የታገተው ሰው እንዲለቀቅ ዘመዶቹ ድርጎ የሚከፍሉት በአካባቢው የማፊያ አለቃ በኩል ብቻ እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ። በሌላ አነጋገር ማፊያ ከወንበዴውም፣ ከታጋች ዘመዶችም በሁለት መንገድ ታክስ ይሰበስባል ማለት ነው።

አንድ የቅርብ ተባባሪ ጁሊያኖ በማፊያ አባልነት መያዙን አጋልጧል። የማፊያ ዋና አለቃ የነበረው ቶማሶ ቡስኬታም ይህንኑ አረጋግጧል። ይህን ወንበዴ ማፊያ በአባልነት ለመያዝ የፈለገው ታዛዥነቱን ይበልጥ ለማግኘትና እንቅስቃሴውን በቅርበት ለመከላከል እንዲያመቸው ነው።

ይህን የመጨረሻው ፋኖ ከሌሎች ቀደምት ፋኖዎች የሚለየው በፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም ውስጥ መሳተፉ ነው። ለፖለቲካቸው ሲሉ በመጀመሪያ የመለመሉት ተገንጣዮቹ ቡድኖች ነበሩ። በ1945 ፀደይ ወራት ጁሊያኖ ከተገንጣዮች መሪና በAMGOT ጊዜ የፓርሌሞ ከንቲባ ከነበረው ታስን ቦርዶናኖ ጋር ተገኝቷል። ወንበዴውም ከታሰበው የተገንጣይ ቡድኑ ሠራዊት ጋር እንዲቀላቀል ከፈለጉ 10 ሚሊዮን ሊሬ እንዲከፍሉት ጠየቃቸው። በኋላ ግን ጥያቄው ወደ 1 ሚሊዮን ሊሬ

ወርዶ ተገንጣይ ጦሩን ተቀላቀለ። የተገንጣዮችን ዓላማ ለማስፈፀም አምስት የወታደራዊ ፖሊስ ካምፖችን አጥቅቷል፣ የፓርሌሞ ትራፓኒ ባቡርንም አግቷል። ምንም እንኳን የጁሊያኖ ጥረት ከፍተኛ ቢሆንም የተገንጣይ ቡድኑ እንቅስቃሴ ተደፍጥጧል።

የተገንጣይ ቡድኖቹ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መክሰም ጁሊያኖንም የፖለቲካ ድንክዬ አድርጎታል። በተለይ መንግሥት የወሰደው ወታደራዊ ርምጃ አደገኛ ነበር። በዚህ ወታደራዊ ሂደት ውስጥ ደግሞ እንደተለመደው ማፊያ ቀሳጢ እጁን ከተተ። ይህም በመሆኑ ማፊያና ፖሊስ እየተባበሩ ወንበዴዎቹን ለቀሟቸው። እንዲያውም አንዳንድ የወንበዴ መሪዎች በማን እንደተገደሉ ሳይታወቅ በየቦታው ይጣሉ ነበር። ባጠቃላይ በምዕራባዊ ሲሲሊ ማፊያ መረጋጋትን ለመፍጠር ራሱን እንደ ኃይል አሰለፈ።

ጁሊያኖ ሌላ ስልት ቀየሰ። አዲስ የፖለቲካ ጓደኞችን ለማፍራት ፈለገ። መሣሪያውን በኮሚኒስቶች ላይ ለማዞር ወሰነ። በአንድ አሜሪካዊ ጋዜጠኛ በኩል ለፕሬዚዳንት ትሩማን የኮሚኒስቶችን አደጋ ለመጋፈጥ መነሳቱን አረጋገጠላቸው። በ1947 የተካሄደው ምርጫ ለጁሊያኖና ለሌሎች አስደንጋጭ ሆነ። በሕዝባዊ ምድብ የተሰለፉ የግራ ኃይሎች 30 በመቶ ድምፅ አግኝተው ጠንካራ የፖለቲካ ኃይል መሆናቸውን አስመሰከሩ። ይህ ነበር እንግዲህ ለመጨረሻው ወንበዴ «ለሞንተሊብሬው ንጉሥ» አሠቃቂውን ወንጀል ለመፈፀም ያነሳሳው።

የሰልቫቶሬ ጁሊያኖ ሥም ይበልጥ የተሳሰረው ፓርቴላ ዴላ ጂኔስትራ ከሚባለው ሥፍራ ጋር ነው። በዚህ ሥፍራ ነበር የአካባቢው ገበሬዎች የዓለም ሠራተኞች ቀንን /ሜይ ዴይ/ ለማክበር የተሰባሰቡት። ሁሉም ገበሬዎች የክት ልብሳቸውን ለብሰው፤ እየደነሱ፤ እየዘፈኑና ያሸበረቁ ጋሪዎቻቸውን እየነዱ በተለያዩ ባነሮች ደምቀው ወደ ሥፍራው ተጓዙ።

ልክ አራት ሰዓት ከሩብ ላይ የሕዝባዊ ምድቡ ፀሐፊ የተሰቀሉ ቀያይ ባንዲራዎች መካከል ቆሞ የመክፈቻ ንግግር ለማድረግ ሲነሳ ያልተጠበቀ ሁኔታና ፍንዳታ ተፈጠረ። በመጀመሪያ ለክብረ በዓሉ ሲባል የተተኮሰ ርችት ነበር የመሰላቸው። ዳሩ ግን እንዲያ አልነበረም።

በወንበዴው ጁሊያኖ ቡድን የተተኮሰው ጥይት ጊላማውን ማግኘት ጀመረ። ከአካባቢው ጉብታዎች ላይ የተተኮሰው መትረየስ አሥራ አንድ ሰዎችን ረፈረፈ፤ ከሚቆቹም መሐከል ወላጆቻቸውን ተከትለው የሄዱ እምቦቃቅላ ህፃናት በብዛት ይገኙበታል። ሰላሳ ሦስት ሰዎች ቆሰሉ። የዕለቱ የበዓል አከባበር በዚህ ዓይነት አሰቃቂ ድራማ ተጠናቀቀ።

በ1961 የፊልም አዘጋጁ ፍራንቼስኮ ሮሲ በሥፍራው ላይ ለመቼቱ እንዲመች 1000 ገበሬዎችን ለፊልሙ ሥራ አሳተፈ። የማስመሰያ የመትረየስ ተኩስ ሲከፈት ከገበሬዎቹ አእምሮ የዕልቂቱ ሁኔታ አልጠፋ ኖሮ እውር ድንብራቸው ጠፍቶ እግሬ አውጪኝ ተከሰተ። ሴቶች እያለቀሱና እየተንቀጠቀጡ ወደቁ። አንዲት ሴት እያነባች ልጆቼ የት ደረሱ? እያለች ትጮህ ነበር። ታዲያ የዚች ሴት ሁለት ልጆች በጁሊያኖ እጅ በሜይ ዴይ በዓል ላይ የተገደሉባት መሆኗ ታውቋል።

???

በፓርቴላ ዴላ ጂኔስትራ በደረሰው ጭፍጨፋ ሕዝባዊ ተቃውሞ ቢከተልም የሞንቴሌብሬው ንጉሥ ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ውንብድናውን ቀጥሏል። ከጭፍጨፋው በኂላ የሲሲሊም የፖለቲካ ገፅታ እየጠነከረ ሄዶ ክርስቲያን ዴሞክራቶች የበላይነታቸውን ተቀዳጁ። የዚህ የፖለቲካ ሁኔታ መፈጠር ነው የጁሊያኖንም ድርጊት አውሬአዊና ሥርዓተ አልበኛ ተደርጎ እንዲታይ ያደረገው።

ጁሊያኖ በፋኖነቱ በአካባቢው እየተዘዋወረ በገበሬ ተቋማትና ግንባር ቀደም መሪዎች ላይ ጥቃት ማድረሱን ቢቀጥልም የቡድኑ አባላት ቀስ በቀስ በመንግሥት እጅ እየወደቁ ሄዱ። ይህም የሆነው ከማፊያ በሚገኝ መረጃ መሠረት ነው። በ1948 በጋ ወቅት ጁሊያኖ ያልተጠበቀ ድርጊት ፈፀመ። «ሳያሽ የበላ ዝንጀሮ ሲስል...» እንዲሉ አምስት የማፊያ አባላትንና የፓርቲኮን ከተማ የማፊያ አለቃ ገደላቸው። ምክንያቱ በግልጽ የታወቀ ባይሆንም የጁሊያኖ መጨረሻ መቃረቡን አረጋገጠ። ዳሩ ግን ከዓመትም በኂላ አቅሙ የተጠበቀ በመሆኑ ተጨማሪ ስድስት ወታደራዊ ፖሊሶችን በደፈጣ ገደላቸው።

በፓርቴላ ዴላ ጂኔስትራ በደረሰው ጭፍጨፋ በሕብረተሰቡ ዘንድ ብዙ አሉባልታዎች ተነዙ። አብዛኛው ግን ጣቱን የቀሰረው በሀገር ውስጥ

የደህንነት ሚኒስቴር ላይ ነበር። ምክንያቱም ጁሊያኖን ይህን ድርጊት እንዲፈፅም በስውር አሰማርተውታል በሚል። ራሱም በዓፊው ግልፅ ደብዳቤ ድርጊቱን መፈጸሙን አምኖ ገዳይ አባሎቹ እንዲያስደነግጡ እንጂ እንዲገድሉ አላዘዝኩም ሲል ስህተቱን ተቀበለ። ህፃናት ልጆች መገደላቸውም በስህተት መሆኑን አሳወቀ። ልቤ ድንጋይ መሰላችሁን? ሲልም ጠየቀ። በኋላ ላይ በተገኘው 800 ያህል የጥይት ቀለህ ክህደቱ ፍፁም ውሸት መሆኑን አስመሰከረ።

በ1950 የተያዙ የጁሊያኖ ቡድን አባላት በቪተርቦ ከተማ ፍ/ቤት ቀርበው ጥያቄ በመመለስ ላይ ሳሉ ጁሊያኖ ከመሸገበት ተራራ አጠገብ በአንድ በካስቴሎቬተራኖ አጥር ጊቢ ውስጥ አስክሬኑ ተጥሎ ተገኘ። በማንና እንዴት እንደተገደለ ግልጽ ባይሆንም ረዥም ጊዜ በፊጀ ውጊያ እንደተግላገሉት ወታደራዊ ፖሊሶቹ ገለፁ። በገበሬዎች ላይ የደረሰው ጭፍጨፋም በማንም ባለሥልጣን ትዕዛዝ እንዳልተሰጠ ፍ/ቤቱ አረጋግጦ ፋይሉን ዘጋ።

ጉዳዩን ከኋላ የሚያጠኑ ጠበብት (Behindologist) የሚከተለውን መላምት ለማቅረብ ተገደዋል፦

- የፓርቴላ ዴላ ጀንስትራ እልቂት ከመፈፀሙ በፊት ጁሊያኖ አንድ ደብዳቤ ደርሶት እንደነበር ብዙ ዕማኞች ያስታውሳሉ። ደብዳቤውን ካነበበ በኋላ በጥንቃቄ አውድሞት ለቡድኑ አባላት - «ልጆች.. የነፃነታችን ሰዓት በእጃችን ገብቷል» ካላቸው በኋላ የገበሬዎችን በዓል ለማጥቃት ተነሳ። ዳሩ ግን ደብዳቤው ከየት እንደተላከ ማንም አላወቀም።
- ከፓርቴላ ዴላ ጄኔስትራ እልቂት በኋላ የሲሲሊ የፖሊስ አዛዥ የሞንሪያሌን የማፊያ ዋና አለቃ በሮማ ከተማ ቤቱ አግኝተውታል። እዚያም ለፓርሌሞ ፍ/ቤት ዋና አቃቤ-ህግ የሚሰጥ ጁሊያኖ የመሰከረበት ደብዳቤ አስይዘው ልከውታል። የማፊያ አለቃው ከጁሊያኖ ጋር ግንኙነት ያለው ሲሆን ጁሊያኖ የመሰከረበት ደብዳቤ ግን አልተገኘም።
- ከላይ የተገለፀው የፖሊስ አዛዥ በተለመደው የማፊያ የግንኙነት መስመር በኩል ደብዳቤ ይላላክ ነበር። አንድ ጊዜ

ከወንበዴዎች መሪ ጋር ተገናኝቶ ፓኒቶኔ ኬክና የተለያዩ የአልኮል መጠጦችን ተካፍለዋል፡፡

የእልቂቱን ጉዳይ በሚመለከት ዕውነታውን ፍንትው አርጎ ሊገልፅ የሚችለው የጁሊያኖ የወንድም ልጅ የሆነው ጋስፓሬ ፒሾታ ነው፡፡ ይህ ሰው ነው ጁሊያኖን ከዶ የገደለው፡፡ ይህ ሰው የወንበዴዎች አባል ሆኖ ሲሰራ ከወታደራዊ ፖሊስ አዛዡ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ነበረው፡፡ በሳንባ በሽታ ተጎድቶ በነበረ ጊዜ በአንድ የፖሊስ መኮንን አጃቢነት ዶክተር ዘንድ ለህክምና ቀርቦ እንደነበረ ይታወሳል፡፡ በቪተርቦው ፍርድ ቤት ቀርቦ ፒሾታ እንደተናገረው - «እኛ አንድ አካል ነን፤ ወንበዴ፣ ፖሊስና ማፊያ - ልክ እንደ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ» ሲል አረጋግጧል፡፡

የካቲት 1954፡፡ ፒሾታ በእሥር ቤቱ ውስጥ ፊንጃል ቡና አዘጋጀ፡፡ ለሳንባ በሽታው የተሰጠውን ክኒን ከቡናው ጋር አማሰለ፡፡ ወዲያው ሰውነቱ ተመርዞ ሞተ፡፡ ኪኒኑን ለውጦ የመረዘው ግን ማፊያ ነበር፡፡ ፒሾታ በፓርሊሞ እሥር ቤት በማፊያ የወንጀል ዩኒቨርስቲ ተንኮል እስከ ወዲያኛው አሸለበ፡፡ ማፊያ በፓርቴላ ዴላ ጄኔስትራ እልቂትና በጁሊያኖ የውንብድና ቡድን የተንኮል ድርጊት ውስጥ ነበረበት፡፡ ፒሾታ እንዲመረዝ የተደረገውም ዕውነታው እስከ ወዲያኛው እንዳይወጣ በማፊያ የተቀመመ ዘዴ ነበር፡፡

# 11

# ቶማሶ ቡስኬታ፣ የኮንክሪት ፖለቲካና

## የኮዛ ኖስትራ ሴራ (1950-1963)

### የቶማሶ ቡስኬታ የቀድሞ ሕይወት

ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ነበር የሲሲሊ ማፊያ «ኮዛ ኖስትራ» «የእኛ ነገር» ሲል ራሱን መጥራት የጀመረው። አብዛኛዎቹ የማፊያ የቅርብ ጊዜ ስሞች ከአሜሪካ የገቡ ናቸው ማለት ይቻላል።

«ኮዛ ኖስትራ» የሚለው ቃል ከየት እንደመጣ ለማወቅ እንኳ ማፊያ ቃል-ጉባኤ የሌለው ስለሆነ ከዚህ ነው ብሎ መናገር አይቻልም። በተለያዩ ጊዜያት የተነሱት ስሞች ማለትም «ወንድማማቾች»፣ የክብር ማሕበረሰብ ወዘተ. በኋላም «ኮዛ ኖስትራ» ተብሎ መለወጡ በማፊያ መዋቅርና የአሠራር ዘዴ ላይ ለውጥ አሳይቷል ማለት ግን አይደለም።

ማፊያው ቶማሶ ቡስኬታ እንደሚለው «የኮዛ ኖስትራ ስያሜ ጥንታዊ ነው።» በእርግጥ ትክክል ስለመሆኑ ምንም ማረጋገጫ የለም። ምናልባትም ቡስኬታ የማይታመን የታሪክ ሰው ሊሆን ይችላል። ዳሩ ግን ቡስኬታ ከግማሽ ምዕተ ዓመት ወደኋላ ሄዶ መልካም ምስክር የሚሆን ሰው ነው። ቡስኬታ በማፊያ ታሪክ ውስጥ በተዋናይነት የገባው ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ከ1945 - 1963 ባለው ጊዜ ሲሆን እንደ ሌሎች ዋና ማፊያዎች ወደ ውጭ ሀገር ከተሰደደ በኋላ ነው። እንደ ዋና እማኝ ሆኖ የኮዛ ኖስትራን ዕድገት ለመመልከት ችሏል። ከ1950 እና በ1960 መሃል አዲስ የአስተዳደር ኮሚሽን (Cupola) በመመስረት ከአሜሪካው ኮዛ ኖስትራ ጋር የዕፅ ዝውውር ንግድ እንዲጀመር ተደረገ። በእነዚህ ዓመታት ነበረ ኮዛ ኖስትራ አዲስ የገቢ ምንጭ ያገኘውና ራሱን «ከኮንክሪት ፖለቲካ» ጋር ያስተሳሰረው።

ቶማሶ ቡስኬታ 1950ዎቹን «የኮዛ ኖስትራ» መልካም ጊዜያት ሲል ያንቆላጽሰዋል፡፡ ምክንያቱም ከስግብግብነትና ከብጥብጥ ውጭ መከባበርና ክብር ሚዛን ደፍቶ የቆየበት ጊዜ ስለነበረ ነው በማለት፡፡ ቡስኬታ ከሲሲሊ ርቆ መልካም ጊዜን ያሳለፈው በውጭ በመሆኑ እሱ እንደ አንድ ጉበዝ ወንድና የማፊያ ሰው ሆኖ እንዴት እንደኖረ ማየት ጠቃሚ ነው፡፡

ቶማሶ ቡስኬታ ከሴቶች ጋር ያለው የውስለታ ግኑኝነት ብዙ ይታወቃል፡፡ ለዳኛ ጆቫኒ ፋልኮኔም ስለ ኮዛ ኖስትራ መመሪያዎች በመናዘዝ በኩልም የመጀመሪያው ሰው ነው ቡስኬታ፡፡ ይህ ማፊያ እውነተኛ ወሲበኛና የሜዲትራኒያን ወንድ ሲሆን ደልዳላ ሰውነት፣ ምጥን ከንፈር፣ ክብና ሀዘንተኛ ዓይን ያለው ተዋናይ መሰል ሰው ነው፡፡

በ1986፣ የጣልያን ዕውቅ ጋዜጠኛና የቴሌቪዥን ፕሮግራም አቅራቢ ኤንዞ ቢያጂ ይህን የማፊያ አለቃን ኢንተርቪው ለማድረግ ወደ አሜሪካ ተጓዘ፡፡ ከዚያም በተጠበቀ ምቹ ሥፍራ ከቡስኬታ ጋር ብዙ ቀናትን አሳለፈ፡፡ ስለቤተሰብና ስለ እግር-ኳስ (ቡስኬታ የጁቬንቱስ ክለብ ደጋፊ ነው) በማውራት የቡስኬታን እምነት አገኘ፡፡ «የሁለት ዓለም አለቃ» የሆነውን፣ ነፍሰ-ገዳዩንና የማፊያን ሚስጢር አፍኖ የያዘውን ቡስኬታን እንዲህ ሲል አንድ ጥያቄ ወረወረበት «ለመሆኑ ፍቅር የሠራህበትን የመጀመሪያ ጊዜ ታስታውሳለህ?»

ቡስኬታም በተራው ደስተኛ ነበር - ለቢያጂ መልስ ለመስጠት እንዲህም አለ «እናት ተፈጥሮ መልካም ተክለ-ሰውነት አድላኛለች፤ አንድ የተለየ ተጨማሪ ነገር አለኝ» ሲል ፎለለ፡፡

በመሠረቱ ቶማሶ ቡስኬታ ድንግልናውን ያጣው ፊፅሞ በማይታሰብ ጊዜ ገና የስምንት ዓመት ጨቅላ ሆኖ ነበር፡፡ ያኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአንዲት ሴተኛ አዳሪ ጋር ግብረ-ስጋ ግኑኝነት ፈፀመ፡፡ እሱ ደግሞ በወቅቱ የመንገድ ዳር የወይራ ፍሬ፣ ቅቤና እሶች አዟሪ ሆኖ ይሠራ ነበር፡፡ ሴተኛ አዳሪዋ አንድ ጠርሙስ የወይራ ዘይት ነበር ከቡስኬታ የሚሠጣት ክፍያ፡፡ ከዚያ በኋላ ፍቅር በቡስኬታ ሕይወት ከፍተኛ ሥፍራን ያዘ፡፡ እጅግ ቁጥር ሥፍር ከሌለው ውስልትና በተጨማሪ ሶስት ጋብቻዎችን ፈፅሟል፤ የመጨረሻው ጋብቻ ከእሱ በ22 ዓመት ዕድሜ ከምታንሰው ብራዚላዊት ጋር ነበር ያደረገው፡፡ በአጠቃላይ ቡስኬታ ስድስት ልጆችን አፍርቷል፡፡

የቡስኬታ የጋብቻ ሁኔታ በኮዛ ኖስትራ ውስጥ ራሱን የቻለ ችግር ፈጥሮበታል። በ1950ዎቹ በውስልትናው ምክንያት ለስድስት ወራት ከድርጅቱ እንዲታገድ ተፈርዶበታል። በ1972 ከብራዚል እንዲጋዝ ተደርጎ በፓሌርሞ ኡሲያርዶን እሥር ቤት ተወርውሯል።

ቡስኬታ በምሥራቃዊው የፓሌርሞ ዳርቻ በ1928 ከማፊያ ጋር ግኑኝነት ካለው ቤተሰብ ተወለደ። ከቤተሰቡ ከተወለዱት አሥራ ሰባት ልጆች ውስጥ የመጨረሻው ልጅ ነበር። በሕይወት ውስጥ ምንም ልዩ አማራጭ ስላልነበረው ወደ ወንጀል የሚሠማራም ሰው አልነበረም። አባቱ የጌጣጌጥ መስታወቶች መሥሪያ ወርሻ (Workshop) ያለው ሲሆን በስሩም አሥራ አምስት ሠራተኞችን ያስተዳድራል። በኋላ ግን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ምክንያት እንደማናቸውም የሲሲሊ ቤተሰብ መራር ጊዜን አሳለፈ። ገና በኮበሌነቱ የጥቁር ገበያ ቸርቻሪ ሆነ። ነዳጅ፣ ማርማላት፣ ቅቤ፣ ዳቦና በቅመም የታሸ የአሳማ ሥጋ (Salame) ከጀርመኖች እየሰረቀ ይሸጣል። የፓሌርሞን ድብቅ ሥራዎች ሁሉ ተለማመደ። የተባበሩት ኃይላት ወታደሮች ሲሲሊን ነፃ እንዳወጡ ቡስኬታ አንድ ሃምሳ የሚሆኑ ወጣቶችን ተቀላቅሎ ናዚዎችን ለመዋጋት ወደ ኔፕልስ አቀና። ወደዚያም ሲሄድ በሁለት ልብ ነበር። አንድም በወጣት ጀብደኝነትና ሌላም ለዘረፋ። ከሁለትና ሶስት ወራት በኋላ ደፈጣና ሻጥር በናዚዎች ላይ ከከወነ በኋላ አንገቱን አንቅቶ ወደ እናት ምድሩ ሲሲሊ ተመለሰ። በዚያን ጊዜ ነበር ድብቅና ጠንቃቃ ከሆኑ ሰዎች ጋር የተገናኘው። እነዚህ ሰዎች ተከታትለው ያጠኑት እንደነበር ቡስኬታ አስተውሏል። በተለይ አንዱ የቤት ዕቃዎች ሠራተኛ የሆነው ስለቤተሰብ ሞራላዊነት፣ ለፖሊስና ለሕቃቤ ሕጐች ስላለው አመለካከትና ለጓደኛ ስላለው ታማኝነትን በሚመለከት በሚገባ ሰልሎታል።

ይህ ሰው፣ ጆቫኒ አንድሮኔኮ ሲባል ቡስኬታ በ1945 «የፓርታ ኖቫ (Porta Nuova) የኮዛ ኖስትራ ቤተሰብ» አባል እንዲሆን ለማፊያ ካፖ ሀሳብ አቀረበ። በዚህ ጊዜ ካፖው ደግሞ ለሁሉም የፓሌርሞ አካባቢ የማፊያ ቤተሰቦች ስሙን በማስተላለፍ የራሳቸውን ተጨማሪ ማጣራት እንዲያደርጉ አዘዘ። በዚህ ረገድ አንድ ለማፊያ ሊመለመል የተፈለገ አባል ከፖሊስ ጋር ያለው ግኑኝነት በሚገባ እንዲጣራ ይደረጋል። ማጣራቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በአባልነት አቀባበል ሥነ-ሥርዓት ላይ የቡስኬታን ጣት የበጣውና ደም እንዲፈስው ያደረገው ጠቃሚው አንድሮኒኮ ነበር።

ቡስኬታ የተቀላቀለው የፓርታ ኖቫ የማፊያ ቤተሰብ አባላት ቁጥር ከ25 የማይበልጡ ቢሆንም ምርጥ ማፊያዎች ነበሩ። ከአባላቱ መካከል አራት ዕውቅ ሰዎች ይገኙበታል። እነሱም የሲሲሊ የቢራ የሽያጭ ኃላፊ፣ የፓርላማ አባል፣ አማካሪ ሳይካትሪስትና ሲሲሊ እንድትገነጠል ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረገው አንድሪያ ፊኖኪያሮ አፕሪሌ።

በ1947 ከቡስኬታ ጋር የተዋወቀው ዕውቅ ሰው የመጨረሻው ወንበዴ የነበረው ሳልቫቶሬ ጁሊያኖ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ቡስኬታ እንደ ጄንኮ ሩሶ አይነት ሌሎች ዕውቅ የማፊያ አለቆችን በመገናኘት ተወያይቷል።

በኋላም ቡስኬታ ወደ ውጭ ሀገራት መጓዝ ጀመረ። ከ1949 እስከ 1952 በአርጀንቲናና በቢራዚል ኖረ። በ1956 እንደገና ከአርጀንቲና ቆይታው በመመለስ የሲጋራ ሥውር ንግድ ውስጥ ለመሠማራት ፕላን አወጣ። ያኔ ወደ ፓሌርሞ በተመለሰ ጊዜ አዲስ የማፊያ ሕይወትን ተቀላቀለ። ይህ አዲስ ሕይወት ደግሞ «በኮንክሪት ፖለቲካ» ውስጥ በመግባት በተደራጀ ወንጀልና ከፖለቲካ ሥልጣን ጋር የፈጠረው ልዩ ሴራ ነው ማለት ይቻላል።

## የፓሌርሞ መፈራረስና የፓርቲ ፖለቲካ ሻጥር

«የፓሌርሞ መፈራረስ» የተባለው ጊዜ በ1950ዎቹ የህንፃዎች ግንባታ ዕድገት በፓሌርሞ ነዋሪዎቹን እጅግ ያመሰበት ወቅት እንደነበር ይታወሳል። ነዋሪዎቹ ያደረባቸውን ሀዘን ለመረዳት የፓሌርሞን ዋና መንገዶች ከኩአትሮ ካንቲ ጀምሮ የባሮክ አገነባብ የነበረባቸውን ቤቶች መመልከት ብቻ ይበቃል። በሊበርታ፣ በጂያርዲኖ ኢንግሊዜና በሌሎች ጐዳናዎች እየተመላለሱ በመመልከት የከተማው ጥንታዊ ገፅታ ፈርሶ መለወጡን በሚገባ መረዳት ይቻላል። እንግዲህ እነዚያ ቅርስ የነበሩ ቤቶችና ቪላዎች መፈራረስ «የፓሌርሞ መፈራረስ» የተባለውን ታሪክ ፈጠረ። ከፓሌርሞ መፈራረስ ጋር «የኮንክሪት ፖለቲካ» የዘረፋ ጥርሱን ሞርዶና ድር ፈጥሮ ተንሰራፋ።

«የፓሌርሞ መፈራረስ» ታሪክ ከቤቶች ግንባታ ይልቅ ዋና ይዘቱ ፖለቲካዊ ነበር። ኢጣልያኖች ማፊያ «ከሮማ ነው የሚመራው» ብለው የሚተቹትን ጥርጣሬ አልባ ዕውነታን ይፈጥራል። ፖለቲከኞች፣ ኮንትራክተሮችና ማፊያዎች ለፓሌርሞ መፈራረስ የተያያዘ ሻጥር

እንዳለበትና ከሮማ የዴሞክራሲያ ክሪስቲና የፒያሳ ዴል ጄሱ ህንፃ ውስጥ ካለው አመራር ጋር መያያዙ የግድ ነው። ከዚህ ህንፃ ውስጥ ነው አዲሱ የዴሞክራሲያዊ ዘመን ሥራዎች የመነጩት።

የመጀመሪያ የዚህ ሻጥር ሰንሰለት የሚጀምረው ከቱስካኒው የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር አሚንቶሬ ፋንፋኒ ነው። የክርስቲያን ዴሞክራሲ ፓርቲ (DC) በ1954 መሪ እንደሆነ ሥልጣኑን ሁሉ በእጁ አስገባ። ከዚያም የውጭ የፖለቲካ ሥልጣን ያላቸውና እንደ ቫቲካንና የኢጣልያ ኢንዱስትሪ ውስጥ የተሰማሩ ባለሀብቶች ላይ ተፅዕኖ ማሳደር ጀመረ። ከእነዚህ ውጪያዊ ኃይሎች ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ፓርቲውን ዘመናዊ ሕዝባዊ ድርጅት ለማድረግ ያለመ ነበር።

በሲሲሊና በአብዛኛዎቹ ደቡባዊ ጣልያን ግዛቶች «የፋንፋኒ አብዮት» ሁለት ጉዳዮችን የያዘ ነው። አንደኛው፣ አዲስ የፖለቲካ ካድሬዎች በፓርቲው ውስጥ መፍላትና፣ ሁለተኛው እነዚሁ ሰዎች በአካባቢም ሆነ በብሔራዊ ደረጃ በመንግሥትና በተወረሱ ኩባንያዎች ውስጥ ወሳኝ ሥልጣን ማስያዝን ያካትታል።

እነዚህ አዳዲስ የፖለቲካ ካድሬዎች የፋንፋኒን ፕሮግራም በተለይም በሲሲሊ ደሴት ላይ ለማስፈፀም ወሳኝ ሰነዶች ነበሩ። በዚህ ሰንሰለት ውስጥ ደግሞ ሮምን ከፓሌርሞ ጋር የሚያገናኘው ሰው ጆቫኒ ጆያ ነው። ጆያ ምንም እንኳ የፖለቲካ ሥልጣን ያለው ሰው ባይሆንም በከተማዋ ታሪክ ውስጥ ሁነኛ ሥፍራ ነበረው። የውስጥ አዋቂዎች «ገዢው» እያሉ ሲጠሩት የከተማዋ ከንቲባ ማን መሆን እንዳለበት የመወሰን ሥልጣን ያለው ነው ሲሉ ሁነኛ ሥፍራ ይሰጡታል። በ1954፣ በ28 ዓመት ዕድሜው የፓሌርሞ ክፍለ ሀገር የፓርቲው ፀሐፊ ሆነ። ጆያና ሌሎች ተከታዮቹ ከዚያ በኋላ ለሩብ ምዕተ ዓመት የድርጅቱን ፅ/ቤት ተቆጣጠሩት። ከዚህ ቁልፍ ቦታ በመሆን ነው ጆያ የሲሲሊን የፖለቲካ ማሽን ማንቀሳቀስ የጀመረው።

በፋንፋኒ የለውጥ አሠራር የአካባቢ የክርስቲያን ዴሞክራት ፓርቲ ቅርንጫፎች በመላዋ ኢጣልያ ተከፈቱ፤ በፓሌርሞ ብቻ ቁጥራቸው 59 ደርሶ ነበር። ዋና የፓርቲው ዓላማ ወደ ማህበረሰቡ ለመቅረብና ከማህበረሰቡ ውስጥ አባላትን ለመመልመል መስመር ለመዘርጋት ያለመ ነው። የፋንፋኒ ተከታዮች «የማካሮኒ ፖለቲካ ያብቃ!» የሚል መሪ መፈክር በማውጣት ድምፅ ለመግዛት ጣሩ። የተፈጠረው ፖለቲካን

የማዘመን ሂደት ግልፅና ተራ አቀራረብ ያለው ነው። ይኸውም የአባልነት ካርድ የያዙ አባሏት የፓርቲውን መሪዎች ይመርጣሉ። አባላቱ ደግሞ የምርጫ ዕጩዎችን የሚመርጡ ተወካዮችን እንዲመርጡ ይደረጋል። ይህ እንግዲህ በንድፈ-ሃሳብ ደረጃ የተቀመጠ ሲሆን በተግባር ግን በፓሌርሞ ባለው ሁኔታ ሥልጣን የተያዘው በአባላት ሳይሆን በጆያ እጅ ነው። ጆያ በፓርቲው ፅ/ቤት ፈላጭ ቆራጭ በነበረበት ጊዜ የፓርቲ አባልነት የሚሰጠው ለጓደኛ፣ ለዘመድ አዝማድ፣ በሕይወት ለሌሉ ሰዎችና ከስልክ መዝገብ ላይ ለተወሰዱ ስሞች ነበር። አንድ የአካባቢ ፓርቲ ብዙ አባላት ካለው ብዙ ተወካዮችን ለፓርቲው ኮንፈረንስ ይልካል። በሌላ አነጋገር ጆያ ብዙ አባላትን በመሰብሰብ ሰበብ ለፋንፋኒ ከፍተኛ ድጋፍ በማድረግ ሥልጣን በእጁ እንዲገባ ለማድረግ ያስችለዋል። ስለዚህ የአባላት ብዛት በሲሲሊ መጨመር የሲሲሊው ፓርቲና ፋንፋኒ በፓርቲው ውስጥ ተፅዕኖ እንዲኖራቸው አደረገ። ለዚህም ይህ የአንድ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር የነበረ ሰው በጠቅላይ ሚኒስትርነት ስድስት ጊዜ እንዲያገለግል መንገድ ከፈተለት።

«ገዥው» በሚል ቅፅል ስም የሚጠራው ጆያ የፓርቲ ስልጣኑን በእጁ ካስገባ በኋላ ሥራ፣ ፈቃድ፣ ድጋፍና ሌሎች ጠቃሚ ንብረቶችን አብረውት ለሚሞዳመዱት ማከፋፈሉን ተያያዘው። የፓሌርሞ መፈራረስ መጀመር ሁለት ዋና ወንጀለኞችን ፈጠረ፤ እነሱም ቪቶ ሲያንሲ ሚኖና ሳልቮ ሊማ ናቸው። ሁለቱም የፓሌርሞ ከተማ ም/ቤት አባላት ሆነው በ1956 ሲመረጡ፣ ሁለቱም የጆያ ጋሻ ጃግሬዎች ነበሩ። እነዚህ ናቸው እንግዲህ የ«ማካሮኒ ፖለቲካን» ወደ «ኮንክሪት ፖለቲካ» የለወጡት።

ከ1959 እስከ 1963 የፓሌርሞ ከተማ የግንባታ ሥራዎች በተሟሟቁበትና ሊማና ሲያንሲሚኖ በከተማ ሥራና ልማት መ/ቤት ውስጥ በሚሰሩበት ጊዜ የከተማው ም/ቤት ከ4205 ኮንትራቶች ውስጥ 80 በመቶውን ለአምስት ሰዎች ብቻ ሰጠ። ስለዚህ የከተማዋ ሀብት በእነዚህ አምስት ሰዎች መዳፍ እጅ ወደቀ።

ምንም እንኳ ሕጉ ኮንትራት የሚሰጠው አካል «ችሎታ ያለው ኮንትራክተር መሆን አለበት» ቢልም ሊማና ሲያንሲ ሚኖ ጨረታውን አሸንፈው ኮንትራክተሮች እንዲሆኑ ካደረጓቸው ሰዎች ውስጥ አንደኛው የድንጋይ ከሰል ነጋዴ ነበር። ሌሎቹ ደግሞ ዘበኛና ተራ የቧንቧ ሠራተኛ ሲሆኑ ኮንትራቱን እንዴት እንዳገኙ ሲጠየቁ ግን የሰጡት መልስ

አጭርና ግልፅ ነበር፡፡ «ከጓደኞቼ በሉል ነው ስምምነቱን የፈረምኩት» የሚል «የሌባ ዓይነ ደረቅ» መልስ ነበር የሰጡት፡፡

ይህ ከላይ የቀረበው ሁኔታ የሚያመለክተው ማፊያ ቀደም ሲል «የሎሚ ማሣ» አሠራርን በመለወጥ ወደ ግንባታ ማሣ ለማጭበርበር መግባቱን ነው፡፡ ማፊያ በከተማ ግንባታ ውስጥ የሚያካሂደው ዘረፋ በሙሰኞች መተሳሰር ላይ የተመሠረተ ሲሆን ግኑኝነቱ የአካባቢ ፖለቲከኞችን፣ የማዘጋጃ ቤት ሠራተኞችን፣ የህግ ሰዎችን፣ ፖሊሶችን፣ የግንባታ ኮንራክተሮችን፣ የባንክ ኃላፊዎችንና ነጋዴዎችን ያስተሳሰረ ወፍራም ድር ነው፡፡ ይህን ድር የሚያስተሳስሩት ማፊያዎች ደግሞ ጆያ፣ ሊማና ሲያንሲ ሚኖ ናቸው፡፡

ሲያንሲ ሚኖ ምንም እንኳ በግንባታ ሥራ ውስጥ ከፍተኛ የሙስኝነት ተግባርን ሲፈፅምና ሲያስፈፅም ቢቆይም ዘግይቶ በ1984 ለእስር ተዳረገ፡፡ ከዚያም በ1992 ለመጀመሪያ ጊዜ እንደሱ ባለ ለማፊያ በሚሠራ ፖለቲከኞች ላይ ፍርድ ተሰጠ፡፡ በዚያው ዓመት ሳልቮ ሊማ ከማፊያነት አባልነቱ ተቃጠለ፡፡ እቤቱ በራፍ ላይ በጥይት ተደብድቦ እስከ መጨረሻው አሸለበ፡፡ የማፊያ ሻጥር ግን በዕፅ ዝውውሩ ተጠናክሮ ወደፊት ቀጠለ፡፡

## ማፊያ፣ ዕፅና የጆ ባናናስ ለእረፍት መሄድ

እንደ ሁልጊዜው የማፊያ ጉዳይ በጣልያንና በመላው ዓለም ማህበረሰብ ዘንድ ጥያቄዎችን እየጫረ ነው፡፡ የደቡብ ኢጣልያ ሁኔታ እንዲህ ማጣፊያው አጥሮት ሕዝቡን ለሥጋት የዳረገው የማፊያ ሁሉ-ሥራ ከሥልጣንና ከገንዘብ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው፡፡

በፓርሌሞ የተካሄደው ከተማ የመገንባት ሥራ የተቆራኘው ከኢጣልያ የኢኮኖሚ «ተአምራት» ጋር ነበር፡፡ በ1950ዎቹ መጨረሻና በ1960ዎቹ መጀመሪያ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ራሱን ሀልቆ-መሣፍርት ወደሆነ የኢንዱስትሪ ምርት አሸጋገረ፡፡ ብዙ የገንዘብ ዝውውር በፖርቲው ታማኝ ካድሬዎች እጅ የገባ ሲሆን የገንዘቡም ፍሰት የሚወርደው ከጄኔዋ፣ ከቱሪንና ከሚላን የኢንዱስትሪ የሰሜን ከተሞች ነበር፡፡ ብዙዎቹ የግንባታ ኩባንያዎች በሰሜኖች በመያዛቸው የሰሜን ኢንዱስትሪዎች ሸቀጦቻቸውን የሚያራግፉባቸውን የደቡብ ከተሞች መፈለጋቸው አይቀሬ ሆነ፡፡ የገንዘብ ዝውውሩ መድራት ነዋሪዎች ሬዲዮ፣ ፍሪጅ፣ ሞተር

ብስክሌትና መኪናዎችን የመግዛት ገበያ እንዲደራ አደረገ። በፖለቲካው ጨዋታ ደግሞ የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲው ኮሚኒስቶችን ከጨዋታው ውጭ ለማድረግ ኳተነ። በዚህም የተነሳ ብዙዎች ጣልያኖች የቀኝ ክንፍ የፖለቲካ አራማጅ ጋዜጠኛ መርሆ የሆነውን «ብትጠየፈውም አፍንጫህን ይዘህ ለክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲ ድምፅ ስጥ!» የሚለውን መንገድ ተከትለው ነበር።

በእርግጥ በ1950ዎቹና 60ዎቹ የተከናወኑ ለውጦችን በሚመለከት ክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲው እገዛ የሚያገኘው ከቤተክርስቲያን ነበር። በዚህም ነው የፓርሌሞ ካርዲናል አርክቢሾፕ ኤርኔስቶ ሩፋኒና በሲሲሊ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የማፊያን የተደራጀ ወንጀልና የፖለቲካ ግጭት የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ በማለት ትኩረት የነፈጉት።

ሩፊኒ ከሰሜን ኢጣልያ ቢሆንም «ከጳጳሱ ቁሱ» እንዲሉ ከሲሲሊያውን በላይ ሲሲሊያዊ በመሆን ለደሴቲቱ ፍፁማዊ ፍቅርን አሳድሮ እንደነበር ይታወሳል። ሲሲሊያዊነትና ክርስቲያንነት፣ ሲሲሊያዊነትና አማኝ መሆን ፈፅሞ የማይነጣጠሉ ሆነዋል። ሰሜነኞቹ የኢጣልያ ነዋሪዎች ወደ ሀብትና ወደ ሥጋዊ ሕይወት ሲያመዝኑ ሲሲሊ ግን የእምነት ተምሳሌት በመያዝ ፀረ ማርክስ፣ ሆነው ቀጥለውበታል።

ካርዲናል አርኪቢሾፕ ሩፊኒ «ማፊያ» ኮሚኒስቶች የፈጠሩት የማስፈራሪያ ስልት እንጂ «ማፊያ የለም» እስከማለት ደረሰ። ያኔ የሰልቫቶሬ ጁሊያኖ ቡድን በመትረየስ የገበሬ ቤተሰቦችን ሲያጭድ ካርዲናሉ ለሮማው ጳጳስ «እንዲህ ዓይነቱ አመፅና ሽብር የኮሚኒስቶች መለያ ነው። ፀረ ኢጣልያና ፀረ ክርስቲያን ንድፈ-ሃሳባቸው የቆመው በሽብር ላይ ነው» ሲል የገለፀው። የ1953ቱ ብሔራዊ ምርጫ ከመደረጉ በፊት ቤተክርስቲያን እያንዳንዱ አማኝ በክርስቲያን ዲሞክራት የምርጫ ሳጥን ምልክት ላይ ክርስቲያናዊ መስቀሉን እንዲያሳርፍ አሳስባ ነበር። ሳጥን ምልክት ላይ ክርስቲያናዊ መስቀሉን እንዲያሳርፍ አሳስባ ነበር። ሌላውን አልፎ ተርፎም አለመምረጥ ማለት የኢየሱስ ክርስቶስን ጠላቶች እንደ መታደግ የሚቆጠር ሃጢያት ነው ብላ አስተምራለች። ምንም እንኳ ይህ ሁሉ ድጋፍ ለክርስቲያን ዲሞክራት ፓርቲው ቢሆንም ድጋፉ በሲሲሊ ከ48 በመቶ ወደ 36 በመቶ ወረደ።

ከዚህ በኋላ ማህበራዊ ለውጦች ባልተጠበቀ ዕመርታ መለዋወጣቸውን ቀጠሉ። እንደ ሩፊኒ ያሉ አስተሳሰቦች ትልቅ አደጋና

ስብራት ደረሰባቸው። የኮሚኒዝም አስተሳሰብ በተለይዩ የጣልያን አካባቢዎች በተለይ ደግሞ በሕብረት ሥራና በቤቶች ማህበራት ድሩን አደራ። የ1950 እና 1960ዎቹ የኢኮኖሚ ዕድገቶች በግንባታና በፋብሪካዎች ውስጥ በጄኔዋ፣ በቱሪንና ሚላን ከተሞች አበቡ። ጥብቅ ሃይማኖተኝነትንም እየተሸረሸረ ሄደ።

የአድባራቱ ግንባር ቀደም የነበረው የክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲ የፀረ-ግራ ኃይሎች ፀር ሆኖ የመቆም አቅሙን አጣ። የክርስቲያን ፓርቲው በዝርክርክ ድርጅታዊ አሠራር፣ የሕዝብ ገንዘብን በትክክል ለተገቢው ሥራ ማዋል ባለመቻሉ የከፍተኛ የቤተክርስቲያን ባለሥልጣናት ሳይቀሩ የትችት ወላፈናቸውን ይለቁበት ቀጠሉ።

በ1953 ምርጫ ክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲው በመንግሥት ሥልጣን ላይ ለመቆየት ከቀኝም፣ ከግራም ተራ ደጋፊዎችን መለማመጥ ጀመረ። ከዚያም በ1963 ሶሻሊስቶች በመጠናከራቸው ከክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲው ጋር ቅንጅት ፈጠሩ። በፓርቲው ውስጥ ዘመናዊ የካፒታሊስት ኢኮኖሚን የሚያጠናክሩ ኃይሎች ቢወጡም የሩፊኒን ድጋፍ ግን ከቶ ሊያገኙ አልቻለም። በ1964 የደብረዘይት በዓል ዕለት ካርዲናል ሩፊኒ «የሲሲሊ ዕውነተኛ ገጽታ» በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ጊዜ ኦፊሴሊያዊ መግለጫ ስለ ማፊያ አወጣ። ይህ ማለት «ማፊያ» የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ከዋለ ከ99 ዓመት በኋላ መሆኑ ነው። የተፃፈው መግለጫ ሚዲያው የሲሲሊን ገጽታ ለማበላሸት ባለ ሦስት ጫፍ ይዞ ይንቀሳቀሳል ይላል። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ጫፎች በጣም የተከበሩ ዝነኛ ሰዎችን ማለትም «የሲሲሊው ጋንዲ» በመባል የሚታወቀውን ዳሎ ዶልቺ፣ አርስቶክራቱን ደራሲ ጁሰፔ ቶማሲ ዲ ላምፔዱሳንና ማሳቀልና ሶስተኛው የሚዲያ የጥቃት ጫፍ ደግሞ ማፊያን በወንጀለኛነት አጋኖ ማቅረብ የሚል ነው። ሩፊኒ እንደሚለው ማፊያ እንደማንኛውም በጣልያን ይሁን በሌላ ሀገር እንደሚገኝ ወንጀል የሚታይ እንጂ ተጋኖ የሲሲሊን ስም የሚያስጠፋ አይደለም ብሎ ያምናል። ግን ለማፊያ ሩፊኒ የሰጠው ድምዳሜ ሚዛን የሚደፋ ሆኖ ካለመገኘቱም በላይ በጣልያን ማፊያ በቤተክርስቲያን ጋር ያለውን ጥብቅ ግንኙነት ያመላክታል።

# የጆ ባናናስ ወደ እረፍት መሄድ

ከኒውዮርክ የማፊያ ቤተሰቦች አለቆች ሁሉ የበለጠ የገዥነት ዘመን ያለው ዱሴፔ «ጆ ባናናስ» ቦናኖ ነው። በ1905 ካስቴሌማሬ ዴል ጐልፎ በተባለች አነስተኛ የባህር ዳርቻ ከተማ ተወለደ፤ ከዚያም የሙሶሎኒን ኢጣልያ ሸሽቶ በ1920ዎቹ ወደ አሜሪካ ተሰደደ። ከአብሮ አደጉ ከሰልቫቶሬ ማራንዛኖ ጋር በመሆን በ1931 ከላኪ ሉቺያኖ በኋላ የኒውዮርክ የማፊያ ማሴሪያ አለቃ ከነበረው ጋር በተፃራሪ ቆሞ ተዋግቷል። እንግዲህ ጆ ባናናስ ከሶስት አሥርተ ዓመታት በላይ የኒውዮርክን የማፊያ ቡድን መርቷል ማለት ነው። በብሩክሊን የማፊያ ሰንሰለት ውስጥ በነበረበት ጊዜ ከኒውዮርክ የማፊያ ቤተሰቦች መካከል ዕውነተኛው ሲሲሊያዊ ሆኖ ማፊያን መርቷል። የሲሲሊን ቀበሊኛ ቋንቋ በመጠቀም ይታወቃል። እንግሊዝኛውን በደንብ ሳያጣራ እየታገለ ኖሯል። ጆ ባናናስ ከ«ቡፋሎዎች ማጋዲኖስ ማፊያዎች» ጋር ከመያያዙ በተጨማሪ የቦናኖ የማፊያ ቤተሰብ ቡድን ከኢጣልያ ካስቴልማሬ ዴል ጉልፎ ማፊያ ጋር ግንኙነት ፈጥሯል።

በ1983፤ ጆ ባናናስ የራሱን ግለ-ታሪክ የሚገልፅ «የክብር ሰው» የሚል መጽሐፍ ጽፏል። በጽሑፉም ውስጥ ይበልጥ ይጠቀምበት የነበረው የክብር ቃል «እንደ ባህሌ» የሚለውን ቃል ሲሆኑ አንድምታውም «እንደ ማፊያ» ማለት ነበር። ቦናኖስ ወደ ቀድሞ ሥረ-መሠረቱ በመመለስ የሚመኘውን የእራሱን ነፃነትና የተሳካለት ሰው መሆኑን ለማስመስከር ወደ ሲሲሊ ተመለሰ። ገና ወደ ሲሲሊ ከመመለሱ ጣልያኖች «የአኗኗር ዘይቤና ሞቅ ያለ እንግዳ ተቀባይነታቸውን» በማድነቅ ገለፀ። ገና ሮማ ከተማ ከአውሮፕላን እንደወረደ በክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲው የውጭ ንግድ ሚኒስትር (ሚኒስተሩ ባናናስ የተወለደባት የካስቴልማሬ ሰው ነው) አማካኝነት የንጉሥ አቀባበል ተደረገለት። ባናናስም «በዚህ አቀባበል የኤፍ.ቢ..አይ ጓደኞቼ አይገረሙም ይሆን?» ሲል የለበጣ ጥያቄ አነሳ። ፓርሌሞን እንዲጎበኝ አድርገውት በከተማው የተሰራውን አውራ ጎዳናና በከተማው እንደ እንጉዳይ የፈሉ ህንፃዎችን አስጎብኝተውታል።

ባናናስ በሲሲሊ ያሳለፈው የእረፍት ጊዜ በሲሲሊና ከአትላንቲክ ማዶ ኮዛ ኖስትራ ልዩ እንቅስቃሴ እንዲይዝ አድርጓል። የአሜሪካዎቹ የኮዛ ኖስትራ ማፊያዎች የዕፅ ዝውውርን በሲሲሊ ላሉት ዋርሳዎቻቸው

አስተላልፈውላቸዋል። ከባባናስ ጉብኝት ጋር በተያያዘ የሲሲሊው ማፊያ እንደ ኒውዮርኩ ሁሉ አደረጃጀቱን በማጠናከር የማፊያ ኮሚሽን እንዲመሠረት ሆኗል። ማፊያ አሠራሩን ለሚቀጥሉት አራት አሥርተ ዓመታት አጠናክሮ እንዲቀጥልም ዋና መንገድ ከፍቶለታል። በ1980ዎቹና 90ዎቹ የታዩት የማፊያ ነውጠኛ እርምጃዎች የተያያዙት ጆ ባናናስ ቀምሞት ከሄደው መርዝ ጋር ነው።

የኮዛ ኖስትራ በዕፅ ንግድ ውስጥ እጁን መክተት በአንድ ወገን ከቢዝነስ ጋር የተያያዘ ሲሆን አደረጃጀቱን ደግሞ በኮሚሽን ደረጃ ማጠናከሩ ፖለቲካዊ አሠራርን የማጠናከር ሂደት ነው። ማፊያ፣ የፖለቲካ አሠራር ውስጥ መንቀሳቀስ ዋነኛው የህይወቱ መዘውር ሲሆን ኮዛ ኖስትራ እንደ ጥላ መንግሥት እስካልታየ ድረስ ፈፅሞ ሊመታና ሊወድም አይችልም ሲሉ ማፊያን የሚከታተሉ አጥኚዎች ያሰምሩበታል። ማፊያ በሕገ መንግሥት ሥር ተጠልሎ ነው እስትንፋሱን ሊያቆይ የቻለውም።

ጆ ባናናስ ከወደፊቱ «የሁለት ዓለም እለቃ» ከሆነው ቶማሶ ቡስኬታ ጋር በፓሌርሞ ስፖኖ ሬስቶራንት ተገናኝተው አምስት ሰዓት የፈጀ ትልቅ ድግስ ላይ ተነጋገሩ። ቡስኬታ ለጆ ባናናስ የተለየ አድናቆቱን ከመግለፁም በላይ ለእሱ ሞዴል ሰው መሆኑን «የተከበረ፣ ጠንበለልና በልዩ ችሎታ የተካነ ነው» ሲል አሞካሽቶታል።

ሁለቱ የማፊያ ነባር አለቆች በታሪካቸው ውስጥ አንድ ነጥብ ጥለው አልፈዋል ይህም ናርኮቲክን ነው። በእርግጥ ሁለቱም ከናርኮቲክ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌላቸው ምለው ቢገዘቱም ራሳቸውን ለማዳን ሲሉ የሸፈጡት ሸፍጥ እንጂ ሌላ አልነበረም።

ቡስኬታ ከጣልያን አሜሪካዊው ባናናስ ይበልጥ ዓይኑን በጨው የታጠበ ውሸታም ነበር። እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ሀብት ያፈራሁት በዕፅ ዝውውር አይደለም ሲል ምሎ ተገዝቷል። ዳሩ ግን በኮዛ ኖስትራ ውስጥ ከናኮርቲክስ ዝውውር ጋር ያልተሰማራ አባል እንዳልነበረ የድርጅቱ ታሪክ ያስረዳል።

በሀገረ-አሜሪካ ማፊያ በናርኮቲክ ዝውውር ብቻ ሳይሆን የሚታወቀው መጠጥ ተከልክሎ በነበረበት ወቅት አልኮልን በጥቁር ገበያ በመሸጥ፣ የቁማር ቤቶችን በማስፋፋትና ሠራተኞች በሠራተኛ

ማህበሮቻቸው እንዲያምፁና ስልፍ እንዲወጡ በማድረግ አሜሪካንን አበጣብጧታል። በተለይ የቴኒሲው ዴሞክራቱ ሴናተር ኬፌቨር አማካይነት የማፊያ የዕፅ ዝውውር ወንጀል እንዲጋለጥ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። ከዚያ በኋላም ነው በአሜሪካ የ1956ቱ የዕፅ ዝውውር ዕገዳ ህግ ሊወጣ የቻለው። በዚህም ምክንያት ለአጭር ጊዜም ቢሆን የማፊያ አሠራር የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብ ሲል የዕፅ ዝውወሩ እንዳይደረግ አዘዘ። ይህ ብቻ ሳይሆን ሌላም ውጭያዊ ሁኔታ በጉዳዩ ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል። ዋናዋ የናርኮቲክ ማዘዋወሪያ ደሴት የነበረችው ኩባ በፊደል ካስትሮና በቼ ጉቬራ ትግል የባቲስታ መንግሥት በመወገዱ ማፊያ ሥራውን ለመሥራት ተቸግሮ ነበር። ስለዚህ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ማፊያ የዕፅ ዝውውሩን ለማጧጧፍ ሶስት መሠረታዊ ነገሮች ያስፈልጉት ነበር፤ እነሱም የሚታመን የሰው ኃይል፣ ንግዱን ሊያዘዋውር የሚችል የንግድ አካልና የማስተላለፊያ ቤዝ።

ይህን ሁኔታ እንደገና ለማነሳሳት ሲባል ጆ ባናናስ በተገኙበት የፓርሌሞ ዕውቅ ሆቴል «ግራንድ ሆቴል ዴስ ፓልምስ» የማፊያ አለቆች ስብሰባ ተቀመጡ። የተለያዩ የኒውዮርክ የቦናና ማፊያ ቤተሰቦችና የቡሩሎዎቹ ስብሰባውን ታድመዋል። በስብሰባው ላይ ዋናው አጀንዳ የነበረው የዕፅ ዝውውር ጉዳይ ነበር።

የሲሲሊ ማፊያዎች ወደ አሜሪካ የሚገቡትን ሞርፌንና ናርኮቲክ ዕጾችን በብርቱኳንና በሎሚ ሳጥኖች አመሳስለው በማስተላለፍ የተካኑ ናቸው። በዚህ ሂደት የሚታወቀው መ/ቤቱን ኒውዮርክ ላይ ያደረገው «ማማ ሚያ» የተባለው አስመጪ ኩባንያ የናርኮቲክ ዕፅ ዝውውሩ ተዋናይ እንደነበር ይታወቃል።

በሆቴል ዴል ፓልምስ ስብሰባ ጄንኮ ሩሶ የተባለው የማፊያ አለቃ ዶን ካ ቪዚኒን ተክቶ የሲሲሊ ማፊያ «የአለቆች አለቃ» ሆኖ ወደ ላይ ወጣ። ጆ ባናናስ ካደረገው የዕፅ ዝውውር የንግድ አዲስ ሀሳብ ለመገንጠል ጄንኮ ሩሶ ወስኗል። ይህም የመጀመሪያው ከጆባናናስ የተለየ ተፎካካሪ የማፊያ አለቃን ለመፍጠር በር ከፍቷል። ሩሶ በሆቴሉ እንግዳ መቀበያ አካባቢ «ብዙ ውሾች ለአንድ አጥንት ሲታገሉ ራቅ ብሎ መመልከት ይሻላል» ማለቱ ተደምጧል። ዳሩ ግን ባናናስ የማፊያ ኮሚሽን የማቋቋም ሀሳቡን ያመጣው ይህን መሰል የተቃዋሚነትና የተፎካካሪነት ሀሳብ እንዳይመጣ ለማድረግ ነበር።

ቡስኬታ ኮሚሽን የማቋቋሙን ወሬ የሰማው በኋላ ነው። የጆ ባናናስን ሀሳብ ሁሉም የማፊያ አለቆች በደስታ ተቀብለውታል። ከዚህ በኋላ ነው ቡስኬታ የባናናስን ሀሳብ ተቀብሎ መተግበር የጀመረው። በዚህም ረገድ ይረዱት የነበሩትና መጪውን የኮዛ ኖስትራን ሥራ የሚሠሩት ሁለት ወጣት ማፊያዎች ጂታኖ ታኖ ባዳለሜንቲና ሳልቫቶሬ ግሬኮ «ዲንቢጡ» ነበሩ። «ዲንቢጡ» (Little Bird) የሲያኩሊ ግሬኮ ቤተሰብ አባል የሆነ ማፊያ ሲሆን የ1946-7 ጦርነትን የተወጣ ነው። ሶስቱ ማፊያዎች አንድ ላይ ሆነው የናርኮቲክ ዕፅ ነጋዴዎች ሆኑ።

እነዚህ ሶስቱ ማፊያዎች ማለትም ባደልሜንቲ፣ «ዲንቢጡ»ና ቡስኬታ ለኮዛ ኖስትራ አዲስ የአሠራር መመሪያን ነደፉ። እያንዳንዱ የሲሲሊ ግዛት የራሱ ኮሚሽን እንዲኖረው አደረጉ። በፓርሌሞ ብቻ ከሃምሳ በላይ የማፊያ ቤተሰቦች ስለነበሩ ሁሉም በአንድነት የሚወከለበትን ኮሚሽን መፍጠር አስፈልጓል። ስለዚህም በመሃል ላይ ወረዳዎችን የሚያገናኝና ሶስት የተቀራረቡ ቤተሰቦችን የሚያዋቅር ሰንሰለት ተፈጠረ። በዚህ ዓይነት ከወረዳ የተውጣጡት ደግሞ በኮሚሽኑ ውስጥ እንዲወከሉ ይደረጋሉ። ሥልጣን በተወሰኑ ሰዎች እጅ እንዳይገባ ለመከላከል ሲባልም የማፊያ ቤተሰብ ካፖ የሆነ በኮሚሽኑ ውስጥ ተወክሎ ሥልጣን አይይዝም። ዋናው የኮሚሽኑ ተግባር በሚወገዱ (በሚገደሉ) የክብር ሰዎች ላይ መወሰን ነው።

እንግዲህ የፓርሌሞው ኮሚሽን የዓለማቀፉ የዕፅ ንግድ የዳሬክተሮች ቦርድ አይደለም። በሚገባ የተደራጀና ታስቦ የተቀናጀ የማፊያ ፖለቲካ ተወካዮች አመራር እንጂ። የንግድ መስመር የያዘ የማፊያ ድርጅት አልነበረም ማለት ነው። ጥያቄው ግን፣ ለምን ኮሚሽን መመሥረቱ አስፈለገ? ሲሲሊያውያን በናርኮቲክ ንግድ ውስጥ ለምን እንዲሳተፉ ተደረገ? የሚለው ነው። ለዚህ ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት የሞከሩት የጣልያን የታሪክ ተመራማሪዎች ሲሆኑ የኮዛ ኖስትራ አሰራር እንብርት የሆነው ነገር ንግድና ፖለቲካን አጣምሮ መጓዝ ነው ሲሉ አስፈላጊነቱን ገልፀዋል።

በቡስኬታ እምነት ኮዛ ኖስትራነት «የሥልጣን ተዋረድ የሌለው የወንድማማችነት ማህበር ማለት ነው» ብሎ ያስባል። የክብር ሰዎች ሁሉ ጓደኛ ሲሆኑ ያስተሳሰራቸው አብይ ጉዳይ የካፖነት ማለትም

የአለቃና ሉሌ ግንኙነት ሳይሆን የወንድማዊ መከባበር ውጤት ነው። «እኛ የልዩ ሊሒቃን አካል ነን» ሲል ነበር ቡስኬታ የተመፃደቀው።

እንደተባለው በኮዛ ኖስትራ የዕድገት እርከን ውስጥ ሁለት ዓይነት ሥራ አለ - ቢዝነስና ፖለቲካ። በፖለቲካው እርከን የተመለከትን ከሆነ አንድ የኮዛ ኖስትራ አለቃ «ከካፖዴቺና» (ጓድ መሪ የአሥር ሰው አለቃ) ወደ ኮንሲሌሬ፣ ከዚያም ወደ ካፖነት እያለ ወደ ላይ ያድጋል። ወይም ደግሞ በኢኮኖሚው ዘርፍ ዓለምን እየዞረ በውንብድና የሚገኝ ሀብት ሊያጋብስ ይችላል። በኮዛ ኖስትራ ውስጥ ቡስኬታ ከማፊያ ወታደርነት ያለፈ ሥፍራ አላገኘም። ዳሩ ግን በማፊያ የውንብድና ኢኮኖሚ ምህዳር ውስጥ በመሳተፍ ወደተለያዩ የዓለም ክፍላት ተዘዋውሯል።

ሉኪ ሊቺያኖን ብንመለከት በሕይወቱ ውስጥ የተከተለው ሁለቱን መስመር ነበር። በ1936 የሸርሙጥና ንግድ በማካሄድ ወንጀል ከመታሰሩ በፊት ከህጋዊና ከሕገወጥ የንግድ አካላት ሕገወጥ ታክስ ይሰበስባል። ከአሜሪካ በ1946 እንዲባረር ከተደረገ በኋላ ነዋሪነቱን በፓርሌሞ አላደረገም። ከዚያ ይልቅ ሕገወጥ የንግድ አሰራርን ለማከናወን ወደ ኔፕልስ አቀና። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የተወሰነ የማፊያ ግዛት የሌለው ወንጀለኛና የሕገወጥ ንግድ አዘዋዋሪ ሆነ። እንግዲህ ማፊያ ራሱን ያጠናከረው የሁለት ዓለም ሰው በመሆን አንዴ በአሜሪካ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በኢጣልያ በመመላለስ ድርጅቱ እንዳይፈርስና እንዲጠናከር በጥብቅ ሰርቷል።

ጆ ባናናስ ከሄደበት እረፍት ከተመለሰ በኋላ በሲሲሊ ኮዛ ኖስትራ አሠራር ውስጥ ንግድንና ፖለቲካን አስማምቶና አቀናጅቶ መሥራት ተለመደ። ይህ አዲስ አሠራር ይበልጥ የተሳለጠው ኮሚሽኑ ከተቋቋመ በኋላ መሆኑ ነው። ኮሚሽኑ ከተቋቋመ ከስድስት ዓመት በኋላ በማይታወቅ ሁኔታ ለጊዜው እንዲፈርስ ተደረገ። ከዚያም በኋላ የመጀመሪያው ጦርነት በማፊያ ላይ ተሰነዘረ።

# 12

# ፀረ-ማፊያ

## የመጀመሪያው የማፊያ ጦርነትና መዘዝ (1962-1969)

ከሲያኩሊው ፍንዳታ በፊት ባሉት ዓመታት ማፊያን ተቃውሞ መናገር ፈፅሞ የሚቻል አልነበረም። ቤተክርስቲያንም ሆነች የክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲው ጭምር ስለ ማፊያ መኖርና ስለ ችግሩ አሳሳቢነት ትንፍሽ ብለው አያውቁም። አንድ ነፃ አመለካከት ያለው ድምፅ ነው ዝምታውን የሰበረው። ስለ ማፊያ ለማውራት የቻለው ይህ ድምፅ ደግሞ ነፃውና የግራ-ክፍል ልሳን የነበረው ላኦራ (L'ora) ጋዜጣ ነበር። ጋዜጣው በሚጥም አቀራረቡ በሥነ-ፅሁፍ፣ በሙዚቃና በሥነ-ጥበብ ላይ ያተኮር እንጂ በስፖርትና ፒኪኒ የለበሱ ሴቶችንም በጋዜጣው ላይ ስለሚያወጣ ተነባቢነቱ ወደር አልነበረውም። ይህ ብቻ አይደለም ድፍረት የተሞላበት የምርመራ ጋዜጠኝነትንም ይሰራ ነበር። እንዲያውም እነዚህን የምርመራ ሪፖርቶች ነበር የጋዜጣው ማሻሻጫ አድርጎ የሚጠቀመው። ለመጀመሪያ ጊዜም በ1958 የማፊያ አለቆችን ስም፣ ፍላጎትና የፖለቲካ ግንኙነት ጠቅሶ ባጋለጠ ጊዜ ጋዜጣው ላይ ያልተጠበቀ አደጋ ደረሰ። በቢሮዎች ላይ በማፊያ አቀነባባሪነት ዲናሚት እንዲፈነዳ ነበር የተደረገው።

በወቅቱ በሀገረ-አሜሪካ (በ1950ዎቹ) በተደራጁ ወንጀለኞች ላይ የፍርድ ቤት ስሚ የሚካሄድበት ወቅት ስለነበር የኢጣልያ ኮሚኒስት ፓርቲ በእንዲህ አይነቱ ዓለማቀፋዊ ሁኔታ በመበረታታቱ የማፊያ ጉዳይ በፓርላማ ደረጃ ምርመራ እንዲካሄድበት ጥያቄ አቀረበ። በ1959 መጨረሻ የክርስቲያን ዲሞክራት ፓርቲ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ዴሌታ ጉዳዩን አሳንሶ በማቅረብ በፓርላማ ደረጃ ምርመራ ማካሄድ የማያስፈልግ እንደሆነ ፓርላማውን ለማሳመን ሞከረ። እንዲያውም የደሴቲቱ ሰዎች «ፍትህን በእጃቸው ለማስገባት የሚያደርጉት ወከባ ነው» ሲልም ለጉዳዩ ሌላ መልክ ሰጠ።

በዚህን ጊዜ ግን የኢጣሊያ የፖለቲካ ማኘ ፍፁም ተለውጧል፡፡ የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲ ከመስነጣጠቁም በላይ ተስፈንጣሪ ቡድኖች አቋማቸውን ከሶሻሊስት ፓርቲው ጋር ማስተካከል ጀምረው ነበር፡፡ እንደሚታወቀው ሶሻሊስቶች የማፊያ ታሪካዊ ጠላቶች ናቸው፡፡ በወቅቱ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ማፊያ ያካሄዳቸውን ጭፍጨፋ ፈፅሞ አልረሱትም፡፡ ስለዚህ የማፊያ ጉዳይ ፓርላማው ይጣራ ብለው ያቀረቡት ጥያቄ በሌሎች ተስፈንጣሪ ፓርቲዎች ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱ ግልፅ ሆነ፡፡ መስከረም 1961 የሲሲሊ ክልላዊ ምክር ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ «ግራ-ዘመም» (Centre-Left) መንግስትን ስለ አቋቋመ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ኮሚኒስቶችን ደግፎ ቆመ፡፡ የሚቀጥለው አዲስ ዓመት ከመጀመሩ በፊት ም/ ቤቱ በአንድ ድምፅ በማፊያ ላይ ምርመራ እንዲያደርግ ለኢጣሊያ ምክር ቤት ጥያቄውን አቀረበ፡፡ እንዲያውም የማፊያ ፖለቲከኞች ጉዳዩ የማይቀርና ገፍቶ የመጣ መሆኑን በመረዳታ ቸው ሳይወዱ ቢሆንም ይህንኑ ሀሳብ ተቀብለው አፀደቁ፡፡ የሀገሪቱ የፖለቲካ ስበት ወደ ግራ ሀይሎች ባጋደለ ቁጥር ፀረ-ማፊያ ድምፆች እየጎሉ መጡ፡፡ ከእነዚህ ድምፆች ውስጥ ተሰሚነት የነበረው ሊዮናርዶ ሲያሲሊ ሲሆን፤ ይህ ሰው መምህርና የራካልሙት ከተማ ነዋሪ ነው፡፡ ይህ መምህር «የጉጉትዋ ወፍ ቀን» የሚል ኖቬላ የፃፈ ሲሆን ታሪኩ ደግሞ የሚያጠነጥነው ስለማፊያ ሸፍጠኛ ድርጊት በማሳየት ነው፡፡ ከመፅሐፉ ገፀ-ባህርያትም ፈፅሞ ከአንባቢ አእምሮ የማይጠፋውን የማፊያ አለቃን ድርጊት የሚገልፅ ዶን ማፊያኖ አሬናን ስሎ አልፏል፡፡

የደራሲው መፅሐፍ እንደታተመ በዚያው ዓመት የኮዛ ኖስትራ ኮሚሽን ፓሌርሞ በመሰብሰብ ማፊያ በኢጣሊያ መንግስት ላይ የሚወስደው አፃፋ ምን እንደሚሆን መከሯል፡፡ ፖለቲከኞች እስኪሰላቹ ድረስ ማፊያ የመግደል ርምጃውን እንዲቀጥል የወሰነ ቢሆንም ውሳኔው ሊቀጥል የቻለው እስከ 1962 የመጀመሪያው የማፊያው ጦርነት እስኪጀምር ድረስ ብቻ ነው፡፡

ከሲያኩሊው ፍንዳታ በኋላ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የፓርላማው ምርመራ ተጀመረ፡፡ ምንም እንኳን በ1875 ተደርጎ ከነበረው የመጀመሪያ ሙከራ በኋላ ምርመራው በጣልያን ታሪክ ሁለተኛው ቢሆንም የነበረው የፖለቲካ ሁኔታ ለዚህ ምርመራ አመቺ ነበር ማለት ግን አይቻልም፡፡ ቢሆንም ግን የሶሻሊስት ፓርቲው አዲስ አቅጣጫና ለውጥ እንዲፈጥር በማድረጉ ህዝቡ በምርመራው ውጤት ተስፋ አድርጓል፡፡ ይህ «ፀረ-ማፊያ» (Anti Mafia) በሚል የሚታወቀው አዲሱ

ምርመራ ፈጣን እርምጃውን ጀመረ። በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊ የውሳኔ ሀሳቦችን በኢጣሊያ ታሪክ ውስጥ አቀረበ። ከነዚህም ውስጥ ልዩ የወንጀለኛ ህግ በማፊያ ላይ አነጣጥሮ እንዲወጣ ያቀረበው ሀሳብ ይገኝበታል። ከዚህ በኋላ የኢጣሊያ ዴሞክራሲ የተቀናጀ ወንጀልን ለመቋቋም ዝግጁነቱን አሳየ።

የኮሚሽኑ የምርመራ ርምጃ እንደተጠበቀው ፍጥነቱን አላሳየም። እንዲያውም ለተከታታይ አሥራ ሦስት አመታት አዝጋሚነቱን ቀጠለ። በማፊያ ላይ የተቃጣው ምርመራም በኢጣሊያ ውስጥ ረጅሙ የምርመራ ጊዜን እንደወሰደ ይታወቃል። ይህ ደግሞ ከኢጣሊያ የፖለቲካ ህይወት ተነጥሎ የሚታይ አሰራር አልነበረም።

በምርመራው የሚገኙት ውጤቶች እጅግ አጓጊ ይሁኑ እንጂ የፖለቲካ እርምጃ ወይም ህጋዊ እርምጃ የሚያስወስኑ ሆነው ሊቀርቡ አልቻሉም። በፀረ-ማፊያ ግፊት የቀረበውና በ1965 የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ህግም ቢሆንም ምንም አይነት ውጤት አላስገኘም። ህጉ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያስቀምጠው አንድ በማፊያነት የተጠረጠረና የተያዘ ግለሰብ ከሚኖርበት አካባቢ ርቆ ፍርድ እስኪያገኝ ድረስ እንዲታሰር የሚደነግግ ስለሆነ አቀራረቡ የሲሲሊን ስዎች ለመጉዳት ሆን ተብሎ የወጣ ህግ ስላስመሰለው ማፊያም ይህንን ቀዳዳ በመጠቀም አዲስ የማፊያ አሰራርን ለመገንባት ቻለ። ይህ «የማጋዝ» ውሳኔ ማፊያ በመላው ጣሊያን ድርጅቱን ለማስፋፋት ተጠቀመበት።

የፀረ-ማፊያ የምርመራ መሪዎች ሲቀያየሩ እንኳ ወግ ያለው ተከታይ የማፊያን ድርጊት የሚያመላክት ዶክመንት ለአዲሱ ምድብተኛ ሰው ስለማይደርሰው የማፊያ ነገር ገና ከጅምሩ ጥሬ እየሆነ ይሄዳል። እንዲያውም በአንድ ወቅት የፀረ-ማፊያ ምርመራ ሊቀመንበር የሆነው ሰው ሲናገር «ስለ ማፊያ ይበልጥ ያወኩት ከሚተላለፍልኝ ዶክመንት ይልቅ የማርዮ ፑዞን «የጡት አባት» የሚለውን መፅሐፍ ከማንበብ ያገኘሁት መረጃ ይበልጣል» ሲል የክትትሉን አስቸጋሪነት ተናግሯል። ሌላው ከዚሁ ጋር የሚያያዘው የቀዝቃዛው ጦርነት ሁኔታና የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የግል ፍላጎቶች ተደማምረው የማፊያ ነገር «ሾላ-በድፍን» ሊሆን ችሏል። እያንዳንዱ በኢጣሊያ የፖለቲካ መድረክ ላይ የሚገኝ ቡድን ሁሉ (ማፊያን ጨምሮ) በኮሚሽኑ አባልነት የሚሳተፉ ሰዎችን አስርጎ ማስገባት የተለመደ ሆነ። በዚሁ ጉዳይ ላይ እርስ በርስ ገመድ የሚጓተቱ ኮሚኒስቶችና ክርስቲያን ዴሞክራት ፓርቲዎች ትግል ውስጥ

ገቡ። ይህ ደግሞ ማፊያን ሾልኮ እንዲወጣና እንዲያውም እንዲጎለብት ረዳው። በ1972 አዲስ መንግስት በሚመሰርትበት ጊዜ ከማፊያ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው የተባሉ ፖለቲከኞች ስልጣን ያዙ። ለምሳሌ ሳልቮ ሊማ በገንዘብ ሚኒስቴር መ/ቤት የሚኒስትሩ ፀሐፊ ሲሆን፤ ጆቫኒ (ጆያ) ተብሎ የሚታወቀው ማፊያ ደግሞ የፖስታና ቴሌኮሚኒኬሽን ሚኒስትር ሆኖ ተሾመ። በእጅ አዙር ማፊያ የፖለቲካ ስልጣኑን ተረከበ።

በመጨረሻም ፀረ-ማፊያ ኮሚሽኑ ስራውን በ1976 ሲያጠቃልል አከናወነ የተባለው ነገር ቢኖር ያከማቸው የወረቀት ቁልል ብቻ ነበር። ፀረ-ማፊያ ኮሚሽኑ ለቤተ-መፃህፍት ፍጆታ የሚውል አርባ ትላልቅ ቅፆችን ለማውጣት ቢቻልም ማፊያን ግን ለማጥፋት አልተቻለውም። በእርግጥ በ1972 የቀረበውን ጊዜያዊ ሪፖርት ማለትም 1262 ገፆችን የያዘውን በማንበብ ስለ ማፊያ ምንነት በሚገባ መረዳት ይቻላል። ይህ ግን ለታሪክ ተመራማሪዎች ፍጆታ ካልሆነ በስተቀር ማፊያን ወደ ህግ ፊት አቅርቦ ቅጣቱን እንዲቀበል ሊያደርገው አልቻለም።

በ1963 ከፀረ-ማፊያ ኮሚሽኑ ተጠብቆ የነበረው ውጤት ተመልሶ ሲታይ ፍፁም ግራ የሚያጋባና ተስፋ አስቆራጭ ነገር ተፈጠረ። ለምሳሌ በተግባር እንደታየው በካካሞ ከተማ ም/ቤት ውስጥ አንድ ሁነኛ ወንበር ለአንድ ማፊያ አለቃ በግልፅ የተለቀቀ እንደነበር የተሰበሰቡት ዶክመንቶች ያስረዳሉ። ሆኖም የተፈጠረ ምንም ነገር አልነበረም። እንግዲህ ማፊያ ህምጥ ይሁን ስምጥ ገብቶ ክትትሉን ሲያኮላሽና ራሱን አፈርጥሞ ሲወጣ ታየ እንጂ ሊከስም አልቻለም።

## «የቡድን ወንጀለኝነት ክስተት»

በመጀመሪያው የማፊያ ጦርነት ወቅት 117 የማፊያ ነፍሰ-ገዳዮች በ1968 ወደ ካላብሪያ ለፍርድ ተላኩ። በዚያም ለረዥም ዓመታት ጥቂት ማፊያዎች ብቻ ፍርደኞች ሆኑ። የኢዲቶሪው የማፊያ አለቃ የሆነው ፒዮትሮ ቶሬታ ሁለት ሰዎችን እቤታቸው ድረስ ዘልቆ በመግደል ወንጀል 27 ዓመታት ተፈረደበት። አንጄሎ ላ ባርቤራ ደግሞ 22 ዓመት ተኩል ሲፈረድበት «ድንቢጡ» ግሪኮና ቶማሶ ቡስኬታ በሌሉበት 10 እና 14 ዓመታት እንዲታሰሩ ተፈረደባቸው። ሌሎች ግን የማፊያ ድርጅት አባል በመሆናቸው ይቅርታ ተደርጎላቸው ወይም ደግሞ አነስተኛ እስር ተፈርዶባቸው ተለቀቁ። ብዙዎቹም የታሰሩበት ጊዜ እየተቆረጠላቸው ወዲያው ከእስር ተፈቱ።

የካላብሪያው የጣሊያን ፍ/ቤት ያሳለፈው ውሳኔ የሚያሳየው የጣሊያን መንግስት በማፊያዎች ላይ ጥርስ የሌለው አንበሳ መሆኑን ነው። ከዚህ ቀደም በሳንጆርጆ ሪፖርት እንደተመለከተው በማፊያና በጣሊያን የፍትህ ሥርአት መካከል የእከክልኝ ልከክልህ ግንኙነት መስፈኑን እንደሚያመላክት ተረጋግጧል።

በፖለቲካ ድጋፍ በማፊያ ወንጀል ላይ ምስክርነት የሚሰጡ ሰዎች የሚያውቁትን ሁሉ ለመመስከር ከየቤታቸው ብቅ ብቅ አሉ። ሆኖም ግን እንደተጠበቀው ድፍረቱን አግኝተው ፍ/ቤት ለመቆም አልተቻላቸውም። የፍርሀት አንቀጥቅጥ ይዞ ሀሳባቸውን አስቀየራቸው። ደግሞም እስካሁን በየቦታው የማፊያ አሰራር ምስክሮች ባልታወቁ ነፍሰ-ገዳዮች ታንቀው ሲገደሉ እንጂ ማፊያ (ኮዛ ኖስትራ) ተሸንፎ ስላልተመለከቱ ፍራቻና ዝምታቸው ምክንያት ነበረው።

ስለዚህ አቃብያነ-ህጎች ከ60 ዓመት በፊት መርማሪው ሳንጆርጆ እንዳደረገው ሁሉ ስማቸው ሳይገለፅ በድብቅ ስለማፊያ የሚያውቁትን እንዲያጋልጡ ተደረገ። ሆኖም ግን እንደነዚህ አይነት ምስክሮች ማንነታቸው ግልፅ ባለመሆኑ ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት ሲቀርብ ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አልተገኘም። ስለዚህ ማፊያን በህግ መረብ ጠልፎ መጣል የሚቻል አልሆነም።

ታህሳስ 10 ቀን 1969 ከምሽቱ አንድ ሰአት ከሩብ፣ አምስት ሰዎች የተሰረቀ የፖሊስ ዩኒፎርም ለብሰው በፓርሌሞ ላዚዮ ጎዳና ወዳለ ቢሮ ዘለቁ። ከዚያም የያዙትን መትረየስ ማርከፍከፍ ቀጠሉ። በተካሄደው የተኩስ ልውውጥ አንዱ ተገደለ። የሞተውን ነውጠኛ በራፍ ላይ በሚጠብቃቸው መኪና የኋላ ኮፈን ላይ ጥለውት ፈረጠጡ። በዚህ ተኩስ መሃል አራት ገድለውና ሁለት አቁስለው ነበር ያፈተለኩት። ይህ ጦርነት የተከፈተበት ሰው የማፊያ መርማሪው ሚኬሊ ካቫቶዮ (በቅፅል ስሙ ኮብራ) ነበር።

በላዚዮ ጎዳና የተካሄደው ግድያ የእውነተኛ ዘመናዊ ወንበዴዎች አሰራር መሆኑን ያሳያል። ከማፊያ ወዶ ገቦች (Pentiti) የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ራሳቸውን በፖሊስ ልብስ አመሳስለው ጦርነት የከፈቱት የተለያዩ የማፊያ ቤተሰብ አለቆች «ኮብራን» የማስወገድ ውሳኔ በጋራ አስተላልፈው ነው። በዚህ አይነት የመጀመሪያው የማፊያ ጦርነት ተከላሽቶ መርማሪውን እስከማጥፋት ደረሰ። ማፊያ ላይ የሚስነዘረው ጡጫ ግን በዚህ አያቆምም። ሁለተኛው የማፊያ ጦርነት ደግሞ ወደፊት ይቀጥላል።

# 13

# የሁለተኛው የማፊያ ጦርነት ሥረ-መሠረት (1970-1982)

## ሉቺያኖ ሌጂዩ (1943-1970)

የፍራንሲስ ፎርድ ኮፓላ ፊልም የሆነው «የጡት አባት» (The God father) በ1972 በኢጣሊያ ሲለቀቅ በትችት ነበር ተቀባይነት ያገኘው:: ሌሎች ሆሊውድ በማፊያ ጉዳይ ያወጣቸው ፊልሞችንም ቢሆን በመደዴ አቀራረባቸው ሲተቹና በጣሊያኖች ዘንድ ቅሬታን አዝለው ነበር ያለፉት::

ዋና የጡት አባት ገፀ-ባህርይ የነበረው ማይክል ኮርሊኦን በገሀዱ ዓለም አባቱ የተወለደበትን ኮርሊኦን ከተማን በሚጎበኝበት ጊዜ በወቅቱ ከማፊያ ወንጀል ይልቅ ለነዋሪው በዋና ጠላት የቆመው ታይፈስ በሽታ ነበር:: ማይክል የጎበኛት የኮርሊኦን ከተማ በአሜሪካኖች ታንክ መንገዶችዋና ዋና የፍሳሽ ማስወገጃዎቿ በመበላሸታቸው እጅግ የተደቆሰች ከተማ ነበረች:: በጡት አባት ተጋኖ እንደቀረበው እየተገደሉ የሚጣሉ ሰዎች ቁጥር እንዲያ ባይበዛም በ1944 አስራ አንድ ሰዎች ተገድለዋል:: ከዚያም በኋላ በ1945 አስራ ስድስት፣ በ1946 አስራ ሰባት፣ በ1947 ስምንት ሰዎች በ1948 ደግሞ አምስት ተገድለው ተጥለዋል:: በኮርሊኦን የተፈፀመው ወንጀል በማፊያ ታሪክ ውስጥ ልዩ ስፍራ ይሰጠዋል:: ምክንያቱም የመጀመሪያዎቹ ወንጀሎች በሙሉ የተፈፀሙት በሉቺያኖ ሌጂዩ በመሆናቸው ነበር:: ሉቺያኖ ሌጂዩ በኮዛ ኖስትራ ውስጥ እንደ ሌሎች የማፊያ አለቆች ሁሉ ወሳኝ ቦታ የያዘ ቀንደኛ ማፊያ ነው:: ሌላው ተከታዩ «ድንክዬው» ቶቶ ሪና ሰው አራጅ የማፊያ የክብር ሰው ሆኖ ሲታወቅ ሁለተኛው የማፊያ ጦርነት ተዋናይ ሆኖ ብቅ ያለ ነው:: እነዚህን የመሳሰሉ የኮርሊኦን አካባቢ የማፊያ

አለቆች በማፊያ ውስጥ ሁነኛ ስፍራ መያዛቸው ልዩ ያደርጋቸዋል። የጡት አባት ደራሲ ማሪዩ ፑዞ በፊልሙ ውስጥ የዋናውን ገፀ-ባህርይ ዶን ቪቶ ኮርሊኦንን ሲመርጥ የፊልሙ ኮርሊኦን ደግሞ በዓለም ላይ ተፈሪዎቹን የክብር ሰዎች ያፈራች ሥፍራ መሆኗን ግምት ውስጥ በማስገባት በመሆኑ አድናቆት ይቸረዋል።

ሉቺያኖ ሌጂዩ ገና ፍርድ ቤት ከመቅረቡ ከ1974 በፊት ነበር ፎቶግራፉ ይፋ የተደረገው። ሆኖም ለመላው ታዳሚ በግልፅ ተክለ ሰውነቱ የታወቀው «የጡት አባት» ፊልም ከተለቀቀ በኋላ ነበር ማለት ግን ይቻላል። የሌጂዩ የፊት ገፅታው እውነተኛው አሸባሪ መሆኑን ይመሰክራል። አንድ ወዶ-ገባ ስለ ሌጂዩ ሲናገር የሚንከባለሉ ዓይኖቹና ቀሳጢ አመለካከቶቹ እኛ ማፊያዎችን እንኳን ያስበረግገን ነበር ሲል መስክሮለታል። በመቀጠልም «ዓይኖቹ በአካባቢው ባሉ ሰዎች ላይ በድንጋጤ በድን እንዲሆኑ የማድረግ ስልጣን አለው። በዚህ ጊዜ ፃዕረ-ሞት እያንዣበበ መሆኑን ትረዳዋለህ» ብሏል። ይህ ሰው ነው እንግዲህ በአንድ ወቅት አንዱን ማፊያና ወዳጁን ከገደለ በኋላ የአስራ አምስት ዓመት ኮረዳ ልጁን አስገድዶ በመድፈር የገደላት።

እነ ሌጂዩ በኮዛ ኖስትራ ውስጥ ሀይለኛ ሊሆኑ የቻሉት በአባቶቻቸው መካከል ፍርሀትን በመልቀቃቸው ብቻ አይደለም። ከዚያ ይልቅ የጥንካሬያቸው ምንጭ አሮጌውን የማፊያ አሰራር ዘዴ በመቀመር አዲስ የማፊያ ስልትን በመተግበራቸው ነው። እነዚህ የኮርሊኦን ሰዎች ከፀረ-ማፊያ ጦርነት በኋላ አዳዲስ የማፊያ አሰራሮችን በመፍጠር ለሚከሰቱ ችግሮች ማፊያ ጠንቃቃ ሆኖ እንዲቆይ አስችለውታል። ይህም «ኮርሊኦኔዎች» የኮዛ ኖስትራ ዋና አካል ሲሆኑ ኮዛ ኖስትራ ደግሞ የሲሲሊ ውህድ አካል እንዲሆን አድርገዋል። ይህ ስልት እያደገ እንደሄደ ለማወቅ የ1940ዎቹን የሌጂዩን የመጀመሪያ ግድያዎች ከስረ-መሠረቱ ማየት ያስፈልጋል። ለመሆኑ ሊቺያኖ ሊጂዩ ማነው?

ሊቺያኖ ሊጂዩ በድህነት አረቋ ውስጥ በ1925 ተወለደ። ከተባበሩት የጦር ሀይላት (በሁለተኛው የዓለም ጦርነት) በ1943 ወረራ ባደረጉበት ጊዜ በክብ-ጭንቅላታሙ ዶክተር ሚኬሌ ናቫራ ነበር ወደ ክብር ማህበረሰቡ የተቀላቀለው። በናቫራ በኩል ገና በ20 ዓመቱ ኮርሊኦን አካባቢ የጥበቃ ሠራተኛነት ተቀጠረ። እንደዚህ ዓይነት የጥበቃ ሥራዎች የሚካሄዱት በኮርሊኦን ማፊያ ሲሆን ይህን ሥራ ለሥርቆት፣

ሠራተኞችን ለማስፈራራት፣ ንብረት ለማሸሽና ከባለንብረቶች ገንዘብ ለመንጠቅ ሲሉ ማፊያዎች ሠራተኞችን ይጠቀሙ ነበር።

ከጦርነቱ በኋላ በአስቃቂነቱ የተመዘገበ የነፍስ ግድያ በ1948 በናቫራ ትዕዛዝ ሊጂዮ እንዲፈፅም ተደረገ። የኮርሊኦን ገበሬዎች አንድ ሰማዕት ይዘው በሀዘን እንዲቆራመዱ ሆነ። የፀረ-ፋሽስት ትግል አርበኛና የሙያ ማህበር መሪ ፕላሲዩ ሪዞቶን በከተማ ውጪ እንዲበረከክ ካስገደደው በኋላ ጭንቅላቱን በሦስት ጥይት ደበደበው። የሪዞቶ አስክሬን ከሌሎች ሁለት ሟቾች ጋር ከአንድ ሸጥ ውስጥ ከአስራ ስምንት ወራት በኋላ ተቆፍሮ ወጣ። አስክሬኑ በሚቹ እናት አማካይነት ሊታወቅ የቻለው በለበሰው ጨርቅና በወቅቱ አድርጎት በነበረው የአሜሪካ ጫማ ምልክትነት ነበር። ሊጂዩ ግን ባደረሰው ወንጀል ተጠያቂ አልሆነም። በጣም የሚገርመው ሰውዬውን ለማፈን ለሊጂዩ ርዳታ ያደረጉት ሁለት ሰዎች የት ቦታ ሟች እንደሚገኝ ለባለስልጣናት ጥቆማ ሰጥተዋል። ሟች ፕላሲዩ ሪዞቶ ቋሚ ሐውልት ባይቆምለትም በ1946 ከወገብ በላይ ሐውልት ተሰርቶለት ካርሊኦን ማዘጋጃ ቤት አዳራሽ ውስጥ ለማስታወሻ እንዲቀመጥ ተደርጓል።

ከሪዞቶ ሞት በኋላ ሊጂዩ ተሰወረ። በ1946 እንደገና ተያዘ። ሆኖም በ1970 ደግሞ ተመልሶ ጠፋ። ለመጨረሻ ጊዜ ተይዞ እስር ቤት ውስጥ የተቆለፈበት በ1974 ነበር። ከፍርደኛነት እያመለጠ በማስቸገሩ «ቀዩ ሳማ» የሚል ቅፅል ስም ተሰጠው። ከፍተኛ በሆነ የኩላሊትና የጀርባ ሕመም በእጅጉ ይሰቃይ ስለነበር፣ ከሕግ ባመለጠበት ጊዜ ሁሉ ውድ ለሆኑ ክሊኒኮችና የፍል ውሃዎች ገንዘቡን ማውጣት ነበረበት። «ቀዩ ሳማ» ከሕግና ከተቀናቃኝ የማፊያ ቡድኖች ተደብቆ መኖር መቻል በራሱ የጃዊሳ ማፊያዎች ተግባር ነው እየተባለ ይወደሳል።

ወደኋላው የሊጂዩ ታሪክ ስንመለስ፣ 1956 ከሕግ ተሰውሮ የእንስሳት ርቢ ንግድ በማካሄድ ለማፊያ ሥራው እንዲያመቸው ተንቀሳቅሷል። ለመለመለውና ለሊጂዩ ቡድን አለቃ ለነበረው ሚኬሌ ናቫራም ለቁጥጥር አስቸገረ። ከማንም በላይ እንደሆነ ራሱን በመቁጠር መመፃደቅ ጀመረ። አልፎ ተርፎም አንዱ የናቫራ የቅርብ ሰው ከጎኑ መሬት ቢገዛም የውንብድና ተግባሩ ዓላማ አድርጎት እንደነበር መረጃዎች አስፍረውታል። ሰኔ 1958 ሊጂዩ በራሱ የእርሻ ማሳ ላይ በናቫራ ገዳይ ቡድኖች ጥቃት ደረሰበት። ጥቃት አድራሾቹ ግን ለሊጂዩ ባላቸው ፍራቻ

የተነሳ ከርቀት ተኩስ በመክፈት በቀጥታ ሊጋፈጡት አልቻሉም። በናቫራ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ለመፈፀም እንጂ ሊመቱት ከቶ አልደፈሩም። ይህ ሁኔታ ግን ዶክተር ናቫራ ላይ መዘዝ ሳያስከትል አልቀረም።

ከሁለት ወራት በኋላ ዶክተር ናቫራ ከአንድ ሌላ ጓደኛው ዶክተር ጋር ወደ ኮርሊኦን ተመለሰ። ጓደኛው ዶክተር በማፊያ ቡድን ውስጥ የሌለ ጨዋ ሰው ቢሆንም አንድ ጠመዝማዛ መንገድ ላይ ሲደርሱ በሌጂዩ አልፋ ሮሚዩ መኪና መንገዱ ተዘጋባቸው። የመጨረሻው የዶክተር ናቫራ ሕይወት እራሱ በመለመለው ሌጂዩ እጅ አለፈች። ከጥቂት ሰዓት በኋላ ፖሊሶችና ጋዜጠኞች በሥፍራው ሲደርሱ የዶክተር ናቫራ መኪና አፋፍ ላይ ተንጠልጥላና በጥይት ተበሳስታ ተመለከቱ። በኮርሊኦን የጋዜጦችን የፊት ገፅ የሸፈነው ጉድ ያስኘ ወንጀል ነበር የተፈፀመው። እንዲያ ኮዛ ኖስትራ በፖለቲካና በሕክምና ዘርፍ የሚተማመንበት የኮርሊኦኑ «ሰይጣኑ ዶክተር» ናቫራም በጥይት ተደብድቦ አበቃለት። የአካባቢው ገበሬዎች ሳይቀሩ «አባታችን» የሚሉት ሰው አከተመ። የሪዞቶን ደም ሌጂዩ በተራው ተበቀለለት።

ከናቫራ ገደላ በኋላ የሌጂዩ ቡድኖች ጥቃታቸውን ከመቀጠል በቀር ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። ናቫራ ከተገደለ አንድ ወር በኋላ ሦስት የዶክተሩ ጋሻ ጃግሬ ማፊያዎች በተኩስ ተገደሉ። በወቅቱ ኮርሊኦን በተኩስ በመናወጧ በአካባቢው የነበሩ ነዋሪዎች ህፃናት ሳይቀሩ ቆሰሉ። ከዚህ በኋላ ነበር ኮርሊኦን «የመቃብር ሃውልት» የሚል የቅፅል ስም የተሰጣት። በዚያው ዓመት (1958) ጥቅምት ላይ ሎኦራ (L'ora) ጋዜጣ የሌጂዩን አድራጎት በመኮነንና «አደገኛ!» የሚል ትልቅ ርዕስ በመጠቀም በፊት ገፁ ላይ አወጣ። ወዲያው ከሦስት ቀናት በኋላ ግን የጋዜጣው ፅ/ቤት በቦንብ ጋዬ።

የሌጂዩ መፈንቀለ-ማፊያ በኮርሊኦን ተኩስና አፈና ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ቀጠሉ። የሌጂዩ ሰዎች በናቫራ ቡድኖች ላይ የበላይነታቸውን የያዙ ቢሆንም በ1963 ከሲያኩሊው ቦንብ ፍንዳታ በኋላ እጅግ ብዙ ሰዎች በመያዛቸው በአብዛኛው የምዕራባዊ ሲሲሊ የማፊያ እንቅስቃሴ ቆሞ ነበር። «ቀዩ ሳማም» በኮርሊኦን በ1964 ተያዘ። ሌጂዩ (ቀዩ ሳማ) የተያዘው እጅግ በማያስጠረጥርና የቀድሞው የማፊያ መሪ በነበረውና በተገደለው የፕላሲዶ ሪዞቶ እጮኛ ቤት ውስጥ ነበር።

በሌጂዩና በናቫራ ቡድን ተገድነው የነበሩ 64 የማፊያ ወንጀለኞች በ1969 ፍ/ቤት ሲቀርቡ ሁሉም የሚተዋወቁ ነበሩ:: ሌጂዩ ያንን ሁሉ ወንጀልና ገደላ አከናውኖ የነበረ ቢሆንም በፖሊስ የተመዘገበበት ግን የጥቂት ዱውላ የበቀሉ ሥርቆት ብቻ መሆኑ ብዙዎችን አስገርሟል:: በአብዛኛው የማፊያ እስረኞች መስካሪዎችን ስለሚያስፈራሩ እዚህ ግባ የሚባል ማስረጃ ማግኘት እጅግ ከባድ ነበር:: ለዚህም ነው የፀረ-ማፊያ የፓርላማ ኮሚሽኑ ባደረገው ማጣራት የፍ/ቤት ውሳኔውን አጥብቆ የተቸው:: ለዚህ ደግሞ አንድ የሌጂዩን ምሳሌ ማንሳት ጠቃሚነት አለው:: ሌጂዩ ሲያዝ ዶ/ር ናቫራን በገደለ ጊዜ ከመኪናው ላይ የተወሰደው ቁራጭ ኤግዚቢት በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲታይ ሲደረግ የቀረበው ቁራጭ ከሌጂዩ መኪና ላይ የተነሳ ሳይሆን ሆን ተብሎ ከሌላ ላይ የተለወጠ ቁራጭ በመሆኑ ታዳሚውን አስደምሟል:: ሌጂዩ በወቅቱ ባካባቢው ባለመገኘቱ ሕቡዕ ገባ::

ከ1969 የፍርድ ሁኔታም በኋላ የሌጂዩ ማፊያ ቡድን አሰራሩን ቀጠለበት:: ከዚህ በኋላ አዲሱ የማፊያ የይዞታ ካርታና ሀይል ግልጽ ሆነ:: ሚኬኤሌ (ኮብራውን) ፖሊስ መስለው የገደሉት መቺ ቡድኖች የሌጂዩ ቡድን ቀንደኛ ገዳዮች ነበሩ:: እነሱም ካሎጀሮ ባጋሬላ እና በርናርዶ ፕሮቬንዛኖ «ትራክተሩ» ናቸው:: የሌጂዩ ደረጃ በኮዛ ኖስትራ የአመራር ኮሚሽን ውስጥ አደገ:: በዚህ ኮሚሽን ውስጥ ደግሞ አድራጊ ፈጣሪዎች ጋኢታኖ ባዳልሜቲ (ዋና የእፅ ዝውውር መሪ) ስቴፋኖ ቦንታንቴ (የፓርሌሞ አካባቢ የማፊያ ቤተሰብ መሪና «የቪላግራዚያ ልዑል») እና ሶስተኛው ሉቺያኖ ሌጂዩ በአብዛኛው የሚወክለው ቡቶቶ ሪና (ድንክየው) ነበር::

በሶስት የማፊያ አለቆች የተደራጀው ኮሚሽን በ1957 ጆ ባናናስ ከአሜሪካ መጥቶ ሲሲሊን በጎበኘና ኮሚሽኑን ባቋቋመ ጊዜ ካለው ሁኔታ ለየት ይላል:: የማፊያ ቤተሰብ ሃላፊዎች ኮሚሽን ውስጥ መቀመጫ አይኖራቸውም የሚለው አሰራር ተለውጧል:: እነዚህ ሶስት ሰዎች በፓርሌሞ ምድር እጅግ ፈርጣማዎች ናቸው:: ከ1974 በኋላ ደግሞ የማፊያ ኮሚሽን ተጠናክሮና የዕዝ ሰንሰለት በመፍጠሩ ኮዛ ኖስትራ ተጠናከረ:: ቶማሶ ቡስኬታም ለዳኛ ፋልኮኔ ይህንኑ የተጠናከረ ሰንሰለት መኖሩን ያጋለጠ ሲሆን አሁንም ቢሆንም ማፊያ ይህንኑ የዕዝ-ጠገግ ይጠቀማል::

ሌጂዩ ብዙ ጊዜውን ተሸሽጎ የኖረባት ከተማ ፓርሌሞ ስትሆን፣ የፓርሌሞን የሥጋ ገበያም ተቆጣጥሮት ኖሯል። በስጋ ጫኝ መኪኖቹ ህገ-ወጥ እርዶችን አጓጉዞበታል:: የሲጋራ ኮትሮባንዶችን በማዛወር ተጠቅሞበታል። ስለዚህ የፓርሌሞ አካባቢ ዋና የማፊያ አለቃ መሆኑ የሚያስገርም አልነበረም:: የጡንቸኝነቱ ሌላው መስኪያ ደግሞ በመጀመሪያው የማፊያ ጦርነት ወቅት ተዋጊዎች የነበሩት እነ ላባርቤራ፣ ቡስኬታ፣ ካቫታዩና ቶሬታ ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበረው መሆኑ ነው:: ስለዚህ ሌጂዩ በፓርሌሞ ስር የሰደደ የማፊያ አለቃ ሲሆን ፓርሌሞ ደግሞ ዋናዋ የማፊያ የመሰረት ቤት ናት። ስልጣን በማፊያ የክብር ማህበረሰቦች እጅ ተጠቃሎ የገባባት የማፊያ የሀይል ማዕከልም ናት - ፓርሌሞ::

## ሊዎናርዶ ቪታሌና መንፈሳዊ ቀውሱ

የሲሲሊ የማፊያ ታሪክ በከፍተኛ ፖለቲከኞች፣ ነጋዴዎችና በጦርነት ላይ ብቻ ተገድቦ የቀረ አልነበረም:: የማፊያ ጦርነት ማናቸውንም ወንዶችን፣ ሴቶችንና ልጆችን ጭምር የበከለ ነበር ማለት ይቻላል::

ከሌሊቱ አምስት ሰአት፣ መጋቢት 1973:: በዚያ ምሽት አንድ አዲስ ነገር ተፈጠረ:: የሊዎናርዶ ቪታሌ መንፈስ ተረበሸ:: ጊዜ ሳያጠፋ ቪታሌ ወደ አየር ወለድ የበረራ ቡድን ካምፕ አዘገመ:: ወዲያውም ኃይማኖታዊና ያልታሰበ ለውጥ ማድረጉን እንዲሁም አዲስ ህይወት መጀመሩን አበሰረ:: ከዚያም በዝርዝር ራሱን ማስተዋወቁን ቀጠለ:: እንዲህም አለ፤ የ32 ዓመት ጎልማሳና «የአልተሬሌ ዲባይዳ» የማፊያ ቤተሰብ አባል እንደሆነና የአንድ ጓድ (የአስር ሰው) መሪ መሆኑንም ተናዘዘ:: በጉዳዩ በተገረሙ የአየር ወለዱ መኮንኖች ፊት በሁለት ጊዜ የነፍስ ማጥፋት፣ የማፊያንና ሌሎች ወንጀሎችን ሁሉ መፈፀሙን ዘከዘከ:: ከዚያም የኮዛ ኖስትራ የማፊያ ቤተሰብ እንዴት እንደተደራጀ፣ የአባላቱን ዝርዝርና የማፊያ ኮሚሽኑን በበላይነት ማን እንደሚመራ አንድ ባንድ ሆዱን ረግጠው የጠየቁት ያህል ምንም ሳያስቀር ግልፅ አደረገ:: አልፎ ተርፎም በእሱ የማፊያ ቤተሰብና በሌላው ተቀናቃኝ ቡድን መካከል ጠብ በተፈጠረ ጊዜ ቶቶ «ድንክየው» መጥቶ መፍትሄ መስጠቱንም ጭምር ሳያስቀር የውስጡን አወጣ:: ከዚህ በኋላ ጉዞው ወደ እስር ቤት ሆነ::

ዳሩ ግን በሌዎናርዶ ቪታሌ ማጋለጥና ወዶ-ገባነት የተጠራጠረው አቃቤ-ህግ ለትክክለኛነቱ አንድ የሥነ-ልቦና መርማሪ ቡድን ወደ እስር ቤቱ መላክ ነበረበት። ምንም እንኳን ሊዎናርዶ ቪታሌ ያልተማረ ሰው ቢሆንም የዚህ ሰው የውስጡን መናገር ትክክለኛነትና ከውስጥ መንፈሳዊ ቀውስ የተነሳ ራሱን ማጋለጡ መርማሪዎቹ አመኑ። በነበረበት ድብቅ ድርጅት ውስጥ በዝምታና በሞት መሀል ሆኖ በመንፈስ መሰቃየቱን የሥነ-ልቦና ሙያተኞቹ በሚገባ አረጋገጡ።

በሌዎናርዶ ቪታሌ ላይ በዋናነት ተፅእኖ አድራጊ የነበረው ሰው አጎቱና እርሱ ራሱ ካፖው ሆኖ ሲመራው የነበረው ሰው ነበር። በዚህ ሰው ምክንያት እምነት የለሽና እግዚአብሔርን ጭምር የካደ ሰው ሆነ። ቪታሌ ገና በ14 ዓመቱ የማፊያ አባል ሆነ። በራሱ ቋንቋ ምንነቱን ሲገልፅ «እግዚአብሔር በሰጠኝ የተፈጥሮ ውስብስብነት የተነሳ የራሴ ተፈጥሮ ተቃራኒ ሆንኩኝ። የእግዚአብሔር ፍጡር መሆኔን ክጄ ፀረ-እግዚአብሔር ሆንኩኝ» ብሏል።

ሌዎናርዶ ቪታሌ እንዲህ ዓይነት ከንቱ ሰው የሆነው በእግዚአብሔር ቁጣ ሳይሆን፣ ራሱ የማፊያ አሰራር የፈጠረውና በከንቱ ውዳሴ የሚነዳ የማፊያ ተገዢ በመሆኑ ነው። ማፊያዎች ከሰው ልጅ የሞራል ብስለት አሽቀልቁለው ወደ ወንጀለኛና ከንቱነት የተለወጡ ነፍሰ-ገዳዮች ናቸው። በአንድ ወቅት ገና ቪታሌ ማፊያን እንደተቀላቀለ የገዛ አጎቱ እንዲህ ነበር ያለው፤ «እጆቼን ታያቸዋለህ? በደም የተጨማለቁ ናቸው፤ የአባትህ እጅ ከእኔ እጅ የባሰ በደም የተጨማለቀ ነበር» በማለት ወደ ፈተና ከተተው። ከዚህ በኋላ የልጁን (የቪታሌ) ታማኝነት ለማረጋገጥ በመጀመሪያ ፈረስ እንዲገድል ከዚያም በ19 ዓመቱ ሰው እንዲገድል ጠየቀው። እንደተጠየቀውም እድሜው ሲደርስ ሌዎናርዶ ቬታሌ «ፊያት ሞዴል 500» መኪና በመያዝ የመጀመሪያ ግዳዩን ከመኪናዋ የኋላ ክፍል በመሆን በጥይት ጨረሰው። ከዚያ በኋላ እሱም እንደ አባቱና እንደ አጎቱ እጁ በደም ተጨማለቀ። ወዲያው በ«አልታሬሎ ዲ ባይዳ የማፊያ ቤተሰብ» አባልነት ተመለመለ። በማፊያ ህይወት ውስጥ ተጠመቀ። ቤት ጠባቂ ውሾችን በመርዝ መግደል፣ የፍራፍሬ ማሳ ውስጥ ገብቶ በመስረቅና ሰዎችን በመግደል ተካነ። የጭንቅላት አፅም ስእል እየላከ ባላንጣዎቹን በማስፈራራት፣ ቦንብ በማፈንዳትና በዘረፋ ነገሠ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ለተከታታይ 30 ዓመታት ወንጀል

ፈፀመ:: ታዲያ ቬታሌ ከፍተኛውን ክብር ያገኘው በ1969 አንድ እንዲጠፋ የተወሰነ ማፊያ ከገደለ በኋላ ነው:: ይህን በማድረጉም ወደ ጓድ መሪነት (ካፖነት) አደገ:: ከዚያ በኋላ አንቱ የማፊያን ሚስጢሮች በዝርዝር ያካፍለው ጀመር:: ከነዚህ ሚስጥሮች ውስጥ የማፊያ ኮሚሽን መቋቋሙንና የአካባቢው የማፊያ ትእዛዝ የሚተላለፈው ከዚህ ማዕከል መሆኑንና የሳአራ ጋዜጠኛ ማሮዲ ማውሮ በማፊያ እጅ መሞቱን ሳይደብቅ ነገረው::

ታዲያ ሊዮናርዶ ቪታሌ ይህን የፈፀማቸውን ጥፋቶች ሁሉ ለስነ-ልቦና አዋቂዎች ሲናዘዝ ፀፀት ውስጡን እየቆሰቆሰው መሆኑን አስረድቶአቸዋል:: ከዚህ መናዘዝ በኋላም እግዚአብሔርን ማግኘቱንና ውስጣዊ ሰላም መጎናፀፉን ተናገረ:: ከዚህ በኋላ ግን ራሱን ጣለ:: ባዶ እግሩን መሄድና ጺም መላጨት አቆመ:: «እብድ ነኝ፣ እብድ ሰው ነኝ!» ሲል ይፋ አደረገ::

በራሱ የእጅ ፅሁፍ የፈረመውም የግማሽ ንክነት ኑዛዜም እንደሚከተለው ይነበባል:: «የስነ-ልቦና ህመም፣ ማህበራዊ ህመም፣ ፖለቲካዊ ማፊያ፣ ማህበራዊ ህመም:: በሙስና የተበከሉ ባለስልጣናት፣ ማህበራዊ ህመም:: ሽርሙጥና፣ ማህበራዊ ህመም:: ውርደ፣ የአባላዘር በሽታ ወዘተ ከልጅነት ጀምሮ አብሮ የኖረ የአዕምሮ ህመም:: እነዚህን ሰይጣናዊ ስራዎችን ነው እኔ ሌዎናርዶ ቬታሌ ተላቅቄ እውነተኛውን እግዚአብሔርን ዛሬ ያገኘሁት::»

አልቀረለትም - በ1977 ለመጨረሻ ጊዜ ፍ/ቤት ቀረበ:: ከ28 የማፊያ ተጠርጣሪዎች መሀል እሱና አንቱ ተፈረደባቸው:: ለ25 ዓመታት በእስር እንዲቆይ ሲፈረድበት አብዛኛውን ጊዜውን በአእምሮ ህመምተኞች ሆስፒታል እየተመላለሰ እስሩን ሳይጨርስ በ1984 ተለቀቀ:: ብዙም አልቆየም - አንድ የሠንበት ዕለት ከእናቱ ጋር እየተጓዘ ሳለ ያልታወቀ ሰው ከህዝብ መሀል ወጥቶ ግንባሩን በጥይት በረቀሰው:: በሚቀጥለው ዓመት ዳኛ ጆቫኒ ፋልኮኔና ፓውሎ ቦረሴኖ ለከፍተኛ የፀረ-ማፊያ የፍርድ ሂደት በሚዘጋጁበት ጊዜ የፍርድ ድርሳናቸውን በመግቢያነት የተጠቀሙት የሊዮናርዶ ቬታሌን ታሪክ በማቅረብ ነበር::

# 14

# የግራ-ቀደሙ ፒፒኖ አሟሟት

የ1970ዎቹ ዓመታት ለኢጣሊያ ዲሞክራሲ የፈተና ጊዜያት ነበሩ። ፋሽዝም ከተንኮታኮተ በኋላ ኢጣልያ ወደ ጨለማው ዘመን ውስጥ ተደለች። ማፊያን መደቆስና ጨርሶ ማጥፋት በመንግስት በኩል ቅድሚያ የተሰጠው ጉዳይ አልሆነም። ታህሳስ 1969 ሚኬሌ «ኮብራው» በማፊያ ከተጠቃ ከሁለት ቀናት በኋላ የኮዛ ኖስትራ እንቅስቃሴ በእጅጉ በረታ። ከደቡብ ኢጣልያ ወደ ሰሜን ሽብር ተስፋፋ። በኢንዱስትሪ በደመቀችው በሚላን ከተማ «ፒያሳ ፎንታና» በተባለው ስፍራ ቦንብ ፈነዳ። በዚህ የከተማው ማዕከል በፈነዳው ቦንብ 16 ሰዎች ሲሞቱ ብዙዎች ደግሞ ቆሰሉ። ከ3 ቀናት በኋላ ግራ-ቀደሙ አናርኪስስት በተፈጠረው ጉዳይ ላይ ለጥያቄ በፖሊስ ተያዘ። ከዚህ ሰው መያዝ በኋላ ብዙ ማስረጃዎች ተሰባስበው ጣታቸውን በኒዎ-ፋሽስት ቡድኖች ላይ ቀሰሩ። በኢጣልያ ፖለቲካ ውስጥ የተፈጠሩ ግራ-ክንፍ ነውጠኛ ቡድኖች ግን የደረሰውን አደጋ አስመልክተው ያራምዱት በነበረው መፈክር «መንግስት የፈጠረው የጭፍጨፋ ዘዴ ነው» ሲሉ ይደመጡ ነበር። በመንግስት በኩል ደግሞ «ውጥረት የመፍጠር ስታራቴጂ»፣ ወይም ደግሞ የግራ-ክንፍ ነውጠኞች የመፈንቅለ መንግስት ሴራ ተደርጎ ተወሰደ።

ጥርጣሬው ምንም ይሁን ምን ከ1967-69 ድረስ የነበረው ሁኔታና የተከሰቱ ከፍተኛ ተቃውሞዎች ጨው የተነሰነሰበት ቁስል ያህል መንግስትን የሚያንገበግቡ ሆነዋል። ተማሪዎች የግራ ክንፍ አመለካከት ያላቸው ቡድኖችና የሰራተኛው ንቅናቄ አባላት ከሞቃታማው የኢጣልያ የበጋ ጊዜያት ጋር ተዳምረው ተቃውሞውን አጋጋሉት። የኢጣልያ ኮሚኒስት ፓርቲም በእጅጉ ወደ ግራ ተገፋ።

የፒያሳ ፎንታናው ቦምብ በሀገሪቱ ውስጥ የሰላም መደፍረስንና ብጥብጥን ፈጠረ። ሁኔታው በሌላ ከተማም ተደገመ። በቦሎኛ ከተማ መናኸሪያ የፈነዳው ቦንብ 80 ሰዎችን እምሽክ አደረገ። የግራ-ክንፍ ኃይሎች አብዮትን ለመፍጠር ጥድፊያ ላይ የነበሩ ሲሆን በቀኝ ብርጌዶች በኩል ደግሞ «የመንግስት ዋና ማእከልን ማጥቃት» በሚል ሽብር ተስፋፋ። ፖሊሶች፣ የሕግ ሰዎች፣ ኢንተርፕሪነሮች፣ ጋዜጠኞችና አልፎ ተርፎም የኮሚንስት ፓርቲ አባላት ነጭ ሽብር ተፋፋመባቸው።

በተፈጠረው የውጥረት ስትራቴጂዎች ውስጥ የማፊያ እጅ የለበትም ማለት አይቻልም። አንዳንድ ምሳሌዎች ግልፅ ግንኙነት እንደ ነበረው ያመለክታሉ። በ1970 የኒዎ-ፋሽስት መሪ የነበረው የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴርን መ/ቤት በመክበብ መፈንቅለ መንግስት የማድረግ ሙከራው ቢከሽፍም ሁኔታው ከማፊያ ጋር ያለውን ትስስር አመላክ ቷል። ቶማስ ቡስኬታና ሌላው የማፊያ ወደ-ገባ እንዳረጋገጡት የማፊያ ቡድን በመፈንቅለ መንግስቱ እንዲሳተፍ ጥያቄ ቀርቦለት እንደነበር አጋልጠዋል። የማፊያው መሪ ቡስኬታና «ድንቢጡ» ግሬኮ ወደ አሜሪካ ዘልቀው ከሌጂዮ ጋር መማከራቸው ተረጋግጧል። በኋላም በካታኒያ፣ በሮም፣ በሚላንና በዙርክ ከተሞች ተመሳሳይ ስብሰባዎች ተደርገዋል።

ከ1970 የመፈንቅለ መንግስት መክሸፍ በኋላ ማፊያ ለቀኙ-ክንፍ ነውጠኞች ባደረገው ድጋፍ ከሚላን ወደ ኔፕልስ በሚጓዝ ባቡር ላይ ፈንጂ በማጥመድ 16 ሰዎች እንዲገደሉ አድርጓል። ስለዚህ ማፊያ ለሌሎች ኃይሎችም መሳሪያ በመሆን አገልግሏል። ኮዛ ኖስትራ ይህን ሁሉ አገልግሎት የሚሰጠው ከልቡ ሌሎችን ለመታደግ ሳይሆን ለራሱ የሚሆን ትርፍ ማግኘቱን ሲያረጋግጥ ብቻ መሆኑን ታሪክ ይመሰክራል።

ከ1960ዎቹ የደም መፍሰስ በኋላ በፍትህ አካላቱ ዙሪያ ለውጦች መታየት ጀመሩ። ቀደም ሲል የነበረው የፍትህ አካላት ሁኔታ በተለይም በሲሲሊ በቤተሰብ ትስስር የተዘፈቀ በመሆኑ ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የሚያስችል አቅም አልነበረውም። ከትምህርት መስፋፋት ጋር በተያያዘ አዳዲስ የሕግ ምሩቃን የፍትህ አካላቱን በመቀላቀላቸው ከሌሎች የአውሮፓ አገራት ጋር የሚመሳሰል የፍትህ አካላት ነፃነት መታየት ጀመረ። ዲሞክራሲያዊ የዳኞች ማህበርም መቋቋም ለማፊያ ያደላ

የፍትህ አካል ለውጥ አሳየ። በዚህም የተነሳ ባለነጭ ከሳድ ወንጀለኞችን ለፍርድ ማቅረብም ቀጠለ። የፍትህ አካላቱ እየተጠናከሩ በሄዱ ቁጥር እነሱም በየፊናቸው በፖለቲካው መስመር መለያየት ጀመሩ። በማፊያ ላይ የሚደረገው ጥቃት ሁሉ ዋናው መሰረቱ የፍትህ አካሉ ወደ አዲስ አሰራር መለወጥ መሆኑ ምንም አያጠራጥርም። ሆኖም ግን ከኮዛ ኖስትራ ላይ የሚደረገው ትግል በአዝጋሚው ለውጥ ምክንያት ወደፊት ጊዜ መውሰዱ አይቀርም።

1970ዎቹ ለኢጣሊያ ዴሞክራሲያዊ ፈታኝ ወቅት ነበር። ጥቂቶቹ ማለትም የፖለቲካ ውጥረትና የግራ-ክንፍ አሸባሪነት ተደቀኑበት። በዚህም ምክንያት የኢጣሊያ ዲሞክራሲ አደጋ ውስጥ መሆኑ በጥብቅ ተተቸ። እጅግ አሳሳቢው ሁኔታ ደግሞ በ1978 በቀይ ብርጌዶች የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲ መመሪያና የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር የነበረው አልዶ ሞሮ መታገት ሲሆን አጃቢዎችና ሹፌሩም ተገደሉ። የኢጣሊያ ፖለቲከኞች በእገታው ድራማ ላይ 55 ቀናት የአጋቾችን ጥያቄ እንመልስ ወይስ በተቃራኒው እንቁም በሚሉ ሀሳቦች ተካታረኩ። በመጨረሻም እልባት ላይ ባለመድረሳቸው የሞሮ አስከሬን በቀይ ሪኖ መኪና በፓርቲው ጽ/ቤት ፊት ለፊት ተጣለ።

ከዚህ ጊዜ በኋላ የማፊያ የሽብርተኝነት ተግባር ጎልቶ መውጣት ቀጠለ። በተለይ በምእራባዊ ሲሲሊ ይበልጥ ተጠናከረ። ወግ አጥባቂው «ኮሪየሬ ዴላ ሴራ» ጋዜጣ በምእራባዊው አነስተኛ የሲሲሊ ከተማ «ሲንሲ» የደረሰውን ሪፖርት አወጣ። የሪፖርቱ ርእስም እንዲህ ሲል ይነበባል። ግራ-ቀደሙ ነውጠኛ በራሱ ቦንብ ፈነዳ!። «ይህ ግራ-ቀደሙ ነውጠኛ» የተባለው ሰው ጁስፔ ፒፒኖ ኢምፓስታቶ ነበር። ፒፒኖ ነውጠኛ» የተባለው ሰው ጁስቤ ፒፒኖ ኢምፓስታቶ ነበር። ፒፒኖ በሲኒሲ ማፊያ የተገደለ ሲሆን ትክክለኛ ገዳዩ እንዲታወቅ በጓደኞቹና በቤተሰቡ አማካይነት ሩብ ምዕተ-ዓመት ሙሉ ፍትህን የማግኘት ሙከራ ተደርጓል።

ትንሹ ፒፒኖ በአካል እንዳደገ የግራ-ቀደም ተዋጊ ኃይል በመሆኑ ግማሽ ዕድሜውን ካፒታሊዝምንና ጭቆናን በመዋጋት አሳለፈ። በወቅቱ እንደነበሩ ወጣቶች የማርክስዝምን ባንዲራ በማውለብለብ በተለያዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳተፈ። የፒፒኖ አባት የሲኒሲ -

ማፊያ አባል የነበረ ሲሆን ፒፒኖ ደግሞ በተቃራኒው ሆኖ መንሳቱን ማንም የጠበቀው ጉዳይ አልነበረም።

ፒፒኖ በፀረ-ማፊያ ባህል ላይ ተቃራኒ ሆኖ የቀረበ የቤተሰቡ ብቸኛ ልጅ ነው። ፒፒኖ የ15 ዓመት ጎረምሳ ሆኖ የሲኒሲው የማፊያ አለቃ አጎቱ ሲዛሬ ማንዜላ የሞተው በማፊያ ጦርነት በተጠመደ ፈንጂ መሆኑን ያውቃል። የያኔው ለጋ ጎረምሳ ፒፒኖ በተፈጠረው አደጋ ጥልቅ መደናገጥን ፈጥሮበት እንደነበርም ይታወሳል።

17 ዓመት ሲሞላው የግራ-ቀደም ቡድን ዋና ካድሬ ነበር። በስብሰባዎች ላይ ንግግር ያደርጋል፣ የሶሻሊስት ዓላማ የሚለውን በራሪ ወረቀት ያዘጋጅ ነበር። ከማፊያ ጋር ቀጥተኛ ግጭት ነበረው። በ1966 «ማፊያ የቆሻሻ ክምር ነው» ሲል ፃፈ። ይህን የተመለከቱ የአባቱ ጓደኛ «ልጄ ቢሆን ኖሮ ጉድጓድ ቆፍሬ እቀብረው ነበር» ሲሉ አባቱን መከሩት። ከዚህ ጊዜ በኋላ ፒፒኖ ከቤተሰብ ራቀ። ቤተሰቡም እንዳይቀርባቸው አደረጉት።

«ሲኒሲ» ምንም እንኳን ትንሽ ከተማ ብትሆንም ዋናው የኮዛ ኖስትራ እንቅስቃሴ የጎላባት የምዕራብ ሲሲሊ ግዛት ናት። ከዚህ በተጨማሪ በፓርሌሞ አዲስ አይሮፕላን ማረፊያ በመሰራቱ የኮንትሮባንድ ኦፕሬሽኑን ይበልጥ አፋፋመው። (በነገራችን ላይ የሲኒሲ ከተማ የህዝብ ብዛት 8,000 ሲሆን 80 በመቶው ዘመዶቻቸው ግን የሚኖሩት በአሜሪካን ሀገር ነው) ከተማዋ አትላንቲክን የሚያቋርጥ የዕፅ ዝውውር የተስፋፋባት እንዲሁ አይደለም። የሲኒሲ የማፊያ አለቃ ዶን ታኖ ባዳልሜንቷ ከአሜሪካው ዴትሮይት የኮዛ ኖስትራ ቡድን ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው ሲሆን ለዕፅ-ዝውውር ሮማና ሚላን ከተሞችን በማእከልነት ይጠቀምባቸዋል። ሌላው ቀርቶ ከፍተኛ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች በዚህ የማፊያ አለቃ ስር በመሆናቸው በኮዛ ኖስትራ ውስጥ እጅግ ተፅእኖ ፈጣሪ ሰው ነው። የማፊያ ዋና አመራር የሆነው ኮሚሽን እንደገና በ1974 ሲቋቋም በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ሲሰባሰቡ የመጀመሪያው ወንበርተኛ እሱ ነበር።

ወደ ፒፒኖ ታሪክ ስንመለስ የፒፒኖ እናት ፌሊቺያ ከማፊያ አለቆች ጋር ምንም የደም ትስስር የሌላት ስትሆን ልጇን ከመምከር

ታቅባ አታውቅም። «ፒፒኖ እኔም ፀረ ማፊያ ነኝ፤ ግን ደግሞ ልጄ ሆይ ተጠንቀቃቸው!» እያለች ትመክረው ነበር።

ምንም እንኳን የእናት ምክርና የማፊያ ማስፈራሪያ ቢኘኅደኅድም በሀቅና ከትክክለኛ ተግባር የሚያግደኝ የለም ሲል ፒፒኖ በፀረ ማፊያነቱ ቀጠለበት። በማፊያ አለቆች መሬታቸው ከተነጠቀባቸው ገበሬዎችና ከማፊያ ጋር ንኪኪ ካላቸው ነጋዴዎች ስራ ከሚሰሩ የተበደሉ ሰራተኞች ጎን መቆሙን ቀጠለ። አልፎ ተርፎ «ታሪካዊ መቻቻል» እንፍጠር ከሚለው ከኢጣሊያ ኮሚኒስት ፓርቲ (CPI) መስመር በተቃራኒው ቆመ። በፒፒኖ አመለካከት ከክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲው ጋር መቻቻል መፍጠር ከማፊያ ጋር ዕርቅ እንደመፍጠር ይቆጠራል በሚል ግራ-ቀደምነቱን አከረረ።

የፒፒኖ ትግል በዚህ ብቻ አላቆመም፤ ከሚፅፈው በራሪ ፅሁፍ በተጨማሪ በ1977 አንድ የአካባቢ ሬድዮ ጣቢያ ከፍቶ በማፊያና በማፊያ አለቆች ላይ የስላቅ ፕሮግራሙን ቀጠለ። የአካባቢው ዋና የማፊያ አለቃ ዶን ታኖ ባደልሜንቲን የሚያንኳስሱና የሚያዋርዱ ፅሁፎችንም በተከታታይ አወጣበት። ከዚያም የማፊያዎችን ድርጊት በፎቶግራፍ ለማጋለጥ የፎቶግራፍ ኤግዚብሽን አዘጋጅቶ የማፊያ አለቆች ሳይቀሩ ተጠራርተው ኤግዚብሽኑን ተመለከቱት።

ይህን ሁሉ ሲያደርግ ፒፒኖ ከእሳት ጋር እየተጫወተ መሆኑን ያውቃል። እናቱ በተደጋጋሚ ማፊያዎች «አውሬዎች» መሆናቸውን ነግራዋለች። ምናልባት ትንሽ ድፍረት ያገኘው የራሱ አባት የማፊያ የክብር ሰው ስለሆነ ይህን እንደመውጫ ቀዳዳ ተጠቅሞበት ይሆናል። ዳሩ ግን ልጁ ያስነሳው አቧራ ለአባቱ አበሳ ሆነበት። ብዙም ሳይቆይ መስከረም 1977 አንድ የሚያልፍ መኪና አባትየውን ገጭቶ ገደለው። በአባትየው ቀብር ላይ ብዙ የሚያውቃቸው የማፊያ አለቆች ቢገኙም እጁን ለሰላምታ ማንሳት አልፈለገም። በቃ! ከዚህ ጊዜ በኋላ አንድ ቀን ራሱ ፒፒኖ እንደሚገደል አውቋል።

በሚያዝያ 1978 ምሽት ከሬድዮ ጣቢያው ወደ ቤቱ ሲመለስ መንገድ ላይ ፒፒኖ ታፈነ። በፓርሌሞ ትራፒን የባቡር መስመር ላይ ወስደው ቀጠቀጡት። ከዚያም በድኑን አንድ አሮጌ የጭነት መኪና ላይ

ጥለውት ሄዱ። በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ላይ የባቡር መንገድ ሰራተኞች አንድ መኪና ተቃጥሎ መቆሙን ተናገሩ። ወታደራዊ ፖሊሶች ወደ ስፍራው ሲሄዱ የተበጣጠሰው ሰውነቱንና ብጭቅጭቁ ልብሶቹን አገኙ። ከሰውነት ክፍሉ የሚታወቅ ነገር ቢኖር የፊት ክፍሉና እግሩ ብቻ ነበር። ፒፒኖ እስከወዲያኛው አከተመ።

ፒፒኖ ከሞተ ከ22 ዓመት በኋላ በ2000 የፓርላማ መርማሪ አካል ስለ አሟሟቱ ሪፖርት ማቅረብ ጀመረ። የፒፒኖ የቅርብ ወዳጅና ጓደኞቹ ስለ አሟሟቱ ትክክለኛ ምርመራ ተደርጎ ውጤት እንዲገለፅ ቢወተውቱም ቁብ የሰጠው አልነበረም። ወታደራዊ ፖሊሶች ወዲያው ከፒፒኖ ሞት በኋላ ያደረጉት ነገር ቢኖር ፒፒኖ ራሱን መመርመር፣ የጓደኞቹንና የዘመዶቹን ቤቶች በማሰስ አስበረገጉአቸው። ይህ ደግሞ ለቋሚ ጓደኞቹና ዘመዶቹ የልብ ስብራትን ፈጠረ። ፒፒኖ በተቀበረበት ጊዜ አንድ ሺህ ግራ ፅንፍ አባላት «ፒፒኖ በማፊያ ነው የተገደለው!» የፒፒኖን ዓላማዎች ይዘን እንጓዛለን!» የሚል መፈክር ይዘው ሲጮሁ አንዳንዶች ደግሞ በዶን ታኖ በዳልሜንቲ ቤት ፊት ለፊት ቆመው «አንተ ሰው አራጅ!» እያሉ ጮሁ።

ከተለያዩ ምስክሮችና ሹክ ባዮች እንደተረጋገጠው ማፊያና ወታደራዊ ፖሊሶቹ እጅ ለእጅ ተያይዘው ሲሰሩ እንጂ ማፊያን ፖሊሶቹ ሲፈትኑት አለመታየቱ ተረጋግጧል። እንደ ሲኒሲ ባሉ የማፊያ ከተሞች እንዲህ ዓይነቱ ክስተት የአደባባይ ምስጥር ሆኖ ቆይቷል። ሁሉም ጣት ወደ ዶን ታኖ ባዳልሜንቲ ቢያነጣጥርም ገዳዩ እሱ መሆኑ የተረጋገጠው ግን እጅግ ዘግይቶ ነበር። እንዲሁም ዶኑ በዚያን ጊዜ በአሜሪካን ኒውጀርሲ ከተማ ዕፅ በማዘዋወር ወንጀል ተከሶ በእስር ላይ ነበር። የፒፒኖ ጉዳይ በ□ህ ባይዘጋም በፒፒኖ ላይ ያጠነጠነ ፊልም ደግሞ በቬኒስ የፊልም ፌስቲቫል አሸነፈ። ርዕሱ «አንድ መቶ ርምጃዎች» (I Cento Passi) ሲሆን ፊልሙ ይህን ርዕስ ያገኘው የፒፒኖና የዶኑ ቤት የሚራራቁት በመቶ ሜትሮች በመሆኑ ነበር።

በመጨረሻም የሰው ደም መጮሁ ስለማይቀር ሚያዝያ 2002 ዶን ታኖ ዕድሜ ልክ እስራት ተፈረደበት። የፒፒኖ እናት ስለዚህ ጉዳይ የሰጠችው አስተያየት የሚከተለው ነበር።

«ስለ ብቀላ በአዕምሮ አስቤ አላውቅም፡፡ ያደረኩት ነገር ቢኖር ስለ ልጆ አሟሟት ፍትህ ለማግኘት ጩሄያለሁ፡፡ እውነቱን ለመናገር ብዙ ዓመት በመጠበቄ እምነት አጥቼአለሁ፡፡ እዚህ ነጥብ ላይ እደርሳለሁ ብዬ አልገመትኩም፡፡ አሁን ግን በከፍተኛ ደረጃ ረክቼያለሁ፡፡ ምን እንደሆነ አውቅ ነበር፡፡ ዶን ታኖ ወደ ባለቤቴ እየደወለ ስለ ፒፒኖ ስሞታ ያሰማ ነበር፡፡ አባቱም ፒፒኖን እንዳይገድልበት በጥብቅ ተማፅኖታል» ብላለች፡፡

ይህ ከላይ የተገለፀው አባባል በማፊያ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች ክብርና ዝምታ በሚል የማፊያ ዘዴ ተሸብበው በልጆቻቸው ላይ እንኳን የተጋረጠውን አደጋ ለማጋለጥ ትንፍሽ እንደማይሉ ጥሩ ማስረጃ ነው፡፡ የሲሲሊን ማፊያ ለመዋጋት እንደ ፒፒኖና እንደ እናቱ ያሉ የጠንካራ ሰዎችን ትግል ይሻል፡፡ በመጨረሻም በፍ/ቤት በኩል የተገኘው ውጤት የፍትህ መዘግየትን ቢያሳይም ከሩብ ምዕተ-ዓመት በኋላ ግን ፍትህ መገኘቱን መካድ አይቻልም፡፡ ማፊያ ግን ያቆመው ኃይል የለም፡፡ ሽብሩን ቀጥሏል፡፡

# 15

# ማፊያና የሀብት ጉዞው

## ዕፅና የፒሳ ትስስር

ከ1968-9 ድረስ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተለቀቁ የማፊያ አለቆች ከእስር ቤት ሲወጡ እጃቸው አጠረ። ለፍትህ ስርአት ከማፊያ ካዝና እየወጣ ሲከፈል የነበረውና የታሰሩ ማፊያዎችን ለመርዳት በተደረገው ጥረት የማፊያ አለቃ ካዝና በእጅጉ ሳሳ። የካታኒያ ማፊያ አለቃ የነበረውና በኋላም (በ1987) ስለ ማፊያ ድርጊት ለዳኛ ፍልኮኔ የዘከዘከው አንቶኒዩ ያን አስቸጋሪ ወቅት በሚመለከት የጠራ ትውስታ አለው። ለምሳሌ ቶቶ «ድንክየው» በገንዘብ እጥረት እርሱ ፍርድ ቤት በሚቀርብበት ጊዜ እናትየው አብረውት እንዲሆኑ ለማድረግ ባለመቻሉ በወቅቱ ስቅስቅ ብሎ አልቅሷል። ይህ እንግዲህ የሚያሳየው ማፊያ በገንዘብ እጦት ክፉኛ ተመትቶ እንደነበረ ነው። በኋላ ግን ሁኔታዎች ተለወጡ። ካልዲሮን እንደሚለው ማፊያዎች እንደገና አገገሙ። ሁሉም ሚሊየነሮች ሆኑ። በዕፁ ዝውውር ምክንያት በአጭር ጊዜ ውስጥ ድንገተኛ የሀብት ለውጥ አሳዩ ብሏል። በኮዛ ኖስትራ ታሪክ ውስጥ የ1970ዎቹ የዕፅ ዝውውር ማፊያዎችን በሀብት እንዲከብሩ ያደረጋቸው ቢሆንም እጅግ መራራ በሆነ ግጭት ውስጥ የገቡበትም ወቅት እንደነበር ይታወሳል።

ከዕፅ ዝውውር ጎን ለጎን ሌላው የማፊያ ሀብት ምንጭ የሲጋራ ንግድ ነበር። በ1970ዎቹ ማዕከሉን ኔፕልስ ከተማ ላይ ያደረገ የሲጋራ ኮንትሮባንድ ንግድ ተጧጧፈ። ታዋቂው ማፊያ ቶማስ ቡስኬታ ከሲሲሊ ወደ ኢጣሊያ ማዕከላዊ ግዛት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የሲጋራ ሳጥኖችን በኮንትሮባንድ ይልክ ነበር። የካሞራ ማፊያ አለቃ ሚኬሌ

(እብዱ ማይክ) በየወሩ 50,000 ሳጥን ሲጋራዎችን እንደሚያስተላልፍ ለፍ/ቤት ተናዟል።

የሲጋራ ትርፋቸው ከዕፅ ዝውውር ንግድ ትርፍ ጋር ተወዳዳሪ እስከመሆን ተቃርቦ ነበር። የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ሪቻርድ ኒክሰን ምንም እንኳን በኮዛ ኖስትራ ዕፅ በዝውውር ላይ ጦርነት ቢያውጁም እንደሌሎቹ ጦርነቶች ሁሉ ውጤታማ ሊሆንላቸው አልቻለም። እንዲያውም የዕፅ ዝውውሩ ዕፆቹ ከሚበቅሉባቸው ከሩቅ ምስራቅ ሀገሮች ጀምሮ ከዚያም በሲሲሊ ማፊያ ተደራጅቶ በአሜሪካ ጎዳናዎች ላይ መታየት ጀመረ።

በ1975 የቱርክ የዕፅና የመሳሪያ ንግድ ኮንትሮባንዲስቶች ከኮዛ ኖስትራ ጋር የቅርብ ትስስር ፈጠሩ። ከዚህ ጊዜ በኋላ የዕፅ ማበልፀጊያ ላብራቶሪዎች በምዕራብ ሲሲሊ የኬሚስትሪ ባለሙያዎች በሚገባ ተደራጁ። ከዚህ ጊዜ በኋላ በምዕራብ አውሮፓና በአሜሪካ በሚገባ ተደራጁ። የአደንዛዥ ዕፅ ተጠያቂዎች ቁጥርም እጅግ በዛ። ከ1974-1978 ባለው ጊዜ እንኳ የተጠቃሚዎች ቁጥር ወደ ሰባት በመቶ ጨምሮ እንደነበር ማስረጃዎች ይጠቀማሉ።

የሲሲሊ ማፊያዎች ራሳቸው የዕፅ ዝውውሩ ዋና አንቀሳቃሽ ለመሆን ባላቸው ፍላጎት የግድ የማከፋፋያ ድር ለመዘርጋት ተነሳሱ። ለመጀመሪያ ጊዜ ቶማሶ ቡስኬታ ከኒዎዮርኩ ጋምቢኖ የማፊያ ቤተሰብ ባገኘው ብድር አንድ ፒሴሪያ አቋቋመ። እንዲህ እንዲህ እያለ የኢጣሊያ የምግብ ዝግጅት ድሮች በአሜሪካ ማፊያ እየተስፋፉ ሄዱ። የአሜሪካ የፒሳ ንግድ ትስስር ማፊያ በሚቆጣጠራቸው አማካይነት እነ «ማርጋሪታ» ወይም «ኩዋትሮ ፎርማጂ» ዓይነት ኩባንያዎች ተስፋፉ። ስለዚህ የፒሳ ማከፋፊያዎች የማፊያ የአደንዛዥ ዕፅ ማዘዋወሪያ ማዕከሎችም ሆኑ።

በ1982 እንደተገመተው የሲሲሊ ማፊያ በሰሜን ምስራቅ አሜሪካ ውስጥ የዕፅ ማበልፀጊያ፣ መጫኛና ማዘዋወሪያ ድሮችን 80 በመቶ ተቆጣጥሮ ነበር። ከዚህ የሚገኘውም ትርፍ በቀጥታ ወደ ሲሲሊ የሚዘዋወር ሲሆን በዓመት በመቶ ሚሊዮን ዶላሮች ወደዚች የማፊያ ዕንብርት ይዘንብ እንደነበር ታማኝ መረጃዎች ጠቁመዋል። ለዚህም ነው

ኮዛ ኖስትራ ከማናቸውም ጊዜ ይበልጥ በ1970ዎቹ ከበርቴ ድርጅት ሆነ የሚባለው።

የፒሳ ትስስሩ ለማፊያ ሌላ ጠቃሚ ጉዳይም ነበረው። ከአሜሪካው ኮዛ ኖስትራ ይልቅ ለሲሲሊው ማፊያ የኃይል ሚዛን እንዲጠበቅ እገዛ አድርጓል። ይኸውም በሲሲሊያውያኑ ወገን ራሳቸውን ለአሜሪካው ኮዛ ኖስትራ ርካሽ ጉልበታቸውን እንዳይሸጡ ሲያደርግ በአሜሪካ ውስጥ በሚያካሄዱት የዕፅ ዝውውር በራሳቸው የመወሰን አቅም እንዲያገኙም ረድቶአቸዋል። የኒውዮርኩ ኒኬርብሮከር ጎዳና ለቦናኖ የማፊያ ቤተሰብ ዋነኛው የዕፅ ዝውውር መናኸሪያ ሆኖ ማገልገሉን ቀጠለ። በኮዛ ኖስትራ የፊላደልፊያ የማፊያ ቤተሰብ ውስጥ ሰርጎ የገባው አንድ የመረጃ ሰው እንዳረጋገጠው ቡርክሊን ማለት ለኢጣሊያ አሜሪካውያን የሲሲሊያውያን ግዛት ነው ማለት ይቻላል። በአሜሪካ ውስጥ የሚካሄደውን የዕፅ ዝውውር የሚቆጣጠሩት እነሱ ናቸው። ሲሲሊያውያኑ ዕፅ ለማዘዋወር የጣሊያን- አሜሪካ ዝርያ ያላቸውን ይጠቀማሉ ብሏል።

የሲሲሊ ማፊያዎች ራሳቸውን በአሜሪካ ውስጥ ከማቋቋም አልፈው ዋነኛውን የኮዛ ኖስትራን የስልጣን እርከን ለመያዝ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ይህንን በተመለከተ የFBI አባል የሆነው ዮሴፍ ፒስቶን (በቅፅል ስሙ ዶኒ ብራስኮ) በኒው ዮርክ የቦናኖ የማፊያ ቤተሰብ ውስጥ ሰርጎ ከገባ በኋላ በአሜሪካ ሁለት የማፊያ የክብር ሰዎች ራሳቸውን አዛዥና-ናዛዥ ለማድረግ የነበራቸው ዕቅድ አስመልክቶ እርስ በእርሳቸው ያደረጉትን ውይይት እንደሚከተለው ተከታትሎታል።

«እነዚህ የሲሲሊ ሰዎች (የአሜሪካ ማፊያዎች ZIPS ይሏቸዋል።) ሁሉን ነገር ለመያዝ ይፈልጋሉ። እነሱን ዋና አለቃ የምናደርግበት ምንም አይነት ሁኔታ የለም። ያን ካደረግን ጥንካሬያችንን እናጣለን። በአጋጣሚ ስልጣንን ከያዙ ይቀብሩናል። ፈፅሞ ስልጣን ሊይዙ አይገባም። ማን አለቃ ይሁን ለእነሱ ማንም ምንም አይደለም፤ ቁብ አይሰጡትም። ፈፅሞ ክብር አይገባቸውም» የሚል ነበር።

ምንም እንኳን የአሜሪካ ማፊያዎች ስጋት ቢያድርባቸውም በ1979 የሲሲሊው የክብር ሰው ነበር የኒውዮርኩን የቦናኖን የማፊያ ቤተሰብ ለሁለት ዓመታት ሲመራ የቆየው። ሥልጣኑንም ኋላ ላይ የለቀቀው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ለመስራት በመቸገሩ ነበር።

የአሜሪካና የሲሲሊ ማፊያዎች ዘመዳሞች ቢሆኑም በእጽ ዝውውሩ ንግድ ግን ሁሌም ባላንጣዎች ነበሩ። አንድ ማፊያ የሚመቸውን የቢዝነስ ሰውና ሰራተኛ ከፈለገ ሁሌም ትኩረቱ በደም ወደ ተሳሰረው ወገኑ ነው። በ1970ዎቹ አብዛኛዎቹ የማፊያ የክብር ሰዎች ሀብታሞች ሆኑ። በተለይ በሲሲሊ የባህር ዳርቻ ያሉ ከተሞች በቀጥታ በዕፅ ዝውውሩ ከአሜሪካ ኮዛ ኖስትራ ጋር ግንኙነት ስለነበራቸው የዕድሉ ተጠቃሚዎች ነበሩ።

ከዚህም ውስጥ ጥቂቶቹን ብንጠቅሳቸው የዶንታኖ ባልዳሜንቲ ከተማ ሲሲሊ አንዷ ስትሆን፤ ሌላኛዋ ከተማ ደግሞ ካስቴላማሬ ዴል ጎልፎና የአሜሪካ ሲሲሊ ማፊያ ማጋዲኖስና ቦናኖስ ተጠቃሾች ናቸው። የፓሌርሞ ከተማም ተመሳሳይ ግንኙነት ነበራት። የፓሶ ዲ ሪጂኖ የማፊያ ቤተሰብም የዚሁ ንግድ ተጠቃሚ ሲሆን እነዚህ ሁሉ ቤተሰቦች ከአትላንቲክ ማዶ እየተቀባበሉና አንዱ ቤተሰብ ከሌላው ጋር ጋብቻ እየፈፀመ ራሳቸውን አፈረጠሙ። በኋላም ላይ ጉዳያቸው ፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ዳኛ ፋልኮኔ የቤተሰብ ግንኙነታቸውንና ትስስራቸውን በሚመለከቱበት ጊዜ ራሳቸውን ይዘው ነበር የጮኹት።

የዕፅ ዝውውር ህገ-ወጥ አሰራር በመሆኑ የርስ በርስ ግንኙነትን ይፈልጋል። ኢንቬስተሮችን፣ አቅራቢዎችን፣ ቴክኒሺያኖችን፣ አከፋፋይ፣ አጓጓዦችና እንዲሁም በየከተማው መንገዶች ላይ አዘዋዋሪዎችን የዕፅ ዝውውር ሥራ ያገናኛል። የኢጣሊያን የፊናንስ ፖሊስ ማታለል ይፈልጋል። ሌላው ደግሞ ትስስሩ ዓለማቀፋዊ በመሆኑ በማህበረሰቡ ውስጥ ከታች እስከ ላይ ድረስ ተንሰራፍቶ መንቀሳቀስን ይፈልጋል።

ማፊያዎች በዕፅ ዝውውር ተግባር ላይ ይካፈላሉ እንጂ የዕፅ ዝውውር ብቸኛ ቱጃሮች ናቸው ብሎ መደምደም ግን አይቻልም። በእርግጥ ግን የማፊያ የተለያዩ ቡድኖች ዕፅን በማዘዋወር ረገድ በራሳቸው መንገድ ሊሰሩ ይችላሉ። ይህም ሲባል ግን ገደብ የለሽ ነው ማለት አይደለም። ምክንያቱም እያንዳንዱ የክብር ሰው የሚያካሄደው ነገር በኮዛ ኖስትራ እንቅስቃሴ ላይ የራሱ የሆነ ተፅእኖ አለው። አንድ የኮዛ ኖስትራ ቤተሰብ ከሚያገኘው ገቢ ታክስ የማስከፈል መብትም ተሰጥቶታል። ለማፊያ አለቆች ግን ቀላሉ የገቢ መንገድ በዕፁ ዝውውር ለሚሳተፉት ከለላ መስጠት ነው።

እስካሁን በማፊያ አሰራር እንደታየው ትርፍ እየደለበ ሲሄድ በማፊያ ቤተሰብ መካከል ያልተገባ ፉክክርን ስለሚፈጥር የማፊያ ከፍተኛ የአመራር ኮሚሽን ጣልቃ ገብቶ ችግሩን ይፈታል፡፡ በዚህ ጊዜ ግን ከዕፅ ዝውውሩ የሚገኘው ትርፍ ለሁሉም የማፊያ ቤተሰቦች የሚከፈል ይሆናል፡፡

## የባንክ ገዢዎች፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ማፊያዎች

በሀገረ-አሜሪካ ከዕፅ ዝውውር የሚገኘው ገንዘብ በእያንዳንዱ የሲሲሊ ቤተሰብ ውስጥ ያልታሰበ የሀብት ዝናብ አዝንቦ ነበር፡፡

ሲሲሊያውያኑ ቤተሰቦች የድሎት ቡቲኮችን በመክፈት፣ ባህር ዳርቻ ላይ ቪላ ቤቶችን በመገንባት ህጋዊና ህጋዊ ያልሆኑ ንግዶችን በኢጣሊያንና በአውሮፓ ማስፋፋታቸውን ቀጠሉበት፡፡ የዕፅ ዶላር በሲሲሊ የፋይናንስ ሴክተር ውስጥ እስከ ቅርንጫፍ ባንኮች ድረስ ተረጨ፡፡ የኢጣሊያ የባንክ ስርአት በፖለቲካዊ ሙስና ውስጥ እየተሳተፈ አትራፊ ሆነ፡፡ ከገንዘብ ጋር ተከትሎ ማፊያም የማህበረሰቡ የሀብት ቁንጮ ሆኖ ብቅ አለ፡፡

ዳኛ ጆቫኒ ፋልኮኔ በ1978 በፓሌርሞ ፍ/ቤት ተገኙ፡፡ በሁለት ዓመት ውስጥ «የፋልኮኔ ዘዴ» የኮዛ ኖስትራ የዕፅ ዝውውር ንግድን በተመለከተ አዲስ የምርመራ ግኝትን አበሰረ፡፡ ይህ የዕፅ ዝውውር የማፊያ አለቃ የሆነውን ሳልቫትሬ ኢንዜሪሎ የብሩክሊኑ «ቼሪ ሂል ጋምቢኖስን»፣ ታዋቂውን የግንባታ ባለሀብትና ከፍተኛው የሲሲሊ ታክስ ከፋይ የነበረውን ሮሳሪዮ ስፓቶላን፣ ካቴ ፋኖ ቦንታኔታን ያካካ መሆኑን ግኝቱ አጋልጧል፡፡ እነዚህ ሶስት ሰዎች የጋብቻ ትስስር እንዳላቸውም ታውቋል፡፡

ዳኛ ፋልኮኔ ከሚላን የአቃብያነ-ህግ ሰዎች ጋር በኢጣሊያ ማህበረሰብ ውስጥ የታየውን የሙስናና የነፍስ ማጥፋት ወንጀሎችን በጥብቅ መከታተሉን ቀጠሉበት፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ማፊያ የሚያካሄደውን ፀረ ዲሞክራሲ ሴራና በከፍተኛ የመንግስት አካላት የሚያካሄዳቸውን ፖለቲካዊና በገንዘብ ተቋማት ውስጥ የሚታየውን ቅጥ ያጣ ሙስና በፍትህ አካሉ በኩል ይፋ እንዲወጣ ማድረግ ነበረባቸው፡፡

ዳኛ ፋልኮኒ የያዙት ጉዳይ ታዋቂውን የባንክ ሰው ሚኬሌ ሲንደናን ዓላማ አደረገ፡፡ በ1970 ዎቹ መጀመሪያ ሲንደና በኢጣሊያ ውስጥ ተፅእኖ ፈጣሪ የባንክ ሰው ነበር፡፡ ከዚያም በአሜሪካ ላለ የአንድ ታዋቂ ባንክ ተጠሪ ሲሆን የቫቲካንን የውጭ ኢንቨስትመትም ይቆጣጠራል፡፡ በፖለቲካ መስመሩ ደግሞ የክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፖለቲከኞችን በገንዘብ የሚደጉም ጎምቱ ሰው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለኮዛ ኖስትራ ህገ-ወጥ ገንዘብ በማዘዋወር ይጠረጠራል፡፡ በ1974 ዕድሜ ለፍትህ ስርአቱ ይሁንና በማጭበርበር ወንጀል ከተከሰሰ በኋላ የያዛቸው የፋይናንስ ተቋማት ወደቁ፡፡ በዚህ ጊዜ ወደ አሜሪካን ሀገር ተሰደደ፡፡ ከአሜሪካ በመሆን በ1979 በኢጣሊያ እሱ ይዟቸው የነበሩት የገንዘብ ተቋማት እንዲዘጉ የፈረደውን ዳኛ በማፊያ በኩል እንዲገደል አድርጓል፡፡ በኋላም ላይ በኮዛ ኖስትራ ውስጥ ባደረጋቸው የተለያዩ ሻጥሮች አማካይነት በፖሊስ እጅ ወደቀ፡፡ በ1986 በሳይናይድ የተመረዘ ቡና ጠጥቶ እስር ቤት ውስጥ ሞተ፡፡

በ1982 በጋ ወራት ውስጥ ሌላው የኢጣሊያ የባንክ ሰው ሮቤርቶ ካልቪ ብቅ አለ፡፡ ካልቪም እንደ ሳንድራ በሀብትና በሥልጣን ላይ ተሸጋገረ፡፡ ከቫቲካን ጋር ትስስሩ ጠበቀ፡፡ ለገዥ ፓርቲዎች ገንዘብ እየደጎመ ታዋቂነቱ ፈረጠመ፡፡ በኋላ ግን አወዳደቁ አላማረም፡፡ ፈጥኖ ወደ ሀብትና ወደ ስልጣን እንደወጣ ሁሉ የኪሳራ ካባ ተከናነበ፡፡ እንዲያውም በመጨረሻ ራሱን ገደለ ተባለ፡፡ ሆኖም ኋላ ላይ እንደተረጋገጠው ሲንደራ ጋምቢኖ፣ ስቶላና ቦንታቴ የማፊያ ቡድኖች የዕፅ ገንዘብ ሲያዘዋውር እንደነበረው ካልቪኖ ለኮርሊኦኔሲ የማፊያ ቡድን የዕፅ ገንዘብ ሲያዘዋውር ቆይቶ ለማፊያ ታማኝ አለመሆኑ በመረጋገጡ መገደሉን አንድ የማፊያ ወዶ ገብ ገልጿል፡፡

ከላይ የተመለከትናቸው ሳንድራና ካልቢ የተባሉት የባንክ ገዢዎች የማሶኒክ ቡድን ወይም «ፕሮፓጋንዳ 2» ተብሎ የሚታወቀው አካል አባላት ነበሩ፡፡ በሚላንና በሲሲሊ በተደረገው ምርመራ የማሶኒክ ቡድን 962 አባላት የስም ዝርዝር በዋና አለቆቻቸው በሊቼኦ ጄሊ ቢሮ ተገኝቷል፡፡ በኋላም የፖለቲካው የሲቪል ባለስልጣናትና ጋዜጠኞች ተገኝተዋል፡፡ የፓርላማው የምርመራው ቡድን እንዳረጋገጠው «የፕሮፓጋንዳ-2» (P-2) ዋና ዓላማ ዲሞክራሲንና የህዝብን ኑሮ ማመሳቀል ነው» ሲል ገልፆታል፡፡ በማፊያና «በማሶኒክ ቡድን» መካከል

ያለው ግንኙነት ግልፅ ነው። ከ1970 ዎቹ በኋላ ብዙዎቹ የማፊያ የክብር ሰዎች የማሶኒክን ቡድንን ተቀላቀሉ። ዓላማቸውም ከታወቁ ነጋዴዎች፣ ፖለቲከኞችና የመንግስትን ቢሮክራሲ ከሚያሽከረክሩ ሰዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር በሀገሪቱ ውስጥ ተፅእኖ መፍጠር ነበር። በሁለቱ ቡድኖች ውስጥ አባል በሆኑ ሰዎች መካከል የጥቅም ግጭት መከሰቱ አይቀሬ ሲሆን በዚህ ጊዜ ግን ምንጊዜም ቀዳሚው የኮዛ ኖስትራ ጥቅም ነው። የኮዛ ኖስትራን (ማፊያን) ጥቅም የሚነካ አባል በማሶኒክ ቡድን ውስጥ ከተገኘ ወዲያው መወገዱ አይቀሬ ነው። ለዚህም ነው ሁለቱ የባንክ ሰዎች ታማኝነታቸው ሲያጠራጥር ሊወገዱ የቻሉት። አንድ የማፊያ ወደ ገብና የሁለቱን ቡድኖች ትስስር የሚያውቅ አባል እንደተናገረው «የማሶኒክ መሀላ የውሸት ነው። እኛ ሁሌም አጥብቀን የምንከተለው የኮዛ ኖስትራን መሀላ ብቻ ነው!» ብሏል።

ሁለቱ ሀብታም የባንክ ሰዎች የሁለቱንም መሀላ ተቀብለዋል። ሁለቱም ሰዎች የኒኖና የኢግናዞ የአጎት ልጆች ሲሆኑ በተለይ ኒኖ ሳልቮ የሳልሚ ማፊያ ቤተሰብ የክብር ሰው ነው። በሲሲሊ ታክሶች የሚሰበስቡት በተፈቀደለት የግለሰብ ኩባንያ በኩል በመሆኑ ሳልቮ ይህን ስራ ተረክቦ ይሰራው ነበር። በዚህ ሥራ ብቻ በዓመት የ2 ሚሊዮን ትርፍ አግበስብሶበታል። በእንዲህ አይነት ቤተሰባዊና ፖለቲካዊ ትስስር ማፊያ ከህዝብ የሚሰበስበውን ታክስ በረቀቀ ዘዴ ለራሱ የትርፍ ማጋበሻና ውንድብና ድጋፍ እንዲሰጥ ጠንካራ የገንዘብ አቅምን ይፈጥራል።

ይህ ሁሉ የመንግስት ሀብት ምዝበራ ከጠንካራ የፖለቲካ ድጋፍ ውጭ ይከወናል ተብሎ አይታሰብም። በዚህ በኩል ደግሞ ለማፊያ ሁኔታዎችን የሚያመቻቸው የሲሲሊ ክልላዊ ምክር ቤት ነው። በቀረጥ ሰብሳቢዎች (በሳልቮዎች)፣ በባንክ ገዢዎች፣ በክርስቲያን ዲሞክራሲ ፓርቲና በማፊያ መካከል ያለው የእከክልኝ ልከክልህ ፖለቲካ ነው የሲሲሊን የፖለቲካ ስርአት ማፊያዊ ያደረገው።

በ1982 ዳኛ ፋልኮኔ የሳልቫ ቤተሰቦችን ጉዳይ ኦዲት እንዲደረግ አዘዙ። ዳኛው በቀጥታ ከኮዛ ኖስትራ ጋር ግንባር ለግንባር ተጋፈጡ። የማፊያ የዕፅ ዝውውር ንግድም እንዲሁ እየጦፈና ሥር እየሰደደ የማፊያ የደም አካል ሆነ።

# የኮርማዎቹን ውጊያ መመልከት

ጆቫኒ ፋልኮኔ (ዳኛ) እና ፓውሎ ቦርሴሊኖ የቆዩ ጓደኛሞች ናቸው። በወቅቱ በማፊያ ወንጀለኞች ላይ የመጨረሻው ርምጃ እንዲወሰድ ጉዳዮቹን ሁሉ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ጨርሰው ያቀርባሉ። ሁለቱም የዕድሜ አቻዎች በፓርሌሞ አንዲት አነስተኛ ጥጋት መካከለኛ ገቢ ካላቸው ወላጆች ተወለዱ። የፋልኮኔ አባት የኬሚስትሪ ባለሙያ ሲሆን የቦርሲሊኖ ደግሞ ፋርማሲስት። ሁለቱም ሰዎች በሥራዎቻቸው ባተሌዎችና በፍትህ ሥርዓቱም ከፍተኛና የማይናወጥ ዕምነት ነበራቸው። በአንድ ነገር ግን ይለያያሉ - በፖለቲካ መስመሮቻቸው። ፋልኮኔ ምንም ዓይነት የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ሳይኖረው የግራ-ክንፉ የፖለቲካ መስመር ደጋፊ ነው። ቦርሲሊኖ ደግሞ የኒኦ-ፋሺስት ቡድኑን በወጣትነት በመቀላቀል የካቶሊክ ክርስትና ዕምነቱን ከፋልኮኔ ይልቅ አጥብቆ በመያዝ ኑሮውን ይመራል። ታዲያ ሁለቱም የአቃብያነ-ሕግ ሙያተኞች ማንኛውንም ከፖለቲካ ፓርቲዎችና መስመሮች የሚመጡ ተፅዕኖዎችን አጥብቀው በመከላከል ክቡሩን ሙያቸውን ያስጠብቃሉ።

ሌላው ልዩነታቸው ደግሞ ለሚኖሩባትና ለሚሠሩባት ከተማ ሁለቱም የተለያየ አመለካከት አላቸው። ፋልኮኔ በግለሰባዊ ማንነቱ የተለየና የፓርሌሞ ከተማ ሕዝብ ስለሥራው ያለው ድጋፍ ደብዛዛ እንደ ሆነ በማሰብ ጭፍንነት ይታይበታል። ወደሥራው ሲሄድ ሁሌም የጥይት መከላከከያ ጃኬቱን ለብሶ፣ በታጠቁ አጃቢዎቹ መትረየስ አስደግ የጥይት መከላከከያ ጃኬቱን ለብሶ፣ በታጠቁ አጃቢዎቹ መትረየስ አስደግ ኖና እሱ በሚጓዝበት አውራ ጎዳና ከሰማይ ሔሊኮፕተር እያንዣበበ ጠብቆት ወደቢሮው ያመራል። «ጆርናሌ ዲ ሲቺሊያ» ጋዜጣ ላይ በወጣው የአንባቢ ደብዳቤ መገመት እንደሚቻለው በእሱ ጠባቂዎች አማካይነት መንገዱ ስለሚዘጋጋ የከተማው ነዋሪ ትልቁ ችግራቸው ከማፊያ ይልቅ ይህ መሆኑን አጥብቀው ጽፈዋል። በአንድ ወቅት አንድ ጎረቤቱ እሱ በፈጠረው የመንገድ መጨናነቅ ተማሮ ከከተማው ወጣ ብሎ ለመኖር እንደተገደደ በፃፈለት ጊዜ ፋልኮኔ በእጅጉ ተናዶ እንደነበር ይነገራል። ባርሴሊኖ ግን ከዚህ በተለየ ደህንነት የሚሰማውና በሥራውም ውጤት ከተሜው «በርቱ ተበራቱ» እያለ እንደሚያሞካሸው የሚያምን ሰው ነው።

በሲ.ሲ.ሊ. በተከሰተው የፀረ-ማፊያ እንቅስቃሴ ሁለቱም ሰዎች በሥራቸው ጥንካሬን አገኙ፡፡ በሲ.ሲ.ሊ. መንገዶች ላይ ተማሪዎች ሳይታክቱ ፀረ-ማፊያ ሰላማዊ ሠልፎችን አጠናክረው ገፉበት፡፡ የተደራጁ ቡድኖች በፀረ-ማፊያ ላይ ያተኮረና በፒፒኖ ኢምፓሳቶ ስም የተሰየመ የጥናትና ምርምር ማዕከልን መሠረቱ፡፡ በሲ.ሲ.ሊ የማፊያን ስም ጠርቶ ማውገዝና የመንግስትን ልል ርምጃዎች መተቸት የሚፈራ አልሆነም፡፡ እንዲያውም ጎልብቶ ቀጠለበት፡፡ የታችኛው አካል የሀይማኖት አባቶች ሳይቀሩ በማፊያ ተቃዋሚ ረድፈኝነት ሆነው ተቃውሞአቸውን አጋጋሉት፡፡

በክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲው ወገን የነበሩ እንኳ ሳይቀሩ ኃይላቸውን አስተባበሩ፡፡ በሐምሌ 1985፣ ሊዩሉካ ኦርላንዶ የተባለው ሰው ከክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲው ለከንቲባነት ተመረጠ፡፡ ይህ ሰው የማፊያ ተቃዋሚ ሲሆን የከተማው ምክር ቤት በማፊያዎች የፍ/ቤት ሂደት ውስጥ የሕዝብን ድምፅ እንዲያሰሙ መወከል አለባቸው ሲል በርትቶ የታገለ ነው፡፡ በዚህ መንፈሱ የተነሳ ይህ ከንቲባ እንቅስቃሴው «የፓርሌሞው ፀደይ» እስከመባል ደርሶ ነበር፡፡ እንዲያውም ሆኖ ግን የብዙዎቹ የፓርላማ አባላት ከአቅብያኔ-ህጎቹ ትግል አንፃር ሲታይ ሚናቸው ያልለየ እንደነበር ፋልኮኔ ገልፆታል፡፡ «የከተማዋ ሰዎች የኮርማዎቹን ውጊያ እንዴት እንደሚጠናቀቅ ከመስኮቶቻቸው ሆነው በባይተዋርነት የሚመለከቱ ይመስላል» ሲሉ ነበር ፋልኮኔ የገለፁት፡፡

ከአቃብያኔ-ህጎቹ የተቀነባበረው ፀረ-ማፊያ ከፍተኛ የፍርድ ሂደት የካቲት፣ 1986 ተጀመረ፡፡ ከዚያም ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ቀጠለ፡፡ የፍትህ ሂደቱ መታየት እንደጀመረ ውጥረት የተሞላበት አስፈሪ ድባብ ፓርሌሞ ላይ ጥልማሞቱን ጣለ፡፡ የኮዛ ኖስትራ ስኳዶች ህቡዕ በመግባት ፍ/ቤቱ በኮዛ ኖስትራ ላይ የሚያደርገውን የፍርድ ማጣራት ይከታተላሉ፡፡ በኡሲያደን እሥር ቤት ያለው ሁኔታና የሕዝቡ ስሜት የኢጣልያ መንግሥት በኮዛ ኖስትራ ላይ መጨከኑን ያመላከተ ነበር፡፡ በወቅቱ አንድ ጋዜጠኛ «አንድ ትልቅ መንኮራኩር ፓርሌሞ ላይ እንዳረፈ ይቆጠራል» በማለት ነበር ሁኔታውን የገለፀው፡፡ ዋናው የፍርድ ቤቱ አዳራሽ አረንጓዴና ኦክታጎን ቅርጽ ያለው ሲሆን ተከሳሽ ማፊያዎች የሚቆሙበት ሰላሳ የእሥረኛ ማቆሚያ ሥፍራ ነበረው፡፡ በእነዚህ የእሥረኛ ማቆሚያዎች 208 እጅግ አደገኛ ማፊያዎች ቆመውበታል፡፡ በጠቅላላው

474 ማፊያዎች በፍርዱ ሂደት ውስጥ ጉዳያቸው የሚታይ ሲሆን 119ኙ ደግሞ እጃቸው ገና ያልተያዘና ከፖሊስ ኃይል እየተሹለኮለኩ የሚደበቁ ናቸው። ለፍርድ ከቀረቡት ውስጥ ቀንደኞቹ ሉቺያኖ ሌጂዩ፣ «ድንክዬው» ሪናና «ትራክተሩ» ፕሮቬንዛኖ ይገኙበታል። ከእሥረኛ ማቆሚያ ሳጥን (ጉረኖ) ቁጥር 23 ውስጥ በመጀመሪያ ለፍርድ ቤቱ መልስ የሰጠው ሰማያዊ የሩጫ ልብስና የቴኒስ ጫማ የተጫማው ሌጂዩ ሲሆን ባቀረበው መልስ ራሱን ለመከላከል የግል ጠበቃ እንደሚያቆም ገለፀ።

የፍርድ ሂደቱ እንደተጀመረ ጋዜጠኞቹ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠታቸው የሕብረተሰቡን ስሜት ሰቅዘው ያዙት። ዳሩ ግን ብዙዎቹ የፓርሌሞ ሰዎች በግልፅ የሚሰማቸውን ለመግለፅ ፈቃደኞች አልነበሩም። አንዳንዶቹ እንዲያውም በይፋ የፍርዱን ሂደት ተቃወሙ። ሌሎች ደግሞ የተያዘው ፍርድ ውጤት አያመጣም ሲሉ በቀቢፀ-ተስፋ ተናገሩ። «አስቂኝ ትዕይንት ነው። ትላልቆቹ ፖለቲከኞች እንዴት የፍርድ ሂደቱ እንደሚያልቅ ይወስናሉ» ሲሉ በሁኔታው ያላቸውን ከፍተኛ ጥርጣሬ ገለፁ። ቶማሶ ቡስኬታ (የማፊያ አለቃ) በበኩሉ የማፊያን ሚስጢር ዘክዝካ ለማወቅ ኢጣልያ ገና መሆኗን ሲገልጽ፣ ስለ ትላልቆቹ የመንግሥት ባለሥልጣናት የሚታወቀውን ምስጢር ለማውጣት አለመዘጋጀቱን በተዘዋዋሪ ተነግሯል። በማንታዛ (በማፊያ ጦርነት) ወቅት የተጠዛጠዙት ተራ የሠፈር ወንጀለኞች ናቸው፣ ዋናዎቹና ትክክለኛዎቹ ማፊያዎች ግን ከፍተኛ ቦታ ላይ የተቀመጡ መሪዎች ናቸው ሲሉ ብዙዎች ተቹ።

በማፊያዎች የፍርድ ሂደት ላይ ያለው ተጠራጣሪነት በሕዝብ አስተያየት ላይ ብቻ የቆመ አልነበረም። የሲሲሊ አካባቢ የሕዝብ አስተያየት መሪ የሆኑና ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ሳይቀሩ የፍትህ ሂደቱ ዕውነተኛ ውጤት አልተዋጠላቸውም። የካቶሊኩ ካርዲናል ፓፓላርዶ «ጨቋኝ ትዕይንት ነው» ሲሉ ገለፁ። ስለ ማፊያ ከነበራቸው የተቃዋሚነት ጎራ አፈገፈጉ። እንዲያውም «ከማፊያ ጉዳት ይልቅ ጽንስ ማስጨንገፍ ነው የብዙ ዜጎችን ህይወት የቀጠፈው» እስከማለት ደረሱ። ሚዲያው የሰጠው ትኩረት የፓርሌሞን ዝና የሚበክልና የሚያንቋሽሽ እንጂ ሌላ እርባና እንደሌለው በሰጡት ቃለ-ምልልስ አስታወቁ። ጋዜጠኞች መልሰው ራስዎን ፀረ-ማፊያ አድርገው ይቆጥራሉ? ሲሉ

ለተጠየቁት ጥያቄ «አንድን ነገር በተቃራኒ መንፈስ መገንባት አይቻልም። ፀር መሆን ብቻውን በቂ አይደለም» ሲሉ ነበር አቋማቸውን በግልፅ ያስቀመጡት።

በስሩት የተጀመረው የፍርድ ሂደት እያንዳንዱ በማፊያነት የቀረበው ተጠርጣሪ በግለሰብ ደረጃ እንደየጥፋቱ ደረጃ ፍትህን ያገኛል የሚል ዕምነት እንደሌለ በብዙዎች የሕብረተሰቡ አባላት ዘንድ ተስተውሏል። ከዚህ በተጨማሪ የማፊያ ወዶ-ገቦች (Pentiti) ምስክርነትም ጥርጣሬን አስከትሏል። አቃብያነ-ህጎቹ ያቀረቡት የምስክርነት ቃል ምን ያህል ዕውነተኛ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚቻልበት መንገድ አልነበረም። በ1985 ዕውቁ የቴሌቪዥን ፕሮግራም አቅራቢና ታዋቂ ሰው በናፓሊታን ካሞራ ማፊያ በቀረበበት የሀሰት ምስክርነት ተጎጂ መሆኑ ተረጋግጧል። ብዙዎቹ ጉዳዩን የሚከታተሉ ወገኖች ለመግለፅ እንደሞከሩት በቶማሶ ቡስኬታ የቀረበው ምስክርነት በከፍተኛ ደረጃ ሀቀኞቹን እንደሚጎዳ አመላካች ነበር።

የፍርድ ሂደቱ እምብዛም የገለልተኝነት ክፍተት አልታየበትም። የቶማሶ ቡስኬታ አቀራረብ ማንኛውንም ሲሲሊያዊ የሚያነሳሳና የፍርድ ሂደቱን እንዳይቀበለው የሚያደርግ ነበር። በተለይ አቃብያነ-ህጎቹ ፋልኮኔና ቦርሰሊኖ ስለሚያካሄዱት ምርመራና የፍርድ ሂደት ጉዳዩ ለብዙዎቹ ሲሲሊያውያን ግራ የሚያጋባ ከመሆኑም በላይ የማይቀበሉትም ሆነ። በዚህ መሐል ነው እንግዲህ ሊዩናርዶ ሲያሲያ የተባለ ልዩ ስም ብቅ ያለው።

ሲያሲያ በ1950ዎቹ ስለ ማፊያ ብዙ የፃፈ ደራሲ ሲሆን ማፊያን ለህዝብ ይበልጥ ያስተዋወቀው ሲያሲያ ነው ማለት ይቻላል። በዛሬ ጊዜ እንኳ «የጭልፊቱ ቀን» የተባለው ድርሰት ኢጣልያዊ ያልሆኑ ዜጎች ሁሉ በማንበብ ስለ ማፊያ አውቀዋል። የሲያሲያ ሥረ-መሠረት፣ ጽሑፎቹና ግላዊ ታሪኩ ማፊያዎች በጠላትነት እንዲፈርጁት አድርጓል።

የፍርድ ሂደቱ በተጀመረ በአሥራ አንድ ወራት ውስጥ ሲያሲያ «በኮሪየሬ ዴላ ሴራ» ጋዜጣ ላይ በፃፈው አንድ ሀተታ ፀረ-ማፊያ የሆነ መልካም ዝናውን ሊያንኳስስበት ችሏል። የጽሑፉ ሐተታ የሚጀምረው ከዚህ ቀደም በተከሰተ ጉዳይ በፋሽስታዊው ዘመንና በቦሴሊኖ የሥራ ዕድገት ላይ ነበር። ሲያሲያ በጽሑፉ ለማሳመን የሚጥረው የፍርድ

ሂደቱ የፋሽስት መንግሥት ሲያደርግ እንደነበረው የሲቪል ማህበረሰቡን ነፃነት የሚያፍን ነው በማለት ያረጋግጣል። በተጨማሪም የአቃቤ-ህጉን የቦርሴሉን የሥራ ዕድገቶች በሙሉ በሰፊው በመተቸትና በመኮነን ጽሑፉን ይደመድማል።

በፀረ-ማፊያ አቃብያነ-ህጎች ላይ ብዕሩን ካሾረ በኋላ «የጭልፊቱ ቀን» ደራሲ እስከመጨረሻው የአልጋ ቁራኛ ሆነ። በህይወቱ ውስጥ ያደረጋቸው ማፊያን ለማጋለጥም ሆነ የኢጣልያን መንግሥት ደካማነት በማሳየት በኩል ያደረጋቸው ትግሎች ከንቱ መሆኑን ተረዳ። ይህ ዓይነቱ ድምፅ ግን የእሱ ብቻ ሳይሆን ማፊያንም ሆነ መንግሥትን በማፊያ ጉዳይ በሚያወግዙ ሰዎች ዘንድ የሚሰማ ጩኸት ነበር።

ሲያሲያ ራሱን ከልጅነት ጀምሮ ያስተማረና ከተራ የአግራጅነቶ ክፍለ ሀገር የድኝ ማዕድን ሠራተኛነት ተነስቶ ታዋቂ ለመሆን የቻለ ሰው ነበር። ገና በጨቅላ ዕድሜው የፋሽስት አገዛዝን ጨካኝነትንና ክፋትን የቀመሰ፣ ማፊያዎች ደግሞ የድኝ ማዕድን ሠራተኛ መሪዎችን ከጦርነቱ በኋላ ሲገደሉ የተመላከተና በብዙ የሕይወት መሠናክል ውስጥ የተራመደ ሰው ነው። ለእሱ ሁለቱም (መንግሥትና ማፊያ) ተመሳሳዮች ነበሩ። የሕይወት ልምዱ እንዳስተማረው ሲሲሊ የባለሥልጣኖችዋ የችግር ዳፋ ቀማሽ መሆኗን ደመደመ። በጣልያን መንግሥት ላይ ባለው ጭፍንነት የተነሳ ሲሲሊ ሕይወቷን መለወጥ አትችልም ወደሚል መደምደሚያ ወሰደው። እሱ እንደሚያምነው ከሆነ ማፊያ በውኑ የተደራጀና የነቃ ድርጅት ሳይሆን የሲሲሊ እሥር ቤቶች የፈጠሩትና በሲሲሊያውያን ጭንቅላት ላይ ያተሙት ድርጅት ነው ወደሚል ማጠቃለያ ነበር የደረሰው። ለዚህም ነው ስለ ማፊያና ሲሲሊ እንዲህ ሲል የገለፀው - «ፀረ-ማፊያ ሆኜ ስናገር እንደ ማንኛውም ሲሲሊያዊ ውስጤ እንዲሰቃይ ያደርገኛል። የማፊያ ስሜት ሁሌም በውስጤ ታትሞ ይቀራል። እኔ ከማፊያ ጋር ስታገል ከራሴ ጋር እየታገልኩ ነው ማለት ነው። ይህ በራሱ ለሁለት መከፈል ነው - የማይጠግግ ቁስል።»

# 16

# ማፊያ የኢ-አማኒያን ምድር

አንድ የብሪታንያ የታሪክ ሰው በኢጣልያ መንግሥት ሥር ስለተፈጠረው «ሞራለ ብርቱ ህዳጥአን» ጉዳይ ይናገር ነበር። «ሁሉም ሰው በህግ ፊት እኩል ነው፣ ወይም መንግሥት ከጓደኛና ከቤተሰብ ይልቅ የሁሉንም ዜጎች ፍላጎት መጠበቅ አለበት» የሚለውን ብሂል የሚሠራ መርህ አድርገውና አምነው ይመሩበታል። እንደዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎችን እንግሊዛዊው የታሪክ ሰው ሞራለ ብርቱ ህዳጥአን ብሎ ፈርጆአቸዋል። ይህ ማለት ግን አብዛኛዎቹ ኢጣልያውያን ሙሰኞች ናቸው፣ ወይም የኢጣሊያ ሕዝባዊ ሕይወት የበሰበሰ ነው ማለት አይደለም።

የኢጣሊያ «ሞራለ ብርቱ ህዳጥአን» በ1980ዎቹ በደረሰው ሁኔታ እጅግ ተናደው ነበር። ምንም እንኳ አዲሱ የኢኮኖሚ ዕድገት እየፈረጠመ ቢሄድም የሠራተኛው ንቅናቄ ደግሞ ወደኋላ አፈግፍጎ ነበር። ቀደም ሲል የክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲው ያደርግ እንደነበረው አሁን በተራው የሶሻሊስት ፓርቲው ከመንግሥት ጋር ጥምረትን ፈጥሯል። ይህን ወቅት ኢጣልያኖች «የፓርቲ አገዛዝ» ሲሉ ይጠሩታል። በዚህ ወቅት በንግድ የተሠማሩ ዜጎችና ኮንትራክተሮች የፓርቲ ካርድ ከተሸከሙ ባለሥልጣናት ጋር መሞዳሞድ የግዳቸው ነበር። ከተወረሱ ባንኮች የቦርድ አባላት ጀምሮ እስከ ተራ የፅዳት ሠራተኞች ድረስ በፓርቲ አባልነት ሰበብ ቦታ መያዝ የግድ ሆነ። በዚህ ዓይነት የእከክልኝ ልክክልህ ፖለቲካ ውስጥ የተዘፈቁ ሰዎች ክዛ ኖስትራን ለመጋፈጥ ተነሱ። ይህ የፖለቲካ መደብ ቆራጥ መስሎ ክዛ ኖስትራን ለማነቅ ተነሳሁ ቢልም ክዛ ኖስትራ ደግሞ በገንዘብ አቅም ፈርጥሞና እጅግ ደም የጠማው ድርጅት ሆኖ ብቅ ብሎ ነበር።

ጆቫኒ ፋልኮኔ (ዳኛ) ለአንድ የፈረንሳይ ጋዜጠኛ በተከታታይ በሰጡት ቃለመጠይቅ እንደገለፁት «ራሴን እንደ ሮቢን ሁድ ለመሰዋት የቆምኩ አይደለሁም፤ እኔ በኢ-አማኒያን ምድር የኢ-አማኒያን መንግሥት ተራ አገልጋይ ነኝ» ሲሉ ነበር የገለፁት።

ዳኛ ፋልኮኔ በማንኛውም መንገድ የሞራል-ብርቱ ህዳጥአን አካል ሆነው ድፍረትን፣ ራስን አሳልፎ መስጠትንና ጠንካራ ሠራተኛነትን ያሳዩ ሰው ናቸው። ከሰዎች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ታማኝና ትክክለኛነታቸውን አስመስክረዋል።

ብዙ ጊዜ ዳኛ ፋልኮኔን ኢንተርቪው በማድረግ የሚታወቀው ጋዜጠኛ ፍራንቼስኮ ላሊካታ ከፋልኮኔ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ነበረው። ጋዜጠኛ ፍራንቼስኮ ላሊካታ ከፋልኮኔ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ነበረው። በአንድ አንድ ቀን ግን ከማፊያ ጋር የሚያጋፈጥ ጉዳይ ገጠመው። በአንድ ቡናቤት ቡና እየጠጣ እያለ አንድ ሰው ቀርቦት «ታስታውሰኛለህ?» ሲል ጠየቀው። ይህ ሰው ጊርጎሪዩ ሲሆን ላ ሊካታ ከተወለደበት መንደር የመጣ ነው። ጊርጎርዩ በተቀናጀ የወንጀል ተግባር ዳርቻ የሚኖር ሰው ሲሆን «እስቲ ስለ ጥንቱ የልጅነት ህይወታችን እናውጋ» ሲል ወደ ውጭ እንዲወጡ ጋበዘው። ላ ሊኪታ እየተጠራጠረ በጆርጆ ቮልስ ዋገን መኪና ላይ እንደተቀመጠ ሽጉጥ ጭንቅላቱ ላይ ተደገነበት። ጆርጆ ቀጥሎ «አትጨነቅ ሊያነጋግሩህ የሚፈልጉ ሰዎች አሉ» አለው ፈገግ እያለ።

በመኪናው ይዞት እየተጓዘ ጆርጆ ጋዜጠኛውን እንዴት እንደሚገድለው ያሰላስል ነበር። መኪና ቀይረው ወደ ሎሚ ማሳ ወሰዱት። ከዚያም ጋዜጠኛው ከተመለከተው የፖሊስ ጉርድ ፎቶግራፍ ጋር የሚመሳሰል ሰው ማለትም «ካፖፋሚሊያ» ጋር ፊት ለፊት ተገናኘ። ይህ የማፊያ አለቃ (የካፖፋሚሊያ የማፊያ አለቃ) «እዚህ ስለጋበዝንህ ይቅርታ እንጠይቅሃለን፤ እንደምታውቀው ከህግ ተሸሽጌ ነው ያለሁት። ስለ አንተ እናውቃለን፤ አንተ ደግሞ ዕምነት የሚጣልብህ ሰው ነህ፤ ሥራህንም በታማኝነት ታከናውናለህ» አለው። ቀጠለ የማፊያ አለቃ «ከዳኛ ፋልኮኔ ጋር መነጋገር እንዳለብን እናውቃለን። ተራ የስም ማጥፋት ዘመቻ እንደተከፈተብን ለዳኛው ንገረው። መናገር ያለብኝን ነገር ሁሉ ነግሬሃለሁ» ሲል ንግግሩን አሳጠረ። በዚህ የመክፈቻ ንግግሩ የማፊያ አለቃ ከዳኛው ማግኘት የፈለገውን ሁሉ በአጭርና ግልፅ ቋንቋ ነበር ያስተላለፈው።

እንዲህ ዓይነቱን የማፊያ አለቃ ትዕዛዛዊ ጥያቄ መጋፈጥ ከንቱ ድካም መሆኑን ሳሊካታ ያውቀዋል፡፡ በለሰለሰና ደርዝ ባለው ቋንቋ ግን እንዲህ ሲል ተናገረ፡፡ «ከዳኛ ፋልኮኔ ጋር በእንደዚህ ዓይነቱ የማፊያ ጉዳይ መነጋገር ለምርመራ ስለሚዳርገኝ ከዚያ ይልቅ በኢንተርቪው መልክ ቢቀርብ መልካም ነው» ሲል በጥሞና አስረዳው፡፡ የማፊያ አለቃው መልስ ግን ግልፅና አጭር ነበር «ለዚህ ጉዳይ አልታዘዝኩም፤ እንደዚህ ዓይነት ነገር አናደርግም» አለው፡፡ ከዚህ በኋላ ጋዜጠኛው ሁለተኛ ሀሳቡን ሰነዘረ ለዳኛ ፋልኮኔና ለሚዲያ አጭር ማስታወሻ ቢላክ ደግሞ የተሻለ ዘዴ መሆኑን ለማሳመን ሞከረ፡፡ «በጣም ጥሩ፤ ማለፊያ ሃሳብ ነው እንዲያ ከሆነ ያ ቀሳጢ ዳኛ ጥቃት አይወስድብንም» ሲል በቀረበው ሃሳብ ተስማማ፡፡

በእንዲህ ዓይነት ምልልስ ጋዜጠኛው ሕይወቱን ታደገ፡፡ ወዲያውም ምንም ጉዳት ሳይደርስበት ከተወሰደበት ቡናቤት እንዲመለስ ተደረገ፡፡ ከዳኛ ፋልኮኔ ጋር ባደረጉት ውይይት በወቅቱ ይህን ሁኔታ ነግረኸኝ ቢሆን ኖሮ ምርመራ እንዲደረግብህ አዝ ነበር ሲሉ ዳኛው ነገሩት፡፡ ዳሩ ግን የሁለቱ ጓደኝነት እንደቀድሞው ቀጠለ፡፡

## ቁንጮ አስከሬኖች

ከዚህ ቀደም በዚህ ጽሑፍ ላይ እንደተወሳው አማኑኤል ናታርባራቶሎ፤ ማለትም የታወቀው የባንክ ሰውና የፓርሌሞ የቀድሞው ከንቲባ በ1893 በጩቤ እንደተገደለ ተገልጿል፡፡ ጆ ፔትሮሲኖ የኒውዮርኩ ፖሊስም እንዲሁ በ1909 በሲሲሊ ተገድሏል፡፡ በመጀመሪያው የማፊያ የምሥረታ ጊዜ ውስጥ የተገደሉት ሁለት ዕውቅ ሰዎች ብቻ ነበሩ፡፡ በኋላ ብዙ መወገድ ያለባቸው «ቁንጮ አስከሬኖች» በየቦታው ወድቀዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ የማፊያ አለቆችን ትዕዛዝ አናከብርም ያሉ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ግን የኮዛ ኖስትራ ቀጥተኛ ጠላቶች ነበሩ፡፡ ከ1979 በኋላ ማፊያ ከቱባ የማፊያ ኃላፊዎች ጋር ፍልሚያ በማድረግ የቆየበትና በዚያው መጠን ደግሞ ፀረ ማፊያ ኃይሎች ኮዛ ኖስትራን ለመጋፈጥ ሁነኛ ትግል ያደረጉበት ጊዜ እንደነበር ይታወሳል፡፡

ወደኋላ ስንመለከት፣ አዲስ የኮዛ ኖስትራ ጥቃት በ1970 ሲሰነዘር አሀዱ ያለው የሊኦራ (L'Ora) ጋዜጣ የምርመራ ጋዜጠኛን ማውሮ ዲ ማውሮን በማስወገድ ነበር፡፡ በ1971 ደግሞ የፓርሌሞ አቃቤ-ህግ

የነበረው ፔትር እስካሊዩን የሚች ሚስቱን መቃብር ለመጎብኘት እንደሄደ በማፊያ ጥይት እዚያው ተደፋ። በወቅቱ ይህ ግለሰብ ሲገደል የቪቶ ሲያንሲኖ የቁማር ጓደኛ ስለነበር የማፊያዎች የርስ በርስ ግጭት ተደርጎ ነበር የታሰበው። ሌላው ቀርቶ የወታደራዊ ፖሊሶቹ ኮሎኔል ግድያ እንኳ የተወሰደው በተሳሳተ መንገድ እንደነበርና በተከታታይ ጋዜጠኛን (የጆርናሌ ዲ ሲሲሊያ የወንጀል ሪፖርተርን)፣ የፖሊስ አዛዦችን (የፓርሌ ፈጥኖ ደራሽ አዛዥ)፣ አቃቤ ህጎችን (ሲሳሬ ቴራኖቫ የተባለውንና የመጀመሪያውን የማፊያ ጦርነት ምርመራ ጉዳይ የመራው ሰው) ማፊያ አከታትሎ ፈጅቷቸዋል።

ከላይ ከተጠቀሱት ውስጥ አንዱ ቴራኖቫ የተገደለው በፓርሌሞ ቤቱ በራፍ ላይ ከሰላሳ ጥይት በላይ ተኩሰው አካባቢውን ድብልቅልቁን በማውጣት ሲሆን በቀድሞው የአቃቤ ህግ ጽ/ቤትና አስተዳደር ላይም ተታኩሰዋል። በተከታዩ ዓመት በ1980 ሶስት «ቁንጮ አስከሬኖች» ታይተዋል። እነሱም የሞንሪያሉ የወታደራዊ ፖሊስ አዛዥ፣ የሲሲሊ ግዛት ፕሬዚዳንትና የፓርሌሞ ዋና አቃቤ ህግ ናቸው። የመጨረሻው ሰውዬ (የፓርሌሞ አቃቤ ህግ) በከተማዋ ዋና ማዕከል ነበር የተገደለው። ይህ ሥፍራ ከኒውዮርኩ ታይም ስኩየር ወይም ፒካድሊ ሰርከስ አደባባይ ላይ እንደመግደል የሚቆጠር «ቲያትሮ ማሲሞ» በሚባለው የፓርሌሞ ዕምብርት መሆኑ የኮዛ ኖስትራን ማን አለብኝነት ያበሰረ ነበር። እነዚህን ሰዎች የማስወገዱ ተግባር የተከናወነው በማፊያ አለቆች በሆኑት በቦንታንቴና በኢንዜሪሎ ትዕዛዝ መሆኑ ተደርሶበታል።

ከ1981 በኋላ ደግሞ «የዓሣ አጥማጆች ጦርነት» የተባለውን ጊዜ የሚያስታውስ ሲሆን በየዕለቱ ማፊያ የፈለገውን የሚደፋበት ጊዜ ሆኖ ይታሰባል። ብዙዎች በማፊያ ነፍሰ-በላዎች ታርደዋል። ፒዩ ላ ቶሬ የገበሬዎች ዋና ታጋይ ሲሆን በኋላም ከኮሙኒስት ፓርቲው ተመርጦ የፓርላማ ተወካይ የሆነ ሰው ነው። ከዚህ በተጨማሪ ቀንደኛ የፀረ-ማፊያ መርማሪ ኮሚሽን አባልም ነበር። ሚያዚያ 1982፣ ሰዎች በሚበዙበት የፓርሌሞ ከተማ በተዘጋጀ ደፈጣ ሊገደል ችሏል።

ለተደረገው ተከታታይ የማፊያ ጥቃት የጣልያን መንግሥት የወሰደው ርምጃ ጄኔራል ካርሎ አልቤርቶ ዳላ ኪየሳን የፓርሌሞ ከተማ ዋና የፖሊስ አዛዥ አድርጎ ሾማቸው። በእርግጥ ጄኔራሉ ማፊያን በመዋጋት ረገድ የረዥም ጊዜ ልምድ ያላቸው ሲሆኑ የማፊያ መሪ

ሉቺያኖ ሌጂዩ በካርሊኦን የማፊያን ጦርነት ሲያውጅ ተጋፍጠውታል። ከሁሉም በላይ ጄኔራሉ እንደ ብሔራዊ አርበኛ የተወሰዱት ግራ ክንፍ አሸባሪዎችን ለመዋጋት ባደረጉት ቆፍጣና ተጋድሎ ነው። ጄኔራሉ ወደ ፓርሌሞ ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ለበላይ አለቆቻቸው በማፊያ የፖለቲካ ክንፍ ላይ ምንም ዓይነት ልስልስ አቋም እንደማይወስዱ አሳውቀዋቸው እንደነበር ይነገራል። ፓርሌሞ ከደረሱ ከጥቂት ወራት በኋላ የተጠናከረ የማፊያ ወታደራዊ ስኳድ የካሪኒን መንገድ ዘግቶባቸው በከፈተው ተኩስ ወጣት ሚስታቸውና አጃቢዎቻቸው ተገደሉባቸው። ከቀናት በኋላ አንድ ያልታወቀ ፀሐፊ ሰዎቹ በተገደሉበት ግድግዳ ላይ «በእነዚህ ሥፍራ የሁሉም ሲሲሊያዊ ተስፋዎች ተገደሉ!» ሲል ጽፏል። የሰዎቹን የቀብር ሥነ-ሥርዓት በተካፈሉ የመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ የተናደዱ ታዳሚዎች «በገንዘብ የተገዛችሁ ባለሥልጣናት በሜራው እጃችሁ አለበት» በሚል አንድምታ ሳንቲሞችን ፊታቸው ላይ ወረወሩባቸው።

የኢጣልያ ፖለቲከኞች ጄኔራል ዴላ ኪየሳ የፈለጉትን እውነተኛ ሥልጣን ግን አልሰጡአቸውም። ጄኔራሉ ጥርስ የሌለው አንበሳ ሆነው ታዩ። አልፎ ተርፎም የማግለል ሥራ ተከናወነባቸው። የጄኔራሉ ልጅ፣ ቀብሩ ከተፈፀመ ከአምስት ቀናት በኋላ

«አባቴ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት በተነሳበት ጊዜ ከጀርባው ሁሉም ፖለቲከኞች እንዲያግዙት ጠይቋል። በተለይ ደግሞ የክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲውን። ዳሩ ግን ፓርሌሞ እንደደረሰ አብዛኛው የክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲው ሰዎች ድጋፋቸውን ነፈጉት። ከዚያ ሁሉ በላይ ተቃራኒው ነበሩ» ብሏል።

የጄኔራሉ ሁኔታ በቅርብ የሚከታተለው ኮዛ ኖስትራ ከዚህ በኋላ ድጋፍ የሌለውን ጄኔራል መግደል የፖለቲካ ዋጋው አነስተኛ መሆኑን በመረዳቱ ለእርምጃ አልተጣደፈም። ማፊያ ለኢጣልያ መንግሥት የሰጠው ሥፍራ እጅግ አናሳ ሲሆን ከአሸባሪ በተጨማሪ የንቀት ዘመቻን ጭምር አስፋፍቷል። በኋላም ጄኔራሉ ከማፊያ ጥይት አላመለጡም፣ ተገደሉ። ከዚህና ከኮሙኒስቱ የፓርላማ አባል ቶሬ መገደል በኋላ መንግሥት ወሳኝ ርምጃን ለመውሰድ ተነሳ። «ማፊያን መሰል ድርጅት» ውስጥ መሳተፍ ወንጀል መሆኑን የሚደነግግ ህግ ወጣ። ህጉ እነዚህን መሰል የወንጀል ድርጅቶች ለይቶ ሲያስቀምጥም፡- ሥርዓት ዘርግቶ ማስፈራራት፣ የተፈፀመ ወንጀልን ተመልክቶ ዝምታ መፍጠር

(Omerta)፣ ኢኮኖሚውን መበጥበጥና · በኢኮኖሚው ውስጥ ወንጀል መፈፀም የማፊያ መሰል ድርጅት አካል ያደርጋል ሲል ደንግጓል፡፡ ይህ ህግ አሜሪካ ካወጣችው የ1970 የRICO እርምጃ (Racketter Influenced and Corrupt Organizations) ከሚለው ጋር ተመሳሳይ መሆኑ ነው፡፡ የተደነገገው ህግ ማፊያ በህገወጥ መንገድ ያገኘውን ሀብትም ይወርሳል፡፡ ይህ ሕግ ኮዛ ኖስትራን ወደ ፍትህ አደባባይ አስገድዶ ለመመለስ ዋነኛው መሣሪያ ሆኖ አገልግሏል፡፡ ዳሩ ግን ከፖለቲከኞች የተገኘው ምላሽ ወሳኝ ውሳኔዎችን ለመውሰድ የሚያመች አልነበረም፡፡ ስለዚህ የሚፈለገው ለውጥ ሊመጣ አልቻለም፡፡ በማፊያ ላይ የተቃጣው ጦርነት እጅግ በጣም አናሳ በሆኑትና በቆራጦቹ የአቃብያነ-ህግና የፖሊስ ኃይል ብቻ ትንቅንቅ የገጠመው ሲሆን፤ እነዚህን ኃይላት አናሳ ፖለቲከኞች፣ ጋዜጠኞችና አስተዳዳሪዎች ጭምር ደግፈዋቸዋል፡፡

ሐምሌ 1983፣ ኮዛ ኖስትራ በፓርሌሞ ማዕከላዊ ክፍለ ከተማ የዳኛ ፋይኮኔን አለቃ ሮኮ ቺኒሲን ለመግደል ፈንጂ አጠመደ፡፡ ዋና አቃቤ ህጉ ሮኮ ቺኒሲና ቤቱን ሲጠብቁ የነበሩ ሁለት ጠባቂዎች በፈንጂው ተገደሉ፡፡ በወቅቱ ስሙ ያልተጠቀሰ አንድ ፖሊስ ለላኦራ ጋዜጣ የነበረውን ሁኔታ እንደሚከተለው ገለፀ፡፡

«እኛ በጦርነት ውስጥ ነን፡፡ ዳሩ ግን በደሴቲቱ ያሉ ባለሥልጣናትና መንግሥት ግን ምንም እንዳልሆነ ያህል ዝም ብለዋል፡፡» ማፊያዎች በመትረየስና በቲኤንቲ ፈንጂ እየተጠቀሙ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ እኛ ግን የአፀፋ መልሳችን ቃላት ብቻ ነው፡፡ እነሱ በሺዎች ሲቆጠሩ እኛ ግን መቶዎች ነን፡፡ እኛ ማዕከላዊ የከተማ ክፍል ዘግተን ስንጠብቅ እነሱ ግን በኮርሶ ዲ ሚሌ፣ በብራንካሲዩና በኡዲቴሬ እንደልባቸው ይርመሰመሳሉ» ብሏል፡፡

የቺኒሲ መሞት ለአናሳዎቹ ፀረ-ማፊያ ተዋጊዎች መልካም አጋጣሚን መፍጠሩ አልቀረም፡፡ አንቶኒዩ ካፖኔቶ የተባለው ዋና አቃቤ ሕግ በፍሎሬንስ ቤቱ ሆኖ ለጡረታ የተቃረበ ሲሆን ከቺኒሲ ሞት በኋላ እሱን እንዲተካ ትዕዛዝ ደረሰው፡፡ አዲሱን መ/ቤቱን በፓርሌሞ የፍትህ መ/ቤት ሲጀምር ያልጠበቀው የእንኳን ደስ ያለህ ቴሌግራም ጠረጴዛው ላይ አገኘ፡፡ «በሥራህ መልካም ውጤት እንድታመጣ እመኝልሃለሁ፡፡ መልካም ሞት እመኝልሃለሁ!» ይል ነበር ቴሌግራሙ፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ

ካፓኔቶ በወታደራዊ ፖሊሶች ካምፕ ውስጥ በአንዲት ጠባብ ክፍል ለአራት ዐመታት ተኩል በሥጋት ኖረ፡፡

በኋላ ላይ በተደረሰ ስምምነት መሠረት ማፊያን በጥብቅ ለመዋጋት አንድ የተጠናከረ የአቃብያን ህግ ቡድን ማቋቋም አስፈላጊነቱ ጎልቶ ወጣ፡፡ ካፓኔቶ እነ ጆቫኒ ፋልኮኔን፣ ፓውሎ ቦርሴሊኖን፣ ጁሴፔ ዲ ሌሎንና በሊኦናርዶ ጉዋርኖታን በማካተት ቡድኑን አጠናከረ፡፡ ከዚህ በኋላ ወሳኙ ፀረ-ማፊያ ትግል ጎለበተ፡፡

ሕብረተሰቡ ጠንካራ ሥራ መሠራቱን ያወቀው መስከረም፤ 1984 ላይ ካፓኔቶ አንድ የፕረስ ኮንፈረንስ ጠርቶ መግለጫ ከሰጠ በኋላ ነው፡፡ ካፓኔቶ እንደገለፀው «የሁለት ዓለም አለቃ» የነበረው ማፊያ ቶማሶ ቡስኬታ ከፍትህ አካላት ጋር በመተባበሩ 366 ማፊያዎች እንዲያዙ መጥሪያ መበተኑን ተናገረ፡፡ ከዚህ በኋላ አካባቢውን ሲያብጡ የነበሩ ቱባ ማፊያዎች እነ ሲንሱሚኖና የሳልቮ የአጎት ልጅም ተያዙ፡፡ ኮፖኔቶ በቀጭን ፊቱ ላይ ደስታ እየፈካ «እዚህ የያዝነው የተለያዩ የማፊያ ጉዳዮችን ብቻ አይደለም፡፡ ማፊያ ወደ ፍርድ መቅረቡ ነው፡፡ በእርግጥ ተቻኩለን ይህ ዘመቻ ታሪካዊ ነው አንልም፡፡ ዳሩ ግን የማፊያን መዋቅር ሰርስረን በጥሰነዋል» አለ፡፡

ኮርሌኦኔሲዎች የቡስኬታን ወዶ-ገባነት በሰሙ ጊዜ እጅግ ተናደው ለብቀላ ተዘጋጁ፡፡ የቡስኬታ ዘመዶች የሆኑ የማፊያ ሰዎች ሁሉም እየተፈለጉ በጥይት ተደበደቡ፡፡ የፀረ-ማፊያ ፈጥኖ ደራሽ ቡድን መሪ የነበረው ቤፔ መንታናም ተገደለ፡፡ ሆኖም የሀገር ውስጡን ደህንነት ሚኒስቴር የተጠናከረ እርምጃ በማፊያ ላይ ለመውሰድ ማቀዱን በመግለፅ ሌላ የፈጥኖ ደራሽ ጦር ወደ ሥፍራው አሰማራ፡፡ አጅሬ ማፊያ ግን የፈጥኖ ደራሹን አዛዥ ካሳራን አድፍጦ ገደለው፡፡ በፍራቻ የተወጣጠሩት የፈጥኖ ደራሽ አባላት ወደ ሌላ ቦታ እንዲቀየሩ ጥያቄ እስከ ማቅረብ ደረሱ፡፡ በቀብር ላይ በተገኙ ባለሥልጣናት ላይ የስድብ ውርጅብኝ ፈሰሰ፡፡ «እናንተ ደደቦች! ነፍሰ ገዳዮች! አሻንጉሊቶች!» እያለ ወረፏቸው፡፡ አልፎ ተርፎም በፈጥኖ ደራሾችና በወታደራዊ ፖሊሶች መካከል ግርግር ተነሳ፡፡

ለማጠቃለል ያህል ኢጣልያ በሀገር ደረጃ ማፊያን ተዋጋች ማለት አይቻልም፡፡ ማፊያን ከልባቸው የተዋጉትና የሚዋጉት ጥቂት ኃላፊነት የሚሰማቸውና የቡድን ስሜት ያላቸው እናሳ ክፍሎች ናቸው፡፡

# 17

# የፍርዱ ሂደት ዕጣ-ፈንታ

የከፍተኛው የፍርድ ሂደት ውሳኔ ያገኘው ታህሳስ፣ 1987 ነበር፡፡ ከ474 ተከሳሾች መካከል 114ቱ ነፃ ሲሆኑ የተቀሩ/360ዎቹ/ በማፊያ ወንጀለኝነታቸው በጠቅላላው የ2,665 ዓመታት እሥር ተከፋፍሎ ተፈረደባቸው፡፡ ይህ የፍርድ ውሳኔ መልዕክት ግልፅ ነበር፡፡ ብዙዎቹ የሲቪል ሊበርተሪያን አቀንቃኞች የፈሩት የጅምላ ፍርድ-ገምድልነት ሊከሰት ይችላል የሚለው ፍርሃት አልደረሰም፡፡ ሌላው ቀርቶ በቀንደኛ ማፊያነቱ የሚታወቀው ሉቺያኖ ሌጂዩ እንኳ ማስረጃ ያልቀረበበት በመሆኑ ነፃ ሆነ፡፡ ፍርደኛ ሆኖ እንኳ የማፊያን ድርጊት ስለመምራቱ ምንም ማወቅ አልተቻለም፡፡

የፍርድ ውሳኔውን ተከትሎ አቃቤያነ-ህጎቹን የሚደግፉ ጋዜጦች የማፊያነትን ምንነት ከሲሲሊያውያን ባህል ያልተነጠለ አድርገው ማቅረባቸውን ቀጠሉ፡፡

አቃቤ-ህግ የሆኑት ፋልኮኔ የፍርድ ውሳኔውን በተመለከተ «የዲሞክራሲን ደንቦች በመጠበቅ የተደራጀ ወንጀል ላይ እጅግ ጠቃሚ ውጤት ላይ ደርሰናል» ሲሉ ነው የገለፁት፡፡ አቃቤ ህጉ በማፊያ ላይ የሚታይ ውጤት መገኘቱ ግልጽ ሆኖላቸዋል፡፡ በተካሄዱት ሦስት ከፍተኛ የፍርድ ሂደቶች እንዳበቃ አንድ ወሳኝ የሆነ የማፊያ ወዶ ገባ - አንቶንዮ ካልዴሮን ወደ አራተኛው ከፍተኛ የፍርድ ሂደት ሊመራ የሚችል ማስረጃ በመስጠቱ 160 የማፊያ ተጠርጣሪዎች መጋቢት 1988 ዓ.ም. ላይ ተያዙ፡፡ በተለያዩ ሲሲሊ ግዛት የሚገኙ አቃብያኔ ህጎች ከማፊያ ጋር የተያያዙ የፍርድ ሂደቶችን ያካሂዱ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ፋልኮኔ ከፍተኛው የፍርድ ሂደት በፀረ - ኮዛ ኖስትራነት አንፃር ሲታይ መልካም ጅምር መሆኑን ብቻ ነው የተመለከቱት፡፡

በኋላ ላይ አንድ ወዶ ገባ ተናገረ እንደተባለው «ከፍተኛው የፍርድ ሂደት የመንግስት ጉረኝነት ከማሳየት ያላለፈ መሆኑን እናውቃለን:: የመጨረሻው ፍርድ የሚፈጸመውን አለቃና ወዶ-ገባ የቡስኬታን ባህሪ ሀሳብ የሚቀበል አይደለም::» ይህ የፍርድ ሂደት ከማፊያ «ጦርነት» በኋላ የታየ «የፖለቲካ ቁርጠኝነት ማሳያ» እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም:: በመጀመሪያው የፍርድ ጊዜ ውሳኔ ይሰጥ እንጂ በኋላ ላይ የቀረበው ግን ይግባኝ ብቻ የሚሰጥበት ሆኖ ነበር::

በኋላም፣ በ1990 የፓሌርሞ ፍርድ ቤት የተወሰኑ የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔዎችን ቀልብሶት ነበር:: ከዚህ ቀደም በአቃቤ-ህጉ ፋልኮኔ የቀረበውን የፍርድ ሂደት አኮላሹት:: የፓሌርም ፍ/ቤት ኮሚሽን ሥልጣናቸውን በመጠቀም ኮዛ ኖስትራ በነፍስ ወንጀል የሚፈለግበትን ሂደት ሁሉ እርባነ ቢስ አደረጉት::

እዚያው በፍርድ አካሉ ውስጥ እንኳ በፋልኮኔ ላይ መሰሪ ተቃውሞ ተደቅኖባቸዋል:: ከከፍተኛው የፍርድ ሂደት መካሄድ በኋላ የፀረ-ማፊያን የፍርድ ሂደት የፈጠረው አንቶንዮ ካፓኔቶ ወደ ፍሎሬንስ ለመመለስ ወሰነ:: በካፓኔቶ የመሸኛ ግብዣ ላይ ያነባው ፋልኮኔ የካፖኔቶን የኃላፊነት ወንበር እንደሚቀዳጅ ግልጽ ነበር:: የፖለቲካ ሽኩቻ፣ በየኮሪደሩ የተደረገ ሸፍጠኝነትና በሙያ ምቀኝነት የተነሳ «በራሱ ዝና ታጥሯል» በሚል ፋልኮኔ ላይ ተነሱበት:: በትረ-ሥልጣኑን ፋልኮኔ እንዳያገኘው ተደርጎ ወደ አንቶንዮ ሜሊ ዞረ:: አንቶኒዩ ሜሊ ግን የማሪያን ጉዳይ የመመርመር ምንም ዓይነት ልምድ የሌለው ሰው ነበር:: ፊልኮኔ በፈጠረው ሁኔታ ከመደናገጡም በላይ ለህይወቱም ፈራ:: ለጓደኞቹ «እኔ የሞትኩ ሰው ነኝ!» ሲልም ተናገረ:: መንግሥት ይህን ሰው እንዳልደገፈው ደግሞ ኮዛ ኖስትራ የማወቅና የመገንዘብ ብቃት እንዳለው ግልጽ ነው::

አዲስ የተመደበው ሜሊ የማፊያንና የሌሎች ወንጀሎችን በመለየት ካስቀመጠ በኋላ የፀረ-ማፊያ ኮሚሽኑን የውስጥ አሠራር በወዘው:: እንዲያውም የማፊያን ጉዳይ ከተለያዩ የሲሲሊ ክፍሎች ለተውጣጡ አቃቢያነ-ህጎች ለይቶ ሰጠ:: ይህ እንግዲህ ከፋልኮኔ መሰረታዊ አሰራር ፈጽሞ የወጣና መርሁንም የሚጥስ መሆኑ ያደባባይ ምስጢር ነው::

የተፈጠረውን አዲስ ሁኔታ በቅርብ የሚመለከታቸው ዋና አቃቤ-ህግ ቦርሰሊኖ /የፀረ-ማፊያ የፍርድ ሂደቱን ከፋልኮኔ ጋር በመጀመሪያ መመልከት የጀመረው/ ያደረበት ሥጋት ለሕብረተሰቡ መግለፁን መረጠ፡፡ «አንድ የሆነ ሰው ሰዓቱን ወደ ኋላ እየመለሰው መሆኑ ይሰማኛል» ሲል ተናገረ፡፡ በዚህ ጊዜ ያልተጠበቀ የፖለቲካ መደናገጥ በመፈጠሩ የአቃብያነ-ህጎች ዋና ጉባዔ የቦርሰሊኖ ስሞታ እንዲጣራ ውሳኔ አስተላለፈ፡፡ ፋልኮኔም በበኩሉ በሜሊ አሰራር የተጀመረው የፀረ-ማፊያ የምርመራ ሥራ ወደ መቆም ማምራቱን አሳስቦ ዓፈ፡፡ በአቃቤ-ህጉ ቦርድ የተያዙ ምስጢራዊ ጉዳዮች በፋልኮኔ ደጋፊዎችና በፋልኮኔ ተቃዋሚዎች ማፈትለካቸውን ቀጠሉ፡፡ ከሁለቱም ወገኖች በሚወረወረው የነገር ፍላፃ የፖለቲካ ቁርጠኝነት አለመኖርና «የግለሰብ አምባገነንነት» መንሰራፋቱን የሚያትቱ እንጂ ዋናውን ጉዳይ የሚዳስሱ አልነበሩም፡፡ ፋልኮኔ በመጀመሪያ ከቦታው መልቀቁን የሚገልፅ ደብዳቤ ካስገባ በኋላ መልሶ ሀሳቡን ቀየረ፡፡ የአቃቤ-ህግ ቦርዱ በበኩሉም ሁለቱ ተፈላጊ ወገኖች ልዩነታቸውን አስወግደው ወደ አንድ መስማሚያ ነጥብ እንዲደርሱ ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡ የፋልኮኔ የሥልጣን ሁኔታ ከቀድሞው የበለጠ ደካማ እንዲሆን ተደረገ፡፡ በዚህ ጊዜ የፓሌርሞ የፍትህ ተቋም «የመርዝ ተቋም» የሚል መጠሪያ አገኘ፡፡

ፋልኮኔ በራሱ የሥራ ባልደረቦች የደረሰበት አስቸጋሪ ሁኔታ የኢጣሊያ ሕዝባዊ ተቋማት ያሉበትን አሳዛኝና ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ያሳያል፡፡ በብዙ ፖለቲከኞችና አቀንቃኞች ዘንድ የፀረ-ማፈሪያ አቃቢ-ህግ ዋና ማዕከል የሚያደርገው እንቅስቃሴ ፈጽሞ አልተወደደለትም፡፡ ህቀኞችን ጠቅሞ ወንጀለኞችን ለመቅጣት የተቋቋመ ሳይሆን መንግሥት ሌላ ተጨማሪ ክንድ ለማሳየት እንደፈለገ ተቆጠረ፡፡ ፋልኮኔና ቦርሴሊኖ በተቻለ መጠን ሁኔታውን ግልፅ ለማድረግ ቢሞክሩም የሚሆን አልነበረም፤ አልፎ አልፎ ስጋትና አደጋ እየተረጋገጠባቸው ሄደ፡፡

ሰኔ 1989፣ ከፓሌርሞ ውጭ እሱና ባለቤቱ በተከራዩበት ቪላ ቤት አጠገብ በአዳዲስ ቦርሳ የተሞላ ፈንጂ ተገኘ፡፡ ፋልኮኔ በግልጽ ስለሁኔታው አስመልክቶ ከኮዛ ኖስትራ ጎን የቆሙና ተሞዳሟጅ የፖለቲካ ሰዎች በዚህ ድርጊት ውስጥ እንደሚካፈሉና ሕይወቱን ለመቅጠፍ እንደተዘጋጁ ግልጽ አደረገ፡፡ በፋልኮኔ ላይ በቅርብ አብሮት የሚሰራ ሰው

ስሙን በመበከል የዓፊው ደብዳቤ ቀረበ፡፡ የደብዳቤው ዋና ዓላማ ፋልኮኔ የማፊያን ወዶ ገብን በመጠቀም ሆን ብሎ በኮርሊኦኒዎች ላይ ሊወስድ የቃጣውን አስቀያሚ ጦርነት ያትታል፡፡ በሚቀጥለው ጥር ወር፣ ሊኦሉካ ኦርላንዶ የፓሌርሞው ፀረ-ማፊያ ከንቲባ የከተማውን የፖለቲካ ሁኔታ ለማርገብ ሲል ከኮሙኒስቶች ጋር ራሱን በማቆራኘቱ የክረስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲ ባለስልጣናት ከሥልጣኑ እንዲወርድ አደረጉት፡፡ ይህም ሁኔታ ለነፋልኮኔ ለፀረ-ማፊያ ትግሉ መጪው ጊዜ ደብዛዛ መሆኑን ያሳየ ሆነ፡፡

የካቲት፣ 1991 ላይ ፋልኮኔ የፖለቲካ ተጎጂ ከመሆን በማለፍ ተጠቃሚነቱ ጎልቶ ወጣ፡፡ ወቅቱ የፀረ-ማፊያ እንቅስቃሴው የተኮላሸበት ጊዜ ነበር፡፡ ከበርሊኑ ግንብ መፍረስ 1989 በኋላ የቀዝቃዛው ጦርነትና ከዚያው ጋር የተያያዘው የኢጣሊያን ፖለቲካም ተፍረከረከ፡፡ የኮሙኒስት ፓርቲውም ራሱን ወደ ሶሻል-ዲሞክራቲክ ፓርቲነት ለወጠ፤ ስለዚህ ኢጣሊያኖች ሳይወዱም ቢሆን ለክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲውን ለመምረጥ ጥሩ ምክንያት አገኙ፡፡ ለውጦች መካሄድ ቀጠሉ፡፡ ከፀረ-ማፊያ የፍርድ ሂደት በኋላ የሕብረተሰቡ ስሜት ላሽቀ፤ በኋላም አዲስ ሶሻሊስታዊ የፍትህ ሚኒስትር ሥልጣን ተቆናጠጠ፡፡ ይህ ሚኒስትር የፀረ-ማፊያ ትግሉ ዋና አቀንቃኝ ስለነበር ህግንና ሥርዓትን ለማክበር ቆርጦ ተነሳ፡፡ ፋልኮኔን የወንጀል ጉዳዮች ዋና ዳይሬክተር በማድረግ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ውስጥ መደበው፡፡ ይህ ለፋልኮኔ የተሰጠው አዲስ ሥልጣን በሀገር ደረጃ የተደራጁ ወንጀለኞችን ለመከላከል ከፍተኛው የኃላፊነት ሥራ ነው፡፡

ምንም እንኳ አንዳንድ የቅርብ ጓዶቹ የሥፍራውን መያዝ በተመለከተ ደስተኛ ባይሆንም ኃላፊነቱን ተረከበ፡፡ የተፈጠረውንም የፖለቲካ ሁኔታ መለወጥ በመጠቀም ሥራውን በዓላማ ጀመረ፡፡ በዳይሬክቶሬቱ ሥር ሁለት ክፍሎችን አቋቋመ፡፡ አንደኛው የፀረ-ማፊያ የምርመራ ዳይሬክተር ቢሮ ሲሆን ይህ ክፍል የወታደራዊ ፖሊሶችን፣ ፖሊሶችንና ሌሎች የሚመለከታቸው የህግ አስፈፃሚ አካላትን የማፊያና ማፊያ መሰል ድርጅቶችን ለመዋጋት የሚያስችል አስተባባሪ አካል ነው፡፡ ሁለተኛው ብሔራዊ የፀረ-ማፊያ ክፍል ሲሆን 26 የፀረ-ማፊያ የአቃቤ-ህግ ቢሮዎችን በመላ ሀገሪቱ ያስተባብራል፡፡ ሁለቱም ክፍሎች

በኮምፒዩተር የታገዘ የተደራጁ ወንጀለኞችን የመከታተያ ፋይሎችን የማደራጀትና የመያዝ ግዴታ ተጥሎባቸዋል። ከርማ ማዕከል ሆኖ ቀደም ሲል በፓሌርሞ መሥራት ያልቻለውን ሥራ ፋልኮኔ መሥራቱን ቀጠለ።

ከዚህ ቀጥሎ የከፍተኛው የፍርድ ሂደት መወሰን አለበት። የፍርዱ ሂደቱ እንደሚታወቀውና እንደተጠበቀው አልጋ በአልጋ አልነበረም። የፓሌርሞው የይግባኝ ፍርድ ቤት ዳኛ አንቶንዮ ሳኤታና ዝግምተኝነት ያለበት ልጁ መስከረም 1988 በጥይት ተደብድበው ተገድለዋል። አንቶኒዮ ኮፖሊቲ የተባሉ ዳኛም ነሐሴ 1991 በካላብሪያ ማፊያ (ልዩ ስማቸው «ንድራጌታ») ተገደሉ። ከሦስት ሳምንት በኋላ የታወቁት ከበርቱና ነጋዴ ፀረ-ማፊያ ሰው እንዲሁ ተገደሉ።

እነዚህ ያልጠበቁ ወንጀለኞች ይበልጥ ለፋልኮኔ ሥራ መጠናከር ወሳኝ ሆኑ። ለሁለት ተከታታይ ዓመታት በታየው የፍርድ ሂደት የፋልኮኔና ቦርሶሊኖ ያቀረቡት ማስረጃ ታይቶ በማፊያ አለቆች የዕድሜ ልክ እሥራት ፍርድ ተሰጠ። የማፊያው ወዶ-ገብ ቡስኬታ ያቀረበው ምሥክርነትም የተረጋገጠ በመሆኑ የኮዛ ኖስትራ መሪዎች የሚገባቸውን አገኙ። ፋልኮኔም የሚያስፈልገውን ሁሉ ሥልጣን ይዞ «የኢ-አማኒያን ምድር» ለማጥፋት ትግሉን ወደፊት ቀጠለ።

## የኮርሊኦኔሲዎቹ ማንሰራራትና የዓሣ አጥማጆቹ ጦርነት

ከ1981-3 የተካሄደው የማፊያ ጦርነት በጣልያንኛ «La Mattanza» ተብሎ ሲታወቅ ቃሉም የተያያዘው ከዓሣ ማጥመድ ኢንዱስትሪ ጋር ነው። የዚህን ውስጠ-ወይራ ቃል ትርጉም ለመረዳት የሮቤርቶ ሮዜሊኒና ወዳጁ እንግሪድ ቤርግማን የምትተውንበትን የ1950 «ስትሮምቦሊ» ፊልምን መመልከት ያስፈልጋል። በፊልሙ ውስጥ በርግማን የሉቲኒያ ስደተኛ ሆና ትጫወታለች፣ ሲሲሊያዊውን ደሃ ዓሳ አጥማጅም ታገባለች። ከተሰደደችበት ካምፕ ለማምለጥ ያግዛት ዘንድ ነው ሲሲሊያዊውን ያገባችው። ይህ የፊልሙ ዋና አካል ሲሆን ባሏ በዚህ የዓሣ ማጥመድ ውስጥ የሚያጋጥመውን ፍዳ በራስዋ ዓይን እንድትመለከት ሆኖ ነው ፊልሙ የተዘጋጀው። እንግዲህ ይህ ነው

የኮርሊኦኔዚ.ን የማፊያ ዳግም ማንሰራራት በተመለከተ ከጓሣ ማጥመድ ፊልም ጋር አያይዘው ማፊያዎች ልዩ መለያ የሰጡት።

በሚያዝያ 1978 ጁሴፔ ዲ ክርስቲና የተባለው የማፊያ የክብር ሰው ከወታደራዊ ፖሊሶች ኮማንደር ጋር በሚስጢር በአንድ ድብቅ ጎጆ ውስጥ እንዲነጋገር ይደረጋል። ይህ የማፊያ አለቃ ለፖሊስ ኃይሉ ዋና ጆሮ ጠቢ ሲሆን በተደራቢነት ደግሞ በደቡብ ሲሲሊ የምትገኘው የሪየሲ የማፊያ አለቃ ነው። በማፊያ ተከታታዮች እንደሚገመተው ይህ ሰው ነበር የፖሊስ ዩኒፎርም ለብሶ በ1969 «በቪያሌ ሊያዞ» የማፊያ ፍጅት ውስጥ የተሳተፈው። በአጭር አገላለፅ ዲ ክርስቲና በማፊያ ሥርዓት ውስጥ ዋናው ተዋናይ ነበር ተብሎለታል።

ሌላው የማፊያ መልቲ ሚሊየነር ሉቺያኖ ሌጂዩ ወይም በቅፅል ስሙ የሚታወቀው የካርሊኦን «ቀዩ ሳማ» ለአራት ዓመታት በእስር ላይ ነበር። እንደዚያም ሆኖ ጉዳዮቹን ሁሉ በወኪሎቹ «በአጭሬው» ሪና እና «በትራክተሩ» ፕሮቬንዛኖ በኩል ያራምዳል። ዲ ክርስቲና እንደሚገምተው ከሆነ እነዚህ «አውሬዎች» ተብለው የሚታወቁት እያንዳንዳቸው በ40 ነፍስ የሚጠየቁ ወንጀለኞች ናቸው። የሌጂዩ ቱጃርነት ምስጢርም የተገነባው በኢጣልያ መሐል ሀገር በሚፈጥረው የአፈና ርምጃ ነው። በ1973 በዓለም ላይ ካሉ ሀብታሞች አንደኛው የሆነው «የኢዮጂን ፖልጌቲ III ኛ» የልጅ ልጅ በሮማ ከተማ ውስጥ ታፈነ። ይህ የ17 ዓመት ልጅ የተፈታው ከአምስት ወራት በኋላ የ2.5 ሚሊዮን ዶላር ድርጎ በተከፈለ ጊዜ ነበር። በወቅቱ የወጣቱ ጆሮና የፀጉሩ ቁራጭ ለአንድ ጋዜጣ ስለመታፈኑ ማስረጃ እንዲሆን ተልኮ እንደነበርም ይታወሳል። ዲ ክርስቲና እንደሚለው ይህ ሁሉ ግፍ የሌጂዮ ሥራ ነው ሲል መስክሯል።

የዲ ክርስቲና ስለ ሉቺያኖ ሌጂዮ የዘከዘከው ሁሉ አንድ መልዕክትን ያስተላልፋል። ይህም በኮዛ ኖስትራ ውስጥ የፖለቲካ መከፋፈል መኖሩን። የአንደኛው ቡድን መሪ ሌጂዮ ሲሆን ባላንጣው ደግሞ ዶን ታኖ ባዳልመንቲ «የሲኒሲ ጨካኝ» ተብሎ የሚታወቀው የማፊያ አለቃ ነው።

ዲ ክርስቲና በሚገባ እንደተረዳው ከሆነ የኮርሊኦኔሲ ማፊያዎች ተቀናቃኝ ቡድኖችን ለመጋፈጥ የረዥም ጊዜ ስትራቴጂ ነድፈው እንደሚንቀሳቀሱ ደርሶበታል። በዚህ ዕቅዳቸው መሠረት በፓሌርሞ ክፍለ ሀገርና በሌላውም የሲሲሊ ግዛት ባሉ ትንንሽ ከተማዎች ሳይቀር ታማኝ ተከታዮቻቸውን መዘገቡ። የነሌጂዮ ቡድን (ኮርሊኦኔስዎች) አባላት ከፊት ለፊታቸው የተጋረጠ ተቀናቃኝ ቡድንን ለማስወገድ ይወስናሉ። በዚህ መሠረት ሌጂዮ የተራቀቁ የሞት ስኳዶች የሆኑ 14 አባላትን በሲሲሊ ብቻ ሳይሆን በሮም፣ በኔፕልስና በሌሎች የኢጣልያ ከተሞች በመደልደል ርምጃ እንዲወስዱ ያዛል። ኮርሊኦኒዎች (ሌጂዮ የሚመራቸው) በጠላቶቻቸው ቤተሰብ ውስጥ ሰርገው እስከመግባት ድረስ ሁኔዎችን ያመቻቻሉ። (በኋላ ላይ በዚህ አካሄዳቸው ገፍተው ለሌሎች ተባባሪ የማፊያ ቡድን አለቆች ሳይነግሩ ምስጢራዊ የማፊያ ጦር ይገነባሉ።) የዲ ክርስቲና ተስፋ ግን የነበረው እነሌጂዮ እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት ወታደራዊ ፖሊሶቹ ጥቃት ይፈፅማሉ የሚል ነበር። እንዲያውም የኮርሊኦኔሲው ማፊያ የነበረውን ፕሮቬንስኖን ለአሥራ አምስት ዓመታት ከተደበቀበት ሕምጥ ወታደራዊ ፖሊሶቹ ማጅራቱን ይዘው ለፍርድ ያቀርቡታል የሚል እምነትም ነበረው - ክርስቲና።

ዲ ክርስቲና ለወታደራዊ ፖሊሶች ፕሮቬንዛኖ («ትራክተሩ») ባገሪያ ከተማ አጠገብ ወጣቱ ጆቫኒ ቡርስካ («ክርስቲያን-አራጁ» በመባል የሚታወቀው) ነጭ ማርቸዲስ እየነዳለት መሆኑን ሹክ ይላቸዋል። «የሳን ጁሰፔ ጃቶ» አካባቢ ቡርስካዎች ደግሞ የሌጂዮ የቆዩ ሸሪኮች ናቸው። ዋናውን የኮርሊኦኔስን የማፊያ ተነጣይ ቡድንን የሚወክሉ ጠንካራ የተባሉ የፓሌርሞ ክፍለግዛት የማፊያ ሰዎች መሆናቸው ይታወቃል። «አጭሬው» ቶቶሪና ደግሞ በ1976 ጆቫኒ ቡርስካ የማፊያ አባል ሆኖ ሲመለመል የጡት-አባት ሆኖለት ነበር በአባልነት ያቀፈው። እስካሁን በተግባር እንደታየው ተቀናቃኝ የማፊያ አባላት ምንም እንኳ ከወታደራዊ ፖሊሶች ጋር የተለየ ቀረቤታ ቢያሳዩም «ሲያልቅ አያምር» እንደሚባለው በጥይት ሲወገዱ እንመለከታለን። የዲ ክርስቲና ሕይወትም ከዚህ የሚያመልጥ አልነበረም።

ዲ ክርስቲና ከወታደራዊ ፖሊሶች ጋር ያደረገውን ንግግር ትንቢት በሚመስል አኳኋን እንዲህ ሲል ደመደመ። «በሚቀጥለው ሳምንት

መጨረሻ ጥይት ተከላካይ መኪና አስገባለሁ... የማያስተስርይ ኃጢአት ውስጥ ተነክሬያለሁ፣ ሂሲናዬን ይፀፅተኛል...» በማለት ተናዘዘ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ግን ኃጢያቱ ሠራ መሰል ከፖሌርሞ ወጣ ብላ በምትገኘው የፖሶ ዲ ሪጃኖ ሥፍራ ደሙ ደመከልብ ሆነ። የዚህን ድንገተኛ ሁኔታ መከሰት ወታደራዊ ፖሊሶቹ የሚሰጡት ትርጉም ግልፅ ነው። የዲ ክርስቲና ሞት የሚያመጣው መዘዝም ብዙ ነው። ምክንያቱም ዲ ሪጃኖ የተባለችው ሥፍራ ሰልቫቶሬ ኢንዜሬሎ የሚመራው የፀረ-ኮርሊኦኔስ ማፊያ ቡድን ዋና አጥቢያ ናትና። ይህ ማለት አንድ የማፊያ አለቃ በሚያስተዳድረው አካባቢ የዚህ አለቃ ፈቃድ ሳይጠየቅ ርምጃ መወሰድ ክልክል ስለሆነ የሚያመጣው ጣጣ ብዙ መሆኑ ይታወቃል። ይህ ደግሞ በማፊያ አሠራር የቆየ አሠራር ነው።

እንደተለመደው ዲ ክርስቲናን ብዙ ሰው በሪየሲ ከተማ ወጥቶ ቀበረው። ስለ ሁኔታው የሚከታተሉት ወታደራዊ ፖሊሶች ወዲያውኑ ዝርዝር ሪፖርት በማቅረብ የዲ ክርስቲና ሪፖርት እጅግ ተጨባጭ መሆኑን አመለከቱ። ሪፖርቱ ዕውነታውን ያስቀምጥ እንጂ የዲ ክርስቲና ጉዳይ አከተመ። በዲ ክርስቲና አማካኝነት ለፖሊሶቹ የተሰጠው ቃል ድብቅና ፍቺው የሚያስቸግር፣ አጥንት ዘልቆ የሚጠዘጥዝ ቁጭት ቢፈጥርም ዕውነታነቱ ግን አያጠራጥርም። ከዚህ እልፍ ተርፎም ርምጃ ወሳጁ ኃይል ርምጃ ወሳጅ፣ ገዳይና ገንዘብ የሚሠራ፣ እልፍ ተርፎም ከባለሥልጣናት ጀርባ ሆኖ የራሱን ፍርድ ሰጪ መሆኑን ያሳያል።

የእነ ዲ ክርስቲና ዓይነት ማፊያዎች ወደ መንግሥት በወደ ገባነት በሄዱ ቁጥር ሁለተኛው የማፊያ ጦርነትም (የዓሣ አጥማጆች ጦርነት) በመባል የሚታወቀው ተጀመረ። ኮርሊኦኔሲዎች የበላይነታቸውን በኮዛ ኖስትራ ውስጥ እየተቀዳጁ ለመሄድ ወሳኝ ጥቃቶችን ቀጠሉ። የዚህ እንቅስቃሴ መጠናከር ደግሞ የተያያዘው እነ ቦንታንቴ ባዳልማንቲ እና ለጂዮ አሠራሩን በሶስትዮሽ በ1970ዎቹ እየተቆጣጠሩ በሄዱ ጊዜ ነው። ወቅቱ እነዚህ አደገኛ የማፊያ ቡድኖች በወታደራዊ አቋማቸው ምንም እንኳ ጠንካራ ቢሆኑም፣ በፋይናንስ አቅማቸው ግን የተዳከሙ ነበሩ። ሌጂዮና ግብረ አበሮቹ (አውሬዎቹ) ሰዎችን በማፈን ኃይላቸውን ማሳየትና ንብረት ማከማቸታቸውንም ቀጠሉበት። የነዚህ ጥቃቶች ሰለባ የነበረው አንድ የዶን ሲሲዎ ቫሳሎ ልጅ ሲሆን ይህ ሰው በፓሌርሞ

የማንባታ ወቅት ዋነኛው የኮንስትራክሽን ዘርፉ ከበርቴ ነበር፡፡ ሁለቱ ባዳልሜንቲና ቦንታንቴ ለቫላሎ እጅግ የቅርብ ሰው ቢሆኑም የታገተውን ሊያስፈቱት አልቻሉም፡፡ ከአምስት ወራት በኋላ ግን በተደረገ ስምምነት አድርጎ ከፍሎ ሊወጣ ችሏል፡፡ ኮርሊኦኔሲዎች ለረዥም ጊዜ ጥቅምና ውጤት አሳቢ በመሆናቸው ያገኙትን ሀብት በኮዛ ኖስትራ መዋቅር ውስጥ መልሰው ተጠቀሙበት እንጂ ወደ ሌላ ንግድ አላዞሩትም፡፡

በ1975፣ የኒኖ ሳልቮን የሚስት አባት በማገት «አጭሬው ሪና» ስቴፋኖ ቦንታንቴን አሳቀለው፡፡ ኒኖ ሳልቮ የሚታወቀው ዋናው የሲሲሊ የግል የታክስ ሰብሳቢ ኩባንያ ባለቤት ሆኖ ነበር፡፡ በፖለቲካ ግኑኝነታቸው፣ በሀብታቸውና ባላቸው የክብር ሰውነት የኒኖ ሳልቮን የሚስት አባት ከአፈናው ሊታደጉአቸው እንኳ አልቻሉም፡፡ ሪና ስለተደረገው እገታ ምንም እንደማያውቅ አቀዝቅዞ ተናገረው፡፡ ይህ ማለት ግን «አጭሬው ሪና» አንድ ከባድ መልዕክት ለሌሎች ድኩማን የማፊያ ቡድኖች ማስተላለፉ እንደነበር አይካድም፡፡ ስለዚህ በየስፍራው የነበሩ የተለያዩ የማፊያ ቡድን አለቆች የሪናን ጉልበትና እንቢ-ባይነት ከመመልከት አልፈው የእነ ቦንታንቴን ድኩምነትና እውርነትን መታዘብ ጀመሩ፡፡ አልፈው ተርፈውም አንድ የማፊያ ጦርነት ቢነሳ ከማን ወገን መሆን እንዳለባቸው በውስጣቸው መወሰንም ነበረባቸው፡፡

በ1977፣ ኮርሊኦኔሲዎች ባልተጠበቀ ሁኔታና መንገድ ዶንታና ባዳልሜንቲን ከኮዛ ኖስትራ አባረሩ፡፡ የክሱ ምክንያትም ከሌሎች የማፊያ አለቆች ጀርባ በዕፅ ዝውውር ገንዘብ እየደለበ መምጣቱን የቀረበበት ክስ ያስረዳል፡፡ አንድን የማፊያ ዶን ከኮሚሽኑ ውስጥ ማባረር መቻል ኮርሊኦኔሲዎች ምንኛ በማፊያ ዋና ኮሚሽን ውስጥ ፈርጥመው እንደወጡ ያመለክታል፡፡

በባዳልሜንቲ ምትክ በኮሚሽኑ ውስጥ ሥፍራውን የተቆናጠጠው ሚኬሌ ግሬኮ (ጳጳሱ) የተሰኘው የመቶ አለቃ ዮርዱ ልጅ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው የማፊያ ሥርወ-መንግሥት ከፖሌርሞ አልፎ በግሬኮዎች ግዛትና የክፍለ ሀገር ዋና ከተማ በሆነችው ኮርሊኦን ባሉ ማፊያዎች ጋር ሁሉ መተሳሰር መፍጠሩን ያመላክታል፡፡ ይህ ጥብቅ ትስስር ነው እንግዲህ ወደ 1981 ጦርነት ያመራው፡፡

ከጁሰፔ ዲ ክርስቲና መገደል በኋላ ኮርሊኦኔሴዎች ስልጣኑ-ግዛታቸውን ወደ ማዕከላዊው ሲሲሊ - ካልታኒሴታ ማስፋፋታቸውን አስመሰከሩ። ከጥቂት ወራት በኋላ ደግሞ ፒፓ ካልዲግንን በ1975 ከገደለ በኋላ ለመላዋ ሲሲሊ ማዕከላዊ አመራር ሰጪ የማፊያ ተቋምን መሠረቱ። ከተገደለው የካልዲሮን የማፊያ ቤተሰቦች ፊንታ የኮሊኦኔሴዎች ጋሻ ጃግሬ የሆኑት የማፊያ ቤተሰቦች ሥፍራውን ተረከቡት። የዚህ የማፊያ ቤተሰብ መሪ ኒቶ «የሳንታፓኦላው አዳኝ» ተብሎ የሚታወቀው ነው። በአጠቃላይ ሲታይ ኮፖሌርሞ ውጭ ያለው የማፊያ መዋቅር በኮርሊኦኔሴዎች ሙሉ ቁጥጥር ሥር ወደቀ።

ከዚህ ጊዜ በኋላ የሌጂዮ የማፊያ ቡድን አመራር ወደ ተከታዮቹ ወደ «አጭሬው ሪና» የተላለፈ ሲሆን ይህም የማፊያ አለቃ በቅርብ የሚረዳው «ትራክተሩ ፕሮቬንሳኖ» እንዲሆን ተደረገ። አንድ በማፊያ ወዶ የገባ ሰው እንደተናገረው «ሪና ልስልስና ግብቡ ነው፣ ሌጂዮ ግን ክፉ ጃዊሳ ነበር» በማለት ነበር የገለፀው። «ሪና ተናዶ እንኳ አይቼው አላውቅም» ሲል ጨምሮ ስለ ሪና ባህርይ አስረድቷል። ይህ ግን በተከታዮቹ ላይ የማስመሰል ባህርይን ለማላበስ ያደረገው እንደሆነ የማፊያ ተንታኞች ይናገራሉ። ስለ ተከታዮቹም ወዶ-ገባው ሲናገር «ሁሌ ፈገግታን እንደረጩ ነው። ሪና እንደነዚህ አይነት ሰዎችን መልምሎ ያስገባ ሲሆን የመሬት መንቀጥቀጥ ቢደርስባቸው እንኳ ሁሌም እንዲስቁ አስለጥኖአቸዋል።»

ከአንድ ሌላ አቅጣጫ ሲታይ ደግሞ፣ ቦንታንቴ፣ ኢንዜሪሎና ባዳልመንቲ ከሳቂታዎቹ ኮርሊኦኔሴዎች ይልቅ ከፍተኛ ሥልጣን ይዘዋል ማለት ይቻላል። እነዚህ ሰዎች የማፊያ ቤተሰቦቻቸውን ካፖዎች በመላዋ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ማስተሳሰር የቻሉ ናቸው። በገንዘብ አቅማቸው ደግሞ የዕፅ ዝውውሩን መስመር የተቆጣጠሩ፣ ባስፈለገ ጊዜም የፖለቲካ ከለላ መስጠት የሚችሉ ቁንጮ ሰዎችን ይዘዋል። ቦንታንቴ በማፊያና በዓለም ምስጢራዊ የማሶኒክ ማህበረሰቦች (Masonic Societies) መካከል አያያዥ ሰው ሆኖም ያገለግላል። (ማሳኒክ ማህበረሰብ ወይም Freemasonry በ16ኛውና 17ኛው ክፍለ ዘመን ተመስርቶ እስከአሁንም ድረስ በምስጢራዊ ማህበረሰብነት የሚታወቅ ድርጅት ነው) ኮርሊኦኔሲዎች ግን በተቃራኒው ከአትላንቲክ ማዶ ካለው የናርኮቲክ ንግድ የተነጠሉ ሲሆን በኮዛ ኖስትራ ውስጥ ግን ስልጣን ጨብጠዋል።

በሚስጢራዊ መንገድ ገንዘብና የማፊያ ክብር ኢንቬስት እያደረጉ ኮሚሽኑን የማፊያን ቤተሰቦችና የአመራር ኮሚሽኑን ተቆጣጥረውታል። ኮሚሽኑን በመቆጣጠራቸውም በአጠቃላይ የኮዛ ኖስትራ የውሳኔ አሠጣጥንም ተቆጣጥረውታል። ይህም ብቻ አይደለም በፍትህ ሥርዓቱ፣ በፕሮፓጋንዳ ቢሮውና በወታደራዊ ክንፉ አዛዥና ናዛዥ የሆኑት እነሱ ናቸው። ኮዛ ኖስትራ አንድ መንግሥት ሆኗል ብለን ብንገምት ኮርሊኦኔሲዎች ደግሞ በቀላሉ መፈንቅለ መንግሥት ለማካሄድ ምንግዜም ዝግጁ ናቸው ማለት ይቻለናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ቶማሶ ቡስኬታ በ1980 ከእሥር ተፈታ። በደቡብ አሜሪካ ወጣት ሚስቱን ከማግኘቱ በፊት በፓሌርሞ ብዙ ወራትን አሳለፈ። ዓለምን እየዘነጠና እየተቀናጣ ዞረ። በፓሌርሞ በነበረበት ጊዜ በሳልቮ አጐቶች ሆቴል አርፎ እንደነበር ይታወሳል። በወቅቱ ኒኖ የሪና ተቀናቃኝ ሆኖ እንዲቆም ጠይቆት የነበረ ቢሆንም ጥያቄውን ሳይቀበል ወደ ውጭ የመሄድ ፕላኑን ገፋበት። ከቦንታቴና ኢንሴሪሎ ጋር ስለሚተዋወቅ ከእነሱም ጋር ጊዜውን አሳልፏል። እነ ኢንሴሪሉ በዕፅ ዝውውር ንግድ የሚታወቁ በመሆናቸውና ክብርም ስለነበራቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ መኪኖች በኡንዜሪሎ ቪላዎች ዙሪያ ይሰባሰቡ ነበር። የማፊያ ወታደሮችና ዕፅ አዘዋዋሪዎች እንደ ግብረ-ጉንዳን ተተራምሰው ይታያሉ። ቦናታቴና ኢንዜሪሎ በባህር ዳርቻና በተራሮች ላይ ስለሚያንጣልሉአቸው ድንቅ ቪላዎች፣ ስለ ቢልዮን ሊሬዎች፣ የመዝናኛ ጀልባዎችና ስለሚመሠርቱአቸው አዳዲስ ባንኮች እንደ ቀላል ጉዳይ አድርገው ያወሩ ነበር። ቡስኬታ ግን በእንደዚህ ዓይነቱ አስጐምዥ ሁኔታ ከመሳተፍ ይልቅ መሄዱን መረጠ። ጥር፣ 1981 «የሁለት ዓለሞች አለቃ» የተባለለት ሰው ሁለተኛ ላለመመለስ በአውሮፕላን ተሳፍሮ ወደ ብራዚል በረረ።

???

ጁሴፔ ዲ ክርስቲና የተነበየውና ኮርሊኦኔዜዎች ለረዥም ጊዜ የተዘጋጁበት ጦርነት ማያዚያ፣ 1981 ተጀመረ። የመጀመሪያው የጦርነቱ ተጠቂ «የቪላግራሲያው ልዑል» ስቴፋኖ ቦንታቴ ሆነ። ከልደት ዝግጅቱ ሲመለስ ነው በትራፊክ መብራት ላይ መትረየስ ያርከፈከፉበት። ከሁለት ሳምንት በኋላ ደግሞ ተመሳሳይ ዕጣ በኢንዜሪሎ ላይ ደረሰ። በእርግጥ በልዩ ሁኔታ በተሠራቸው ቀይ አልፋ ሮሚዮ መኪና ክልደት ፌሽታው

ይህ ሰው ጥይት የማይበሳው አልፋ ሮሚዮ መኪና እንዳለው በማወቃቸው ከፍቅረኛው ቤት ወጥቶ መኪናው ዘንድ ከመድረሱ በፊት አስቀሩት።

ቶማሶ ቡስኬታ በብራዚል፣ ባዳልሜንቲ በአሜሪካ እያሉ ኮርሌኦኔዚዎች የተቀናቃኝ ቡድን መሪዎችን ቦንታንቴንና ኢንዜሪሎን ከምድረ ገፅ አጠፉ። ብዙ የማፊያን ጉዳይ የሚከታተሉ ሰዎች በወቅቱ ከቦንታንቴና ከኢንዜሪሎ ተከታዮች የአፀፋ መልስ ጠብቀው ነበር። ግን አልሆነም። የተሸናፊው ቡድን አባላት የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ግራ ገብቷቸው በነበረበት ወቅት ቶማሶ ቡስኬታ ከብራዚል በመደወል የኮንስትራክሽን ባለቤት ከነበረውና ከሟቾች ጋር ቅርበት ካለው ሰው ጋር በስልክ ተነጋገረ። ይህ ባለሀብት በስልክ ንግግሮቹ ቡስኬታ ከብራዚል ወደ ፓሌርሞ ተመልሶ ኮርሌኦኔዚዎቹን እንዲቋቋም ጠየቀው። ዳሩ ግን «የሁለት ዓለሞች አለቃ» የሆነው ቡስኬታ ሕይወቱን ላለቀለትና ለደቀቀለት ጉዳይ ጭዳ ማድረጉን አልፈለገም።

ከሳምንታንትና ከወራት በኋላም የእነ ኮርሌኦኔዚዎች ጥቃት አላቆመም። የቦንታንቴና ኢንዜሪሎ 200 አባላት በፓሌርሞ ክፍለ ሀገር ተገደሉ። ይህ ቁጥር የሚያሳየው አስከሬናቸው የተቆጠረውን እንጂ በየጉድባው ወድቀው የቀሩትን አይመለከትም። በህዳር 1982 እንኳ አሥራ ሁለት የክብር ሰዎች በተለያዩ ጊዜያትና ሥፍራ ተገድለዋል። ብዙዎቹ የኮርሌኦኔዚዎች ባላንጦች የሞቱት ሀገር ሰላም ነው ብለው በተቀመጡበት ሁኔታ ነበር። በጣም አስገራሚው ነገር የክብር ሰዎቹ ኮርሌኦኔዚዎቹን በተቀላቀሉ በራሳቸው የቤተሰብ አባላት መታለላቸው ነው። እንዲያውም አንዳንዶቹ የተገደሉት እራሳቸው በሚያምኑአቸው ዘመዶቻቸው መሆኑ ደግሞ የሚያስደነግጥ ድርጊት ነበር።

ይህ «የዓሳ አጥማጆች ጦርነት» ተብሎ የሚታወቀው ከኢጣልያ አልፎ ወደ አሜሪካም ተሻግሯል። ጆን ጋምቢኖ ከኒውዮርክ ወደ ፓሌርሞ ተልኮ ሁኔታውን በትክክል እንዲያረጋግጡ ከተደረገ በኋላ አንድ ግልፅ መመሪያ ተሰጠው። ቶማሶ ቡስኬታን ለማስወገድ አስፈላጊው ሁሉ እንዲደረግና ከተሸናፊው የማፊያ ቡድን አምልጠው ወደ አሜሪካ የሚሰደዱ ሁሉ ጉርቤአቸው እየተያዘ እንዲገደሉ መመሪያ ተሰጠ። ይህ ጥብቅ መመሪያ ከተላለፈ በኋላ የኢንዜሪሎ ወንድም

በኒውጀርሲ ምንት ላውሬል ከተማ አፉና ብልቱ ላይ አምስት ድፍን ዶላር ተለጥፎበት ተገደለ።

ኮርሲኦኔሴዎች ጠላቶቻቸውን ብቻ ሳይሆን ለእነሱ ታማኝ ያልመሰሉአቸውን የክብር ሰዎችን ሁሉ እያሳደዱ ፈጁአቸው። በዚህ አሳበቃም ፍጅቱ፣ ለቦንታቴ ኢንዜሪሎ ቡድን አባላት መጠለያ የሰጠ ዘመድ ሳይቀር ተጨፈጨፈ። ለዚህ የሚሆን ማስረጃ አንድ ሰው መጥቀስ ይቻላል። ሳልቫቶሬ ኮንቶርኖ የተባለው የተቀናቃኝ ቡድን መሪ ከተጠመደበት የመትረየስ ተኩስ ወጥመድ ካመለጠ በኋላ በማይታመን ሁኔታ 35 ዘር ማንዘሮቹ እየተለቀሙ ጭዳ ተደርገዋል።

የ«ዓሣ አጥማጆቹ ጦርነት» የተባለው አሁንም አላቆመም። «አጭሬው ሪና» ጠላቶቹን የገቡበት እየገባ ማሳደዱን ቀጥሎበታል። ሌላው ቀርቶ በራሱ ላይ ወደፊት አደጋ ሊያመጡ ይችላሉ ያላቸውን ወዳጆቹን ሳይቀር ከማስወገድ አልታቀበም። ለዚህ ደግሞ አንዱ ምሳሌ ፒኖ ግሬኮ (በቅፅል ስሙ ጫማው ተብሎ የሚታወቀው) ነው። ፒኖ የሲያኩሉ ማፊያ ቤተሰብ ረዳት አለቃ ሲሆን ቦንታንቴንና ኢንዜሪሎን የገደለ ነበር። በወቅቱ አባቱን ብቻ ሳይሆን የኢንዜሪሎን ታዳጊ ልጅም እጁን ከቆረጠ በኋላ ነበር በአሰቃቂ ሁኔታ የገደለው። ይህን ያደረገውም በኮርሲኦኔዜዎች ላይ ማንም ተመልሶ ማመፅ እንደማይችል ለመቀጣጫ ያደረገው መሆኑ በሰፊው ተነገሮለታል። እሱም በተራው አልቀረለትም። ማፊያ የራሱንም ወገን ቢሆን ወደፊት ሊነሳብኝ ይችላል ካለ ከማጥፋት ስለማይመለስ «ጫማው» በራሱ ሰዎች ተገደለ።

የኮርሲኦኔሲዎች ጦርነት ለሶስት አሥርተ ዓመታት በዚህ መልክ ቀጥሎ ተጠናቀቀ። በኮዛ ኖስትራ ውስጥም አምባገነንነታቸውን አስጠበቁ።

# 18

# ፍንዳታዎቹና በሻጥር መዘፈቅ

## የቶቶሪና ቪላና የአጐት ጁልዮ ነገር

የኮርሲኦኔ የእርሻ ኮሌጅ ህንፃ መልካም የዓይን ማረፊያ ነው:: ከአንድ የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የሚጠበቅ ይዞታ አለው:: ፍፁም አዲስ፣ ባለ ሦስት ፎቅ ህንፃና በመሬት ሥር መኪና ማቆሚያ ተሟልቷል:: መወጣጫ አሳንሰር፣ የአየር ማቀዝቀዣና ለክረምት ጊዜ ማሞቂያ እንዲኖረው ሆኖ ፀዳ ባለ አፀድ ተውቧል:: ፊት ለፊቱ በደመቀ የብረት ሥራ አጊጧል:: ሰገነቶች፣ ያጌጡ ፍርግርጐችና መስህብነት ያለው ዋና በሩ፣ ለጥበቃ በሚያመች መብራቶች ፏ! ብሏል:: የህንፃው የውስጥ ክፍል ባማሩ ወንበሮች፣ ጥቁር ሰሌዳዎች፣ ወለሉ ደግሞ በጥቁርና ነጭ ዕብነበረድ ተሽቆጥቁጦ ሲታይ ዓይን ይማርካል:: ኮምፒዩተሮች ተሟልተውለታል:: የእንጨት በሮቹና በሚገባ የለሰለሱ ግድግዳዎቹ ለህንፃው ተጨማሪ ውበትን አላብሰውታል:: ኮሌጁ በመጀመሪያ ሥራውን ሲጀምር በኮሌጅነት ሳይሆን የቶቶ ሪና ወይም «የቶቶ አጭሬው» የቅምጥል መኖሪያ ቪላ ሆኖ ነው::

ይህን ግዙፍ ህንፃ ቶቶ ሪና መያዝ ለምን እንደፈለገ የጠየቀው ሰው አልነበረም:: እንደተገመተው ከሆነ ግን ቤተሰቡ ብዙ በመሆኑ ጡረታ ሲወጣ በአጠገቡ አሰባስቧቸው ለመኖር እንዳሰበ ግን መናገር ይቻላል:: ስለዚህ ቪላው የጡረታ ዘመኑ መኖሪያና ከፍርዱ ሂደት በኋላ ቀሪ ህይወቱን የሕይወት ፍራፍሬዎቹን እያጣጣመ ለመኖር ስላቀደም ሊሆን ይችላል:: በተጨማሪ ምንም እንኳ ለአሥርተ-ዓመታት ሕይወት እየቀጠፈ ያሰባሰበውን ሀብት ልጡ በራሰ፣ ጉድጓዱ በተማሰ ወቅት

መንግሥት መብቱን እንደማይዳፈረው በመገመቱም ነው ብሎ ማሰብም ይቻላል።

ይህን ሁሉ ማን አህሉኝነትና ልበ-ሙሉነትን ያዘለው የቶቶ ሪና ሀሳብ የተገጣጠመ ሆነበት። በ1995 መጨረሻ ያወጣበት የ125 ሚልዮን ፓውንድ ንብረት ከዚህ የማፊያዎች ማፊያ ከሆነው ሰው ላይ እንዲወረስ ተደረገ። ከላይ የተገለፀው የገንዘብ መጠን በእርግጥ የማፊያውን አለቃ ንብረት ሙሉ ለሙሉ የሚገልፅ አይደለም። የኮርሊኦኔው ቪላ በመንግሥት ተነጠቀ፣ በ1997 ደግሞ በወጣቱ ፀረ-ማፊያ ከንቲባ አማካይነት ንብረቱ በቤተሰቡ እጅም እንዳይገባ የፍርድ ውሳኔ ተሰጠ።

መንግሥት እንዲህ ያለውን ነገር ደፈር ብሎ ከማፊያ የክብር ሰዎች ከገንዘብ አንፃር ከመጉዳቱ ሰዎች ላይ ሲነጥቅ የማፊያን የክብር ሰዎች ከገንዘብ አንፃር ከመጉዳቱ ባሻገር፣ እነሱ በሚፈፅሙት ጉዳይ ላይ ምክንያታዊነታቸውን ሁሉ ብላሽ ያደርገዋል። በአካባቢው ሰዎች ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት ያኮላሸዋል።

ቶቶ ሪና (አጭሬው) የፍትህ ሥርዓቱ በኮዛ ኖስትራ ላይ የሚካሄደውን ጫና በፓሌርሞ የማይቆም ከሆነ በሮም ያሉ የፖለቲካ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ሊያጨናግፉት እንደሚችሉ ለተከታዮቹ ቃል ገብቶ ነበር። ቶቶ ሪና ይህን ቃል የተገባለትን ሁኔታ ሊፈፀምለት ያልቻለው ኮዛ ኖስትራ ከክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲው ጋር ያለው ግኑኝነት በመቀዝቀዙ ነው። በ1980ዎቹ የወጡት ፀረ-ማፊያ ህጐችን ኮዛ ኖስትራ ሊቀለብሳቸው አልተቻለውም። ሪና የተመኘው ቁርጥራጭ ውለታዎች እንዲደረጉለት ሳይሆን ፈርጣማ የሆኑ ህጐችንና ፖሊሲዎችን የሚያኮላሹ ውለታዎች እንዲዋሉለት ነበር። ሆኖም ኮዛ ኖስትራ አቅሙ እየኮሰሰ በሄደ ቁጥር ፖለቲከኞችም ማፊያን ለመከላከልና ራሳቸውን ከዚህ ድርጅት ጋር ለማስተሳሰር አላሹም።

ችግሩ ደግሞ ይበልጥ አፍጥጦ የመጣው ዳኛ ፋልኮኔ በ1991 ወደ ሮም ከተማ በሄደ ጊዜ ነበረ። ወደ ዋና ከተማው የተደረገውን የዳኛ ፋልኮኔን የቦታ ለውጥ ማፊያ የተረጐመው በተቃራኒ ሲሆን ፋልኮኔ በኢጣልያ የፖለቲካ ማጥ ውስጥ ተዘፍቆ፣ ሚናው ኮስሶና አቅመ-ቢስ እንደሚሆን ገምቶ ነው። ዳሩ ግን ዳኛ ፋልኮኔ በፍትህ ሚኒስቴር ውስጥ ተቃራኒ ሁኔታ ገጠመው። ሁኔታው ማፊያን ፀጉር ያስቆመ ትዕይንት ሆነ። ይኸው የኮዛ ኖስትራ ደመኛ ጠላት በክርስቲያን ዴሞክራቲክ

ፓርቲው ሥር የተደራጀውን የፍትህ ሚኒስቴርን ፀረ-ወንጀል ፖሊሲ ዎችን እንዲቀርጽ ተቀመጠ። ከበኩዎቹ ለውጦች ውስጥ በ1991 የታየው የሕገ-ወጥ ገንዘብ ዝውውር ሕግ፣ የማፊያዎችን ስልክ የመጥ ለፍ መብትና የተደራጁ የወንጀል ቡድኖች ሠርገው የገቡባቸውን የከተማ ካውንስሎችን እንደ አስፈላጊነቱ የመበተን ሥልጣን ተጠቃሾች ናቸው።

በጥር 1992 በፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ለሪና፣ ለቤተሰቡና ባጠቃላይም ለኮዛ ኖስትራ ተስፋ አስቆራጭ ጊዜ ሲሆን ሪና በኮዛ ኖስትራ ውስጥ ያለውን ክብር አንኳሷል። በማፊያ ታሪክ እጅግ ጡንቸኛ የነበረው ሪና ድርጅቱን ወደ ፖለቲካዊ ድሁርነት ለወጠው።

የሪና «አጭሬው» ሕልውና አደጋ ሥር ወድቋል። የአቃቤ-ሕጉ መርማሪ የሆነው ሉ ፎርቴ «በማፊያ ውስጥ ሥራህን መልቀቅህን ማሳወቅ አትችልም። እንዲያ ካደረክ ወዲያው ትጠፋለህ። የሪናና ተከታዮ ቹም ሁኔታ ይኸው ነው። ወይ እነሱ ለመጥፋት መወሰን አለባቸው። ወይ ደግሞ በመላው የማፊያ አባል ዓይን ሥልጣናቸውን ጠብቀው እንዳሉ ማስመሰል አለባቸው» ሲል ገልጿል። ሪና ግን የመረጠው ሥልጣኑን አስጠብቆ መቀጠልን ነው። ከዛ ኖስትራ የፖለቲካ ሂደቱ ላይ ብጥብጥ በመፍጠር ተፅዕኖ ማድረግን መረጠ። ሪና «ሰላምን እስተካክሉ ለማስጠበቅ ጦርነት ማካሄድ አለብን» ማስቱም ተሰማ። ዳኞቹ ፋልኮኔና ቦርሴሊኖ እንዲገደሉ በማፊያ ኮሚሽን አማካኝነት ተወሰነ።

በ1992ና 1993 ዓመታት፣ ማለትም ከዋናው የፍርድ ሂደት ውሳኔ በኋላ የሲሲሊ ማፊያ ታሪክ ሁኔታዎች በነውጠኝነት ገዘፉ። በኢጣልያ ዋና ክፍሎች ውስጥ በቦምብ ፍንዳታዎች ሀገሪቱን የማመስ ዘመቻ ተጧጧፈ። ይህ ያልተጠበቀ ወታደራዊ ርምጃ ከሙሶሊኒ መሞት በኋላ የጣልያን መንግሥት ቀጣይነትን በጥርጣሬ ውስጥ ጣለ። ኮዛ ኖስትራም ሆነ ኢጣልያ ባልተሳካው የሪና «አጭሬው» ጡረታ የመውጣት ተስፋ ከተጨናገፈ በኋላ በዚያ የብጥብጥ ጦስ ውስጥ መዳከራቸውን ቀጠሉ።

## ከካፓቼው ፍንዳታ በኋላ

«ቪቶ፣ የእኔ ቪቶ። የእኔ መልአክ! ወሰዱህ አይደል!? ከእንግዲህ ልስምህ አልችልም። ከእንግዲህ ላቅፍህ አልችልም። ከእንግዲህ ልዳብስህ

አልችልም፡፡ አንተ የእኔ ብቻ ነህ» ስትል ማቅ ለብሳ ሮዛሪያ በዕንባ ታጠበች፡፡

ከካፓቺው ፍንዳታ በኋላ መንግሥት ባዘጋጀው የቀብር ሥነ-ሥርዓት ላይ የቪቶ ሺፋኒ ትንሽዬና የገረጣችው ባለቤቱ ሮዛሪያ ሀዘኗን የገለፀችለት ከላይ በቀረበው መንገድ ነበር፡፡ ባለቤትዋ አንቶኒዮ ሞንቲናሪዩና ሮኮ ዲ ሲሎ ከተሰኙ መኰንኖች ጋር በአንድ መኪና ውስጥ ነበሩ ያኔ ዳኛ ፋልኮኔን የገደለውና መሬት ከሰማይ ያደበላለቀው ፍንዳታ በተከሰተ ጊዜ፡፡ መናገሪያው መድረክ ላይ በመቆምና በብዙ የብሔራዊ ቴሌቪዥን ካሜራዎች ፊትፊት ቆሞ «የማፊያ ሰዎች የሆናችሁና በዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥም ላላችሁ ማፊያዎች ሁሉ አንድ ነገር ለማለት እፈልጋለሁ፡፡ እባካችሁ ክርስቲያኖች ሁኑ! ለዚች ወደ ደም ምድር ወደ ለወጣችኋት ለፓሌርሞ ከተማ ስል እለምናችኋለሁ» ስትል ጮኸች፡፡ የቤተክርስቲያኒቱ ካርዲናል ፍትሀታቸውን ከማብቃታቸው በፊት በሞቱት የፖሊስ አባላት አስከሬን አካባቢ ባለሥልጣናት እንዳይደርሱ የሚች ቤተሰቦችና ጓደኞች ተከላከሉ፡፡ ኖዛሪያ ሺፋኒ ለያዥ-ለገናዥ በቸገረ ሁኔታ ዋይታዋን ታቀልጠዋለች፡፡ የተሰጣትን ውሃ በእጇ ይዛ ወለሉ ላይ በቀቢፀ-ተስፋ ትወረውረዋለች፡፡ እንደገና መልሳ የቤተክርስቲያኒቱን ታዳሚ «የማፊያ ሰዎች ሆይ! ይቅርታ እላችኋለሁ፣ ዳሩ ግን መንበርከክ አለባችሁ!» ይህ አባባሏ በየመገናኛ ብዙሃኑ እየተመላለሰ ተደመጠ፡፡

የኢጣልያ ፖለቲከኞች በዳኛ ጆቫኒ ፋልኮኔ ግድያ ውስጥ እጃቸው አለመኖሩን ማረጋገጫ መስጠት አለመቻላቸው በራሱ ኃላፊነት የጐደላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ በሚቀጥለው ዕለታትም የሚች ቤተሰቦችን በዕንባ የቀላ ዓይን በመመልከት ከሳን ደሚኒኮ ቤተክርስቲያን ፊትለፊት በመገናኘት የተከሰተው ልብ-ሰባሪ ሀዘን እንዲለወጥ የበኩላቸውን ጥረት ማድረጋቸውን ቀጠሉ፡፡ በከተማው መሃልና በየነዋሪው ቤት መስኮት ላይ «ማፊያን ከመንግሥት ውስጥ አስወግዱ! ከተማችንን ከመግደል ተቆጠቡ!» የሚሉ መፈክሮች ከተማዋን አጥለቀለቁ፡፡ በታችኛው ሕብረተሰብ ደረጃ ብዙ ፀረ-ማፊያ ድርጅቶች እንቅስቃሴያቸውን አጠናከሩ፡፡ የሮዛሪያ ሺፋኒ «ማፊያዎች ተንበርከኩ!» የሚለው ቃል በየካኔቴራው ላይ ታትሞ እጅ ለእጅ የተያያዙ ተቃውሞዎቹ ከወር በኋላ ከተማዋን አጥለቀለቁ፡፡ ዳኛ ፋልኮኔ በሚኖርበት የኢማኑኤሌ ባራቶሎ

ጐዳና ፊት ፊት ያለው ትልቅ ዛፍ በአበባ ዕቅፎች፣ በፎቶግራፎችና በተለያዩ ማስታወሻዎች የማምለኪያ ሥፍራ እስኪመስል ድረስ ተቀየረ።

በማይታመን ሁኔታ፣ ሐምሌ፣ 1992 የዳኛ ፋልኮኔ ቅርብ የሆነውን ፓውሎ ቦርሰሊኖን መንግሥት ሊጠብቀው እንደማይችል አንድ የማፊያ ድርጊት አመላከተ። ቦርስሊኖንና አምስት ተከታዮቹን የያዘው መኪና ሲፈነዳ ከርቀት ያሉ የከተማዋ ነዋሪዎች ሁሉ እስደንጋጭ ድምፁን ይሰሙ ነበር። ባርሰሊኖ ከሞተ ከሶስት ቀናት በኋላ፣ ሪታ አትሪያ የተባለች የማፊያ ቤተሰብ ኮረዳ ለአቃቤ ህግ መ/ቤት ስለሞቱባት ቤተሰቦችዋ መረጃ እየሰጠች ባለበት ጊዜ ጥበቃ ካለበት ባልኮኒዋ ተወርውራ ተገደለች። ገዳዮችዋ የተውት ማስታወሻ «እሷን መታደግ የሚችል የቀረ ሰው የለም» ሲል ይነበባል። አንድ የፀረ-ማፊያ እንቅስቃሴ ቀስቃሽ ፓሌርሞ በደም የተጨማለቀችና የትራጀዲ ከተማ መሆኗን ሲጽፍ... «እኛ ከዚህ ትራጂዲያዊ ትያትር ውስጥ መውጣት እንፈልጋለን፣ ዳሩ ግን ተከርችሞብናል» ብሏል።

ምንም እንኳ ተስፋ አስቆራጭ ነገር ቢገጥማቸውም የፓሌርሞ ሰዎች የተቃውሞ ድምፅ ማሰማታቸውን አላቆሙም። ሕዝባዊ የፀረ-ማፊያ እንቅስቃሴ በተካሄዱባቸው ሥፍር ቁጥር በሌላቸው ተቃውሞዎች ውስጥ አንድ ገጠመኝ በተለይ ይጠቀሳል። አንድ ትንሽ የሳንዲዊች ማስታወቂያ በሚባለው ዘዴ በተዘጋጀው የተቃውሞ ሰሌዳ ከፊት ለፊት «ፋልኮኔን መሆን እሻለሁ» ከኋላው ደግሞ «በርሴሊኖን መሆን እሻለሁ» የሚል ተጽፎበታል። ለተከታታይ ወራት ተራው ሕዝብ የፀረ-ማፊያን እንቅስቃሴ በማጐልበት አስፈላጊውን ሚና ተጫውቷል።

በሲሲሊ ብሔራዊ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ እንዲታወጅ ተደረገ። በአካባቢው ግዳጅ ስልቹ የሆነውን የፖሊስ ኃይል የሚተካ ሰባት ሺህ ጦር ወደ ደሴቲቱ ተላከ። የሪናንና የገዳይ ቡድኖቹን ጋማ ለመያዝ ተሠማራ። ሁለቱን የአቃቤ-ህግ ሰዎችን ሊከላከሉ ያልቻሉ ባለሥልጣናት እንዲነሱ ተደረገ። የፓሌርሞ አቃቤ-ህግ ዋና መ/ቤት ኃላፊ የሆነውና ከዳኛ ፋልኮኔ ጋር ሲጨቃጨቅ የነበረው እንዲዛወር ሆነ። ከዚህ በተለየ አንድ ግላዊ ጀግንነትም ታየ። በፓሌርሞው ክፍት የሥራ ቦታ ላይ ከሰሜን ኢጣልያ ቱሪን ከተማ ጂያን ካርሎ ካሴሊ አዲስ የፓሌርሞ ኃላፊነት በመውሰድ በኮዛ ኖስትራ ጦርነት ውስጥ እጁን አስገባ። ከዚህ

በኋላ ብዙ ሰዎች ታሰሩ። ወደ ገቦችን የሚከላከል ሕግም እንዲፀድቅ ተደርጐ ማንነታቸውን የመለወጥ መብትም ተሰጣቸው። በፋልኮኔ ዲዛይን የተደረገው አዲስ ፀረ-ማፊያ ተቋም ሥራውን እንዲጀምር ሆነ። ፖሊስ በማፊያ መዋቅር ውስጥ ሠርጐ እንዲገባ ማለትም የዕፅ አዘዋዋሪ ወይም ሕገ-ወጥ ገንዘብ አዘዋዋሪ ለመሆን የሚያስችል ኃላፊነት ተሰጠው። ከሁሉ በላይ ደግሞ የማፊያ አለቆች ከተያዙ በኋላ ከእሥር ቤት ሆነው አመራር የሚሰጡበት ሁኔታን ለማስወገድ ጥብቅ የእሥር ቤት አስተዳደር ተግባራዊ ሆነ።

ብዙ ጊዜ በኮዛ ኖስትራ ታሪክ እንደታየው ግራ የሚያጋባ ሁኔታ ይፈጠራል። ማፊያ ሊጠፋ ነው ሲባል ተመልሶ በሌላ ዘዴና መንገድ ጉልበት ይገዛል። በ1992-93 የፖለቲካ ሥርዓቱ ያደረገው ፀረ-ማፊያ እንቅስቃሴ ያልተጠበቀ ውርጅብኝ ወረደበት። አንድ የሶሻሊስት ፖለቲከኛ 30 ሚልዮን ሊሬ (የወቅቱ የጣልያን ገንዘብ) ጉቦ የተቀበለውን ወደ ሽንት ቤት ሊከት ሲል ተያዘ። በወቅቱ «የንፁህ እጅ ኦፕሬሽን» ተብሎ የሚታወቀው ዘመቻ በየከተሞችና ሌሎች ፓርቲዎቹም ላይ አነጣጠረ። በ1993 በፓርቲ ጉጆ ሥር የመጠሰል (Partyocracy) አባዜ አከተመለት። በ1993 የሙስና መጨረሻ አንድ ሦስተኛ የሚሆኑ የጣልያን የፓርላማ አባላት የሙስና ወንጀል ምርመራ ይካሄድባቸው ነበር። ሁለቱ ገዥ ፓርቲዎች ማለትም ክርስትያን ዴሞክራሲና ሶሻሊስቶች ህልውናቸው ወደ ማክተም ተቃረበ። የኢጣልያ ሕዝብ የሚያየውን ማመን እያቃተውና እየተደመመ የሚካሄደውን ፀረ-ማፊያ አብዮት በግል ቴሌቪዥኑ መመልከቱን ቀጠለ።

በኮዛ ኖስትራ ውስጥ ያለው ሁኔታ እየተለዋወጠ መጣ። ወደፊት ሊመጣ የሚችለውን አደጋ በመገንዘብ ይመስላል ከዋናው የፍርድ ሂደት በኋላና ከካፓቹው ፍንዳታም በፊት «የክብር ሰዎች» ለፖሊስ ኃይል እጃቸውን መስጠት ጀምረው ነበር። ከዚህ ቀደም እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ተከስቶ አያውቅም። ብዙዎቹ ማፊያዎች ለመንግሥት አንዳንድ ማስረጃዎችን ማቅረብ ጀመሩ። በሪና «አጭሬው» በ1973 ተመልምሎ የነበረው ጋስፓሬ ሙቶሎ ዋነኛው የአደንዛዥ ዕፅ አዘዋዋሪ ሆኖ ቆይቷል። በ1992 እሱ ነበር ለዋናው አቃቤ-ሕግ ኮዛ ኖስትራ በፋልኮኔ የሚካሄደውን አደገኛ እርምጃ አንኳሶ እንደነበር የገለፀው። የዋናው የፍርድ ሂደት መካሄድም ፋልኮኔና ቦርሰሊኖ በኮዛ ኖስትራ እንዲገደሉ

መደረጉን አጋልጧል። ከዚህ ሁኔታ በኋላ አቃቤ ህጋውያኑ የሪና አስተሳሰብ ለምን እንደተለወጠ ግልጽ ስዕል አግኝተውበታል። ስለሆነም ወታደራዊ ፖሊሶች ሊይዙት ወሰኑ። ብዙ ጊዜ የማፊያ የኮሚሽን አባላት ቤቱን ስለሚያዘወትሩ ወታደራዊ ፖሊሶች በቁራኛ ቤቱን ይከታተሉት ነበር። አንድ ዕለት ጠዋት ሲከታተሉት የነበሩት ወታደራዊ ፖሊሶች ከቤቱ ሲወጣ ተከተሉት። ሪናና ሹፌሩ በፒያሳ አንስቴን መብራት ላይ እንደቆሙ አራት ፖሊሶች አስቆሙአቸው። ሪና ምንም ዓይነት ማንገራገር አላደረገም። የወታደራዊ ፖሊሶቹ እሥረኛ እንጂ የማፊያ ጠላቶቹ እሥረኛ እንዳልሆነ ሲነግሩት ግን የመርበድበድና የፍራቻ ምልክት ያሳይ ነበር። በሚቀጥለው ቀን የሪና ዋና አማካሪና የጡት አባት የሆነው ሉቺያኖ ሌጂዮ እሥር ቤት እንዳለ ልቡ ቀጥ ብላ ሞተ።

አንድ የኢጣልያ መጽሔት በግልጽ የተንጠለጠለ የዓይኑን ገጽታ በፊት ገጹ ላይ አቅርቦ «ሰይጣኑ» የሚል ርዕስ በመስጠት ስለማንነቱ በአጭሩ ገለፀ። ፍርድ ቤት አቅርበው ከቶማሶ ቡስኬታ ጋር ፊት ለፊት ሲጋፈጥ ከሳሾቹን ምንም ለመናገር አልፈለገም። ግን «በከተማችን ኮርሊኦን በትክክለኛና ሞራላዊ መንገድ ነው የምንኖረው» ሲል ተመፃደቀ።

በኮዛ ኖስትራ ታሪክ ውስጥ የሪና «አጭሬው» መያዝና ለፍርድ መቅረብ በውል መልስ ያላገኘ ነው። ከ1960ዎቹ ጀምሮ ከፍትህ ተሰውሮ ኖሯል። በእነዚህ ጊዜያት አግብቶና ከብዶ፣ ለስኳር ሕመሙ መድኃኒት እየተከታተለ፣ ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት እየላከና በወንጀል ድርጅቶች ላይ ጠንካራ እጆቹን እያሳረፈ ቆይቷል። በመጨረሻዎቹ አምስት ዓመታት ተሰውሮ የቆየበት ሥፍራ በኡዲቶሬ የሚገኝ ሲሆን ልክ እንደሱ ሁሉ የማፊያ አለቃ የነበረው አንቶኒዮ ጂያምና በ1870ዎቹ ይኖርበት የነበረበት ሥፍራ እንደሆነ ታውቋል። ታዲያ ያልተመለሰው ጥያቄ ሪና ለእነዚህ ረዥም ጊዜያት እንዴት ከመያዝ ሊያመልጥ ቻለ? የሚለው ነው።

ሪና ተይዞ ከታሠረ በኋላ የኮዛ ኖስትራ አመራር የተላለፈው የወንድሙ ልጅና ተባባሪው ወደነበረው ሊዮሊካ ባጋሬላ ነው። የኮዛ ኖስትራ አመራር ለ20 ዓመታት በሪና «አጭሬው» ከተያዘ በኋላ በአዲሱ አመራር ሥር እምብዛም አልተንቀሳቀሰም። የኮርሊኦኔዎቹ አክራሪ

ማፊያዎች እነ ጆቫኒ ቡርስካ (የክርስቲያን አንገት ቆራጮች) የለውጡን ሁኔታ አልተቀበሉትም።

አንድ መረጃ እንዲህ ይጠቁማል፡- «ሪና ከታሠረ በኋላ እንደ በፊቱ የሰከነ ነገር አይታይም.... ብዙዎቹ የማፊያ አለቆች የየራሳቸውን የማፊያ ቡድን እንደሚያመቻቸው አድርገው መምራት ቀጠሉ። እንደበፊቱ ወጥነት ያለው አንድነት አልነበረም።»

ያልተለወጠው ነገር የኮርሊኦኔ ቡድን አመራርና የጅምላ ጭፍጨፋ ስትራቴጂው አካሄድ ነው። «ትራክተሩ» ፕሮቬንዛኖ ተናገረ እንደተባለው «አሎት ቶቶሪና ያቀደው ሁሉ ይፈፀማል፣ አናቆመውም» ሲል ቁርጠኝነቱን ገልጿል። ከሪና መታሰር አንድ ወር በኋላ ማፊያ ማናቸውም ከደሴቲቱ ውጪ ያለውን እንቅስቃሴ የማደራጀት ነፃነት እንዳለው ለማሳየት ቱባዎቹ የማፊያ አለቆች ባጋሬላ፣ ቡርስካ እና ሌሎች የፓሌርሞና የትራፓኒ ዋና ዋና አለቆች በመንግሥት ላይ የማፊያ ጦርነቱን ለመቀጠል የተለያዩ መርሐ-ግብሮችን አዘጋጅተው ተገናኙ። ቡርስካ እንዳረጋገጠው በማውሪዚዮ ኮስታንዞ ላይ ጥቃት በመሰንዘር ጦርነቱ ይጀመራል። ቦምቦችን በፒሣ መሸጫዎች፣ በሱፐርማርኬቶች የህፃናት መጠጫዎችን በመመረዝ፣ የሪምኒን የባህር ዳርቻ መዝናኛዎችን በኤች.አይ.ቪ. በተመረዙ መርፌዎች በማጥለቅለቅ ሽብር መንዛት እንደሚያሻ ተወያዩ። ይህ ሁሉ አደገኛ ዕቅድ የተነደፈው ሕብረተሰቡን በማሸበር መንግሥትን አስገድዶ ወደስምምነት ጠረጴዛ ለማምጣት ነው።

ግንቦት 14፣ 1993 የሮም የቴሌቪዥን አቅራቢ የሆነው ማውሪዞ ኮስታንዞ መኪና ወደ ቢሮው እንደተቃረበች ቦምብ ፈነዳ። ዳሩ ግን እንደ ዕድል ሆኖ አልተጎዳም። ግንቦት 27፣ 1993 ደግሞ በፍሎሬንስ ከተማ ዕምብርት በሆነው በጂኦርጎፊሊ ጎዳና ላይ የመኪና ቦምብ ፈንድቶ አምስት መንገደኞች ሲገደሉ፣ አርባ ቆሰሉ። በዚያው ዕለት በሚላን ከተማ ደግሞ በጎዳና ፓሌስትሮ ተጨማሪ አምስት ሰዎች የፍንዳታ ሰለባ ሆኑ። ጥቅምት 21፣ 1993 በሮማ የኦሎምፒክ ስታዲየም አጠገብ ላዚዮና ኡዱኔሴ ቡድኖች ሲጫወቱ ብዙ ወታደራዊ ፖሊሶችን ለመግደል በሚል ፈንጂ ቢጠመድም ሳይፈነዳ ቀረ።

በዚያም ዓመት ነበር ኮዛ ኖስትራ ከመንግሥት ጋር ብቻ ሳይሆን ቤተክርስቲያንን ጭምር ጠላት ያደረገው። ህዳር 1982 ነበር ጆን ፖል

ዳግማዊ ሲሲሊን ሲጎበኙ አንዴ ብቻ አይደለም «ማፊያ» የሚለውን ቃል በንግግራቸው የተጠቀሙት፡፡ ግንቦት፣ 1993 ዳኛ ፋልኮኔና ቦርሶሊኖ ከሞቱ በኋላ የመጀመሪያ ጉብኝታቸውን በደሴቲቱ አደረጉ፡፡ ሶስት ቀናት ከሚፈጀው ጉብኝት ቀዜማ የቫቲካን ልሳን የሆነው «ኦሰርቫርቶሬ ሮማኖ» የሚች ቦርሴሊኖን ባለቤት በመጋበዝ ደብዳቤ እንድትፅፍ አደረገ፡፡ በደብዳቤዋ የባልዋን ዕውነተኛ ክርስቲያናዊነት ከገለፀች በኋላ ለአንባቢዎቿ «ቤተ-ክርስቲያን ዕውነተኛውን የክርስቶስን መንገድ ከመከተል ያለፈ ከሌላ ዓይነት ግጭት ጋር መስማማት የለባትም» ስትል አስታወቀች፡፡ የተወሰኑ የካቶሊክ ሊሂቃን ደብዳቤዋን በመንተራስ በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተወካዮችና በማፊያ ሥልጣን አቀንቃኞች መካከል ያለውን ሻጥራዊ ግንኙነት አወገዙ፡፡

የካቶሊኩ ዋና አለቃ የማፊያን ባህላዊ ሁኔታ ለማውገዝ ሲል በዋጋ የማይተመኑ የጥንት የግሪክ ሃውልቶች የቆሙበትና መልክአ-ምድራዊው አቀማመጡ እጅግ ውብ ወደ ሆነው አግሪጂንቶ ሸለቆ አመራ፡፡ ይህ እጅግ ያማረ ሥፍራ በማፊያ ሕገ-ወጥ ጨረታ ቤቶች እንዲጠፉ ተደርጎ ነበር፡፡ ዋና አለቃው የማፊያን ባህል... ማለትም የገዳይነት ባህል፣ የፀረ-ሰብዕ ባህልና ፀረ-ወንጌል አካሄዳቸውን አወገዘ፡፡ ቀጥሎም ሁሉም ማፊያዎች ወደ ዕውነትና ክርስቲያናዊነት እንዲለወጡ በማለት «አንድ ቀን የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን ይመጣል!» ሲል አስጠነቀቀ፡፡ ዳሩ ማፊያ ለበቀል የማይተኛ ነውጠኛ በመሆኑ ለካቶሊኩ አለቃ የሚሆን ምላሽ ወዲያው ሐምሌ 27 ላይ ሰጠ፡፡ ይኸውም በላቴራኖ ያለው የቅዱስ ጆቫኒ ቤተክርስቲያንና የሮማው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በፈንጂ እንዲጎዳ ተደረገ፡፡ በሰዎች ላይ ግን ምንም ጉዳት አልደረሰም፡፡ መስከረም 15 ቀን ደግሞ በምሥራቅ ፓሌርሞ በምትገኘው ብራንካሲኦ መንደር ፀረ-ማፊያ ቄስ የነበረው ፒኖ ፑግሊሲ እበሩ ላይ ተገደለ፡፡ አንድ የማፊያ ነፍሰ ገዳይ በኋላ ላይ እንደተናዘዘው ቄስ ፒኖ ከመገደሉ በፊት «ይህ እንደሚሆን ጠብቄ ነበር!» እንዳለው ተናግሯል፡፡

ከጥር፣ 1992 የፍርድ ውሳኔ በኋላ ማፊያ ወደፊት ዕድሜውን ስለማርዘሙም ሆነ ስለማሳጠሩ ምንም አላለም፡፡ የራሱን አጋዥና ሕይወት አድን ሥርዓቱን በራሱ እጅ ቆራረጠ፡፡ በዚህም የተነሳ በ1996 የማፊያ ወደ-ገቦች ቁጥር ወደ 424 አሻቀበ፡፡ መፈናፈኛ ያጣው

የኮርሊኦኔዚ ማፊያ ጥብቅ የዘብጢያ ሁኔታ ተደምሮበት ታላላቆቹ የማፊያ አለቆች እንኳ ሳይቀሩ ከፍትህ ጋር መተባበር ጀመሩ፡፡

ለዚህ አንድ አነስተኛ ምሳሌ ማስረጃ ይሆናል፡፡ ሰልቫቶሬ ባንሴሚ የተባለው የማፊያ አለቃ በዳኛ ፋይኮኔና በቦርሴሊኖ ላይ የሞት ፍርድ ሲተላለፍ የማፊያ ኮሚሽን ውስጥ ሆኖ ውሳኔ ያስተላለፈ ሰው ነበር፡፡ ከዚያም የካፓቺን ፍንዳታ ያከናወነ ጨካኝ ማፊያ በመሆን ይታወቃል፡፡ በኋላ ሪና በወዶ-ገብ ማፊያዎች ላይ ጨካኝ ርምጃ ለመውሰድ ፕላን ሲያቀርብና የወዶ-ገቦችን ቤተሰቦች ከእነ ህፃን ልጆቻቸው ለመግደል ሲወስኑ፣ በ1993 ካንሴሚ ከሕሊናው ጋር ተከራክሮ በቀጥታ ወደ ወታደራዊ ፖሊሶቹ ካምፕ ነበር የተጓዘው፡፡ እጁን ብቻ ሳይሆን ለሕግ የሰጠ 33 ሚልዮን ፓውንድ ያወጣል ተብሎ የተገመተውን ሀብቱን ጭምርም አስረከበ፡፡ በፍርዱ ሂደት ላይ ከእነ ቶማስ ቡስኬታ ጋር ሲቀርብ (በነገራችን ላይ ሁለቱም አንድ የማፊያ ቤተሰብ ነበሩ ከዚያም በ1970ዎቹ እሥር ቤት ውስጥ ነው የተወዳጁት) ሁለቱን የቡስኬታን ልጆች ራሱ አንቆ መግደሉን አጋልጧል፡፡ ቡስኬታም በዚህ ጊዜ ያለው ነገር ቢኖር «የማፊያ ትዕዛዝ ልትቃወም አትችልም፡፡ ይቅርታ አደርግልሃለሁ! ምክንያቱም የኮዛ ኖስትራ አባል መሆን ምን እንደሆነ አውቃለሁና!» ነበር ያለው፡፡

በእንደነዚህ ዓይነቱ በአዲስ የማፊያ ወዶ-ገቦች የተጥለቀለቁት መርማሪዎች የፋልኮኔና የቦርሴሊኖን አሟሟት፣ በየሀገሩ የፈነዱትን የፈንጂዎች አደጋ፣ ቄስ ፑሊሲን ማን እንደገደለና ሌሎችንም ብዙ ነፍሶችን የጨረሰው ማን እንደሆነ ለማወቅ ጥረታቸውን ቀጠሉ፡፡ ኮርሌኦኔሲዎች ግን የማፊያን ሽብር በመዝራት ጭፍጨፋቸውን አላቆሙም ነበር፡፡ እንዲያም ሆኖ አንዳንድ የማፊያ አለቆች በወታደራዊ ፖሊሶቹ ተጠመዱ፡፡ ሊዩሉካ ባጋሬላ ሰኔ፣ 1995 በመሀል ፓሌርሞ አፓርትመንቱ ተያዘ፡፡ ይህ እንግዲህ ከሦስት ዓመት ባነሰ ጊዜ ሁለተኛው የማፊያዎች የአለቆች - አለቃ መያዙ ነው፡፡ ትንሹ ጁሴፔ ዲ ማቲዎ ታንቆና በአሲድ ሰውነቱ እንዲያር ከተደረገ ከአራት ወራት በኋላ ደግሞ ወታደራዊ ፖሊሶች አግሪጀንቶ መንደር አጠገብ በድንገት በመግባት «የክርስትያኖች አንገት ቆራጭ» የሆነው ቡርስካ ከነቤተሰቡ ከተደበቀበት

ያዙት፡፡ ቡርስካ በተያዘበት በዚያን ጊዜ ኮዛ ኖስትራ በታሪኩ እጅግ አደገኛ ቀውስ ውስጥ ተዘፍቆና እንዲያውም ፍፃም ለመሸነፍ ተቃርቦ ነበር፡፡

## አጉት ጁሊዮ

ዋናው የፍርድ ሂደት ከተካሄደ በኋላ ኮዛ ኖስትራ የወሰደው አውሬያዊ ብቀላ የራሱን የወደፊት ተስፋ አደጋ ውስጥ ጥሏል፡፡ በ1992-93 የነበረው የኮዛ ኖስትራ የሽብር ድራማዎች በፖለቲከኞችና በማፊያ መካከል ግጭትን ፈጥሯል፡፡ ለሩብ ምዕተ-ዓመት ያህል ሀገሪቱን የመራውና እጅግ ስልጣንን ያግበሰበሰው ፖለቲከኛ በ1995 ለማፊያ በመሥራት በሚል ተከሶ ለፍርድ ቀረበ፡፡ ይህ ሰው የክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲው መሪና ለሰባት ተከታታይ ጊዜያት የኢጣልያ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው ጁሊዮ አንድሮቲ ነው፡፡

የጁሊዮ አንድሮቲ ድራማ የሚጀምረው መጋቢት፣ 1992 ሲሆን ይህም ከሳልቮ ሊማ መገደል ጋር ነው፡፡ ሪና «አጭሬው» በከፈተው ጦርነት ፋልኮኔና ቦርሶሊኖ ከመገደላቸው አንድ ሳምንት በፊት የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲው ፖለቲከኛ ሳልቮ ሊማ እንዲገደል ተደርጓል፡፡ ሊማ የተገደለው ከፓሌርሞ አጠገብ ባለች ትንሽ ከተማ ቤቱ በሆነች «ሞንዴሎ» ሲሆን መጀመሪያ ሞተር ሳይክል በያዘ ማፊያ የመኪናው ጎማ ላይ ተተኰሰ፡፡ በዚህ ጊዜ «እነዚህ ሰዎች ተመልሰው መጡ! እመቤቴ ማሪያም! ተመልሰው መጡ!» ካለ በኋላ ከመኪናው ውስጥ ሮጦ ወጣ፡፡ ከገዳዩ በ30 ሜትር ርቀት ላይ የነበረው ሊማ ጀርባውን በጥይት ተደብድቦ ወደቀ፡፡

ብዙዎቹ የማፊያ ወዶ-ገቦች ያረጋገጡት ራሱ ሳልቮ ሊማ በማፊያና በብሔራዊ መንግሥት መካከል አደራዳሪ መሆኑን ነው፡፡ ሊማ ከሞተ በኋላ ታዋቂው ጋዜጣ «ላ ሪፑብሊካ» ያወጣው ካርቱን እንደሚያመለክተው አገዳደሉ ግልጽ የፖለቲካ ትርጉም አለው የሚል መልዕክት አዝሎ ታተመ፡፡ በካርቱኑ ግርጌ የተፃፈው ሽሙጥ ጉዳዩን ከጁሊዮ አንድሮቲ ጋር አያይዞታል፡፡ ይህም ማለት ሳልቮ ሊማ ላይ ጥቃት የደረሰውና ዋና ዒላማ የሆነው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጁሊዮ አንድሮቲ መሆኑን በተዘዋዋሪ ጠቁሟል፡፡ በሌላ አነጋገር የወጣው ካርቱን ለማስተላለፍ የተፈለገው «ኮዛ ኖስትራ ጓደኛውን ከጀርባ ወጋ!» የሚል መልዕክት ነበር፡፡

ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በተደጋጋሚ መመረጥና ማሸነፍ ሊማ ወሳኝ ሰው ሆኖ አገልግሏል። ሊማ በምርጫው ሂደት ባያግዝ ኖሮ ኢንድሪዩቲ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን ባልቻለ፤ ሆኖም ግን መጨረሻው ከኋላ መወጋት ሆነ። ከሊማ መሞት በኋላ የነዳኛ ፋልኮኔ ጉዳይ፣ የሙሰኞች ሁኔታ ለፍርድ በሚቀርብበት ጊዜ የፓሌርሞ አቃቤ-ህግም ጁሊዮ አንድሮቲ ከኮዛ ኖስትራ ጋር ያለው የግኑኙነት ጠረን የጠነነ በመሆኑ ለፍርድ እንዲቀርብ ጠየቀ። የታሰረው የማፊያ አለቃ ቶማስ ቡስኬታ በቅርብ እጅ ከሰጡ የማፊያ ወዶ-ገቦች ጋር ኮዛ ኖስትራ ከፖለቲከኞች ጋር ስላለው መሞዳሞድ ምስክርነቱን ሲሰጥ ሁለት ዋና ስሞችን አጉልቶ አውጥቷል - የሳልቮ ሊማንና የጁሊዮ አንድሮቲን።

በጠቅላይ ሚኒስትሩ አንዲሮቲ ላይ የቀረበው ውንጀላ እጅግ ጠንካራ ነበር። ይህም የኢጣልያው ወሳኝ የፖለቲካ ሰው በ1970ና 1980ዎቹ ከዋናዎቹ የማፊያ አለቆች ከስቴፋኖ ቦንታንቴ፣ ከታኖ ባዳልማባቲና ሚኬሌ ግሬኮ ጋር ፊት ለፊት ተቀምጠው ስለ ቢዝነስ እንደተመካከሩ ያትታል። ከዚሁ ጋር መገናኛ ብዝሃኑ ትኩረት አድርገውና ታዳሚን እንዲስብ በሚል አንዲሪዩቲ በአንድ ምስጢራዊ ግኑኙነት ወቅት የማፊያውን የአለቆች አለቃ ቶቶ «አጭሬውን» አቅፎ መሳሙን አተኩሩበት። ጠቅላይ ሚኒስትር አንትሪዩቲ ባለው የጠበቀ ግኑኙነት በኮዛ ኖስትራ ውስጣዊ ቡድን ውስጥ «አጐት ጁሊዮ» ተብሎ ይታወቃል። ምንም እንኳ አንድሪዩቲ ከኮዛ ኖስትራ ጋር የጠበቀ ግኑኙነት አለው ቢባልም የገባላቸውን ቃል ባለመጠበቁ ወዳጁ ሳልቮ ሊማ ተገደለበት፣ በኋላም አበሳው ወደ እሱ መጣበት። አንዳንድ የማፊያ ወዶ-ገቦች ተናገሩ እንደተባለው ሪና «አጭሬው» አንድሪዩቲን ወይም ከልጆቹ አንዱን ለመግደል ዕቅድ ይዞ ነበር ሲሉ ገልፀዋል።

በ1999 በማፊያ ወዶ-ገቦች የቀረበው ማስረጃ እርስ በእርሱ ይጣረዛል በሚል አንድሪዩቲ ከክሱ ነፃ ሆነ። ምንም እንኳ የፍርዱ ሂደት በዚህ ሁኔታ ቢቋጭም አንዲሪዩቲ ከማፊያ አለቆች፣ በሙሰኞችና ታክስ ከሚያጭበረብሩ የማፊያ ውልዶች ጋር ትብብርና እገዛ ያደርግ እንደነበር የ1970ዎቹና 80ዎቹ የኢጣልያ ሁኔታዎች ይመሰክራሉ።

እጅግ ወሳኝ በሆነው ከማፊያና ከፖለቲካ ግኑኙነት ጋር በነበረው ውጥንቅጥ ሻጥር ያልታሰረው ጠቅላይ ሚኒስትር አንድሪዩቲ በ1979

ስሜን በክሎታል በማለት አንድ ጋዜጠኛን ማፊያን በማዘዝ በማስገደሉ 24 ዓመት ተፈረደበት። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትርና በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የዕድሜ ልክ ሴናተር የሆነው አንድሪዩቲ በዋናው ፍ/ቤት እንደገና ካልታየ በስተቀር ለጊዜውም ቢሆን ወደ እሥር ቤት የሚሄድበት ሁኔታ የለም።

በአብዛኛው ጉልህ የማፊያ የሽብር ተግባር ካልተፈፀመ ሁሌም ቢሆን ሲሲሊ ከሚላንና ከሮም የራቀች ናት። በተረጋጋና ሰላም በሰፈነ ሁኔታ ውስጥ ደግሞ ኮዛ ኖስትራ እንደገና ራሱን ያደራጃል።

## «ትራክተሩ» ወይም «አጉት ቢኑ»

ከፖሊስ በማምለጥና በመሰወር ቤርናርዶ ፕሮቬንሳኖ ከፍተኛ ሪከርድ ጨብጧል። ከመስከረም 10፣ 1963 ጀምሮ በኮርሊኦን በፈፀመው የመግደል ወንጀል በፖሊስ ሲፈለግ ቆይቷል። ለ40 ዓመታት ከፍትህ ተሰውሮ መቆየት ቀላል ነገር አይደለም። እንደ ቶቶ ሪና ሁሉ ፕሮቨንሳኖ እነዚያን ሁሉ ጊዜያት ያሳለፈው በምዕራብ ሲሲሊ ነበር። በ1959 በተነሳው ፎቶ መሠረት ፖሊስ የፎቶውን ተመሳሳይ ሰው ሁሌም እንደፈለገ ነው። የዚህ ሰው ተደብቆ ለረዥም ጊዜ መቆየት ማፊያ ምን ያህል ክልሎችን እንደያዘና እንደሚያስተዳድር ማለፊያ ምስክር ይሆናል።

በኮዛ ኖስትራ ውስጥ ፕሮቬንሳኖ ያለው ሚና ተንኳሶ ከመቅረቡ የተነሳ ሞቷል ተብሎም ተወርቷል። ፕሮቬንሳኖ «ትራክተሩ» በሚል ቅጽል ስሙ አንሶ የቀረበ ይሁን እንጂ ርህራሄ የለሽ ነፍስ-ገዳይ በመሆን ይታወቃል። የደለበ መረጃ ያላቸው የማፊያ ወዶ-ገቦች ግን ለዚህ ሰው የተለየ ስዕል ሲሰጡ የኮርሊኦኔሴ ነዋሪዎች ደግሞ «አጉት ቢኑ» ሲሉ ያቆላምጡታል። ፕሮቬንሳኖ ከሪና ይልቅ ጮሌ የንግድ አዋቂና አእምሮው ለፖለቲካ የሰላ አድርገው ያቀርቡታል። ጂያኦቺኖ ፔኒኖ የተባለው ዶክተርና፣ የክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲው አባል፣ እንዲሁም የማፊያ የክብር ሰው የነበረው ለመንግሥት በ1994 በሰጠው ማስረጃ የቪቶ ሲያንሲማኖን የፖለቲካ ዕድገት ያደናቀፈ ብሎ ይፈርጀዋል።

ለብዙ ዓመታት ፕሮቬንሳኖ በሪና ጥላ ተጠልሎ ይንቀሳቀስ ነበር። ሪና በመንግሥት ላይ የማፊያ ጦርነትን በማካሄድ ሲጠመድ አጅሬው

ፕሮቬንሳኖ ደግሞ የንግድና የፖለቲካ ድሩን ያደራ ነበር። ይህም ለሲሲሊ ማፊያ ትልቅ የገቢ ምንጭን የፈጠረ ነው ማለት ይቻላል። የንግድ አካሄዱን የጀመረው በሉቺያኖም ሌጂዮ በተመሠረተው የዕፅ ዝውውር ገንዘብን በመሥራት ሲሆን ከዚያም በጤናና በግንባታ መስኮች ብዙ ገንዘብ በማግበስበስ ይታወቃል።

«አጐት ቢኑ» የዋዘኛ ባህርይ ያለው ሰው አይደለም። የማፊያ ከፍተኛው ወሳኝ አካል የሆነው ኮሚሽን አባል በመሆን ፋልኮኔና ቦርሴሊኖን ጨምሮ እጅግ ብዙ ዜጐች እንዲገደሉ ውሳኔ አስተላልፏል። በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ በኮዛ ኖስታራና አፈንጋጭ በሆኑትና ከማፊያ ከተባረሩት «አንፀባራቂ ኮከብና መጥፎ ዕድል» በተሰኙ ቡድኖች ላይ ኃላፊነቱን ወስዶ ጦርነት የከፈተው ይኸው ሰው ነው። በፕሮቬንሲኖ ዘመቻም በሦስት ዓመት ውስጥ 300 ያህል ሰዎችን ጨርሶአቸዋል።

በ1995 የማፊያ አለቆች አለቃ ከሆነ በኋላ ፕሮቬንሳኖ ለኮዛ ኖስትራ አዲስ ስትራቴጂ ቀየሰ። ዋና ዕቅዱም ኮዛ ኖስትራ ከሕዝብ የዕይታ መድረክ ራዳር እንዳይታይ ማድረግ ነበር። እሱ ስልጣኑን ከያዘ በኋላ እንደ ከዚህ ቀደሙ የታዩ የግድያ ሁኔታዎች አልነበሩም። ሌላው ቀርቶ ከፓሌርሞና ከካታኒያ ግዛቶች ተራ ወንጀሎች እንኳን አልታዩም። በተቀናጀ ወንጀል፣ በንግድና በፖለቲካ መካከል ያለውን ግኑኝነት የሚያ ጠናው አንድ የአቃቤ-ህግ ሙያተኛ እንዳለው አጐት ቢኑ «ሚዲያ ላይ የሌለ፣ በተግባርም የለም» የሚለውን መርህ እንደሚከተል ገልጾአል።

ፕሮቬንሳኖ ተደጋግሞ እንደሚነሳው ከሪና ይልቅ በአስተዳደራዊ አቀራረቡ የማቻቻል መንገድን ይከተላል። በአብዛኛው ደግሞ ትርፍን በጋራ ለማካፈል የቆመ ነው። «እንብላና ይብሉ!» የሚለው አባባል በማፊያ አሠራር ውስጥ የተለመደ ነው። በአጠቃላይ አነጋገር በፕሮቬንሳኖ አሠራር ኮዛ ኖስትራ የተማከለ ቢሆንም በሪና «አጭሬው» ጊዜ እንደታየው የግለሰብ አምባገነንነት አይታይበትም።

አጐት ቢኑ በኮዛ ኖስትራ ኃላፊነቱ ማፊያ በንግዱ ዓለም ገብቶ እንዲጠቀም ምንም እንኳ መንግሥት ፀረ-ሙስና የጨረታ ሂደቶችን ለመቆጣጠር ጥረት ቢያደርግም በሲሲሊ ግን በተለየ ሁኔታ እንዲከሽፍ ተደርጓል። የፓሌርሞ የአቃቤ-ህግ ኃላፊ እንደገመተው 96 በመቶ የሚሆነው የመንግሥት ኮንትራት ሥራዎች በማፊያ እንዲጭበረበሩ ተደርገዋል።

በሲሲሊ የሚወጣው የሕዝባዊ አገልግሎት ገንዘብ የሚመጣው ከኢጣልያ ሳይሆን ከብሩሴልሱ የአውሮፓ ሕብረት ነው፡፡ የአውሮፓ ሕብረት «የ2000 አጀንዳ» ተብሎ የሚታወቀው በአውሮፓ ያሉ ደሃ አካባቢዎችን ለማበልፀግ ያለመ ሲሆን ለሲሲሊ ብቻ 7586 ቢልዮን ዩሮ ከ2000-2006 ለማውጣት አቅዶ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ነውጠኛው ኮዛ ኖስትራ ይህንን ዕቅድና ራዕይ ፈፅሞ አይጋራም፡፡

ትልቁና ለማፊያ የገንዘብ ጉልበት የሰጠውን የዕፅ ዝውውር ንግድን መልሶ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ማፊያ የምሥራቅ አውሮፓ ሀገሮች ከሶሻሊዝም መውደቅ ጋር ሲፈራርሱና አዳዲስ መንግሥታት ሲቋቋሙ ዓላማ ያደረገው ከነዚህ ሀገራት ማፊያዎች ጋር የዕፅ ዝውውር ንግድን ማጧጧፍ ሆነ፡፡ የኢጣልያና የሩሲያ የምሥጢር ሠራተኞች እንዳረጋገጡት በ1992 የማፊያ የክብር ሰዎችና የሩሲያ ማፊያ ኃላፊዎች በፕራግ ከተማ ስለ ዕፅ ዝውውር ንግድ መክረዋል፡፡ ቀጥሎም ሁለተኛ ስብሰባቸው ዕፅንና የጦር መሣሪያ ንግድን በተመለከተ የተደረገ ሲሆን በዚህ ስብሰባ ላይ የአሜሪካ ማፊያ ተወካዮችም ተገኝተው ነበር፡፡

ከነዚህ ሕገ-ወጥ ንግዶች የሚገኙ ትርፎችን ለማፊያ ማጠናከሪያነት ከእነ እስቴፋኖ ቦንታቴና ከነቶቶ ሪና ዘመን የበለጠ ትኩረት ተደርገውበታል፡፡ ለእንደነዚህ ያሉ አሻጥሮች ደግሞ ማፊያ ሙያተኞችን ይጠቀማል፡፡ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ የማፊያ የክብር ሰዎች ተከታዮች በሕግ፣ በባንክና በሌሎች የንግድ ዘርፎች ለመሠማራት በብቃት ተዘጋጅተዋል፡፡ ስለዚህ ማፊያ የራሱን በዕውቀት የበለፀጉ ሰዎችን በመጠቀም ራሱን ያደለባል፣ ሀገሪቱን ደግሞ እንደ መዥገር ተጣብቆ ያኮስምናታል፡፡

በዘመነ-ፕሮቬንሳኖ ትልቁ ትኩረት የተደረገው የማፊያ እሥረኞችን መንከባከብ ነው፡፡ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የዋሉት የማፊያ እሥረኞች ይከፈላቸው የነበረውን ደሞዝ ማግኘት አልቻሉም ነበር፡፡ በፕሮቬንሳኖ የኮዛ ኖስትራ አገዛዝ ዘመን ግን ታሣሪ ማፊያዎች ደሞዛቸውን እንዲያገኙ ጥረት ተጀመረ፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ ጥረቶች በማድረጉ ከዚህ ቀደም ተጉድተው የነበሩ የማፊያ የግንኙነት ድሮች ተመልሰው ተጠገኑ፡፡ በወቅቱ አንዳንድ ኮሜንታተሮች የኢንተርኔት ዕድገትና የግሎባላይዜሽን መምጣት ማፊያን ይገድላል ቢሉም

የተሳካላቸው አልሆነም። ምክንያቱም ማፊያ ባሳለፋቸው የ150 ዓመታት ዕድሜ ውስጥ የተለያዩ የዘመንኛ ተግዳሮቶችን እያለፈ ህይወቱን አርዝሟል። ካፒታሊዝምን፣ የብሔራዊ መንግሥት መቋቋሙን፣ የሶሻሊዝምን ዘመን፣ ፋሽዝምን፣ የዓለም ጦርነቶችን፣ ዴሞክራሲያዊ ነትንና የኢንዱስትሪ ዕድገቶችን ሁሉ ስለተመለከተ የ19ኛውም የ20ኛው ክ/ዘመን ለውጦች ኮዛ ኖስትራን አሽቀንጥረው ሊጥሉት አልቻሉም። ስለዚህ የ21ኛውን ክ/ዘመንም ተግዳሮቶችን ሊወጣ ይቻለዋል። አቃቤ-ህግ የሆነው ስካርፒናቶ «የጋራ አእምሮ በመጠቀም ማፊያ ካለፉት ስህተቶቹ መማር መቻሉና እነዚህንም ለመዋጋት የሚያስችል ርምጃ መውሰዱ ማፊያን እንዳይሞት ያደርገዋል» ሲል ገልጿል።

እነ ዳኛ ፋልኮኔና ቦርሴሊኖ፣ በመሀል ሀገር የቦምብ ፍንዳታዎች መዘውተር ጋብ ካለ ከአሥርተ-ዓመታት በኋላ አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች አሁንም የሚያስጋቸው ኮዛ ኖስትራ የሚፈልገውን የሚሰጡትን ሰዎች በመንግሥት አካል ውስጥ አግኝቷል የሚለው ነው።

## አንጋቹና የማስታወቂያው ሰውዬ

አንቶኒዮ ጂዩፍሬ ወይም ደግሞ «ባለትንሹ እጅ» የካካም ኮዛ ኖስትራ ቡድን ኃላፊ ሲሆን ሚያዝያ 16፣ 2002 ተያዘ። የዚህ ሰው የቅጽል ስም የወጣው ለአደን ወጥቶ በነበረ ወቅት በቀኝ እጁ ላይ ጉዳት ከደረሰበት በኋላ ነው። በመለማመዱ የተነሳ በግራ እጁ እንደፈለገው ጠበመንጃ ይዞ መታኮስ ይቻላል። ጂዩፍሬ ተደብቆ በሚኖርበት ብቸኛና በእርሻ ማሳ ላይ በተሰራ አንድ ህንፃ ለበርናርዶ ፕሮቬርሳኖ (አጐት ቢኑ) የሚላክ አንድ ፊስታል ሙሉ ደብዳቤ ይገኛል። አንዳንድ ኢንተርፕረነሮች በኩባንያቸው የማስታወሻ ወረቀት ላይ ሳይቀር አጐት ቢኑ እንዲታደጋቸው ይማፀኑታል።

በአንድ የሰኔ ወር ላይ ከመርማሪ አቃቤ-ህጐች ጋር መነጋገር ጀመረ። «እኔ የፕሮቬርሳኖ ዋና ተባባሪ ነኝ፣ ለእኔ የተሰጠኝ ሥራ ኮዛ ኖስትራን በከፍተኛ ደረጃ እንደገና ለማደራጀት ነው» ብሎአቸዋል። ከሁሉ ግን በጣም ድንገተኛውና አስደንጋጩ ጉዳይ በ1993 ኮዛ ኖስትራ ቀጥተኛ ግኑኝነት ከሲሊቪዮ ቤርሉስኮኒ ተወካዮች ጋር ማድረጉን

የሚጠቁመው ጉዳይ መርማሪዎቹን አስበረገገ። ሲልቪዮ ቤርሉኮኒ በኢጣልያ እጅግ ሀብታምና፣ የሚዲያ ተቋማት ባለቤት የሆነ ሰው ነው።

በ1993 ኮዛ ኖስትራ ወደ መሀል ሀገር የቦንብ ጥቃቱን ሲሰነዝር በቤርሊስኮኒ ደግሞ አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ በመመሥረት ሂደት ላይ ነበር። በቤርሊስኮኒ ሰዎችና በኮዛ ኖስትራ መካከል ለነበረው ውይይት ዋናው ጉዳይ በማፊያና በቤርሊስኮኒ በታቀደው የፖለቲካ ፓርቲ መካከል መልካም ግኑኝነትን መፍጠር ሲሆን ይኸው ፓርቲም ተመሥርቶ «ፎርሳ ኢጣልያ» (Come on, Italy!) የሚል የክርስትና ሥም ወጥቶለታል።

በሚቀጥለው ዓመት ቤርሊስኮኒ ተባባሪዎቹን በአጠቃላይ ምርጫው አሸነፈ። ዳሩ ግን ተባባሪዎቹ 1994 ሳይጠናቀቅ ተፈረካከሱ። ከዚያ በግንቦት 2001 ጅዩፍሬ ከመያዙ አንድ ዓመት በፊት ፎርሳ ኢታሊያ በምርጫው አሸንፎና ቤርሉስኮኒም ሁነኛ የፓርላማ የበላይነት አግኝቶ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነ። ይህ «ፈረሰኛው» መባልን የሚወደው ቱ□ር ሰው በ2001 ምርጫ ወቅት ሀብቱ 10.3 ቢልዮን ዶላር ደርሶ ነበር። ከብዙ ሀብቱ መካከልም ሦስት ዋና የግል ቴሌቪዥን ኔትዎርኮችና የማተሚያ ተቋማት ተጠቃሾች ናቸው። ከሞሶሎኒ በኋላ በኢጣልያ፣ በተለይም በሲሲሊ ላይ ወሳኝ ኃይል ያለው ሰው ቤርሊስኮኒ ሲሆን የደሴቲቱን 61 የፓርላማ መቀመጫዎች ሁሉ Aየያዘው ፎርሳ ኢጣልያ ፓርቲ ነው።

ከ1994 በኋላ የማፊያ የክብር ሰዎች ለፎርሳ ኢጣልያ ፓርቲ ዕጩዎች ድምፅ እንዲሰጡ መመሪያ መስጠታቸውን የሚጠቁሙ ብዙ ማሳያዎች አሉ። ባለፉት የአንድ ምዕተ-ዓመት ተኩል የማፊያ ዕድሜ ውስጥ እንደታየው የፖለቲካ ሥልጣን ያላቸው ፖለቲከኞች ሁሉ የዚህ የተደራጀ የወንጀል ድርጅት ሰለባዎች መሆናቸው ታይቷል። በ1980ዎቹ ከክርስቲያን ዴሞክራቲክ ፓርቲ ጋር ከተለያዩ በኋላ ኮዛ ኖስትራ ሌላ ጠቃሚው የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ሲያፈላልግ ቆይቷል። በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ «ሪና አጭሬው» አዲስ የሲሲሊ የተገንጣይ እንቅስቃሴ መመሥረት ይቻል እንደሆን ካሉት ፖለቲከኞችና ነጋዴዎች ጋር ተመካክሯል። በኮዛ ኖስትራ ከፍተኛ አለቆች ዘንድ ከ1993-94 ባለው ጊዜ የፎርሳ ኢጣልያ ፓርቲ መምጣት ለማፊያ ተፅዕኖ ማስገኛ መንገድ

መሆኑ ታመነበት፡፡ ማንም ሰው በርሉስኮኒ በቀጥታ የማፊያ ሰው ነው ብሎ መናገር ባይችልም ኮዛ ኖስትራ ላለፉት ሦስት አሥርተ-ዓመታት ከቦርሉስኮኒ ረዳት ከሆነ ሰው ጋር ቀጥተኛ ግኑኝነት ነበረው፡፡

በ1974፣ በርሉስኮኒ ሚላን ከተማ አጠገብ ላለ ድርጅቱ ደህና «አንጋችና የቅርብ ረዳት» የሚሆን ሰው ይፈለግ ነበር፡፡ ከዚያም ማርቼሎ ዴልኡትሪ የተባለውና በሲ.ሲ.ሊ. የባንክ ዓለም ውስጥ ሲረማመድ የቆየውን በርሉስኮኒ ንግዱን እንዲመራለት ወሰደው፡፡ ማርቼሎን ደግሞ የጠቆመው ሰው የፓሌርሞው ቪቶሪዮ ማንጃኖ ሲሆን ይህ ሰው ሁለት ሰዎችን በመግደል ወንጀል ዕድሜ ልክ እሥራት ከተፈረደበት በኋላ በካንሰር ታሞ ሞቷል፡፡ ይህ በበርሉስኮኒ በቅርብ «ረዳትነት» የተመረጠው ሰው በኮዛ ኖስትራ የፓርታ ኖቫ ቤተሰብ ማፊያ ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ሚያዚያ 2000፣ በ72 ዓመት ዕድሜው ቶማሶ ቡስኬታ በካንሰር ህመም እስከወዲያኛው አሸለበ፡፡ ለ40 ዓመታት ኮዛ ኖስትራን ካገለገለ በኋላና ለ16 ዓመታት ኮዛ ኖስትራን መልሶ ለማጥፋት ተግቶ ከሠራ በኋላ 200 የሀሰት ስሞችን እንደያዘ ወደማይቀረው ሶስት ክንድ መሬት ውስጥ ገባ፡፡ እሱና ጆቫኒ ፋልኮኔ በ1984 ስለማፊያ የተናገሩት ቃል መራራ ትውስታ ሆኖ ቀረ እንጂ አልተፈፀመም፡፡ እንዲህ ሲልም ያን መራራ ትውስታውን ይገልፃል፡፡

«በመጨረሻው ቃለምልልስ፣ እኔና ጆቫኒ ፋልኮኔ ማፊያ ድራሹ እንደሚጠፋ ገምተን ነበር፡፡ ከእንግዲህ በኋላ በመሬታችን ላይ ማፊያ አይኖርም ብለን፡፡ አሁን ግን... ያደረግኩት ትንበያ ስህተት መሆኑን መቀበል አለብኝ» ሲል ስለማፊያ አይሞቴነት ለመመስከር ተገዷል፡፡

ኮዛ ኖስትራ አንዴ እየተዳከመ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ እየተጠናከረ ቢሄድም የተጓዘበት ነውጠኛ የታሪክ ሂደት ወደ አዲስ ሌላ ሰው በላ ታሪክ እየለወጠ መጓዙ ግን አይቀርም፡፡

## ተፈፀመ




ኮዛ ኖስትራ የሲሲሊ ማፊያ ምስጢራዊ ድርጅት ነው። ማፊያ "በደም መሐላ" የሚሠራ፣ ከመቃብር በኋላም ቢሆን ደመኞቹን የማይለቅ እጅግ ጠንካራና አደገኛ ምስጢራዊ ማህበር ነው። ይህ የተወሳሰበ ታሪክ ያለው የማፊያ ማህበረሰብ እንዴት ጠንካራና ለመረዳት የሚያስቸግር ሆነ?

◆ ◆ ◆ ◆

በመጀመሪያው ሲሲሊያዊ ጠቅላይ ሚኒስትር ፍራንቼስኮ ክሪስፒ አማካይነት ጣልያን ያጋጠማትን ቀውስ ባልተጠበቀ አደገኛ መንገድ ለመፍታት ታቀደ። ይኸውም በኢትዮጵያ ላይ የቅኝ ግዛትን ድል ለመጎናፀፍ በሚል። ውጤቱ ግን የተገላቢጦሽ ሆነ። በ1896 በአድዋው ጦርነት 17500 የኢጣልያና በተጨማሪ የባንዳ (Askari) ጦር (በአብዛኛው ኤርትራውያን) የተጠናከረው ሠራዊት የተሻለ የውጊያ ብቃትና ወኔ በነበረው የኢትዮጵያ ጦር ብትንትኑ ወጣ። ይህም የመጀመሪያው የቅኝ ግዛት ኃይል ውርደቱን የተከናነበበት እንደነበር ይታወሳል።

ዋጋው ብር 40.55